45


# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት


# ስግ ሥርዓት (Cloze Procedure) በአማርኛ ትምህርት አቀራረብ ውስጥ የአንብቦ መረዳትን ብሎም አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ለማበልጸግ ያለው ሚና


ጌታቸው ወዬሳ


ሰኔ፥ 1991 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት


# ስግ ሥርዓት (Cloze Procedure) በአማርኛ ትምህርት አቀራረብ ውስጥ የአንብቦ መረዳትን ብሎም አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ለማበልጸግ ያለው ሚና


ጌታቸው ወዬሳ



አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ. ጥ. ተ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA U


ሰኔ÷ 1991 ዓ.ም

# ስግ ሥርዓት (Cloze Procedure) በአማርኛ ትምህርት አቀራረብ ውስጥ የአንብቦ መረዳትን ብሎም አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ለማበልጸግ ያለው ሚና

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
በአማርኛ ማስተማር ሥነ-ዘዴ /TEAM/
ለማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ቴሲስ

በ
ጌታቸው ወዬሳ

ሰኔ፥ 1991 ዓ.ም.

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## ስግ ሥርዓት (Cloze Procedure) በአማርኛ ትምህርት አቀራረብ ውስጥ የአንብቦ መረዳትን ብሎም አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ለማበልጸግ ያለው ሚና

በ

ጌታቸው ወዬሳ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተወጥኖ እስኪጠናቀቅ ጊዜያቸውን ሰውተው የጥናቱን ረቂቅ በማንበብ በማቃናት፥ በማረምና የማሻሻያ ሐሳብ በመስጠት ትእግስት የተሞላበት ክትትል በማድረግ ለረዱኝ ለአማካሪዬ ለዶ/ር ደጀኔ ለታ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፤ በሥራ ሰዓታቸው ብቻ ሳይሆን ከእረፍት ጊዜያቸውም በማጋራት ስለሰጡኝ የማማከር እርዳታ፥ ጥንካሬ ስለሆነኝ ማበረታቻቸውና ሁሌም ስለሚያደርጉልኝ ትህትና የተላበሰ አቀባባል ልዩ አክብሮት አለኝ።

ከሙያቸውና ከምርምር ጥናት ልምዳቸው በመነሳት ጠቃሚ ሐሳቦችን በመካፈል ድጋፍ የሰጡኝ አቶ ጌታቸው አዱኛ፥ አቶ ሰለሞን ሐለፎምና አቶ ጌትነት ማሞ ባለውለታዎቼ ናቸውና ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ይህ ጥናት በትምህርት ቤታቸው ውስጥ እንዲካሄድ በመፍቀድና ከትምህርት ቤታቸው የምፈልገውን ማንኛውንም ትብብር እንዳገኝ ለረዱኝ ለከፍተኛ ሰባት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ለአቶ ሰይፉ ሲሳይ፥ ተማሪዎችንና መምህራንን በማስተባበር ለረዱኝ ለትምህርት ቤቱ የጠዋት ፈረቃ ዩኒት መሪ ለአቶ ዘነበ ስሚነው፥ በታዛቢነት በጥናቱ የተሞከረውን የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ አቀራረብ በመከታተል አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ለትምህርት ቤቱ የአማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራንና፥ በተጠኚነት አብረውኝ በቆዩበት ጊዜ መልካም ትብብራቸው ላልተለየኝ የትምህርት ቤቱ የ1991 ዓ.ም. የ$11^{9}$ ክፍል ተማሪዎች ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ጥናቱን በኮምፒውተር በመፃፍ ለረዳችኝ ለወ/ሮ ሙሉ በዬራ ስለ ቀና ትብብሯ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

በመጨረሻም በትምህርት ላይ በቆየሁበት ጊዜ፥ ከትምህርት ውጪ የነበረኝን ሃላፊነት በመካፈል በእርጋታ ትምህርቴን እንድከታተል የረዱኝን ባለቤቴን በኃይሏ ከበደን ጓደኞቼን አቶ አዳነ ቂጤሳንና አቶ ፍቅሩ ተገኝን ከልብ አመሰግናለሁ።

# አጠቃሎ (Abstract)

ይህ ጥናት በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት ቢውል በአንብቦ መረዳት ብሎም በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ላይ ምን ያህል ለውጥ ማስከተል ይችላል? የሚለውን የጥናቱን አብይ ጥያቄና ከዚህ ጋራ የተያያዙትን ንኡሳን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚሞክር ሲሆን፥ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመሻት አጥኚው የተከተለው ዋና የአጠናን መንገድ የሙከራ ምርምር (Experimental Research) ነው፤ የሙከራ ምርምሩ ከተጠናቀቀ በኋላም ከዚህ የተገኘውን ውጤት ለማጠናከር ለተጠኚ ተማሪዎችና ለታዛቢ መምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በማስራጨት መረጃዎችን በማሰባሰብ የድህረ ሙከራ ጥናት ተደርጓል።

በሙከራ ምርምሩ ውስጥ የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ-ፈተና ንድፍ (two group pre-test post-test design) ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፥ አጥኚው ስታትስቲካዊ የናሙና መረጣን መርህ በመጠበቅ አንድ የቁጥጥርና አንድ የሙከራ ምድብ በማደራጀት፥ በስግ ሥርዓት በሚታገዝ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ የሙከራ ምድቡን ማስተማር በአንብቦ መረዳትም ሆነ በአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ላይ ልዩነት አያስከትልም የሚል ባዶ መላምት ($H_0$) እና የዚህ ተቃራኒ የሆነውን አማራጭ መላ ምት ($H_1$) ይዞ ተነሳ፡

ከመነሻ የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡ የችሎታ ልዩነት የሌላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ቅድመ-ፈተና (pre-test) ተሰጥቶ ሁለቱ ምድቦች በአንብቦ መረዳት ንኡስ ክፍልና በአጠቃላይ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት በ"t"-ሙከራ (t-test) ሲሰላ፥ በዚሁ ቅደም ተከተል 0.73 እና 0.06 ሆኖ በመገኘቱና ሁለቱ በስሌት የተገኙ የ"t"-ዋጋዎች በ$P < 0.05$ የጉልህነት መጠን በ"t"- ሰንጠረዥ ላይ ተመዝግቦ ከሚገኘው ከ1.96 ያነሱ በመሆናቸው ከመነሻ በሁለቱ ምድቦች መካከል በአንብቦ መረዳትና በአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ (ስታቲስቲካዊ ተቀባይነት ያለው) የጎላ ልዩነት እንደሌለ ታውቋል።

በመቀጠል ለስድስት ሳምንታት በክፍሉ ደረጃ የትምህርት ይዘት ላይ በመመረኮዝ ለቁጥጥር ምድቡ በተለመደው የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ መንገድ ትምህርት ሲሰጥ፥ ለሙከራ ምደቡ በሳምንት ውስጥ ካሉት ሶስት ክፍለ ጊዜያት በመጀመሪያውና በመጨረሻው በአጥኚው አማካይነት በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርትና በቀረው በመደበኛው መምህር አማካይነት በስግ ሥርዓት ያልተሸፈኑ የትምህርት ይዘቶች በተለመደው መንገድ ለትምህርት ቀርበዋል።

የሙከራው ጊዜ እንደተጠናቀቀም ድህረ-ፈተና (post-test) ተሰጥቶ ሁለቱ ምድቦች በአንብቦ መረዳት ንኡስ ክፍልና በአጠቃላይ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት በ"t"-ሙከራ (t-test) ሲሰላ የ"t"-ዋጋዎች በዚሁ ቅደም ተከተል 5.23 እና 5.47 ሆነው በመገኘታቸው፥ እነኚህ የ"t"-ዋጋዎች በ$P< 0.05$ የጉልህነት መጠን በ"t"-ሰንጠረዥ ላይ ተመዝግቦ ከተገኘው ከ1.96 የበለጡ ሆነዋል። ይህም የሙከራ ምድቡ በአንብቦ መረዳትም ሆነ በአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ከቁጥጥር ምድቡ ልቆ መገኘቱን የሚያመላክት በመሆኑ አጥኚው ይዞት የተነሳውን ባዶ መላ ምት ($H_0$) ማስወገድ ችሏል።

በድህረ ጥናት ለተጠኚ ተማሪዎችና ተግባራዊ የተደረገውን የንባብ ትምህርት ከ2 እስከ 3 ክፍለ ጊዜ በታዛቢነት በመገኘት ለተመለከቱ መምህራን የጽሑፍ መጠይቆች በማሰራጨት መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን፥ ተጠኚ ተማሪዎቹም ሆኑ ታዛቢ መመህራኑ የማስተማሪያ ዘዴው የአንብቦ መረዳትንም ሆነ አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ሊያዳብር መቻሉን የሚያመለክት አስተያየት እንደሰጡ ከመረጃዎቹ ማወቅ ተችሏል። ይህ ውጤት ቀደም ሲል ከተገለጸው የሙከራ ምርምር ውጤት ጋር የሚጣጣም በመሆኑ የጥናቱ ጥቅል ውጤት በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳትን ብሎም አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታን የማዳበር ብቃት እንዳለው አመልክቷል።

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

## ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ


1.1. የጥናቱ ዳራ /Background of the study/............................... 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ /Objective of the study/................................ 4
1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት /Significance of the study/.................... 4
1.4. የጥናቱ ወሰን /Scope of the study/ .................................... 6
1.5. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ማብራሪያ/Difinition of Terms/. ......... 6


## ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ...................................................


2.1. ስግ ሥርዓት ምንድነው? ............................................ .......... 9
2.1.1. ለስግ ሥርዓት የሚመረጥ ምንባብ ........................ .......... 11
2.1.2. የምንባብ አገጻደፍ ስልቶች ................................ .......... 11
2.1.3. የስግ መልመጃዎች አስተራረም ........................................ 13
2.2. የስግ ሥርዓት ጠቀሜታ ........................................................ 14
2.2.1. የስግ ሥርዓት የሙከራ ማቅረቢያነት ሚና ................. .......... 15
2.2.1.1. የጽሑፍን የተነባቢነት ደረጃ መለካት........ .......... 15
2.2.1.2. የአንብቦ መረዳት ችሎታን መለካት .......... .......... 20
2.2.1.3. የምንባብን (text) ተያያዥነት የጥብቀት ደረጃ መለካት(ማጥናት) .............................. .......... 22
2.2.1.4. የትምህርት መርሃ ግብርን ውጤታማነት መገምገም ....................................... 25
2.2.1.5. አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን መለካት ......... .......... 26
2.2.2. የስግ ሥርዓት የማስተማሪያ ስልትነት ሚና ........................... 30
2.2.2.1 ስግ ሥርዓትና አንብቦ መረዳት .................................... 34
2.2.2.2. የማስተማሪያ ስግ ምንባብ አዘገጃጀት ............................ 39
2.2.2.3. የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት ሂደት ........................... 40
2.2.2.4. የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ አቅጣጫዎች.......................................................... 42
2.2.2.5. የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል ................................................... 43
2.2.2.5.1. ለክፍል አቀፍ ቡድን የሚቀርብ የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል...... 44

2.2.2.5.2. በቡድን ለተከፋፈሉ ተማሪዎች የሚቀርብ የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል.............................................. 47

## ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

3.1. የትምህርት ቤት፥ የተማሪዎችና የመምህራን አመራረጥ................................ 48
3.1.1. የሙከራ ምርምር....................................................................... 48
3.1.2. የድህረ ሙከራ ጥናት................................................................ 50

3.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች............................................................. 50
3.2.1. የሙከራ ምርምር....................................................................... 50
3.2.2. የድህረ ሙከራ ጥናት................................................................ 53

3.3. የመረጃ ትንተና.......................................................................................... 55
3.3.1. የሙከራ ምርምር................................................................. 55
3.3.2. የድህረ ሙከራ ጥናት............................................................ 55

## ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ውጤት ትንተና.................................................. 56

4.1. የሙከራ ምርምር....................................................................................... 56
4.1.1. የቅድመ ፈተና(pre-test) ውጤት ትንተና........................................ 59
4.1.1.1. የቅድመ ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት ትንተና............................................... 59
4.1.1.2. የቅድመ ፈተና የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ውጤት ትንተና........................................................ 61
4.1.2. የድህረ ፈተና (post-test) ውጤት ትንተና..................................... 63
4.1.2.1. የድህረ ፈተና(post-test) የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት ትንተና....................................... 63
4.1.2.2. የድህረ ፈተና (post-test) የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ውጤት ትንተና ............................................. 65
4.2. የድህረ ሙከራ ጥናት.............................................................................. 71
4.2.1. ለሙከራ ምድብ አባላት ከተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ

የተገኙ መረጃዎች ትንተና.................................................... 71
4.2.2. ለተጋባዥ መምህራን ከተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና.................................................................... 80

## ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት................................................................ 86
5.1. ማጠቃለያ............................................................................... 86
5.2. አስተያየት.............................................................................. 89

ዋቢዎች (Bibliography).................................................................. 92

## አባሪዎች

አባሪ 1÷ ቅደመ-ፈተና (pre-test)........................................................ 96
አባሪ 2÷ የቅድመ-ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የአማካይና የመደበኛ ልይይት ስሌት.............................. 106
አባሪ 3÷ የቅድመ-ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የ"t"-ዋጋ ስሌት................................. ..................... 109
አባሪ 4÷ የቅድመ-ፈተና አጠቃላይ ውጤት የአማካይና የመደበኛ ልይይት ስሌት........................................................ 111
አባሪ 5÷ የቅድመ-ፈተና አጠቃላይ ውጤት የ"t"- ዋጋ ስሌት.. ................. 112
አባሪ 6÷ ለማስተማሪያ በአገልግሎት ላይ የዋሉ ስግ ምንባቦች.. .................. 113
አባሪ 7÷ ለማስተማሪያ አገልግሎት ከዋሉ ስግ ምንባቦች ውስጥ የተደገፉ ቃላት.............................................................. 123
አባሪ 8÷ ድህረ ፈተና (post-test)........................................................... 125
አባሪ 9÷ የድህረ ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የአማካይና የመደበኛ ልይይት ስሌት................................. 131
አባሪ 10÷ የድህረ ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የ"t"- ዋጋ ስሌት........................................................ 132
አባሪ 11÷ የድህረ-ፈተና አጠቃላይ ውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት ስሌት........................................................... 133
አባሪ 12÷ የድህረ-ፈተና አጠቃላይ ውጤት የ"t"- ዋጋ ስሌት....................................................................... 134
አባሪ 13÷ ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ.................................. 135
አባሪ 14÷ ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ.................................................. 138

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1፥ የአፍ-ፈት ተናጋሪዎችና የኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች
የስግ ሙከራ መስፈርት ንጽጽር.................................................... 18
ሰንጠረዥ 2፥ በተለያዩ ተመራማሪዎች የቀረቡ የተለያዩ የስግ
ሙከራ ውጤት መስፈርቶች ማጠቃለያ....................................... 19
ሰንጠረዥ 3፥ በተገደፉ ቃላት ተተንባይነት ላይ ክብደት
የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ማጠቃለያ............................................ 40
ሰንጠረዥ 4፥ ለተጠኚ ተማሪዎችና ለተጋባዥ መምህራን በቀረቡ
መጠይቆች ላይ አስተያየት እንዲሰጥባቸው የቀረቡ
ሐሳቦች መጠንና ስርጭት.......................................................... 54
ሰንጠረዥ 5፥ የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ አባላት ጾታ፥ የአፍ መፍቻ
ቋንቋ፥ እድሜና በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ..................... 57
ሰንጠረዥ 6፥ የቅድመ-ፈተና (pre-test) የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ
ክፍል ውጤት.................................................................... 59
ሰንጠረዥ 7፥ የቅድመ-ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት
የ"t"-ሙከራ (t-test) ስሌት ማጠቃለያ..................................... 60
ሰንጠረዥ 8፥ የቅድመ ፈተና የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ውጤት .................. 61
ሰንጠረዥ 9፥ የቅድመ-ፈተና አጠቃላይ ውጤት የ"t"-ሙከራ (t-test)
ስሌት ማጠቃለያ............................................................ 62
ሰንጠረዥ 10፥ የድህረ-ፈተና (post-test) የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ
ክፍል ውጤት................................................................ 63
ሰንጠረዥ 11፥ የድህረ-ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት
የ"t"-ሙከራ (t-test) ስሌት ማጠቃለያ፡፡ .................................... 64
ሰንጠረዥ 12፥ የድህረ-ፈተና የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ውጤት........................... 65
ሰንጠረዥ 13፥ የድህረ-ፈተና አጠቃላይ ውጤት የ"t" ሙከራ
ስሌት ማጠቃለያ.................................................................... 66
ሰንጠረዥ 14፥ የቅድመ-ፈተናና የድህረ ፈተና የ"t"-ሙከራ
ስሌት ማጠቃለያ.................................................................. 67
ሰንጠረዥ 15፥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የአንብቦ
መረዳትን ብቃት ከማበልጸግ አንፃር ስላለው ሚና
ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘ መረጃ................................................ 69
ሰንጠረዥ 16፥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቃላት
ችሎታን ከማበልጸግ አንፃር ስላለው ሚና ከተጠኚ
ተማሪዎች የተገኘ መረጃ......................................................... 71
ሰንጠረዥ 17፥ በስግ ስርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የሰዋሰዋዊ
አገባብ ችሎታን ለማዳበር ስላለው ሚና ከተጠኚ
ተማሪዎች የተገኘ መረጃ......................................................... 73
ሰንጠረዥ 18፥ በስግ ስርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቋንቋ
ክሂሎችን በጥምረት ከማዳበር አንፃር ስለላው ሚና
ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘ መረጃ................................................ 74

ሰንጠረዥ 19፥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የአንብቦ
መረዳትን ብቃት ከማበልጸግ አንፃር ስላለው ሚና
ከተጋባዥ መምህራን የተገኘ መረጃ................................................ 77
ሰንጠረዥ 20፥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቃላት
ችሎታን ከማበልፀግ አንፃር ስላለው ሚና ከተጋባዥ
መምህራን የተገኘ መረጃ.......................................................... 79
ሰንጠረዥ 21፥ በስግ ሥርዓት የሚቀረብ የንባብ ትምህርት የሰዋሰዋዊ
አገባብ ችሎታን ለማዳበር ስላለው ሚና ከተጋባዥ
መምህራን የተገኘ መረጃ.......................................................... 80
ሰንጠረዥ 22፥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት
ለመምህራን የሚሰጠውን ሙያዊ እገዛ በሚመለከት
ከተጋባዥ መምህራን የተገኘ መረጃ................................................ 82
ሰንጠረዥ 23፥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቋንቋ
ክሂሎችን በጥምረት ከማዳበር አንፃር ያለውን ሚና
በሚመለከት ከተጋባዥ መምህራን የተገኘ መረጃ፡፡............................. 83

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ /Background of the study/

በአገራችን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሚመለከት በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች ነባሩን የትምህርት አሰጣጥ መነሻ በማድረግ በአመዛኙ በተማሪዎች ችሎታ ምዘና፥ በማስተማሪያ መጻሕፍት ግምገማ፥ በመምህራንና ተማሪዎች አመለካከት መለካትና በመሳሰሉት አቅጣጫዎች የተደረጉ ናቸው፡፡ በውጤታቸውም በተጠቀሱት ሁኔታዎች ያሉትን ችግሮች ገልፀው በማሳየት መፍትሄዎችን ለማመላከት ችለዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የ2ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋን የንባብ ትምህርት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የመረመሩ ጥናቶች ተደረገዋል፡፡

ከነዚህ ጥናቶች ውስጥ ለምሳሌ ጌታቸው አዱኛ /1986 ዓ.ም*/ ለ10ኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦችን ብቃት በሚመለከት በአማርኛ ቋንቋ ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ ባደረገው ጥናት፥ ምንባቦቹን በፍላሽና ፍሪ ግራፍ ቀመሮች በመለካት፥ የፍላሽ ቀመር ልካቸው ድህረ ምረቃ ፥ የፍሪ ግራፍ ልካቸው የ17ኛ ክፍል ደረጃን የሚያመለክት መሆኑን በመጠቆም፥ ምንባቦቹ ለ10ኛ ክፍል ደረጃ የሚከብዱና ተገቢነት የሌላቸው መሆኑን ለማሳየት ሞክሮአል፡፡ እነዚህ ምንባቦች - ምንባቦቹ ከተዘጋጁላቸው ተማሪዎች ችሎታ ጋራ ያላቸውን ተመጣጥኖ ለመመዘን የሰጠው ስግ ሙከራ ውጤት፥ከተጠኚዎቹ 95.6% የሚሆኑት እየተጨነቁ የማንበብ ክልል (frustration level) ውስጥ እንዳሉ ሲያመለክት ያለምንም ድጋፍ ማንበብ በሚችሉበት ክልል (independent level) ውስጥ የሚገኙ ግን እንደሌሉ አስረድቶአል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ማስተዋል ውበቱ /1989 ዓ.ም./ ለመምህራን ካሰራጨው መጠይቅ፥ በክፍል ውስጥ ካደረገው የንባብ ትምህርት ምልከታና ለተጠኚዎች ካቀረበው የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ፥ በአማርኛ ቋንቋ ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ በአራት የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ባካሄደው ጥናት፥ የተጠኚዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ አመልክቶአል፡፡

---

*በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱት ዘመኖች "ዓ.ም." እስካልታከለባቸው ድረስ የአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠርን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

ከመጠይቅ ያገኘው መረጃ የትምህርት አሰጣጡና የመማሪያ መጽሐፉ ድክመት ለተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን ከፍተኛ ድርሻ ያበረከቱ ሁለት ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸውን እንደጠቆመም አመልክቷል:: በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርት ተማሪዎችን እንደማያሳትፍ፥ አብዛኛዎቹ ተግባራት በመምህራን እንደሚከናወኑ ተማሪዎች በቂ ልምምድ እንደማያደርጉ በምልከታ ማረጋገጥ እንደተቻለ ገልጿል::

በተጠቀሱት ሁለት ጥናቶች ውስጥ የተጠቆመው የምንባቦች ከተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለመጣጣም ችግር በመማር/ማስተማር ሂደት ላይ የተደቀነን ጉልህ ችግር ያሳያል:: የትምህርት አሰጣጥ ድክመት፥ የመማሪያ መጽሐፍ ድክመትና የተማሪዎች የተሳተፎ እድል መነፈግ በሚል የተጠቀሱት ችግሮችም በቀላሉ የሚታዩ ጉዳዮች አይደሉም:: በመሆኑም የንባብን ብሎም የቋንቋን ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች መንስኤና መፍትሄ ምንድነው የሚለውን ዋና ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል:: ይህንን ጥያቄ በአንድ አቅጣጫ ብቻ በተሟላ ሁኔታ መመለስ አስቸጋሪ ቢሆንም ምላሽ ለመስጠት መሞከር ግን ተገቢነት ይኖረዋል:: የተነሳውን ጥያቄ ምላሽ በሚመለከት ኃይለሚካኤል አበራ /1984:7/

> አንድን መጽሐፍ አንብቦ ለመረዳት እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች አንዱ የራሱ የመጽሐፉ የክብደት ደረጃ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፤ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተግባራዊ በተደረገ ረብ-የለሽ የማስተማር ሥነ-ዘዴ ሳቢያ የሚጠበቀውን ያህል ሳይዳብር መቅረትም ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፋቸውን አንብበው ለመረዳት እንዳይችሉ እንቅፋት ሊሆን የመቻሉም ጉዳይ በእኩል ደረጃ እውነትነት አለው::

በማለት፥ የችግሩ ምንጭ ምናልባት የረብ-የለሽ የማስተማር ሥነ-ዘዴ ተግባራዊ መደረግ ሊሆን እንደሚችል በመጠቆም ይህንን ዝቅተኛ ጠቃሚነት ያለው የማስተማር ሥነ-ዘዴ በውጤታማ የማስተማር ሥነ-ዘዴ በመቀየር ሊመጣ የሚችለውን አዎንታዊ ውጤት በመፈተሽ ላይ ያነጣጠረ ጥናት ማካሄድ ችግሩን ሊቀርፍ እንደሚችል አመልክተዋል::

በዚህ አቅጣጫ በቋንቋ ማስተማር/መማር ሂደት ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን ለማቃለል የሚያስችሉ ዘመናኛ የንባብ ማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎችን ውጤታማነት ለመሞከር ከተደረጉት ጥናቶች መካከል "የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጀማሪ ተማሪዎችን በእንግሊዝኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ከተግባቦታዊና ከዘልማዳዊ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ የትኛው ይሻላል?" በሚል ርእስ ኃይለሚካኤል አበራ /1984/ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጠቃሚ ንጽጽራዊ

ጥናት ይገኛል። በዚህ ጥናት ውጤት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ተግባቦታዊ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ከዘልማዳዊ የንበብ ማስተማሪያ ስልት ብልጫ እንዳለው ተገልጿል።

ከዚህ ጥናት ሌላ ገብረመድህን ስምኦን /1993/ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ "እንግሊዝኛ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህብረተሰብ ሳይንስ ጀማሪ ተማሪዎች የቀለም ትምህርት ክትትል (E.A.P) ይበልጥ ይረዳ ዘንድ ግላዊ ንባብ በአማራጭ የማስተማር ሥነ-ዘዴነት ያለው ሚና" በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናት ሌላው ዘመነኛ የንባብ ማስተማሪያ ስልትን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሞከረ ጠቃሚ ጥናት ነው።

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ሥነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከተደረጉ ጥናቶችም በዚህ አቅጣጫ የኔሰው ደሴ/1990ዓ.ም./ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ማዳበር ይችሉ ዘንድ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ያለውን አዎንታዊ ሚና ያመለከተበት ጥናትና ሰለሞን ሐለፎም/1989 ዓ.ም./ የቃል ጽሕፈትን እንደ አንድ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ስልት መጠቀም ያለውን ውጤታማነት ያሳየበት ጥናት በአርአያነት መጠቀስ የሚገባቸው ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አዲስና ዘመነኛ የማስተማሪያ አቅጣጫ ያመለከቱ ጥናቶች ናቸው።

ያሁኑ ጥናትም ከላይ የተጠቀሱትን ጥናቶች ፈለግ በመከተል እስካሁን በአገር ውስጥ የተካሄዱ ጥናቶች እንደ መፈተኛ መሳሪያነት ከመጠቀም በስተቀር በማስተማሪያ ስልትነቱ ያላተኮሩበት ስግ ሥርዓት (Cloze Procedure) ለአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ማቅረቢያነት ቢውል የሚኖረውን ጠቀሜታ ለመመርመር ይሞክራል።

የስግ ሥርዓትን የማስተማሪያ ዘዴነት ሚና ናታል /1996፡208/ "ስግ ስልት በሙከራ መስጫ ዘዴነቱ የተለመደ የመሆኑን ያህል በማስተማሪያ ስልትነቱ እምብዛም አይታወቅም።" በማለት ያመለከቱ ሲሆን፥ ሥርዓቱ በመፈተኛ መሳሪያነት የሚጫወተው ጉልህ ሚና ጥላውን እየጣለበት ጎልቶ አይታይ እንጂ በማስተማሪያ ዘዴነትም ተማሪዎችን በሚያሳትፍ መንገድ ለንባብ ትምህርት ማቅረቢያነት ሊውል እንደሚችልና በተግባር ተሞክሮ አመርቂ ውጤት እንዳሳየ የሚጠቁሙ ጥናቶች እንዳሉ በርካታ ምሁራን ለምሳሌ /ቦርትኒክና ሎፖርዶ1973፤ሀሪሰን. 1980፡98፤ ሲልበርስታይን፡ 1987፤ዋላስ. 1992፡151፤ ናታል. 1996፡208/ አመልክተዋል።

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ / Objective of the study/

የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፥ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ መልመጃዎች አቀራረብ ጉድለት /በየነ ማሞ፥ 1985 ዓ.ም./፥ ለማስተማሪያ በተመረጡ ምንባቦች ክብደት /ጌታቸው አዱኛ፥ 1986 ዓ.ም./ በምንባብ ማራኪ አለመሆንና ከቋንቋ ይልቅ ወደ ሌላ ትምህርት ማዘንበል /አስፋው አመና፥ 1975 ዓ.ም./ በትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ድክመት፥ በተማሪዎች ተሳትፎ መገደብና /ማስተዋል ውብቱ፥ 1989 ዓ.ም./ በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት የሚጠበቀውን ያህል ውጤት ማምጣት እንዳልቻለ በጥናቶቻቸው አመልክተዋል:: ያሁኑ ጥናት ዋና ዓላማም በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ተግባራዊነት የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ፥ ብሎም አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት በማበልጸግ የተጠቀሱትን ችግሮች በከፊልም ቢሆን ማቃለል ይችል እንደሆነ ለመሞከር በመሆኑ፥ መልስ የሚፈልግላቸው:-

ሀ. በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ሊያበለጽግ ይችላል?

ለ. የንባብ ማስተማሪያ ስልቱ የተማሪዎችን አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ምን ያህል ሊያሻሽል ይችላል?

ሐ. በስግ ስልት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ከተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች ጋራ ምን ያህል ትስስር ይኖረዋል?

መ. በስግ ስልት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ለመምህራን የማስተማር ተግባር ስምረት የሚኖረው እገዛ አለ?

ለሚሉት በዓብዩ ዓላማ ስር ሊታቃፉ የሚችሉ ዋና ዋና ጥያቄዎች ነው::

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት /Significance of the study /

በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ያዳብራል በሚል በተለመዱ ተማሪዎች ከምንባብ ቀጥለው የሚቀርቡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይደረጋሉ:: ይሁን እንጂ ናታል /1996:181/ "የመረዳት ሂደት ረቂቅ የመሆኑ ነገር ሲታሰብ፥ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ተማሪዎች 'ምን?' መማር እንዳለባቸው፥ ይህንንስ 'እንዴት?' መማር እንዳለባቸው መለየት ያስቸግራል::" በማለት የገለጹት፥ የአንብቦ መረዳት ችሎታን እንዲህ በቀላሉ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን በመመለስ ብቻ ማበልጸግ እንደማይቻል ያስገነዝባል::

የአንበቦ መረዳት ችሎታን ለማበልጸግ ተማሪዎች ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን መመለስ ብቻ ሳይሆን÷ መልሶቹን ለምን እንደሰጡም ሊጠየቁ ይገባል:: በዚህ መንገድ የሚቀርብ የንባብ ትምህርት÷ ተማሪዎች ለምላሻቸው ምክንያት ለማቅረብ ሲሉ ምንባቡን መልሰው መላልሰው እንዲመረምሩ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ረቂቅ በሆነ መንገድ በአእምሮአቸው ውስጥ የሚብላላውን ሐሳብ ለመምህሩ ገልጸ በማሳየት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል /ሲልበርሰታይን. 1987:30፤ ናታል. 1996:181/::

ተማሪዎች በሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ውስጥ በንባብ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም የቋንቋ ክሂሎች ያላቸው ጥንካሬና ድክመት በግልጽ ይታያል:: በመሆኑም ምክንያቶቹን በሚያቀርቡበት ጊዜ ከጥንካሬዎቻቸው እርስ በርስ በመማመር÷ ድክመቶቻቸውን ደግሞ ከመምህር በሚሰጥ ድጋፍ በማስወገድ አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታቸውን ያበለጽጋሉ:: ዋላስ/1992:74/ "ቋንቋን መማር የሚቻለው በአመዛኙ በንባብ አማካይነት ነው::" ያሉትም ይህን ሀሳብ ያጠናክራል::

ከላይ በተገለጸው መንገድ የንባብን ትምህርት ለማቅረብ ብቃት ካላቸው የንባብ ማስተማሪያ ስልቶች አንዱ÷ በዚህ ጥናት ተግባራዊ ተደርጎ የሚሞከረው በስግ ስልት የሚቀርብ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ነው:: በመሆኑም ጥናቱ ከሚከተሉት ነጥቦች አንጻር ሊጠቅም ይችላል÷

ሀ. የስግ ስልትን ምንነት ጥቅምና ለቋንቋ ትምህርት በተለይም ለንባብ ትምህርት ማቅረቢያነት ያለውን ሚና በሚመለከት የመስኩ ምሁራን ከሚያራምዷቸው ትወራዎችና ትግበራዎች ጋር ያስተዋውቃል::

ለ. አንብቦ መረዳትን ለማዳበር በስግ ሥርዓት የሚቀርብ ትምህርት ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋራ ያለውን ተያያዥነት ያመለክታል::

ሐ. ለአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርትና ትምህርት መሳሪያ አዘጋጆች በአሰራራቸው ውስጥ ሊደረግ ስለሚገባ ተሃድሶ ፍንጭ ይሰጣል::

መ. ተማሪ - መራሽ (student-centered) የሆነው በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ለመምህራን የማስተማር ተግባር የሚሰጠውን ድጋፍ ያመለክታል::

ሠ. የጥናቱ ውጤት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ለወደፊቱ በዚህ አቅጣጫ ምርምር ለማድረግ ለሚልፈጉ አጥኚዎች እንደመነሻ በመሆን መጠነኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል::

## 1.4. የጥናቱ ወሰን /Scope of the study/

ስግ ሥርዓት ከማስተማሪያ ስልትነቱ ይበልጥ በችሎታ መመዘኛ መሳሪያነቱ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ ይህ ጥናት ሥርዓቱ በማስተማሪያ ስልትነት ባለው ሚና ላይ የሚወሰን ስለሆነ የችሎታ መመዘኛነት ሚናው ከጥናቱ ክልል ውጭ ነው:: ስለዚህ በጥናቱ ተግባራዊ በሚደረገው የንባብ ማስተማሪያ ስልት፥ ተማሪዎች ለስግ ምንባብ (cloze passage) መልመጃዎች ትክክለኛ መልሶች ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት በተለያየ መንገድ በማጠናከር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ብሎም የቋንቋ ችሎታቸውን ለማበልፀግ ጥረት ከማድረግ አልፎ - ለስግ ምንባብ መልመጃዎች የሚሰጡዋቸውን መልሶች አንድ ባንድ በማረምና ስህተቶችን በመተንተን ላይ አያተኩርም::

## 1.5. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ማብራሪያ /Definition of Terms/

**መረዳት (comprehending)** በንባብ ወቅት በምንባብ ውስጥ ወደፊትና ወደኋላ በመቃኘት የተለያዩ መረጃዎችን በመፈለግ፥ ዳራዊ እውቀትን በምንባብ ውስጥ ከሚገኙ መረጃዎች ጋራ በማገናዘብ ትርጓሜን በማመንጨትና በመሳሰሉት መንገዶች፥ በንባብ ክንዋኔ ሂደት ውስጥ የምንባብን መልእክት ፈልፍሎ ለማውጣት የሚደረጉትን የተለያዩ ጥረቶች ይመለከታል:: /ቻፕማን. 1983:126/

**ምርጫ ሰጪ ስግ (multiple choice cloze)** በስግ ምንባብ ውስጥ ለሚገኙ ክፍት ቦታዎች በስልት የተዘጋጁ አማራጭ መልሶችን ለተማሪዎች በማቅረብ ትክክለኛውን መርጠው እንዲመልሱ የሚጠይቅ የስግ ሙከራ ዝርያ ነው:: /ጆንዝ. 1976:256/

**ምክንያታዊ ገደፋ (rational deletion)** ለመፈተን በተፈለገው ይዘት ላይ ለማተኮር ሲባል፥ የውሱን ተራርቆን (fixed ratio) ህግ ሳይጠብቁ ቃላትን እየመረጡ ከምንባብ ውስጥ ማጉደልን የሚመለከት የገደፋ ሥርዓት ነው:: /አለር. 1979:345/

**ስግ (cloze)** በቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ የተከማቸን አጠቃላይ የቋንቋ እውቀት ወይም ግምታለም ሰዋሰውን (expectancy grammar)በመጠቀም ስግ ምንባብን መሙላትን ከሚመለከተው 'ስኬት' (closure) ከሚለው ቃልና፥ እያንዳንዱን የስግ ምንባብ ክፍት ቦታ ማሟላትን ከሚመለከተው 'ዝግ' (close) ከሚለው ቃል - ከ'ስኬት' የመጀመሪያውን ፊደል "ስ' ን፥ ከ'ዝግ የመጨረሻውን ፊደል 'ግ' ን

በመውሰድ የዚህ ጥናት አቅራቢ በ'cloze' የአማርኛ አቻነት ይጠቀምበት ዘንድ የፈጠረው ቃል ሲሆን፥ ቃሉ አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን በመጠቀም ስግ ምንባብን አሟልቶ ማየትን (መተርጎምን) ይመለከታል::

ስግ ምንባብ (colze passage) ከተሟላ ምንባብ ውስጥ በተለያዩ ስልቶች ቃላትን በማስወገድ፥ በቃላቱ ምትክ ተመጣጣኝ ርዝመት ያላቸው አግዳሚ መስመሮች በመተካት የሚዘጋጅ ምንባብ ነው::

ስግ ሥርዓት (cloze Procedure) የተማሪዎችን የተለያዩ ችሎታዎች ለመመዘን ወይንም አንብቦ መረዳትን ለማስተማር (የስግ ምንባብን አዘገጃጀት፥ አቀራረብ አስተረራምና የመሳሰሉትን በማካተት) የሚያገለግል ሥርዓት ነው::

ረቂቅ መረጃዎች (nonvisual information) አንባቢ አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ተግባር የሚጠቀምበትን (በምንባብ ውስጥ የማይገኝ) ዳራዊ እውቀቱን (የቋንቋ፥ የይዘትና ባህላዊ እውቀቱን) እና አጠቃላይ የአነባበብ ስልት ችሎታውን የሚመለከት ነው:: /ስሚዝ. 1985፡13/

ተቀባይነት ያለው ምላሽ (acceptable answer) ከምንባብ ውስጥ ከተገደፉት ቃላት ሌላ ከሰዋሰዋዊና ከትርጉማዊ አቻነት አንፃር ሌሎችንም ቃላት እንደ ትክክለኛ መልስ በመውሰድ ማረምን የሚመለከት የስግ ሙከራ የአስተራረም መንገድ ነው:: /ብራወን. 1980፡311/

ተነባቢነት(readability) የምንባብ አቀራረብ በአንባቢ የመረዳት ጥረት ላይ የሚፈጥረውን ጫና መጠን የሚያሳይ ሁኔታ ነው:: /ዋላስ. 1992፡147/

ትንበያ (guessing) ከምንባብ ውስጥ ውሱን እይታዊ መረጃዎችን በናሙናነት በመውሰድ በአመዛኙ በዳራዊ እውቀት ላይ በመመርኮዝ እየገመቱ ማንባብን ያመለክታል:: /ጉድማን. 1967/

ትክክለኛ ምላሽ (exact answer) ከተሟላው ምንባብ ውስጥ የተወገደውን ቃል ብቻ እንደ መልስ ወስዶ ማረምን የሚመለከት የስግ ሥርዓት የአስተራረም መንገድ ነው:: /ኦለር. 1979፡365/

አቦሰጣዊ ገደፋ(random deletion) ከተሟላ ምንባብ ውስጥ ከወደ መጀመሪያ አካባቢ በመነሳት በተመጣጠነ አማራጭ ርቀት፥ ማለትም 4 ቃላት እያለፉ 5ኛውን ቃል፥ ወይም 5 ቃላት እያለፉ 6ኛውና ቃል ... ወይም 11 ቃላት እያለፉ 12ኛውን ቃል እስከ ምንባቡ መጨረሻ በማስወገድ ስግ ምንባብን መዘጋጀትን ይመለከታል/ኦለር. 1979፡345/

አፍ ፈት መራሽ አስተራረም (clozentropy) ስግ ሙከራን ለአፍ ፈት የቋንቋ ተናጋሪዎች በማቅረብ ለያንዳንዱ ክፍተት የሰጡትን ምላሽ ድግግም በማስላት (የሚሰላው ሎጋሪዝም በሚባለው የሂሳብ ስሌት ነው) በዚህ በመመራት ስግ ሙከራን ማረምን ይመለከታል::
/ብራውን. 1980:311/

እይታዊ መረጃዎች (visual information) አንባቢ ምንባብን አንብቦ ለመረዳት ከገጸ-ንባብ የሚያገኛቸውን የተለያዩ መረጃዎች ይመለከታል::
/ስሚዝ. 1985:121/

ግምታለም ሰዋሰው (expectancy grammar) በስግ ምንባብ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በትክክል ለመሙላት የሚያግዘንን በቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ የተከማቸ የቋንቋ ብቃት ወይም የቋንቋ አላባውያን (elements) አሰዳደር ህግ እውቀት ይመለከታል::
/ኦለር. 1972:151/

ግንዛቤ (Comprehension) አንድ ሰው ካነበበ በኋላ የጨበጠውን ሃሳብ ወይም በንባብ ሂደት ውስጥ አልፎ የደረሰበት ውጤት የሚያመለክት ነው:: /ቻፕማን .1983:126/

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### 2.1. ስግ ሥርዓት ምንድነው?

'ስግ ሥርዓት' የሚለው ሐረግ÷ ከቋንቋ ጥናትና ምርምር÷ በተለይም ከንባብ ከፈተናና ከመሳሰሉት ምርምሮች ጋራ ግንኙነት ለሌለው ሰው ግር የሚያሰኝ እንግዳ ሐረግ ነው:: ስግ ሥርዓት ከተፈጠረ ገና ግማሽ ምዕተ ዓመት እንኳን ያልሞላው መሆኑን ቻፕማን " በመጀመሪያ ጊዜ በ1953 የኢሊኖይስ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ተማሪ በነበሩበት ጊዜ ከምንባብ ውስጥ የተወሰኑ ቃላትን በመግደፍ ተገባቦትን ለመለካት የተጠቀሙበትና ያስተዋወቁት ቴለር ናቸው" /1983፡103/ በማለት አመልክተዋል:: 'ስግ' የሚለው ቃል በማን እና እንዴት እንደተፈጠረ ኦለር /1979፡34/ " 'close the door' በሚለው ሐረግ ውስጥ የሚገኘውን 'close' ትንሽ ዞር አድርገው 'cloze' የሚለውን ቃል የፈጠሩት ቴለር ናቸው::" ብለዋል:: ይህ በነባር ቃል ውስጥ የሚገኝን ፊደል ለወጥ በማድረግ በቴለር የተፈጠረ አዲስ ቃል ያልተለመደ በመሆኑ አያሌ አታሚዎችንና ተያቢዎችን ቁጥር ስፍር ለሌለው ስህተት እንደዳረገ ሀሪሰን /1980፡85/ የገለጹ ሲሆን÷ ቴለር ስግ ሥርዓትንና 'cloze' (ስግ) የሚለውን ቃል በመፍጠራቸው ላይ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ምሁራን ለምሳሌ /አልደርሰን. 1975፡220፤ ሀሪሰን. 1980፡84፤ ራይ. 1982፡2/ ይስማማሉ::

ቴለር 'ስግ' የሚለውን ቃል ከምን ጋራ በማዛመድ እንደፈጠሩ ሀሪሰን /1980፡85/ "ቴለር ይህንን ስያሜ በጊዜያዊነት የተጠቀሙበት አባባሉን የጌስታልት ሥነ-ልቡና (Gestalt Psychology) ጽንሰ-ሐሰብ ከሆነው ከስኬት (closure) ጋራ ለማያያዝ ነው::" በማለት ከገለፁ በኋላ ተያያዥነቱ ምን እንደሚመስል እራሳቸው ቴለር /1953/ የሰጡትን ሐሳብ እንደሚከተለው በመጥቀስ አቅርበዋል::

> ጌስታሊስቶች ሰዎች ያልተሟሉ ምስሎችን እንደተሟሉ አድርገው የማየት ዝንባሌ እንዳላቸው በአፅንኦት ይናገራሉ፤ በተቆራረጡ መስመሮች የተሰራን ክብ ምስል ስናይ ክፍተቶቹን በሐሳባችን እየሞላን ክብ ምስል የምናይ መሆኑም ይህንን አስተሳሰብ የሚያንፀባርቅ ነው:: ስግ ሙከራን የሚያከናውኑም በዚሁ መንገድ ከስግ ምንባብ ውስጥ የጎደሉትን ቃላት በማሟላት በምልአት የተዋቀረ ምንባብ ይገነባሉ::

ብዙዎች ምሁራን ስግ ምንባቦችን ለማሟላት የሚደረግ ጥረትንና የተለመዱ ጂኦሜትሪያዊ ምስሎችን በእይታ ቃኝቶ እንደተሟሉ አድርጎ መመልከትን በተመሳሰይ መንገድ ማየት ትክክል አይደለም በማለት ይተቻሉ /ሀሪሰን. 1980፡86፤ ቻፕማን. 1983፡104፤ ራይ. 1982፡3፤ ኦለር. 1979፡343/ ከነዚህ ውስጥ ለምሳሌ ራይ /1982፡2/

> የስግ ሥርዓት በጌስታልት ሥነ-ልቡና አስተሳሰብ ላይ መመስረት በአንድ ወቅት አድናቆትን ያስገኘ ቢሆንም ከፍተኛ ድክመት ይታይበታል:: የጌስታልቱ ስኬት አንዳንዴ በእይታ ላይ የሚከሰትን ሁኔታ ይመለከታል:: የስግ ክፍተቶችን መሙላት በተቆራረጡ መስመሮች የተሰራ ክብ ምስልን በሀሳብ አሟልቶ አጠቃላይ ቅርጹን እንደማየት ሊቆጠር የሚችል አይደለም:: ስግ ሥርዓት የሚጠይቀው አእምሮአዊ ክንዋኔን (cognitive task) ነው::

በማለት የተቃውሟቸውን ምክንያት ገልጸዋል::

አንዳንድ ምሁራን ቴለር በስግ ሥርዓትና በጌስታልት ሥነ-ልቡናው ስኬት መካከል አለ ያሉትን ዝምድና ከመተቸት አልፈው 'ስግ ሥርዓት' የሚለው ስያሜ እራሱ መቀየር ነበረበት በማለት እስከመቆጨት ይደርሳሉ:: ከነዚህ መካከል ለምሳሌ ራይ /1982፡3/ "... ሳይለወጥ ቀይቶ ስር ሰደደ እንጂ ሥርዓቱን 'ስግ ሥርዓት' ከማለት 'የግንባታ ሥርዓት' (construction procedure) ማለቱ የተሻለ ነበር" ብለዋል::

ስግ ሥርዓትንና የጌስታልት ሥነ-ልቡና እሳቤ "ስኬትን" በተመሳሳይ መንገድ መመልከት ትክክል አይደለም በሚል ከላይ የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለውና ብዙ ምሁራንም የሚስማሙበት ነው:: ከዚህ በመነሳት በሙያ ቃልነት ታውቆ የጸናውን ስግ '(cloze) የሚለውን ቃል ለመለወጥ ማሰብ ግን የሚያስኬድ አይደለም:: ከዚህ ይልቅ ስግ ምንባብን መልሶ መገንባት "ልዩና አስደናቂ አይነት ስኬት ነው" /1979፡42/ በማለት ኦለር በሰጡት አስተያየት ውስጥ ካለው ስኬት (closure) ጋራ -የስግ ምንባብን ክፍት ቦታዎች መድፈንን የሚመለከተውን "close' የሚለውን ቃል በማሳሳብ 'cloze' የሚለውን ቃል መፍጠር ይቻላል በሚል አቅጣጫ በማሰብ ቴለር ቃሉን የፈጠሩበትን መንገድ መጽናት ይቻላል::

ባሁኑ ጥናትም ይህንኑ መንገድ በመከተል የ'closure' እና 'close' የአማርኛ ትርጉም ከሆኑት 'ስኬት' እና 'ዝግ' ከሚሉት ቃላት ከ'ስኬት' የመጀመሪያውን ሆሄ 'ስ' ን ከ'ዝግ' የመጨረሻውን ሆሄ 'ግ'ን በመውሰድ፥ በዚሁ ቅደም ተከተል በማያያዝ

'ስግ' የሚለውን መጠቃ የአማርኛ ቃል በመፍጠር በ'cloze' አቻ ፊቺነት መጠቀም ተመርጧል።

### 2.1.1. ለስግ ሥርዓት የሚመረጥ ምንባብ

የስግ ሥርዓትን ምንነት በተሟላ መልክ ለማሳየት የስግ ሥርዓት መሠረት የሆነው ስግ ምንባብ (cloze passage) ስለሚዘጋጅበት መንገድ አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት አስፈላጊ ነው። ስግ ሥርዓት ይኖር ዘንድ አስቀድሞ ሥርዓቱ የሚዋቀርበትን ምንባብ መምረጥ ያስፈልጋል። ምንባብን ለመምረጥ የሚዘረዘሩት ተለምዷዊ መስፈርቶች እጅግ በርካታ ቢሆኑም ለስግ ሥርዓት ተጠቅሞ ግን ማንኛውም ምንባብ ማገልገል እንደሚችል ጥናቶች አረጋግጠዋል /አለር. 1973፡110/። ይህ አባባል ስግሥርዓት የተለያየ የክብደት ደረጃ ያላቸውን ምንባቦች የማስተናገድ አቅም እንዳለው የሚያመለክት ሲሆን፥ በሌላ አንፃር ግን መምህራን ከተማሪዎች የመረዳት ደረጃና ስሜት ጋር የሚስማሙ ምንባቦችን ለስግ ሥርዓት መምረጥ እንዳለባቸው አለር እራሳቸው ያመለከቱ ሲሆን /1979፡364/ ሌሎችም ለምሳሌ አትኬን /1977፡60/ "... የአጠቃላይ አንብቦ መረዳት፥ የተነባቢነት ወይም የቋንቋ ብቃት ሙከራ ለማቅረብ የሚውል ምንባብ የክብደት ደረጃ በተቻለ መጠን ከተማሪዎች ችሎታ ደረጃ ጋራ ይጣጣማሉ ከሚባሉ ተነፃፃሪ ምንባቦች የክብደት ደረጀ እንዳይበልጥ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።" በማለት ገልጸዋል።

### 2.1.2. የምንባብ አገዳደፍ ስልቶች

የስግ ምንባብን አዘጃጀት በመንተራስ ስለ ስግ ሥርዓት ምንነት ሲገልጹ አለር /1979፡344፡ "ስግ ሥርዓት የተሟላ ምንባብን ስልታዊ (systematic) በሆነ መንገድ በመግደፍ የሚዘጋጅና ተማሪዎች ባላቸው የተከማቸ ሰዋሰዋዊ እውቀት በመታገዝ ይህንን የተጓደለ ምንባብ ምን ያህል ማሟላት እንደሚችሉ ለመፈተን የሚያገለግል ሥርዓት ነው" ብለዋል። ይህ ስልታዊ በሚል በጥቅሉ የቀረበው ከምንባብ ውስጥ ቃላትን እየገደፉ የማውጣት መንገድ ዝርዝር ተደርጎ ሲታይ ሶስት ዓይነት የምንባብ ገደፋ ስልቶችን በውስጡ አካቶ እንደሚይዝ ድርሳናት ያመለክታሉ።

> ከሶስቱ ስልቶች አንደኛው በጥቅሉ ከምንባብ ውስጥ በስልታዊ መንገድ ቃላት እንደሚገደፉ የሚያመለክትና 'ስልታዊ' የሚለውን ቃል የማያብራራ ነው፤ ሁለተኛው 'ስልታዊ' የሚለውን ቃል በመውሰድ-ከምንባብ ውስጥ ቃላትን በአቦሰጣዊ ገደፋ (random deletion) ማስወገድና-ከምንባብ ውስጥ ቃላትን በምክንያታዊ ገደፋ (rational deletion) ማስወገድ ወደሚሉት ሁለት ዓይነት የገደፋ ስልቶች

የሚከፈል ነው፣ ሰስተኛው ደግሞ ከተወሰነ ቦታ በመጀመር እየቆጠሩ ማንኛውንም አምስተኛ ቃል ከምንባቡ ውስጥ ማስወገድን ይመለከታል።

/አልደርሰን. 1979፡219/

ስለ ምንባብ አገዳደፍ ስልቶች ከላይ የቀረበውን ባጭሩ -ስግ ሥርዓትን ለማዘጋጀት የምንጠቀምባቸው የገደፋ ስልቶች ሁለት ናቸው፣ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ከምንባብ መጀመሪያ አካባቢ ከአንድ ቦታ ጀምሮ በእኩል ተራርቆ የሚገኝን ማንኛውንም 5ኛ፥ 6ኛ፥ 7ኛ ... ወይም 12ኛ ቃል (እንዳስፈላጊነቱ) ማስወገድን የሚመለከተው አቦሰጣዊ ገደፋ (random deletion) ሲሆን ሌላው ሊፈተን በታሰበው ይዘት ላይ ለማተኮር ሲባል የፈለጉትን ቃል እየመረጡ ማስወገድን የሚመለከተው ምክንያታዊ ገደፋ (rational deletion) ነው በሚል ማጠቃለል ይቻላል።

የስግ ምንባብን አገዳደፍ ዝርዝር ጉዳይ አስመልክተው የተለያዩ ምሁራን የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰጥተዋል።

- በአቦሰጣዊ ገደፋ ከ5 ተራርቆ በታች መውረድ ሙከራውን ያከብዳል፣ ከ7 ተራርቆ በላይ ከፍ ማለት ምንባብን ያለቅጥ ረዥም ያደርጋል። ስለዚህ ከ5-7 ተራረቆ መካከል በመወሰን ምንባብን መግደፉ የተሻለ ነው። /ሀሪሰን. 1983፡42፣ ሂተን. 1988፡131/

- ከምንባብ ውስጥ የሚገደፉት አንድ አንድ ነጠላ ቃላት ሲሆኑ አንዳንዶች ግን እንደ can't እና meeting-place ያሉትንም እንደ አንድ ቃል ይወስዳሉ። /ሀሪሰን. 1983፡43/

- ለምርምር ተግባር ለሚውሉ ስግ ምንባቦች ካልሆነ በስተቀር በእኩል ተራርቆ የሚገኝን ማንኛውንም ቃል ማስወገድ ችግር አለው። ስለዚህ ብዙዎች የመገደፉ እጣ የተፀውኦ ስሞች፥ ቁጥሮችና እነዚህን የመሳሰሉት ላይ ሲያርፍ ያንን ቃል በማለፍ በእኩል ተራርቆ መግደፋቸውን ይቀጥላሉ። /ሀሪሰን. 1983፡42/

- በሙከራው ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ውስጥ መግባት ያለባቸውን ትክክለኛ ቃላት ለመገመት የሚያስችል ፍንጭ ይሰጡ ዘንድ ያልተገደፉ ሁለት ሙሉ አረፍተነገሮች አንደኛው በምንባቡ

መጀመሪያ ላይ ሌላው በምንባቡ መጨረሻ ላይ መቀመጥ አለባቸው::
/ኦለር. 1979:365/

- ከምንባብ ውስጥ ቃላት ከተወገዱ በኋላ በቃላቱ ምትክ የሚተኩት መስመሮች ተመጣጣኝ ርዝመት ሊኖራቸው ይገባል::
/ሂተን. 1988:131:/
- በምርምር መስክ በተሰማሩ ባለሞያዎች ዘንድ የሚዘወተረው ከምንባብ ውስጥ ከመጀመሪያ ገደማ በመነሳት ማንኛውንም 5ኛ ቃል የማስወገድ የገደፋ ስልት ነው:: /ሀሪሰን. 1980:101/

## 2.1.3. የስግ መልመጃዎች አስተራረም

በስግ ሥርዓት የሚቀርቡ ሙከራዎች በሁለት መሠረታዊ የአስተራረም መንገዶች ይታረማሉ:: ከነዚህ የአስተራረም መንገዶች አንደኛውና ነባሩ ከምንባቡ ውስጥ የተወገደውን ቃል ብቻ እንደ ትክክለኛ መልስ በመውሰድ ማረምን የሚመለከተው ትክክለኛ ምላሽ (exact answer) ሲሆን÷ ሁለተኛው በትክክለኛነት ከምንባቡ ውስጥ ከተወገደው ቃል የማይተናነስ ምላሽ እንዴት እንደ ስህተት ሊቆጠር ይችላል? ከሚል ጥያቄ በመነሳት -ከምንባብ ውስጥ የተወገደው ቃል ብቻ ሳይሆን ከዚህ ቃል ጋራ ትርጉማዊ÷ መዋቅራዊ÷...ወዘተ ተመሳስይነት ያለው ቃል ሁሉ እንደ ትክክለኛ ምላሽ መቆጠር አለበት ከሚል አስተሳሰብ የመነጨው -ተቀባይነት ያለው ምላሽ (acceptable answer) የሚባለው ነው:: ተቀባይነት ያላቸውን ምላሾች ለመወሰን በመስፈርትነት የሚያገለግለው የአፍ-ፈት ተናጋሪዎች ምላሽ ነው:: /ሀሪሰን. 1983:114፤ ኦለር. 1979:367-368፤ ብራውን. 1980:311፤ አልደርሰን. 1979:219/

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ዘግየት ብለው በተደረጉ ጥናቶች ግፊት ቀደም ብለው ከተጠቀሱት የአስተራረም መንገዶች የሚወለዱ ሌላ ሁለት ዓይነት አስተራረሞች ተፈጥረዋል:: ከነዚህ አንዱ ከትክክለኛ ምላሽ የሚወለደው ምርጫ ሰጭ ስግ (multiple-choice cloze) የሚባለው ሲሆን -ተማሪዎች ለተለመደው ስግ ምንባብ የሚሰጧቸውን ተደጋጋሚ ስህተቶች በማዛቢያነት (distractor) ተጠቅሞ እነዚህን ማዛቢያዎች ከትክክለኛ መልስ ጋራ በመቀላቀል በማቅረብ ተማሪዎች ትክክለኛውን በመምረጥ መልስ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ስልት ነው:: /ጆንዝ. 1976:256፤ ሁባርድ. 1983:281፤ ብራወን. 1980:311/ ሁለተኛው ደግሞ ተቀባይነት ያለው ምላሽ ከሚለው የአስተራረም መንገድ የሚወለደው አፍፈት-መራሽ አስተራረም (clozentropy) ሲሆን-ይህም ስግ ምንባብን በተለመደው መንገድ በማቅረብ አፍ-ፈት የቋንቋው ተናጋሪዎች በከፍተኛ ድግግም ለሰጡት መልስ

(ድግግሙ የሚለካው ሎጋሪዝም በሚሰኘው ሂሳባዊ ስሌት ነው) የበለጠ ማርክ፥ ድግግሙ አነስ ላለው ደግሞ ከዚያ ዝቅ ያለ ማርክ ... ወዘተ በመስጠት ማረምን የሚከተል የአስተራረም መንገድ ነው። /ብራወን. 1980:311፤ አለር. 1979:373፤ አልደርሰን. 1979:219/

የስግ ሥርዓትን ምንነት አዘገጃጀትና ተግባራዊነት በሚመለከት ብዙ ተጽፏል፤ በርካታ ጥናቶችም ተካሂደዋል። በየድርሳናቱ የሥርዓቱን አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታ የሚያንጸባረቁ ከ-እስከ የማይባሉ ውዝግቦች ይሰተዋላሉ። እነዚህን ተጻራሪ አመለካከቶች በየቦታው በበቂ መጠን ማስተናገዱ ስለሚያስቸግር የስግ ሥርዓት ጠቀሜታዎች በሚል ከዚህ ቀጥሎ በምናየው ክፍል ውስጥ በየመካከሉ ጨረፍ አድርጎ ለማቅረብ የሚሞከር ሲሆን፥ እነዚህን ተጻራሪ አመለካከቶች በቅርበት ለማየት የሚፈልጉ አለር/1973/፥አለር/1979:340-379/፥ ሶታብስና ተከር/1974/፥ አትኬን/1977/፥ አልደርሰን/1979/፥ አልደርሰን/1996:222/ እና ባችማን /1985/ን መነሻ ማድረግ እንደሚችሉ ይጠቆማል።

## 2.2. የስግ-ሥርዓት ጠቀሜታ

ስግ ሥርዓት ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በቋንቋ ጥናት በተለይ በንባብ ጥናት ንኡስ ዘርፍና በሌሎችም ተጓዳኝ ጥናቶች ውስጥ የሰጣቸው ጥቅሞች እጅግ ብዙ ናቸው። ይህንን አስመልክተው ዋላስ /1992:145/ ስግ ሥርዓት "... በአካባቢው አውድ በመታገዝ ተማሪዎች ከምንባብ ውስጥ የተወገዱ ቃላትንና ትርጉማቸውን እንዲገምቱ የሚያበረታታ ... ችሎታን ለመመዘን ወይም የፈተናና የማስተማሪያ ሥርዓቶች አካል በመሆን የሚያገለግል ሥርዓት ነው።" በማለት ሲገልጹ፥ ቻፕማን/1983:114/ ደግሞ "ስግ ሙከራ በምርምር መስክ ለረዥም ጊዜ ያገለገለ በርካታ ጥቅሞች ያሉት፥ አስተማማኝ የመመዘኛና የማስተማሪያ መሣሪያ እንደሆነ በተግባራዊ ተሞክሯቸው በተጠቀሙበት ሁሉ ተመስክሯል።" በማለት አክለዋል። ናታል/1996:208/ ስግ ሥርዓት በሙከራ መስጫነት ይበልጥ ይታወቅ እንጂ በማስተማሪያ ዘዴነትም ያገለግላል በማለት ከስግ ሥርዓት ጠቀሜታ ሁለት ፈርጆች ይበልጥ የሚታወቀው ሥርዓቱ በመመዘኛነት ያለው ሚና እንደሆነና እጅግ ጠቃሚና ውጤታማ የሆነው የማስተማሪያ ስልትነት ሚናው ብዙም የማይታወቅ ነገር ግን መታወቅ የሚገባው መሆኑን በመጠቆም ይህንን የስግ ሥርዓት ልዩ ገጽታ ቀደም እንጻሉት ምሁራን ሁሉ አሳይተዋል። አበይት የስግ ሥርዓት ጠቀሜታ ዘርፎችን በሚመለከት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሁራን ያቀረቧቸውን ሀሳቦች የሚደገፉ ተጨማሪ ሀሳቦች በአለር /1979:346/፥ ሀሪሰን /1980:85/፥ ራይ /1982/ እና ሌሎችም ቀርበዋል።

ቀጥለን ሁለቱን የስግ ሥርዓት ዋና ዋና ጥቅሞች ዘርዘር አድርገን እናያለን፡፡

### 2.2.1. የስግ ሥርዓት የሙከራ ማቅረቢያነት ሚና

ስግ ሥርዓት ከሙከራ ማቅረቢያ ስልትነት አኳያ፥ የጽሑፍን ተነባቢነት ደረጃ ለመለካት፥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት፥ የምንባብን ተያያዥነት መጠን ለመለካት (ለማጥናት)፥ የትምህርት ግብ መቺነት ደረጃን ለመገምገምና፥ አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን ለመለካት እንደሚያገለግል ድርሳናት አመልክተዋል፡፡ /ኦለር. 1979፡346፤ ዋላስ. 1992፡145፤ ሀሪሰን. 1980፡87፤ ራይ. 1982፤ አትኬን. 1977፤ ኦለር. 1973፤ ስታብስና ተከር. 1974/ በመሆኑም ቀጥለን የተጠቀሱትን የስግ ሙከራ የመመዘኛነት ጥቅሞች አንድ ባንድ እናያለን፡፡

#### 2.2.1.1. የጽሑፍን የተነባቢነት ደረጃ መለካት

ጸሐፊ አንባቢዬ የጻፍኩትን ምን ያህል ይረዳኛል ብሎ ይጨነቃል፡፡ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችም ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የተዘጋጁ መጻሕፍት የክብደት ደረጃ ምን ያህል ከተዘጋጁላቸው ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋራ ይጣጣማሉ ብለው ያስባሉ፡፡ ለዚህ ዓይነቱ አሳሰቢ ችግር መልስ ለመስጠት የተደረጉ ጥናቶች አጀማመር ታሪክ ወደ 900 ዓ.ዓ. አካባቢ ወደ ኋላው ዘመን እንደሚሄድ ኦለር/1979፡345/ ሎርጅን ጠቅሰው አመልክተዋል፡፡ ከዚህ ጊዜ አንስቶ በተደረጉ ጥናቶች አማካይነት በርካታ የጽሑፍ ተነባቢነት መለኪያ ስልቶች እንደተፈጠሩና እየተበራከቱ ሄደው ከ1960 ቀደም ብሎ እስካለው ጊዜ ብቻ ወደ 30 የሚጠጉ የተነባቢነት መለኪያ ቀመሮች ተፈጥረው እንደነበር ኦለር/1979፡348/ ክሌርን በመጥቀስ አመልክተዋል፡፡

ቀመሮች ጠቃሚ የጽሑፍ ተነባቢነት ደረጃ አመልካች ቢሆኑም የአረፍተ ነገር ርዝመት፥ የቃላት ርዝመትና የቃላት ተደጋግሞ መምጣት ደረጃ (frequency) በሚሉ ጥቂት የተነባቢነት ደረጃ አመልካች ነጥቦች ላይ በመወሰን-የጽሑፍን የተነባቢነት ደረጃ የሚወስኑ በርካታ ጠቃሚ ጠገኖችን (aspects) ይዘነጋሉ /ራይ. 1982፡17/፡፡ ቀመሮች ከሚዘነጓቸው እጅግ ጠቃሚ የተነባቢነት ገጽታዎች፥ ተማሪ በሚያነብበት ጊዜ የሚታይ መቀስቀስ (motivation) እና ወደ ምንባቡ ይዞት የሚመጣው ዳራዊ እውቀት (background knowledge) ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የተጠቀሱትን የተነባቢነት ደረጃ መገመቻ ቀመሮች ድክመት በሚመለከት ኦለር ግላዘርን በመጥቀስ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ቀመሮች ትክክለኛ የተነባቢነት መለኪያ መሆን የተሳናቸው የቋንቋ ፍሬ ጉዳዮች (elements) በሙሉ በተለያየ መልክ በአንብቦ መረዳት ውስጥ ስለሚካተቱ ነው፡፡ እጅግ በርካታ ከሆኑት የቋንቋ ፍሬ ጉዳዮች በቀመሮቹ ውስጥ በቀላሉ ሊካተቱ የሚችሉት እጅግ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውጭ ያሉትን የቋንቋ ፍሬ-ጉዳዮች በቀመሮቹ ውስጥ ማካተት ደግሞ ውስብስብና ተግባራዊ ፋይዳ የሌላቸው ቀመሮች ከመፍጠር አልፎ ጥቅም አላስገኝም፡፡
>
> /ኦለር. 1979፡348/

ከላይ በተጠቀሰው ውስጥ የቋንቋ ፍሬ ጉዳዮችን በሙሉ በግምት ውስጥ በማስገባት የጽሑፍን ተነባቢነት ከዚያ አንፃር በትክክል መለካት የሚችሉ ቀመሮች ማግኘት እጅግ አዳጋች መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህም የአማራጭ የተነባቢነት መለኪያን አስፈላጊነት ያጎላል፡፡ "የቴለር በ1953 ስግ ሥርዓትን ማስተዋወቅ በወቅቱ ይሰራባቸው የነበሩትን የተነባቢነት መለኪያዎች በተሻለ የተነባቢነት መለኪያ ለመተካት የተደረጉ ጥረቶች አካል ነው፡፡" /ዴቪስ. 1984፡190/ የዚህን ደካማ ናቸው የተባሉትን ቀመሮች ይተካ ዘንድ የተፈጠረ የተነባቢነት መለኪያ ጥንካሬ ራይ/1982፡18/ "ስግ ሥርዓት የምንባብን የክብደት ደረጃ የሚለካው በቃላት ርዝመት ወይም በቃላት እሥራ ላይ የመዋል ድግግም ወይም በአረፍተ ነገር ርዝመት ሳይሆን÷ አንባቢ የምንባብን የቋንቋ አወቃቀር ምን ያህል ይረዳልና አንብቦ ስለተረዳውስ ቢጠየቅ ምን ያህል ብቁ ምላሽ ይሰጣል በሚል አቅጣጫ ነው፡፡ በመሆኑም ሥርዓቱ ሥነ-ልሳናዊ ተላውጦዎችን (variables) በሚመለከት የሚሰጥን ግላዊ ምላሽ የሚለካ ነው፡፡" በማለት የገለጹ ሲሆን በማከልም "በምንባብ የተወሰኑ ገጽታዎች ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ በምንባብና በአንባቢ መካከል የሚደረግን ተራክቦ የሚመዘን በመሆኑ ምክንያት ስግ ሥርዓት ከማንኛውም የተነባቢነት መመዘኛ ቀመር እጅግ የተሻለና የረቀቀ የተነባቢነት መመዘኛ መሣሪያ ለመሆን በቅቷል" /ራይ. 1982፡21/ ብለዋል፡፡ ሀሪስን /198፡88/ ክሌርን በመጥቀስ "ከቀመሮች በተቃራኒ ስግ ሥርዓት ተነባቢነትን ይለካል እንጂ አይተነብይም፡፡" ያሉትም ቀደም ሲል ራይ ያቀረቡትን ሐሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

አንዳንድ ምሁራን ለምሳሌ በቻፕማን /1983/ የተጠቀሱት ፖተር ስለ ስግ ሥርዓት ጥንካሬ ማውሳት ብቻ ሳይሆን ይበልጥ አስተማማኝ (reliable) እና እርባና ያለው (valid) የተነባቢነት መለኪያ እንዲሆን በሚከተሉት ነጥቦች መሠረት እንዲዘጋጅ መክረዋል፡፡

1. በእኩል ተራርቆ የሚገኝ ማንኛውንም "ቁ"*ኛ ($n^{th}$) ቃል መግደፍ
2. መቶ ቃላት ከያዘ ምንባብ ከሃያ ቃላት በላይ አለመግደፍ
3. ቢያንስ 250 ቃላት ባሉት ምንባብ መጠቀም
4. ለአንዳንድ ዓላማዎች ከሚውሉ ረዣዥም ምንባቦች ውስጥ በ1:10 እና 1:12 ሬሽዮ ቃላትን መግደፍ የስግ ሥርዓትን እርባና (validity) ከፍ ሊያደርግ ይችላል::
5. ከንባብ ውስጥ በቂ ቃላትን በናሙናነት ማግኘት እንዲቻል ቢያንስ 50 ቃላት መገደፍ አለባቸው::
6. በትክክለኛ መልስ (exact answer) የማረሚያ ስልት መጠቀም
7. የሌላው የአስተራረም መንገድ ማለትም ተቀባይነት ያለው መልስ (acceptable answer) አስተራረም የውስጠ-አራሚዎች አስተማማኝነት (inter-rater reliability) ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ለማረም ብዙ ጊዜ ይወስዳል::
8. ከተገደፉት ቃላት፥ የተለያዩ የንግግር ክፍሎችን የሚመለከቱ ቃላትን፥ የይዘት ቃላትን፤ የተግባር ቃላትን ለየብቻ እየለዩ ማረም ለተለያዩ ጥናቶች ፍንጭ ይሰጣል::

/ቻፕማን. 1983:105-107/

የስግ ሥርዓት የተነባቢነት ደረጃ አመልካች መቶኛ ውጤቶች ከ75% እና 90% የምርጫ አንብቦ መረዳት ውጤት መስፈርቶች የተገኙ ናቸው:: /ሀሪሰን. 1980:42/:: የአሜሪካ መምህራን የአንድ ተማሪ በምርጫ ጥያቄዎች ላይ የተመሰረተ የአንብቦ መረዳት ሙከራ ውጤት 75% ከሆነ፥ ሙከራው የተመሰረተበት ምንባብ፥ በዚህ ተማሪ በመምህር እርዳታ ሊነበብ የሚችል /instructional level/ የሚል ደረጃ እንዳለው፥ የተማሪው ውጤት 90% ከሆነ ደግሞ ሙከራው የተመሰረተበት ምንባብ በተጠቃሹ ተማሪ ያለ መምህር እርዳታ በግል የሚነበብ (independent level) በሚል የተነባቢነት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በማመን 75% እና 90% የሚሉትን መቶኛዎች በመምህር እርዳታ ሊነበብ የሚችል (instructional level) እና ያለ መምህር እርዳታ በግል የሚነበብ (independent level) ለሚሉት ሁለት የተለያዩ የተነባቢነት ደረጃ እርከኖች መለያነት እንደ መስፈርት ይጠቀሙባቸው ነበር:: /ሀሪሰን. 1980:90 ፤ አትኪን. 1977:62/

የስግ ሙከራ የተነባቢነት መለያ መቶኛ ውጤቶች ከላይ ከተጠቀሱትና ከተነባቢነት ደረጃ ጋራ ተገናዛቢነት ካላቸው ከ75% እና 90% መስፈርቶች ጋራ

*"ቁ" ማንኛውንም ቁጥር የምትወክል ምልክት ናት::

ተመጣጣኝ የሆኑ የስግ ሙከራ መቶኛ ውጤቶችን ለይቶ ለማመልከት ከተደረጉ ጥናቶች የተገኙ ናቸው:: ከነዚህ መስፈርቶች ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ የስግ ሙከራ መቶኛ ውጤቶችን ለመለየት አንደርሰን እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት ያገኙትን ውጤት በአፍ-ፈት ተማሪዎች ላይ ከተካሄዱ ሶስት መሰል ጥናቶች ከተገኙ ውጤቶች ጋራ ያነጻጸሩበትን ሰንጠረዥ አትኪን /1977:63/ አንደርሰንን ጠቅሰው እንደሚከተለው አቅርበዋል::

**ሰንጠረዥ 1÷ የአፍ-ፈት ተናጋሪዎችና የኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች የስግ ሙከራ ውጤት መስፈርት ንጽጽር::**

| መስፈርቶች | ተመጣጣኝ የስግ ሙከራ መቶኛ ውጤቶች | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቦርሞዝ (1967) | ቦርሞዝ (1968) | ራንኪንና ኩልሃን (1969) | አንደርሰን (1971) |
| 75% | 38 | 44 | 41 | 44 |
| 90% | 50 | 57 | 61 | 53 |

ከዚህ በላይ ከተነባቢነት ደረጃ አመልካች መስፈርቶች ጋራ (75% እና 90%) ተመጣጣኝ ናቸው ተብለው በተለያዩ ተመራማሪዎች የቀረቡት የስግ ሙከራ መቶኛ ውጤቶች÷ ከዝቅተኛዎቹ መቶኛዎች በታች ያለው በመምህር እርዳታ እንኳን ሊነበብ የማይችል (frustration level)÷ በዝቅተኛዎቹና በከፍተኛዎቹ መቶኛዎች መካከል ያለው በመምህር እርዳታ ሊነበብ የሚችል (instructional level) እንዲሁም ከከፍተኛዎቹ መቶኛዎች በላይ ያለው በግል ደረጃ ሊነበብ የሚችል (independent level) የሚሉትን ሶስት የተለያዩ የተነባቢነት ደረጃዎች የሚመለከቱ ናቸው::

ተመጣጣኝ የስግ ሙከራ መቶኛ ውጤቶችን በሚመለከት ከላይ እንደታየው የተለያዩ ተመራማሪዎች የሚያቀርቧቸውን የተለያዩ አሃዞች በማመዛዘን እንደሚከተለው አጠጋግቶ ወደ አንድ መምጣት እንደሚቻል ራይ /1982:19/ ጠቁመዋል::

ሰንጠረዥ 2፦ በተለያዩ ተመራማሪዎች የቀረቡ የተለያዩ የስግ ሙከራ መቶኛ ውጤቶች መስፈርቶች ማጠቃለያ።

| የመረዳት ደረጃ | እየተጨነቁ ማንበብ (frustration) | በመምህር እርዳታ ማንበብ (instructional) | በግል ደረጃ ማንበብ (independent) |
|---|---|---|---|
| የስግ ሙከራ ውጤት ከመቶ | 0 - 39 | 40 - 59 | 60 - 100 |

ከዚህ በላይ የቀረበው ስግ ሥርዓት በተነባቢነት መለኪያነት ስላለው አዎንታዊ ሚና ሲሆን ይህ ሥርዓት አስተማማኝና እርባና ያለው የተነባቢነት መለኪያ ነው የሚሉ ምሁራን የመኖራቸውን ያህል፥ በርካታ ምሁራን ደግሞ የምርምር ተሞክሯቸው የዚህ ተቃራኒ እንደሆነ ገልጸዋል።

ከነዚህ ውስጥ ለምሳሌ ገብረመድህን ስምኦን /1993፡222-223/ ባደረጉት የአሰሳ ጥናትም ሆነ በዋናው ጥናታቸው ከስግ ሥርዓት ያገኙት የተነባቢነት ደረጃ ውጤት፥ ጎን ለጎን ከተሰጡት ሌሎች የአንብቦ መረዳት ሙከራዎች ጋራ ሊጣጣም አለመቻሉና እንዲያውም ተቃራኒ መሆኑ ሥርዓቱ በግላዊ ንባብ አማካይነት ተማሪዎች በማንበብ ችሎታቸው የሚያሳዩትን መሻሻል ማመልከት የማይችልና የመማሪያ መጻሕፍቱንም የተነባቢነት ደረጃ የመለካት ብቃት የሌለው መሆኑን ያረጋገጠ ይመስላል ብለዋል። ዊሊያምና ዳላስም /1985፡201/ በአገልግሎት ላይ የነበረ ለኢ-አፍ ፈት የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች የቀረበ የህብረተሰብ መጽሐፍ የተነባቢነት ደረጃ ለመለካት ካደረጉት አሳሽ ጥናት ካገኙት የስግ ሙከራ ውጤት በመነሳት "ውጤቱ መጽሐፉ ከተማሪዎቹ 91.4% ለሚሆኑት እጅግ ከባድ መሆኑን ማመልከቱ በጣም የሚረብሽ ነው። መጽሐፉ ከብዷቸዋል የተባሉት ተማሪዎች መቶኛ በጣም ከፍ ያለ መሆኑ፥ ከነዚህ ቁጥራቸው የማይናቅ ተማሪዎች ከናካቴው እንግሊዝኛ ማንበብ አይችሉ ይሆናል የሚል ግምት የሚያሳድር መሆኑም የውጤቱን አሳሳቢነት ይበልጥ ያጎላዋል።" ካሉ በኋላ ውጤቱን እንዳለ ላለመቀበል የሚቻልበትን ምክንያት በመጥቀስ በስግ ሥርዓት የተነባቢነት መመዘኛነት ብቃት ላይ ያላቸውን ጥርጣሬ አንጸባርቀዋል።

እዚህ ላይ ለ10ኛ ክፍል የተመረጡ ምንባቦችን የተነባቢነት ደረጃ በመረመረበት ጥናቱ ከተመዘገበው በጣም አነስተኛ ውጤት በመነሳት ጌታቸው አዱኛ /1986 ዓ.ም.፡95/ "ተማሪዎች መጽሐፉን አንብበው መረዳት እንደሚችሉ

ቢገልጹም የግንዛቤ ሙከራው (የስግ ሙከራው) ውጤት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በጣም አሳሳቢ መሆኑን ያመለክታል ..." በማለት ተጠኚ ተማሪዎቹ ከሰጡት ምላሽ አንፃር የስግ ሙከራው ውጤት አጠያያቂ መሆኑን ማመልከቱም መጠቀስ ይኖርበታል:: በእርግጥም ከስግ ሙከራው የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ መሆን፥ ምንባቦቹ ከባድ በመሆናቸው ሊሆን ይችላል የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ 95.6% ያህል የሚሆኑት ተጠኚዎች፥ ብዙዎች አፍ በፈቱበት ቋንቋ እየተጨነቁ ያነባሉ ማለቱ፥ ስግ ሙከራ የተነባቢነትን ደረጃ በአስተማማኝ የመለካቱን ሁኔታ አጠያያቂ ማድረጉ የማይቀር ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ኤሌይ /1984:287/ በጥናታቸው ያገኙትንና ከድርሳናት የጠቀሷቸውን ዝቀተኛ የሁለተኛ ቋንቋ የስግ ስርዓት የተነባቢነት ውጤቶችን በመረጃነት ካቀረቡ በኋላ "ለመሆኑ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አፋቸውን ከፈቱ ተጠኚዎች በተገኘ ወጤት ላይ የተመሰረተን የስግ ሥርዓት የንባብ ክብደት ደረጃ መወሰኛ መስፈርት እንዳለ ወስዶ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች መጠቀም ትክክል ይሆን?" በማለት በመጠየቅ፥ ባልደሁፍና ፕሮፐስት "ስግ ሙከራዎች ትክክለኛ የተነባቢነት መለኪያ እንዳይሆኑ ያደረጋቸው .. ተማሪዎች (የ2ኛ ቋንቋ) ከመለየት(recognition) ክሂሎች ይልቅ መደበኛ ስግ ሙከራዎችን ለመሙላት እገዛ የሚደረጉ የአፍልቆት (production) ክሂሎች ስለሚጎሏቸው ነው::" በማለት የገለጹትን በመጥቀስ ራሳቸው ላነሱት አብይ ጥያቄ የአንድምታ ምላሽ አቅርበዋል::

## 2.2.1.2. የአንበቦ መረዳት ችሎታን መለካት

በ1953 ቴለር በስግ ሥርዓት ላይ ያተኮረ ጥናት ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ ሥርዓቱ የተነባቢነት መለኪያ ብቻ ሳይሆን የአንበቦ መረዳት ችሎታ መለኪያም እንደሆነ ይታወቅ ነበር:: /ኦለር. 1979:357፤ ጆንዝ. 1976:255/ በኦለር /1975/ የተጠቀሱት ቴለር በተለያዩ ምንባቦች ላይ የተጠኚዎች የግል ውጤት ይለያይ እንጂ በውጤታቸው መሰረት የሚይዙት ደረጃ (rank) አይለዋወጥም በማለት የተጠኚዎች ውጤት በየምንባቦቹ ላይ ከፍና ዝቅ የሚለው ከምንባቡ የተነባቢነት ደረጃ መለያየት ጋራ እንደሚያያዝ ለማመልከት ያቀረቡት መከራከሪያ፥ በሌላ በኩል የያንዳንዱ ተጠኚ ውጤት ከደረጃ አንፃር /rank order/ አይለዋወጥም ወይም ይዛመዳል ማለትን የሚያመለክት በመሆኑ ሥርዓቱ የያንዳንዱን ተማሪ የአንበቦ መረዳት ችሎታ በአስተማማኝ ሁኔታ እንደሚለካ ያመለክታል:: /ኦለር. 1979:357/

ስግ የአንበቦ መረዳት ሙከራ ብቃት ያለው የንባብ ችሎታ መለኪያ እንደሆነ ፍንጭ ከተገኘ በኋላ ተመራማሪዎች ይህ ሙከራ ከሌሎች ማለትም እንደ ምርጫ

ሰጭ የአንብቦ መረዳት ሙከራ ካሉት ጋራ ያለውን የጋራ ተዛምዶ /correlation/ ፈትሸው ጠንካራ ተዛምዶ እንደሚያሳይ (ብዙውን ጊዜ ከ .6 - .7) አረጋግጠዋል /ኦለር. 1979:357/:: እነዚህ እና መሰል ጥናቶች ስግ የአንብቦ መረዳት ሙከራ እንደማንኛውም የአንብቦ መረዳት መደበኛ ሙከራ አስተማማኝነት እንዳለው ካረጋገጡ በኋላ በርካታ በመደበኛ ደረጃ የሚያገለግሉ ስግ የአንብቦ መረዳት ሙከራዎች ተፈጥረው በሥራ ላይ እንደዋሉና ከነዚህም በጣም የታወቁት Gap እና Gapadol የሚባሉት ሙከራዎች እንደሆኑ ሀሪሰን /1980:93/ ያመለከቱ ሲሆን ራይ /1982:33/ እነዚህን የተጠቀሱትን ጨምሮ የሰባት መደበኛ ስግ የአንብቦ መረዳት ሙከራዎችን ዝርዝር ከነፈልሳፊዎቻቸው የሚያሳይ ሰንጠረዥ አቅርበዋል::

አንዳንድ ምሁራን፥ ለምሳሌ ራይ፥ ስግ የአንብቦ መረዳት ሙከራዎች እንዲያውም ውሱን የሆኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታዎችን ከሚለኩ የተለመዱ የአንብቦ መረዳት ሙከራዎች ከሚከተሉት ነጥቦች አንፃር ለተፈታኝ የተሻለ ጥቅም እንደሚሰጡ አመልክተዋል::

i ቃላትን እንዲያስታወሱ ያደርጋሉ

ii. ፍቻዊ፥ አገባባዊ አንዳንዴም ይትበሃላዊ (stylistic) ሁኔታዎችን በማገናዘብ ግምቶችን እንዲያፈልቁ ይረዳሉ::

iii. ከአረፍተ ነገር አውድ ውጭ በመሄድ በአረፍተ ነገር ውስጥ ላጋጠመ ሐሳብ ትርጓሜ እንዲሰጡ ይረዳሉ::

iv. ቀደም ብሎ ተነቦ ያለፈን ሃሳብ በአሰሳ ንባብ እንዲያጠናክሩ ያግዛሉ::

v. ለግመታ ሊረዳ የሚችል ማንኛውንም መረጃ ወደፊትና ወደኋላ እንዲቃኙ ያደርጋሉ:: /ራይ .1982:32/

ስግ የአንበቦ መረዳት ሙከራን በሚመለከት በአጭሩ የቀረበውን ይህንን ክፍል ለማጠናቀቅ አንድ የማይታለፍ ዋና ሐሳብ ማንሳት ያስፈልጋል:: ይህም በዚህ ሥርዓት የሚቀርብ የአንበቦ መረዳት ሙከራ በትክክል የተማሪዎችን የችሎታ ደረጃ እንዲለካ ከተፈለገ ስግ ሙከራው የሚመሰረትበት ምንባብ ከተፈታኝ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አንፃር መመረጥ ይኖርበታል የሚለው ነው:: አትኬን /1977:60/ "ለስግ የአንበቦ መረዳት ሙከራ ተጠቅሞ የሚውል ምንባብ በተቻለ መጠን ሙከራው በሚመለከታቸው ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ተመጥኖ መመረጥ ይኖርበታል::" በማለት ያቀረቡትም ሐሳብ ይህንኑ የሚያመለክት ነው::

## 2.2.1.3. የምንባብን (text) ተያያዥነት የጥብቀት ደረጃ መለካት (ማጥናት)

ምንም ያህል የሀሳብ ተዛማጅነትና ሰዋሰዋዊ ትክክለኛነት ቢኖራቸው ተናጥል አረፍተ ነገሮችን ደርድረን ምንባብ መፍጠር አንችልም፡፡ በሌላም በኩል የምንባብ አካላትን (ቃላት፥ ሐረጋት፥ አረፍተ ነገሮች ... ወዘተ) ቦታ እንደፈለግን በመለዋወጥ የመጀመሪያውን ምንባብ ማግኘትም አንችልም፡፡ ይህ ሁኔታ ምንባብ የብትን አረፍተ ነገሮች ስብስብ ሳይሆን፥ ሥርዓታዊ ቅንጅትና ተሰናስሎ ያለው እራሱን የቻለ አሃድ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ምንባብ እራሱን የቻለ አቀነጃጀትና ውስጣዊ ትስስር ቢኖረውም፥ የሥነልሳን ሊቃውንት ለዘመናት ያተኩሩ የነበረው በአረፍተ ነገር ደረጃ በተገደበ የቋንቋ ትንተና ላይ ስለነበር በተጠቀሰው ከአረፍተ ነገር በላይ ያለ ቅንጅት ምርመራ ላይ ትኩረት አላደረጉም ነበረ፡፡ /ቻፕማን. 1983:48/ ዘግየት ብሎ ግን በእንግሊዝ፥ በአሜሪካ በተለይ በአውሮፓ የሚገኙ የቋንቋ ጠበብት ከአረፍተ ነገር በላይ ያለን የቋንቋ ቅንጅት መመርመር ጀምረዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከተደረጉ ጥረቶች ለምሳሌ ሃሊዴይና ሀሰን (1976) አረፍተ ነገሮችን በማሰናሰል ምንባብን የሚያስገኙትን አያያዦችና እነዚህ አያያዦች እንዴት እንደሚያገለግሉ በዝርዝር ያሳዩበት 'Cohesion in English' የሚለው መጽሐፋቸው ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ምሁራን ባደረጉት ጥናት ዲስኩር (discourse) ምንባብን የሚያያይዝ ሃይል እንደሆነ ያሳዩ ቢሆንም የማያያዝ ሃይሉ ምን ያህል እንደሆነ የመወሰኑ ነገር ግን ለቋንቋ ሊቃውንት ምስጢር ሆኖ ቆይቶ ነበር፡፡ ዲስኩር ምንባብን የሚያያይዝበትን ሃይል መጠን ምስጢር ማወቅ የዲስኩር ሰዋሰውንና (discourse grammar) ተማሪ ይህንን እንዴት እንደሚቀስም የሚያሳይ ትወራ ለማመንጨት ይጠቅማል፡፡ /ቺሃራ et al. 1977:63/ ቺሃራ et al. ይህንን የምንባብ ተያያዥነት መጠን ለመለካት ስለሚቻልበት አማራጭ ካሮልን ጠቅሰው "ዲስኩር ምንባብን የሚያያይዝበትን ሃይል መጠን ለመመርመር ከሚያስችሉ መሳሪያዎች አንዱ ስግ ሥርዓት ነው፡፡" የሚል ጥቆማ የሰጡ ሲሆን፥ ኦለርም /1979:359/ ይህንን አስመልክተው "ስግ ሥርዓት ምንባብን የማያያዝ ባህርይ ያላቸው ነገሮች መኖራቸውንና ... እነዚህ አውደምንባባዊ አያያዦች ምን ያህል የማያያዝ ሃይል እንዳላቸው ለመለካት ይጠቅማል፡፡" በማለት ሥርዓቱ የምንባብን ተየያያዥነት ጥብቀት ልክ ብቻ ሳይሆን ምንባብን የሚያይዝ ነገር መኖሩንም ለማወቅ እንደሚያስችል አመልክተዋል፡፡

በስግ ሥርዓት በመረዳት የምንባብን ተያያዥነት ለመመርመር ከተደረጉ ጥናቶች አንዱ በባችማን /1985:536/ የተጠቀሰው የራማኡስካስ ጥናት ሲሆን እኚህ

ተመራማሪ ለእንግሊዝኛ አፍ ፈት ተናጋሪ ተጠኚዎች ሁለት ስግ ምንባቦችን፥ አንደኛውን ትክክለኛ ክትትል ካለው ምንባብ ሌላውን ሆነ ተብሎ ክትትሉ ከተዘበራረቀ ምንባብ አዘጋጅተው ለፈተና በማቅረብ ባገኙት ውጤት፥ ክትትሉን በጠበቀው ምንባብ ላይ የተመሰረተውን ስግ ምንባብ የተፈተኑ ተጠኚዎች ከሌሎቹ የላቀ ውጤት አስመዝግበው እንደተገኙ አመልክተዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት ውጤቱ ስግ ሥርዓት በምንባብ ውስጥ ከአረፍተ ነገር በላይ ያሉ ሥነ-ልሳናዊ አያያዦች ስለመኖራቸው ፍንጭ የመስጠት ብቃት እንዳለው ያሳያል ብለዋል፡፡

ኦላር (1975) የስግ ሥርዓት ክፍተቶች ከአረፍተ ነገር በላይ ካሉ አውዳዊ ፍንጮች ጋራ ያላቸውን መሳሳብ ለማጥናት፥ የአንድን ምንባብ አምስት ቅጂዎች፥ አንደኛውን እንዳለ ክትትሉን እንደጠበቀ፥ ሁለተኛውን በአምስት አምስት፥ ሦስተኛውን በአስር በአስር፥ አራተኛውን በሃያ አምስት በሃያ አምስት፥ አምስተኛውን በሃምሳ በሃምሳ ቃላት ስብስብ (chunk) ከፋፍለው በየምንባቦቹ ውስጥ የስብስቦቹን አቀማመጥ ካዘበራረቁ በኋላ፥ በአምስቱ ምንባቦች ላይ የተመሰረቱ ስግ ሙከራዎችን ለአፍ ፈት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሰጥተው፥ ትክክለኛ ክትትል በጠበቀው ምንባብ የተፈተኑ ተማሪዎች ውጤት ከሌሎቹ ልቆ ተገኝቷል ብለዋል፡፡ በተዘበራረቁት ምንባቦች ከተፈተኑትም ከባለ አምስት አምስት ቃላት ስብስቦቹ ወደ ባለ ሃምሳ ሃምሳ ቃላት ስብስቦቹ ደረጃ በደረጃ የተማሪዎቹ ውጤት እየጨመረ እንደሄደ አመልክተው፥ ይህ ሁኔታ ለስግ ክፍተቶች የሚሰጠው ምላሽ በአውደ ምንባብ ውስጥ በርቀት ከሚገኙ ፍንጮች ጋራ ያለውን ጥምረት እንደሚያመለክት ገልጸዋል፡፡

አንዳንድ ተመራማሪዎች የኦለር/1975/ ጥናት ቃላትን በስብስብ የከፋፈለው የአረፍተ ነገሮችን ድንበር ባለጠበቀ ሁኔታ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው ባመለከቱት ሃሳብ ግፊት ቺሃራ et al. /1977/ የአረፍተ ነገሮችን ድንበር በመጠበቅ ሁለት ምንባቦችን አንደኛውን ትክክለኛ የአወራረድ ክትትሉን እንደጠበቀ፥ ሁለተኛውን የአቀነጃጀት ክትትሉን በማዘበራረቅ ስግ ምንባብ በመዘጋጀት ለአፍ-ፈትና ኢ-አፍ ፈት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመፈተን በተገኘው ውጤት፥ ሁሉም ተፈታኞች ከተዘበራረቀው ይልቅ ክትትሉን በጠበቀው ስግ ምንባብ የላቀ ውጤት እንዳስመዘገቡና በሁለቱም ዓይነት ስግ ሙከራዎች አፍ-ፈትና ከፍተኛ የቋንቋ በቃት ያላቸው ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ያገኙት መቶኛ ወጤት ልቆ መገኘቱን በማረጋገጥ፥ በአንድ በኩል ቀደም ሲል ኦለር /1975/ ባደረጉት ጥናት ያስመዘገቡትን ግኝት ትክክለኛነት ሲያረጋግጡ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የላቀ የቋንቋ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ከሌሎች በበለጠ በዲስኩር አያያዦች ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉና በዚህም በመረዳት በተሻለ ሁኔታ ከምንባብ ሀሳብ እንደሚያገኙ አመልክተዋል፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ጥናት /ቺሃራ et al. 1977/ የተገኘውን መረጃ በመጠቀም ቻቬዝ et al. /1985/ ባደረጉት ቀጣይ ጥናት ከስግ ክፍተቶች (cloze items) ከሚገኙበት አረፍተ ነገር ውጭ ካለ ፍንጭ ጋራ ይበልጥ የሚያያዙትን ለመለየት እያንዳንዱን ክፍተት በመመርመር ባደረጉት ጥናት ከሁለቱ ስግ ምንባቦች ከያንዳዳቸው 10% የሚሆኑ ክፍተቶች (items) በከፍተኛ ሁኔታ ከአረፍተ ነገር ዘለል ፍንጮች ጋራ እንደሚያያዙ አረጋግጠዋል::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥናቶች በሙሉ ስግ ሥርዓት በምንባብ ውስጥ አያያዥ ኃይል መኖሩን መጠቆም እንደሚችልና የአያያዥ ሃይሉንም የማያያዝ ጉልበት የመለካት ብቃት እንዳለው የሚቀበሉ ሲሆኑ ሌሎች ምሁራን ደግሞ ባደረጉት ጥናት የዚህ ተቃራኒ የሆነ ውጤት ላይ እንደደረሱ አመልክተዋል:: ከነዚህ ወስጥ ለምሳሌ በባችማን /1985:537/ የተጠቀሱት ሻንሃን በአቦስጥ ገደፋ ከተዘጋጀ ስግ ምንባብ ሦስት ቅጂዎች መካከል አንደኛውን ትክክለኛ ክትትሉን እንደጠበቀ÷ ሁለተኛውን ክትትሉን በማዘበራረቅ÷ ሦስተኛውን ደግሞ በመከፋፈል የተከፋፈሉትን ክፍሎች በሌላ ግንኙነት በሌለው ምንባብ ውስጥ በመሰግሰግ ሦስት የተለያዩ ስግ ሙከራዎች በማዘጋጀት ለተጠኚዎች አቅርበው በሦስቱ የተለያዩ ፈተናዎች በተመዘኑ ተጠኚዎች ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት እንደልተገኘ አመልክተው÷ በዚህ ምክንያት ስግ ሥርዓት በምንባብ ውስጥ ያሉትን መልእክቶች ተሰናስሎ ሊለካ አይችልም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል::

ሌላው የስግ ሥርዓትን የምንባብ ተያያዥነት መለካት አስመልክቶ አሉታዊ ግኝት ያመለከቱ ፖርተር /1978/ ሲሆኑ÷እኚህ ተመራማሪ ከአንድ ምንባብ በእኩል ተራርቆ ከተለያየ ቦታ በመጀመር በአቦሰጣዊ ገደፋ ቃላትን በማስወገድ የተለያዩ ስግ ምንባቦችን በማዘጋጀት ተጠኚዎችን ከፈተኑ በኋላ ካገኙት ውጤት በስግ ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ክፍተቶች ከአጠቃላይ ምንባብ ጋራ ያላቸው ተሰናስሎ ከክፍተቶች ግራና ቀኝ ከአምስትና ስድስት ቃላት የሚበልጥ አይደለም ካሉ በኋላ ገደፋው በሚጀምርበት ቃል (ቦታ) መለያየት ብቻ ከአንድ ምንባብ የተገኙ ሁለት ስግ ምንባቦች በተጠኚዎች ውጤት መቶኛ ስሌት አማካይ ላይ ከፍተኛ ልዩነት ያስከተለ መሆኑ ሥርዓቱ የክብደት ተመጣጣኝነት የማይታይበትና የማያስተማምን መሆኑን የሚያመለክት ነው ብለዋል::

አልደርሰን /1979:225/ ካደረጉት ጥናት ከፍቻዊ ተቀባይነት አንፃር ታርመው (semantically acceptable scoring) የተገኙ ውጤቶች÷ ከትክክለኛ መልስ አንፃር ታርመው (exact answer scoring) ከተገኙት ውጤቶች ጋራ የላቸው የጋራ ተዛምዶ

(correlation) በማስላት በውጤቶቹ መካከል ከፍተኛ የጋራ ተዛምዶ እንደሚታይ (ከ.86-.91) በማረጋገጣቸው፥ ቀደም ያሉ ጥናቶች፥ አንደኛ ከፍቻዊ ተቀባይነት አንፃር ታርመው የተገኙ ውጤቶች በረዥም ርቀት ከሚገኙ አውዳዊ ሁኔታዎች ጋራ ያላቸው ተያያዥነት ዝቀተኛ ነው፤ እና ሁለተኛ ከትክክለኛ ምላሽ አንፃር ታርመው የተገኙ ወጤቶች በርቀት ከሚገኙ አውዳዊ ሁኔታዎች ጋራ ጥብቅ ቁርኝት አላቸው ፤ በማለት ከደረሱባቸው ማጠቃለያዎች፥ ከላይ እንደተገለጸው ሁለቱ የአስተራረም ስልቶች ከፍተኛ የጋራ ተዛምዶ ያሳዩ በመሆናቸው ምክንያት ውድቅ ስለሚሆን በስግ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ ክፍት ቦታዎች በርቀት ከሚገኙ አውዳዊ ሁኔታዎች ጋራ ግንኙነት የሌላቸውና ስግ ሥርዓት በአረፍተ ነገር ደረጃ የተቀነበበ መሆኑን ገልጸዋል::

## 2.2.1.4. የትምህርት መርሃ ግብርን ውጤታማነት መገምገም

ስግ ሥርዓት በተለያየ መንገድ የትምህርት መርሃ ግብርን ለመገምገም ይረዳል:: ሥርዓቱ የትምህርት መርሃ ግብርን ለመገምገምያነት ከሚውልባቸው መንገዶች አንዱ ቀደም ሲል ከተነባቢነት መለኪያነት አንፃር ስላለው ጠቀሜታ ከተገለጸው ጋራ ይያያዛል:: ኦለር /1979:362/ ስግ ሥርዓት በተለያየ የክፍል ደረጃ ለማስተማር ተግባር አገልግሎት ተዘጋጅተው የቀረቡ መጻሕፍትን የተነባቢነት ደረጃ በመለካት የትምህርት መሳሪያዎችን አዘጋጃጀት አስመልክቶ የተወሰደውን ሥርዓት ትምህርታዊ ውሳኔ ለመገምገም ሊውል ይችላል ያሉትም ይህንኑ ይመለከታል::

ስግ ሥርዓት፥ ለማስተማር ሲባል የሰዋሰው ክፍሎችን ከተለመደው አውዳዊ ተጠቀሞ ነጥሎ ለትምህርት ከማቅረብ በተቃራኒ፥ ከልዩ የዲስኩር አውዶች (particular context of discourse) ጋራ በማያያዝ ለተማሪው የሚቀርበውን ተግባሮታዊ የቋንቋ ትምህርት (functional language) (ምግብ ቤት ገብቶ ምግብ ማዘዝ፥ አየር መንገድ ቢሮ ሄዶ ቲኬት መቁረጥ፥ በስልክ መልእክት መቀበልና የመሳሰሉትን) ለመገምገም ካለው ተገቢነት አንፃር ልዩ ቦታ ይሰጠዋል:: የዚህ ዓይነቱን የትምህርት አቀራረብ ለምሳሌ ምግብ ቤት ገብቶ እንዴት ምግብ እንደሚታዘዝ በተግባር የቀረበውን ትምህርት - ምግብ ቤት በተካሄደ እውነተኛ የምግብ ማዘዝ ምልልስ ላይ የተመሰረተ ስግ ምንባብ በማቅረብ በተሻለ ብቃት መገምገም ይቻላል /ኦለር. 1979:363/:: ኦለር ከዚህ በማያያዝ ተማሪዎች የተወሰነ ይዘትን እንዲያጠኑ ከተደረገ በኋላ- በዚያ በተጠናው ጽሑፍ ላይ በመመርኮዝ ስግ ሙከራን አዘጋጅቶ በማቅረብ የተከናወነውን ጥናት የስርጸት ደረጃ ለመገምገም ይቻላል ብለዋል::

የቋንቋ ቅርጻዊ ገጽታን አስመልክቶ የተነደፉ ዝርዝር ዓላማዎችን ከመገምገም አንፃር ስግ ሥርዓት ያለውን አስተዋጽኦ ኦለር /1979:362/ "የሰዋሰውን ንኡሳን ክፍሎች (ሥነ-ድምፅ፥ ሥነ-ምዕላድና አገባብን) ነጣጥለው ከሚያቀርቡ ሙከራዎች (discrete point tests) በተቃራኒ ስግ ሥርዓት የሰዋሰዋዊ እውቀትን የተለያዩ ክፍሎች በአውዳዊ ሁኔታዎች ውስጥ ይጠይቃል:: እንዲህም በመሆኑ የተጠቀሱትን የሰዋሰው ትምህርት ክፍሎች ለማስተማር የተነደፉትን ዝርዝር ዓላማዎች ውጤታማነት በመገምገም ረገድ ስግ ሥርዓት ብልጫ አለው::" በማለት ገልጸዋል::

በንባብ ትምህርት መርሃ ግብር የተነደፉ ዝርዝር ዓላማዎችን በመመርኮዝ ተገቢው ትምህርት ከተሰጠ በኋላ የቀረበው ትምህርት የተማሪዎችን ችግር ምን ያህል እንዳቃለለ ወይም በተሰጠው ትምህርት አጋዥነት ሳይወገድ የቀረ ችግር እንዳለ በስግ ሥርዓት መገምገም ይቻላል:: ይህንን አስመልክቶ ራይ /1982:75/ በስግ ሙከራ ላይ የተፈጸሙትን ስህተቶች በመተንተን መምህሩ እያንዳንዱ ተማሪ በሚያነብበት ጊዜ በቋንቋ አፍልቆት (production) ረገድ የሚታይበትን የተለየ ችግር በሚመለከት ግንዛቤ ማግኘት ይችላል::" በማለት ተማሪዎች ስግ ምንባቦችን ለማሟላት በሚሰጧቸው መልሶች ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶች በአራት ከፍለው በማሳየት የያንዳንዱን ተማሪ ስህተት በነዚህ አራት ክፍሎች መድቦ የመቶኛ ስሌቱን በማግኘት እንዴት የሚታየውን ችግር መጠን ማመልከት እንደሚቻል ዘርዘር አድርገው አስረድተዋል::

በስግ ሥርዓት ክንዋኔ ውስጥ ቁልፍ የሆነው ችሎታ ተደራች መረጃን የመጠቀም /redundancy utilisation/ ብቃት ነው:: ይህም በተገደፈው ቃል አካባቢ የሚገኙትን የተለያዩ ፍንጮች የመመርመር ችሎታ የጠፋውን ቃል በትክክል ለመተንበይ መሠረት መሆኑን ያመለክታል:: ሀሪሰን/1980:95/ የተጠቀሰው አውዳዊ ሁኔታን በመመርመር የተጠቀሰውን መረጃ በማጤን ምላሽ የማመንጨት ችሎታ የሌላቸውን ተማሪዎች በቀላሉ ለስግ ሙከራ ከሚሰጡት ምላሽ መለየት ይቻላል በማለት አንድ ተማሪ ለስግ ሙከራ የሰጠውን ምላሽ በመተንተን ምላሾቹ እንዴት የተማሪውን ድክመቶች እንደሚያመለክቱ ገልጸዋል::

### 2.2.1.5 አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን መለካት

የቋንቋ ብቃት ሙከራ (language proficiency test) መደበኛ የቋንቋ ትምህርት ክትትልን ለመመዘን ከሚሰጡት ሙከራዎች የተለየ ነው:: የቋንቋ ብቃት ሙከራን ልዩ ባህርይ በሚመለከት ሂተን /1988:172-173/ "የቋንቋ ብቃት ሙከራ ወደፊት ተማሪ በታላሚ ቋንቋ ያከናውናቸዋል ተብለው ከሚገመቱ ክንዋኔዎች አንፃር-

ተማሪው በዚያ ቋንቋ ያለውን ነባራዊ እውቀት ለመለካት የሚቀርብ ሙከራ ነው፡፡" ብለዋል፡፡ የተጠቀሰውን ሙከራ ምንነት አስመልክተው አልደርሰን /1980፡60/ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> የቋንቋ ብቃት ሙከራዎች በተለምዶ ኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች ምን ያህል ወደ አፍ ፈት ተናጋሪዎች የተቃረበ የቋንቋ ችሎታ እንዳላቸው ለማረጋገጥ የሚሰጡ ሙከራዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሙከራዎች በተለይ ኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች በታላሚ ቋንቋ ድባብ ውስጥ ምን ያህል በዚያ ቋንቋ እንደ አፍ ፈት ተናጋሪዎች የሚጠበቅባቸውን ማከናወን እንደሚችሉ ለመፈተሽ የሚሰጡ ናቸው፡፡ እንዲህም በመሆኑ የቋንቋ ብቃት ሙከራ አፍ-ፈት ተናጋሪዎችን በችሎታ ደረጃ ከፋፍሎ ማሳየት የማይችልና ሁሉም በተቀራራቢ የብቃት ደረጃ የሚያከናውኑት ነው፡፡ የቋንቋ ብቃት ሙከራ በግልጽ ለይቶ ማሳየት የሚችለው በአፍ-ፈት ተናጋሪዎችና በኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች መካከል ያለንና፥ ለቋንቋው እንደመጋለጣቸው መጠን በኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች መካከል ያለን የቋንቋ ብቃት ልዩነት ነው፡፡

የቋንቋ ብቃት ፈተና ከላይ አልደርሰን እንደገለጹት በአፍ-ፈት ተናጋሪዎች ላይ ያተኮረ ሙከራ ባለመሆኑ የሚያካትታቸው ጥያቄዎች ከኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች የቋንቋ ብቃት ጋር የተመጣጠኑ ናቸው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ፊሸር /1981፡208/ የውስጣዊ የቋንቋ ብቃት ሙከራዎች /linguistic competence tests/ በመሠረቱ የእውቀት እንጂ የአፍልቆት (Production) ሙከራዎች አይደሉም፡፡ እነዚህ ሙከራዎች ተማሪ ሥርዓተ ቋንቋን በሚመለከት ያለውን ነባራዊ እውቀት ይጠይቃሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪ የሥርዓተ ቋንቋ እውቀቱን በላያቸው ላይ አውሎ እንዲገመግማቸው እድል የሚሰጡ ሙከራዎች የተማሪውን ችሎታ ጥርት ባላ ሁኔታ ያሳያሉ ብለዋል፡፡ ከፊሸር አባባል እንደምንረዳው የቋንቋ ብቃት ሙከራዎች ተማሪዎችን ከራሳቸው አፍልቀው መልስ እንዲሰጡ አይጠይቁም፡፡ በአንፃሩ ጥያቄዎችን ከአማራጭ የምላሽ ፍንጮች ጋራ በማቅረብ ተማሪው የቋንቋ ችሎታውን በመጠቀም ፍንጮቹን በመገምገም ምላሽ እንዲሰጥ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ ስለ ቋንቋ ብቃት ሙከራ የተሰጠውን መግለጫ ያሚላል የሚሉትን የሙከራ ዓይነትና የመለካት ብቃቱን ፊሸር እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

> የውጭ ቋንቋ ብቃትን በትክክል መለካት ከሚችሉ የቋንቋ ብቃት ሙከራዎች አንዱ ስገ ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ሥርዓት በአንፃራዊነት ሲታይ የተማሪን የቋንቋ ብቃት ደረጃ መለካት ብቻ ሳይሆን ተግባቦታዊ ሁኔታ ከሚጠይቀው አውዳዊነት ጋራም ያስተዋውቀዋል፡፡ ከዚያም ከማህበራዊ አጠቃቀም ተነጥሎ ካለ የቋንቋ ብቃት /language competence/ ወደ ተግባቦታዊ ብቃት (communicative competence) ያሸጋግረዋል፡፡
>
> /1981፡216/

ስግ ሥርዓት ከላይ እንደተገለጸው የውጭ ቋንቋ ብቃትን፥ ከዚህም በተጨማሪ የሁለተኛ ቋንቋ ብቃትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመለካት ያበቃውን ምስጢር ኦለር /1973፡113/ "የስግ ሥርዓት በተፈተኞች መካከል የሚታይን የቋንቋ ብቃት ልዩነት በትክክል የማመልከት ችሎታ - ምንጩ ምን እንደሆነ ያልታወቀውን የሥርዓቱን ልዩነትን አነፍንፎ የመጠቆም ብቃት - በሌላ አባባል ስግ ሥርዓት ምንን ይለካል ለሚለው ጥያቄ ሁኔታውን በጥልቀት መርምሮ ምላሽ መስጠት ይገባል። በኔ እምነት ስግ ሥርዓት የሚለካው አብይ ጉዳይ እኔ ግምታለም ሰዋሰው (grammar of expectancy) የምለውን ነገር ነው።" በዚህ ውስጥ 'ግታለም ሰዋሰው' በሚል በኦለር የተገለጸው አንድ ሰው በቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ በየጊዜው እየቀሰመ በአእምሮው ውስጥ የሚያከማቸው የቋንቋ ሥርዓት ንድፍ ሲሆን፥ /ኦለር. 1979፡30/ ይህ ንድፍ በቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ ምን ከምን ተከትሎ እንደሚመጣ ይጠቁማል። ስግ ሥርዓትን ለማሟላት የሚያስችለውም ይሄው በቋንቋ ለመዳ ሂደት በአእምሮ ውስጥ የተከማቸ የቋንቋ እውቀት ንድፍ ለተፈታኙ ግምት የሚሰጠው ፍንጭ ነው። በሌላ መንገድ ስግ ሥርዓት የሚለካው የተማሪውን 'ግምታለም ሰዋሰው' ነው። /ኦለር. 1979፡344/

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የቋንቋ ብቃት ሙከራ አንዱ መለያ በአፍ-ፈትና በኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች መካከል ያለውን የቋንቋ ብቃት ልዩነት በግልጽ ማሳየትና ኢ-አፍ ፈቶችንም እንደችሎታቸው በደረጃ ለይቶ ማስቀመጥ መቻሉ ነው። ከዚህ አንፃር ባችማን ባደረጉት ጥናት /1985፡546/ ከስግ ሙከራዎች የተገኙ ውጤቶች፥ ሥርዓቱ የተለያየ የቋንቋ ብቃት ደረጃ ባላቸው ኢ-አፍ ፈት ተጠኚዎች መካከል ያለን ልዩነትና፥ ባጠቃላይ በኢ-አፍ ፈትና በአፍ-ፈት ተጠኚዎች መካከል ያለን ልዩነት በግልጽ እንደሚያሳይ ጠቁመዋል። ኦለርም/1973፡111/ ከዚሁ ጋራ የሚመሳሰል ውጤት ማግኘታቸውን ጠቁመዋል።

አልደርሰን /1980፡74/ ስግ ስርዓት ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው አንፃር የተጠኚዎችን የቋንቋ ብቃት ደረጃ የመለየት አቅም ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ለመለየት ካደረጉት ጥናት በመነሳት የሚከተለውን ብለዋል፤

> የአፍ-ፈት ተናጋሪዎች የስግ ትግበራ ከኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች ጋራ ተመሳሳይ ነው። የአፍ-ፈት ተናጋሪዎች ውጤት እንደነገሩ ከኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች ውጤት ሻል ያለ ቢሆንም የሚጠበቀውን ያህል ግልጽ ልዩነት እንዳላቸው የሚያመለከት ውጤት አላስመዘገቡም። ይህ ሁኔታ አንድም ቀደም ሲል ከተደረጉት ጥናቶች ስለ ሥርዓቱ እርባና /validity/ ከተዘገቡት ከፍተኛ የጋራ ተዛምዶ

/correlation/ ውጤቶች በተቃራኒ በዚህ ጥናት የተፈተሹት ስግ ሙከራዎች የቋንቋ ብቃትን ለመለካት ተስማሚ ሆነው አለመገኘታቸውን፥ አለበለዚያም የቋንቋ ብቃት ምንነትና ባህርይው በተዛባ መንገድ ሲተረጎም መቆየቱን ያመለክታል፡፡

አልደርሰን እንዲህ ብለው ያጠቃሉ እንጂ እራሳቸውም እንደጠቆሙት በርካታ ጥናቶች ስግ ሥርዓት ከተለያዩ መደበኛ የቋንቋ ብቃት ሙከራዎች ጋራ ያለው የጋራ ተዛምዶ በተለያዩ ጥናቶች ተሰልቶ እርባና እንዳለው ተረጋግጧል፡፡ ከነዚህ ጥናቶች ውስጥም ለምሳሌ ኦለር/1972፥ 1973/፥ ስታብስና ተከር /1974/፥ አትኬን /1977/ እና ባችማን /1985/ ያደረጉትን ጥናት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኦለር /1973፡111/ የስግ ስርዓትን አስተማማኝነት /reliability/ በሚመለከት የተደረጉትን ጥናቶች ከዘረዘሩ በኋላ ከነዚህ ውስጥ በአቦስጥ ገደፋ ስርዓት ከተዘጋጁት የተገኘው ውጤት በግማሹን መክፈል /split-half/ እና በኩንደር -ሪቻርድሰን ቀመር ተሰልቶ የተገኘው የአስተማማኝነት ደረጃ ከ.80 -.98 እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ከተለያዩ መደበኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃ መለኪያ ሙከራዎች አንዱን (ELBA) እና የቃል ጽሕፈትን (dictation) እንደ መስፈርት በማድረግ ስግ ሥርዓት እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የችሎታ ደረጃ ከመለየት አንፃር ያለውን አርባና (validity) መርምረው ካገኙት ውጤት በመነሳት አልደርሰን /1979፡225-226/ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ስግ ሥርዓት አንብቦ መረዳትን ከሚጠይቀው የELBA ንኡስ ክፍል የበለጠ የጋራ ተዛምዶ ያሳየው ከቃላትና ከሰዋሰው ንኡሳን ክፍሎቹ ጋራ ነው፡፡ ይህም ሥርዓቱ ከአንኳር የቋንቋ ብቃት ይልቅ (አንብቦ መረዳት) በአንፃራዊነት ከዝቅተኛ የቋንቋ ብቃት ጋራ (ቃላትና ሰዋሰው) የበለጠ የጋራ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ስግ ሥርዓትና የቃል ጽሕፈት (dictation) የክሂሎች ተጣምሮ ሙከራዎች /integrative tests/ እንደሆኑ ተደጋገሞ የተነገረላቸውን ያህል ጠንካራ የጋራ ተዛምዶ አላሳዩም ... ሥርዓቱ ከአንኳር የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ከሆነው ከአንብቦ መረዳት ጋራ የጠበቀ የጋራ ተዛምዶ የሌለውና የክሂሎች ተጣምሮ ሙከራ ለመሆኑም ማረጋገጫ ስላልተገኘ (ከቃል ጽህፈት ጋራ ጥብቅ የጋራ ተዛምዶ ባለማሳየቱ) የውጭ ቋንቋን የብቃት ደረጃ ለመለካት አይችልም፡፡

ኦለር /1973/ በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጠውን መደበኛ የ2ኛ ቋንቋ ብቃት መለኪያ (UCLA ESLPE) አራት ንኡሳን ክፍሎች ለስግ ሥርዓት የእርባና መለኪያ መስፈርትነት በመጠቀም ባደረጉት ጥናት ያገኙት ውጤት ስግ ሥርዓት

ከላይ ከተጠቀሰው የ2ኛ ቋንቋ ብቃት መለኪያ ሙከራ የተለያዩ ክፍሎች ይበልጥ የጋራ ተዛምዶ ያሳየው ከአንበቦ መረዳትና ከቃል ጽሕፈት ንኡሳን ክፍሎች ጋራ ነው። ከዚህም በመነሳት ከላይ አልደረሰን ካገኙት ውጤት በተቃራኒ "ስግ ሙከራ በከፍተኛ ደረጃ የክሂሎች ተጣምሮን ከሚጠይቁ ሙከራዎች ጋራ ይበልጥ ያጋራ ተዛማጅነት አለው" /ኦለር. 1973:157/ ብለዋል።

## 2.2.2. የስግ ሥርዓት የማስተማሪያ ስልትነት ሚና

ቀደም ሲል በቀረበው የስግ ሥርዓትን የሙከራ መስጫነት የተለያዩ ገጽታዎች የዳሰሰ ክፍል፥ ስርዓቱ በምዘና መሳሪያነት ያለውን የብቃት ደረጃ በተመለከተ የተለያዩ አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከቶች ተንጸባረቀዋል። ይሁን እንጂ ብዙዎች ለምሳሌ ኦለር /1972፥ 1973፥ 108-111/፥ ስታብስና ተከር /1977/፥ አልደረሰን /1979:220/ እና ሌሎችም እራሳቸው አጥንተው ያገኙትንና የተለያዩ ተመራማሪዎችን ጥናቶች በመጠቃቀስ ስግ ሥርዓት አስተማማኝና እርባና ያለው የምዘና መሣሪያ መሆኑን አመልክተዋል። በተለይ አልደርስን /1979:220/ (እሳቸው የማይቀበሉት ቢሆንም) በርካታ የሙከራ አዘጋጆች በነዚህ በተጠቀሱት ጥናቶች፥ በተለይም ኦለር /1972/ ባደረጉት ጥናት በመገፋፋት ይህንን የሙከራ መስጫ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ እርባና እንዳለው በማመን በስፋት በተግባር ላይ ማዋል እንደጀመሩ ጠቁመዋል።

ማንኛውም በሚያስገኘው ጥቅም ግፊት በሥራ ላይ የዋለ ነገር የአገልግሎቱን አድማስ እያሰፋ መሄዱ አይቀርም። በመሆኑም ስግ ሥርዓት በሙከራ መስጫነት ያስገኘውን ትሩፋት ለንባብ ትምህርት አቀራረብ ጠቀሜታ ለማዋል የተለያዩ ሙከራዎች ባደረጉ ተመራማሪዎችና መምህራን ጥረት ከ1960ዎቹ ጀምሮ የሥርዓቱ አገልግሎት ወደ ማስተማሪያ ስልትነትም መስፋት ችሏል /ሀሪሰን. 1980:97/። አልደርሰን/ 1996:212/ "ለማስተማር አገልግሎት ሊውል የማይችል የሙከራ ስልት አለ ብሎ ለማመን ያስቸግራል፤ አንድ የማስተማሪያ ስልት በመጠኑ ለውጥ ተደርጎበት ወይም እንዳለ ወደ ሙከራ ስልትነት ሊለወጥ አይችለም ብሎ መገመትም በእኩል ደረጃ የሚከብድ ነገር ነው።" በማለት የገለጹት-ስግ ሥርዓትን በቀላሉ ከሙከራ መስጫነት ወደ ማስተማሪያ ስልትነት መለወጥ እንደሚቻል ያመለክታል። ይህም ቀደሞ በሥርዓቱ አማካይነት ይጠየቁ የነበሩ ጉዳዮችን - በዚያው በሥርዓቱ በመጠቀም ማስተማር ይቻላል የሚለውን ያንጸባርቃል። ከዚህ አንፃር ሹልዝ /1983:131/ ስግ ሥርዓትን ለማስተማሪያ ስልትነት በመጠቀም ሥርዓቱ በሙከራ መስጫነት ይጠይቃቸው የነበሩትን የሚከተሉትን ጉዳዮች ለትምህርት ማቅረብ እንደሚቻል እንደሚከተለው አመልክተዋል።

> በስግ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ክንዋኔ የቋንቋ እውቀትን ማለትም የቃላት፥ የንግግር ክፍሎች፥ የአገባብ ... ወዘተ እውቀትን፥ የነባራዊ ዓለም እውቀትን ማለትም የምላሽ ግመታን (guess) ለመቀበል ወይም ለመጣል ቀደም ያለ እውቀትን በምንባብ ውስጥ ከተሰጡ አውዳዊ ፍንጮች ጋራ ማገናዘብን፥ መላሽ ማመሳከርን ማለትም በምንባብ ውስጥ ቀደም ብሎ ከተሰጠ ማስረጃ ምላሽን ማመንጨትን፥ እና ገስጋሽ ማመሳከርን ማለትም ጥርጣሬን ለማስወገድ የሚያስችል በቂ ማስረጃ እስኪገኝ እስከ መጨረሻ ወደፊት ማንበብን ይጠይቃል። በሌላ አነጋገር ስግ ሥርዓት በምንባብ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችንና አውዳዊ ፍንጮችን ማገናዘብን የሚጠይቅ ሥርዓት ነው።

ይህንን ካሉ በኋላ እነዚህን በስግ ሙከራ ክንውኖች ውስጥ የሚታዩ ክሂሎች ለማስተማር የሚቻልበትን መንገድ /ሹልዝ 1983፡131/ "በአውደ ምንባብ ላይ በመመርኮዝ ምላሽን የመገመትን ስልት ለማስተማር ብቸኛው ውጤታማ የማለማመጃ መንገድ ስግ ሥርዓት ነው።" በማለት ጠቁመዋል። ቦርትኒክና ሎፖርዶ /1973፡297/ "አውዳዊ ፍንጮችን እንደ ንባብ ስትራተጂ መጠቀምን ለማስተማር ምቹ መሆኑ ስግ ሥርዓት ለንባብ ማስተማሪያ ስልትነት እንዲመረጥ አድርጓል፤ ከዚህም ሌላ የንባብ ትምህርት ዘርፎች የሆኑትን የቃል ትንተና (word analysis)፤ የቃላት ትርጉም፥ አገባብና የመሳሰሉትን ለማስተማሪያነትም ይጠቅማል።" በማለት የገለጹ ሲሆን፥ ሴልሴሙርሲያ /1988፡152/ "በምክንያታዊ ገደፋ ለማስተማር በተፈለገው የሰዋሰው ትምህርት ክፍል ላይ በማተኮር ቃላትን በመግደፍ በተዘጋጀ ስግ ምንባብ በመታገዝ ሰዋሰውን በአውዳዊ ሁኔታ ውስጥ ማስተማር ቀደም ሲል ጀምሮ ሲሰራበት የኖረ የማስተማር ስልት ነው።" በማለት ስግ ሥርዓት ሰዋሰውንም ለማስተማር እንደሚጠቅም ገልጸዋል።

በቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ውስጥ ቀደም ብሎ የተሰጠን ትምህርት ለመከለስ ስግ ሥልትን መጠቀም እንደሚቻል ብራወን /1980፡316/ የገለጹ ሲሆን፥ ለምሳሌ በተጠቀሰው ክፍል ውስጥ ለትምህርት የቀረቡትን ቃላትና ሰዋሰዋዊ አገባቦች በማስወገድ ስግ ምንባብን በማዘጋጀት በመልመጃ መልክ ለተማሪው በማቅረብ ትምህርቱን መከለስ እንደሚቻል አመልክተዋል። በተማሪዎች የቡድን ስግ ልምምድ (cloze exercise) ወቅት የተከታተሉትን የተማሪዎች እየተረዳዱ መማማር ከገመገሙ በኋላ ሉንዘርና ጋርድነር /1979፡236/ "የታየው ልምምድ ስግ ሥርዓት ቴክኒካዊ ቃላትንና ስያሜዎችን በአውደ ምንባብ ውስጥ የማቅረብ ብቃት እንዳለው ያሳያል። መምህራን የመማሪያ መጽሐፍን አንድ ክፍል ወይም በተከታታይ ሲቀርብ የቆየን ትምህርት በስግ ሥርዓት በማቅረብ መከለስና ማጠቃለል ይችላሉ። ከሁለቱ

በመጨረሻ በተጠቀሰው መንገድ ሲሰራበት የቡድን ስግ የተዋጣ የክለሳ መልመጃ ሊሆን ይችላል" ብለዋል፡፡

ስግ ሥርዓት በተለይ ከፍተኛ የክፍል ደረጃ ላይ ላሉ ተማሪዎች የሥነ-ጽሑፍ ማስተማሪያ በመሆን ሊያገለግል ይችላል /ራይ. 1982:99/ ለዚህ ዓይነቱ ተግባር የሚያገለግልን ስግ ምንባብ በሥነ-ጽሑፍ ስራዎች ማለትም በግጥም፥ በአጭር ልቦለድ፥ ከረዥም ልቦለድ ተቀንጭበው በወጡ ምንባቦች... ወዘተ ላይ በመመርኮዝ፥ ለማስተማር ከተፈለገው ጉዳይ ጋር የተያያዙትን ቃላት በምክንያታዊ ገደፋ በማስወገድ ይዘጋጃል፡፡ ተማሪዎች በሥነ-ጽሑፍ አቀራረብ ልዩ ባህርይ ምክንያት የተገደፉትን ቃላት ለመተንበይ እንዳይቸገሩ ከምንባብ ውስጥ የተወገዱትን ቃላት ከስግ ምንባቡ ግርጌ አሰባጥሮ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡

ስግ የማስተማሪያ ስልት ቋንቋን ለማስተማር ልዩ ድጋፍ እንደሚሰጥና ለዚህም ስላበቃው ሁኔታ ቦርትኒክና ሎፖርዶ /1973:297/ "ስግ ሥርዓት ለማስተማር የሚሰጠው ልዩ ድጋፍ የሚመነጨው የሥርዓቱ መሰረት የሆነው ስግ ምንባብ የቋንቋ ምሉእ ገጽታ ላይ የሚያተኩርና የቋንቋ ክሂሎችን ነጣጥሎ ለትምህርት የማያቀርብ መሆኑ ነው፤ በመሆኑም ተማሪው የምንባብን አውዳዊ ገጽታም ሆነ ምንባቡ የቀረበበትን ቋንቋ አወቃቀራዊ ይዞታ የተለያዩ ጠገጎች በአንድ ላይ አጣምሮ በማየት ልምድ ውስጥ ቋንቋን እንዲማር ያደረጋል፡፡"በማለት አመልክተዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ቋንቋን በተለይም ንባብን ለማስተማር ልዩ ድጋፍ ይሰጣል የተባለውን የስግ የማስተማር ስልት አነሳስና እድገት የተመለከቱ ጥናቶችን እንቃኛለን፡፡

ስግ ሥርዓት እንደማስተማሪያ ስልትነት ይጠቅም እንደሆነ ለመፈተሽ የተደረጉ ጥናቶች መታየት የጀመሩተና አልፎ አልፎም ለንባብ ማስተማሪያ ስልትነት መዋል የጀመረው ከ1960ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ እንደሆነ ቀደም ስል ተጠቅሷል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ሥርዓቱ ለማስተማሪያ ዘዴነት ያለውን ጠቀሜታ ለማጥናት በርካታ ምርምሮች ተካሄደዋል፡፡ እስከ 1970 ድረስ በዚህ አቅጣጫ የተደረጉትን ጥናቶች ውጤት ጆንግስማ /1971/ የቃኙ መሆኑን ሀሪስን /1980:97/ በመጥቀስ እስከ 1967 በስግ ምንባብ ውስጥ የሚሰጠው አውዳዊ ጥቆማ ብቻ የንባብ ችሎታን ያዳብራል በሚል ግምት በተለያየ ችሎታ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ስግ መልመጃዎችን በመስጠት በርካታ ጥናቶች የተደረጉ ቢሆንም አመረቂ ውጤት ግን መምጣት አልቻሉም፡፡" ብለዋል፡፡ ለነዚህ ጥናቶች ውጤት አለመስመር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ የሚባሉትን ነጥቦች ራይ /1982:46/ እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፥

1. አንዳንዶቹ ጥናቶች ተማሪዎችን በስግ ሙከራ ያለማመዱት በጣም አጭር ለሆነ የሙከራ ጊዜ ነው::
2. ብዙዎች አጥኚዎች አውዳዊ ሁኔታዎች እንዴት ለምላሽ ማመንጫነት እንደሚጠቅሙ ለተጠኚዎች ስልጠናና መመሪያ አልሰጡም::
3. እስከ 1967 የተደረጉት ብዙዎቹ ጥናቶች በተማሪዎች የቡድን ውይይትና በመምህር ምጋቤ ምላሽ (feedback) የታገዙ አልነበሩም::

በስግ የማስተማር ስልት የቀረበ የንባብ ትምህርት አመርቂ ውጤት እንዳስገኘ የሚያበስረው የመጀመሪያ ጥናት ማርቲኒ /1968/ ለዶክተሬት ዲግሪ መሟያ በዩቨርሲቲ ጀማሪ ተማሪዎች ላይ ያደረጉት ጥናት ነው /ሀሪሰን. 1980፡97/ ለዚህ ጥናት ውጤታማ መሆን እንደ ዋነኛ ምክንያት የተጠቀሰው የእኚህ ተመራማሪ የአጠናን መንገድ የተማሪዎችን የቡድን ውይይት የሚያካትትና ተማሪዎቹ ለሚሰጡት ምላሽ ምክንያት እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ መሆኑ እንደሆነ ተገልጿል::

እዚህ ላይ ከማርቲኒ በፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናት እንዳደረጉ በሀሪሰን /1980፡98/ የተጠቀሱት ብሉመር -የንባብ ችሎታቸውን ያዳብር ይሆናል በሚል ያለ ምንም ምጋቤ ምላሽ እና ውይይት ለአንድ ሺ ህፃናት የተለያዩ ስግ መልመጃዎችን በመስጠት ያደረጉት ጥናት ውጤቱ መና ሲሆንባቸው - ምናልባትም ግልጽ የሆነ ማጠናከሪያ ቢሰጥ ኖሮ ውጤቱ ያማረ ሊሆን ይችል ነበር በማለት የሰጡት ሀሳብ በማርቲኒ ጥናት ተጨባጭ ሆኗል ማለት ይቻላል::

ከዚህ የተሰካ ጥናት በኋላ ስግ ሥርዓት ያለውን የማስተማሪያ ስልትነት ሚና የሚመረምሩ ጥናቶች እየተበራከቱ ሄደው "ሥርዓቱ በተጠናከረ ሁኔታ ከ1970 አካባቢ ጀምሮ ለማስተማሪያ ስልትነት መዋል የጀመረ ሲሆን ተግባራዊነቱን የመረመሩ ጥናቶችም ከፍተኛ ውጤት ማስገኘቹን አረጋግጠዋል::" /ባስቲዳስ. 1984፡21/

ስግ የማስተማሪያ ስልት ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ ውጤታማነቱን ለመፈተሽ ከተካሄዱት ጥናቶች አንዱ በሀሪሰን /1980፡98/ የተጠቀሱት ኬኔዲና ዊነር በ1973 ላይ ያደረጉት ጥናት ሲሆን፥ እኚህ ተመራማሪዎች የስምንት አመት እድሜ ላለአቸው ህፃናት ያቀረቡት የአምስት ክፍለ ጊዜ የሃያ ደቂቃ የስግ ሥርዓት ልምምድ የተጠኚዎችን የማዳመጥና የማንባብ ብቃት በጉልህ ደረጃ እንዳዳበረ አረጋግጠዋል:: የተጠቀሱት ተመራማሪዎች ተጠኚዎቻቸው ከአንድ ቃል በላይ ባለ የምንባብ ክፍል ላይ እንዲያተኩሩ ማድረጋቸውና ለተጠኚዎቻቸው ቁጥጥር የተሞላበት የምላሽ ማረሚያ መስጠት መቻላቸው ለተገኘው ውጤት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል::

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የምርምር ውጤቶች ሌላ አንዳንድ ምሁራን ተማሪዎች በስግ ምንባብ ላይ በቡድን ያደረጉትን ውይይት ተንትነው በጽሑፍ ማውጣታቸው /ሉንዘርና ጋርድነር 1979፤ ራይ 1982:51-54/ ስግ ስርዓት ለማስተማሪያ ስልትነት ያለውን ጠቀሜታ በግልፅ ማሳየት ችሏል።

እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ቋንቋ ማስተማርን በተመለከተ ስግ እንደማስተማሪያ ስልትነት እያገለገለ እንደሚገኝ የሚጠቁሙ አንዳንድ መረጃዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥ ለምሳሌ ጌፌን /1979/ ስግ ሥርዓት በእስራኤል የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ስርጎ በመግባት በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ላይ በመደበኛ ፈተናነት እስከማገልገል መድረሱን ገልጸዋል። እንዲህም በመሆኑ መምህራን ተማሪዎችን ለማዘጋጀት፥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃትን የተለያዩ ዘርፎች ማለትም አንብቦ መረዳትን፥ አዳምጦ መረዳትን፥ የሰዋሰውና የቃላት ችሎታዎችን ለማዳበር በስግ ስልት ማስተማር መጀመራቸው ተመልክቷል።

## 2.2.2.1. ስግ ሥርዓትና አንበቦ መረዳት

ንባብ ውስብስብ ሂደትን ያካተተ ክንዋኔ ነው። በመሆኑም በርካታ ምሁራን 'ንባብ' ለሚለው ስያሜ አጭር ግላጼ ለመስጠት አይደፍሩም። ለምሳሌ ግራቤ /1991:378/ "እንደ ንባብ ላለው ውስብስብ አእምሮአዊ ሂደት ቀላል ግላጼ እሰጣለሁ ማለት ሂደቱን የማይመጥን ውሳኔ ላይ መድረስ ያስከትላል። በመሆኑም ከዚህ ይልቅ ከርቱእ አነባበብ ጋር ስለተያያዙ እውቀቶችና የክንዋኔ ሂደቶች በማውሳት መጀመር የተሻለ ሃሳብ ይሰጣል።" ካሉ በኋላ የተለያዩ ምሁራንን በዋቢነት ጠቅሰው "ርቱእ አነባበብ (fluent reading) በፍጥነት የሚከናወን፥ በዓላማ ላይ የተመሰረተ፥ የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን እንደሁኔታው መጠቀምን የሚጠይቅ፥ በመጨረሻም ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል የሚታይበት ነው በማለት ንባብ የሚለውን ቃል በቀጥታ ለመግለጽ በመሞከር ፋንታ በርቱእ አነባበብ ውስጥ በሚታዩት ሁኔታዎች ገለጻ በሰያፍ መንገድ ምንነቱን አመልክተዋል። ስሚዝ /1985:100/ንባብ ለሚለው ቃል ግላጼ ለመስጠት መሞከር ከማይወጡት የአተረጓጎም ውዝግብ ውስጥ ስለሚያስገባ፥ የንባብን ሂደት በመግለጽ የቃሉን ምንነት ማመልከት እንደሚሻል ጠቁመዋል። የንባብን ምንነት በተዘዋዋሪ ሊያሳይ ይችላል የተባለውን የንባብ ሂደት ጠቅለል ባለ መልክ ማየት ይቻል ዘንድ የሚከተለውን እንመልከት።

> አንዳንድ በጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎች ለአንጎል መድረስ ስላለባቸው አይን በማንባብ ክንዋኔ ውስጥ ቦታ አለው። ይህንን በማየት የምናገኘውን መረጃ እይታዊ መረጃ (visual information) ልንለው

> እንችላለን:: ለማንበብ እይታዊ መረጃ ብቻ በቂ አይደለም፤ ...ከዚህ በተጨማሪ ጽሑፉ የቀረበበትን ቋንቋ ማውቅ፥ የጽሑፉን ይዘት ማወቅና አጠቃላይ የሆነ የንባብ ችሎታ ያስፈልጋል:: እነዚህ ከእይታዊ መረጃዎች በተጨማሪ ያስፈልጋሉ የተባሉት መረጃዎች በአንድ ላይ ተጠቃለው ረቂቅ መረጃዎች (nonvisual information) ይባላሉ::
>
> /ስሚዝ. 1985፡12-13/

ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ውስጥ በንባብ ሂደት ውስጥ መረጃዎች ከሁለት አቅጣጫ እንደሚገኙ ተገልጿል:: አንደኛው የመረጃዎች ምንጭ እራሱ ምንባቡ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የአንባቢው እውቀት ነው:: ይህም የንባብ ሂደት በምንባብ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችንና አንባቢ ወደ ምንባቡ ይዞት ከሚመጣው እውቀት የሚመነጩ መረጃዎችን የሚያቀናጅ ሂደት እንደሆነ ያስገነዝባል:: ይህም ከተጠቀሱት የመረጃ ምንጮች በአንዱ ላይ ብቻ በመመረኮዝ ማንበብ አደጋች መሆኑን በግልጽ ያመለክታል::

በንባብ ሂዳት ውስጥ "... በነባር እውቀት በከፍተኛ ደረጃ መጠቀምና ከገጸ-ንባብ ብዙም አለመጠበቅ ...መሠረታዊ የሆነን የንባብ ችሎታ ያንጸባርቃል::" በማለት ስሚዝ /1985፡15/ የሰነዘሩት ሀሳብ በንባብ ክንዋኔ ሂደት ላይ ከእይታዊ መረጃዎች ይልቅ ረቂቅ መረጃዎች ወይም ከአንባቢ ዳራዊ እውቀት የሚገኙ መረጃዎች ለርቱእ አነባበብ የላቀ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ያመለክታል:: ይህም ቀደም ሲል ግራቤ /1991/ የንባብን ምንነት በርቱእ የአነባበብ ሂደት ገለጻ ካመለከቱበት ጋራ ይጣቀሳል:: ይህም ማለት ስሚዝ እንደገለጹት ከምንባብ ጥቂት መረጃዎችን በናሙናነት በመውሰድ በዳራዊ እውቀት ላይ በከፍተኛ ደረጃ በመመርኮዝ የሚከናወን ንባብ ግራቤ እንዳሉት፥ በፍጥነት የሚከናወን፥ በዓላማ ላይ የተመሰረተ፥ (በለቀማ ስለማይነበብ)፥ በአቋራጭ ወደ መልእክት የመሄድ የአነባበብ ስልት /reading strategy/ በተግባር የሚታይበትና በዳራዊ እውቀት ጫና የማይታወቅን ነገር በመተርጎም መረዳትና መሻሻል የሚንጸባረቅበት ነው::

ቀደም ሲል ግራቤና ስሚዝ የንባብን ምንነት ለመግለጽ የተጠቀሙበትን የንባብ ሂደት ጉድማን/1967/ "የስነልቦናዊ ስነልሳን የትንበያ ጫዋታ" በማለት ገልጸውታል:: ይህንን ያሉትም እንደሳቸው አመለካከት አንባቢ ከገጸ ንባብ የተወሰኑ መረጃዎችን በናሙናነት በመውሰድ - በዚያ ላይ ዳራዊ እውቀቱን በማከል የምንባብን ይዘት ምንነት ይተነብያል:: በመቀጠል የትንበያውን መስመር ምንባቡን በመቃኘት ያረጋግጣል:: በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ስህተት እንዳለ ከታወቀ ይታረማል:: በመሆኑም እንደ ጉድማን አስተያየት በማንበብ ሂደት ውስጥ በስራ ላይ የሚውሉት የሚከተሉት አራት ስትራተጂዎች ናቸው::

1. ናሙና የመውሰድ ስትራተጂ (sampling strategy)- ከገጸ ንበብ የተወሰኑ መረጃዎችን በመውሰድ መነሳት
2. የትንበያ ስትራተጂ (predicting strategy) - በናሙናነት የተወሰደውን ከግል እውቀት ጋራ በማገናዘብ ስለ ምንባብ ምንነት መላ ምት ማመንጨት
3. የማረጋገጥ ስትራተጂ (confirmation strategy)- የመነጨውን መላ ምት ከምንባቡ አውድ ጋር በማገናዘብ የግምቱን መስመር መፈተሽ
4. የእርማት ስትራተጂ (correction strategy) በማረጋገጥ ክንዋኔ የተገኘ ህጸጽ ካለ ማቃናት

ከዚህ በላይ ጉድማን የንባብ ሂደትን 'የስነልቦናዊ ስነልሳን የትንበያ ጨዋታ' በማለት ከገለጹት ውስጥ 'የትንበያ ጫዋታ' የተባለው ቀደም ሲል ስሚዝ ዳራዊ እውቀትን በበለጠ በመጠቀም ከገጸ ንባብ ጥቂት ናሙና ጨልፎ በማዋሃድ (ቀሪውን እየገመቱ) ማንበብ መሠረታዊ የንባብ ችሎታን ያንፀባርቃል ካሉት ጋር ይጣጣማል፡፡ የንባብ ሂደት ስነልቦናዊ ስነልሳን ነው ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ ለመግለጽ ጉድማን /1988፡12/ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ንባብ አስራጊ (receptive) የቋንቋ ሂደት ነው፡፡ ይህ ሂደት ጸሐፊው በስነ-ልሳናዊ ላዕላይ ቅርፅ ትእምርትነት በሚያስተላልፈው መልእክት ተጀምሮ አንባቢው አቀናብሮ በሚገነባው ትርጉም የሚጠናቀቅ በመሆኑ የስነልቦናዊ ስነልሳን ሂደት ነው፡፡ እንዲህም በመሆኑ በንባብ ሂደት ውስጥ በቋንቋና በሀሳብ መካከል በገሃድ የሚታይ ተራክቦ አለ፡፡ ጸሐፊው ሀሳቡን በቋንቋ አማካይነት በትእምርታዊ መልክ ያስተላልፋል እንዲሁም አንባቢ ቋንቋን ወደ ሀሳብ ይተረጉማል፡፡

ከተጠቀሰው የምንረዳው የንባብ ሂደት የሀሳብና የቋንቋ ተራክቧዊ ግንኙነት የሚፀባረቅበት መሆኑን ነው፡፡ ይህም በመጀመሪያ ደራሲ ሀሳቡን በቋንቋ አማካይነት በጽሑፋዊ ትዕምርቶች ያስተላልፋል ቀጥሎ አንባቢ እይታዊና ረቂቅ መረጃዎችን በተለይ ረቂቅ መረጃዎችን ይበልጥ ተግባራዊ በማድረግ በመተርጎም ደራሲው ያስተላለፈለትን ሀሳብ መልሶ ይገነባል የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

ከላይ የተመለከተው የስነልቦናዊ ስነልሳን የንባብ ሂደት አተረጓጎም ንባብ ምንድነው? የሚለውን ከባድ ጥያቄ ለመመለስ በተደረጉ ጥረቶችና፥ በጥረቶቹ ውስጥ ባጋጠሙ ያተረጓጎም ውዝግቦች ላይ ብርሃን በመፈንጠቅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ

አድርጓል:: ይሁን እንጂ ስለ ንባብ ትምህርት አቀራረብ ስልት የፈነጠቀው ነገር ብዙ አይደለም:: "የንባብ ስነልቦናዊ ስነልሳን መርሆዎች ስለንባብ ሂደት ያለንን ግንዛቤ በማበልጸግ ረገድ አስተዋጽኦ ቢኖራቸውም የስነልቦናዊ ስነልሳን ንባብ ማስተማሪያ ስልት ግን ያካተቱ አይደሉም" /ክላርክና ሲልበርስታይን. 1977:135/::

እንዲህም በመሆኑ መርሆዎቹ የሚያንጸባርቁትን ጠቃሚ ነጥቦች በመውሰድ በተግባር የንባብን ትምህርት ሊረዱ የሚችሉ ማስተማሪያዎችንና አተገባበራቸውን መቀየስ በመምህራን ጫንቃ ላይ ወድቋል:: የስነልቦናዊ ስነልሳን ንባብ መርሆዎች በምን አቅጣጫ ለትምህርት መቅረብ እንደሚችሉ ራይ/1982:7/ "በርቱእ የማንበብ ክንዋኔ ውስጥ የሚታየው ሂደት በአንዳንድ መንገድ የስግ ክፍተቶችን ከመሙላት ሂደት ጋራ ይመሳሰላል:: ስግ ሥርዓት የማንበብ ክሂሎችን ሊያዳብሩ ከሚችሉ መንገዶች አንዱ ሊሆን ይችላል የሚል ሀሳብ የተፀነሰውም በዚህ ተመሳሳይነት ምክንያት ነው::" በማለት ከጠቆሙ በኋላ ቀደም ሲል በስነልቦናዊ ስነልሳን የንባብ ሂደት ውስጥ ይታያሉ በማለት ጉድማን /1967/ ከጠቀሱዋቸው አራት ስትራተጂዎች ጋራ የሚመሳሰለውን የስግ ክፍተቶች አሞላል ሂደት እንደሚከተለው ዘርዝረዋል::

1. .ከስግ ምንባብ ውስጥ ያሉ ጠቃሚ አውዳዊ መረጃዎችን በናሙናነት መውሰድ (sampling)
2. ምላሽን መተንበይ (በስግ ክፍተቶች ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ቃላትን መገመት) (predicting)
3. ማረጋገጥ (በትንበያ በስግ ክፍተቶች ውስጥ የገቡት ቃላት ከምንባቡ አውዳዊ ሁኔታዎች ጋራ ያላቸውን ተጣጣሚነት መፈተሽ) (Confirming)
4. ማረም (ከስግ ምንባቡ አውዳዊ ሁኔታዎች ጋራ ያልተጣጣሙ ምላሾች ካጋጠሙ ማስተካከል::) (Correcting) /ራይ. 1982:7/

የስነልቦናዊ ስነልሳን የንባብ መርሆዎችን ንድፈ ሀሳባዊ ፍሬ ሀሳቦች ወደ ንባብ ትምህርት በመውሰድ ለማስተማር ሊያገለግል ስለሚችል የማስተማሪያ ዘዴ ባስቲዳስ/1984:24/ "በስነልቦናዊ ስነልሳን የንባብ መርሆዎች ውስጥ የሚንጸባረቁትን ጠቃሚ ነጥቦች በንባብ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ እውን ለማድረግ የሚያስችል ከመሆኑ አንፃር ስግ ሥርዓት በጥሩ ምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል::" በማለት ገልጸዋል::

በንባብ ክንዋኔ ውስጥ ግንዛቤ (Comprehension) የሚባለው አንባቢ በንባብ ሂደት ውስጥ የሚያመነጨውን ትንበያ ስምረት ይመለከታል:: ግንዛቤን

የሚያስገኘውን የሰመረ ትንበያ ለማመንጨት ደግሞ በመጀመሪያ መነሞን፤ መተንበይ፣ ማረጋገጥ፣ ማቃናት የሚሉትን በንባብ ሂደት ውስጥ የሚሰራባቸው ስትራተጂዎች ማወቅን፣ ከዚያም በነዚህ ስትራተጂዎች መሣሪያነት ከምንባብ ሃሳብ ለማግኘት መታገልን ይጠይቃል:: ከተጠቀሱት የንባብ ስትራተጂዎች ጋር ተዋውቆ በነሱ መሣሪያነት ከምንባብ ውስጥ ሀሳብን ፈልፍሎ በማውጣት ወደ ግንዛቤ (Comprehension) ለመድረስ የሚደረግ ሂደታዊ ክንዋኔ መረዳት (comprending) ይባላል:: ስሚዝ /1985፡103/ "መረዳት ምንባብን አስመልክቶ የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅን የሚመለከት ሲሆን መገንዘብ ደግሞ ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘትን ይመለከታል::" በማለት በገለጹት ውስጥ መረዳት ጥያቄዎች በመጠየቅ ወደ ምላሽ ፍላጋ መጓዝን የሚያመለክት ሂደት እንደሆነና መገንዘብም በምላሽ መገኘት የተጠናቀቀ የዚህ ሂደት ውጤት እንደሆነ ተመልክቷል::

መረዳትና ግንዛቤ ያላቸውን ልዩነትና ከሁለቱ የትኛው ለንባብ አስተማሪ ፍሬያማ የማስተማር አቅጣጫን እንደሚያመለክት ቻፕማን /1983፡125-126/ እንደሚከተለው ገልጸዋል::

> ንባብ ሂደትንና ውጤትን የሚመለከቱ መረዳት (comprehending) እና ግንዛቤ (Comprehension) የሚባሉ ሁለት እሳቤዎችን አጣምሮ ይይዛል:: ግንዛቤ ለንባብ ውጤት የሚሰጥ ስያሜ ሲሆን በተለምዶ ከምንባብ ቀጥለው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በሚሰጡ መልሶች ይለካል:: መረዳት (comprehending) ግን በንባብ ሂደት ውስጥ አንባቢ የሚያከናውናቸው ረቂቅ የመረዳት ሂደታዊ ትግበራዎችን ይመለከታል:: ፍሬያማ የንባብ ትምህርት በመረዳት ላይ በማነጣጠር የሚቀርብ በመሆኑ የንባብ አስተማሪዎች በዚህ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሊያደረጉ ይገባል::

በመረዳት ወይም በንባብ ሂደት ክንዋኔዎች ላይ ያተኮረ የንባበ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከማበልጸግ አንፃር ከፍተኛ ድርሻ አለው:: /ሲልበረስታይን. 1987፡30/ በንባብ ትግበራ ሂደታዊ ክንዋኔዎች ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች፣ ያፍ ወለምታ አጀማመሮች (false-starts) እና የመሳሰሉት ሳየቀሩ ከምንባብ ለወጡ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን የመስጠት ያህል ንባብን ለመማር ጠቃሚዎች ናቸው:: በመሆኑም የንባብ መምህራን ከምንባብ ለወጡ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶች ለሚሰጡ ብቻ ሳይሆን የመመለስ ሙከራ የሚያደርጉ ተማሪዎችንም የሚያበረታቱ የንባብ መልመጃዎች ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል:: በዚህም ተማሪዎች የመረዳት ስትራተጂዎችን እንዲያዳብሩ ሊረዱ ይችላሉ::

በስግ ሥርዓት በመታገዝ አንብቦ መረዳትን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ባስቲዳስ /1984:20/ ስግ ሥርዓትን እንደማስተማሪያ ስልት በመጠቀም ተማሪዎቻችን ትንበያን እንዲለማመዱ ማስልጠን እንችላለን:: በዚህ ስልት በምንሰጠው ስልጠና ተማሪዎች ብሳሳትስ የሚለውን ፍርሃት አስወግደው በድፍረት የተገደፉትን ቃላት እንዲገምቱ ሊበረታቱ ይገባል:: በዚህ የመተንበይ ሙከራ ውስጥ አልፎ አልፎ የተሳሳቱ መልሶች እንደሚሰነዘሩም ይጠበቃል:: ይሁንና የሚፈሟቸው ስህተቶች ስለተማሪዎቹ ድክመቶች ጠቃሚ ጥቆማዎችን በመስጠት በመማማር ወደ ትክክለኛ የአንብቦ መረዳት ክንዋኔ እንዲገቡ እድል ይሰጣሉ የሚል ሀሳብ ሰንዝረዋል::

ተማሪዎች በተሳካ ሁኔታ በስግ ምንባብ ክፍት ቦታዎች ውስጥ የሚገቡ ቃላትን መተንበይ እንዲችሉ ከስግ ልምምዱ በፊት የእይታዊ መረጃዎችንና የረቂቅ መረጃዎችን አጠቃቀም አስመልክቶ ጥቆማ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል /ባስቲዳስ. 1984:21/:: በዚህ ዓይነቱ ጥቆማ የተማሪዎችን ረቂቅ መረጃዎች ማንቃት የራሳቸውንና የጓደኞቻቸውን ስህተቶች በማረም በተሸላ ሁኔታ አንብበው እንዲረዱ ያግዛቸዋል /ቻፕማን. 1983:118/::

### 2.2.2.2. የማስተማሪያ ስግ ምንባብ አዘገጃጀት

ለማስተማሪያ ስግ ምንባቦች ማዘጋጃነት የተሚሉ ምንባቦች ስንመርጥ በሦስት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ልናደርግ ይገባናል:: እነዚህም የሚመረጠው ምንባብ ይዘት÷ የክብደት ደረጃና ርዝመት ናቸው: /ሹልዝ. 1983:129/ ከተዘረዘሩት ነገሮች የሚመረጥ ምንባብን ይዘት በተመለከተ ከተማሪዎች ፍላጎት ዳራዊ እውቀትና ልምድ ጋራ እንዲገናዘብ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ክብደቱም ከተማሪዎች ችሎታ ጋራ ያለው ተማጣጥኖ ታይቶ ካላቸው ችሎታ ትንሽ ገፋ ያለና መጠነኛ የመፈታተን ብቃት ያለው ቢሆን ይመረጣል:: ርዝመቱም እንዲሁ የተንዛዛ ከሚሆን ይልቅ አጠር ያለ ቢሆን ይመረጣል:: ይህም በአንድ በኩል የተለያዩ ምንባቦችን የማቅረብ እድል የሚሰጥ ሲሆን በሌላ በኩል "ቶሎ እንጨርሳታለን" የሚል አበረታች ስሜት በተማሪዎች ዘንድ ይፈጥራል::

ከላይ በተዘረዘሩት የምንባብ መምረጫ መስፈርቶች አማካይነት ከተመረጡት የተሚሉ ምንባቦች ስግ ምንባቦችን ካዘጋጀን በኋላ ለትምህርት ስለሚቀርቡበት ሁኔታ ቻፕማን/1983:114/ ጆንግስማ/1980/ን ጠቅሰው "ከክብደት ደረጃ÷ ከርዝመትና ከዓላማ አንፃር በጥንቃቄ በቅደም ተከተል የተሰደሩ ስግ የማስተማሪያ ምንባቦች ይህንን መንገድ በመከተል ካልቀረቡት የበለጠ ውጤታማ ናቸው"ብለዋል::

ለማስተማሪያ የሚውል ስግ ምንባብ በምናዘጋጅበት ጊዜ ከተሚላው ምንባብ ውስጥ ቃላትን ማስወገድ ያለብን ለማስተማር በተፈለገው ጉዳይ ላይ እንደፈለጉ

በማነጣጣር መግደፍ በሚያስችለው በምክንያታዊ ገደፋ ስልት መሆን አለበት። /ናታል. 1996፡209፤ ቻፕማን. 1983፡114/።

ከተሟላ ምንባብ ውስጥ የሚገደፉ ቃላት፥ የይዘት ቃላት (content words) (ስም፥ቅፅል፥ግስ፥ ተውሳከግስ) ወይም የተግባር ቃላት (structure words) (ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ) መሆን፥ በአረፍተ ነገር ውስጥ መጀመሪያ መካከል ወይም መጨረሻ ላይ መሆንና፥ ከግራ ቀኛቸው የሚሰጠው የአወደንባብ ርቀት (በቃላት ቁጥር ይገለፃል) የቃላቱን ተተንባይነት የክብደት ደረጃ ይወስናል። /ራይ. 1982፡70/ በነዚህ በተጠቀሱት ሶስት ምክንያቶች እንዴት የተገደፉ ቃላት ተተንባይነት የክብደት ደረጃ እየጨመረ እንደሚሄድ ለማሳየትም ራይ /1982፡71/ የሚከተለውን ማጠቃለያ ሰጥተዋል።

**ሰንጠረዥ፥3** በተገደፉ ቃላት ተተንባይነት ላይ ክብደት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ማጠቃለያ

የክብደት መጨመር ↓

| ገደፋው ያተኮረበት የቃላት ክፍል | ተገዳፊ ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸው ቦታ | የግራቀኝ የአውድ ርቀት (በቃላት ቁጥር) |
|---|---|---|
| የተግባርቃላት (ተውላጠ ስም፥ አያያዥ ቃላትና የመሳሰሉት) | መካከል | 12 |
| | | 11 |
| | | 10 |
| | መጨረሻ | 9 |
| | | 8 |
| | | 7 |
| የይዘትቃላት(ስም፥ግስ፥ ቅፅል፥ተ/ግስ) | | 6 |
| | መጀመሪያ | 5 |
| | | 4 |

(ራይ. 1982፡71)

### 2.2.2.3. የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት ሂደት

ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ስግ ምንባብን በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ ለተደራጁ ተማሪዎች በማቅረብ (ክፍሉን እንደ አንድ ቡድን በመውሰድ በመምህር አስተባባሪነትም ይቀርባል) በቡድኑ አባላት የተናጥል ጥረት የተደረጉ ትንበያዎች ለየቡድኖቹ ቀርበው በያንዳንዱ ቡድን በምክንያት በተደገፈ ውይይት ወደ አንድ፥ አንድ የየቡድኑ የጋር ምላሽ እንዲሰባሰቡ፥ ከዚያም እነዚህ የየቡድኑ ምላሾች በመምህር አሰባሳቢነት ለውይይት ቀርበው አሁንም በምክንያታዊ ውይይት ወደ

አንድ ወጥ ክፍል አቀፍ ምላሽ እንዲሰባሰቡ የሚደረግበት የንባብ ማስተማሪያ ስልት ነው /ባስቲዳስ. 1984፤ ቦርትኒክና ሎፖርዶ. 1973/::

ስግ ሥርዓት ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የተማሪዎችን ተሳተፎ በእጅጉ የሚያነቃቃ በመሆኑ "ተማሪ-መራሽ (student-centered) ስልት ነው::" /ጆንዝ .1976:255/ ለመባል በቅቷል:: በንባብ ትምህርቱ ክንዋኔዎች ውስጥ ሰፊ ድርሻ ያላቸው ተማሪዎች በመሆናቸው ስግ የንባብ ማስተማሪያ የሚከተለው ንቁ (active) የማስተማር መንገድን ነው::

የስልቱን ንቁ ማስተማሪያነት የሚያጎላው በትምህርት አሰጣጡ ውስጥ ማንኛውም ምላሽ፥ የተሳሳተ ምላሽ እንኳ ሳይቀር እንዲሰነዘር የሚበረታታ መሆኑ ነው:: ባስቲዳስ /1984:23/ ይህንን ሁኔታ "በስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አካሄድ መምህሩ ተማሪዎች ያለ አንዳች ፍርሃት ክፍት ቦታዎችን ያሟላሉ የሚሏቸውን ግምቶች እንዲሰነዝሩ ማበረታታት አለበት - ይሁንና ምላሾቹን ለምን እንደመረጡ ማሳመኛ ምክንያት እንዲያቀርቡም መጠየቅ ይኖርበታል::" በማለት ገልጸውታል:: በዚህ የንባብ ማስተማሪያ ስልት የተማሪዎች የተለያዩ ትንበያዎች በአድናቆት የሚታዩ መሆናቸው ጉድማን /1986:18/ "ቤተሰቦች ህፃናት የሚያደርጉትን የመጀመሪያ የቋንቋ ለመዳ ሙከራ በፍቅርና በአድናቆት የማየታቸው ሁኔታ፥ ህፃናቱ ያለፍረሃት ሙከራቸውን እንዲቀጥሉ ያበረታታል::" በማለት ካቀረቡት ሀሳብ ጋራ ሲገናዘብ እሳሳት ይሆን ብሎ የመስጋት ሁኔታን ማስወገድ የቋንቋ መማር ሂደትን እንደሚያነቃቃና የመማር እርምጃን እንደሚያጠናክር ይጠቁማል::

በስግ የንባብ ትምህርት ሂደት ውስጥ የሚከናወኑትን የንባብ ልምምዶች የሚያከናውኑት በአመዛኙ ተማሪዎች እራሳቸው እንደሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል:: ይህም/ናታል. 1996:36/ ንባብ በማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ማከናወን የሚችሉትን እራሳቸው እንዲያከናውኑ እድል መስጠት ያስፈልጋል:: በክንዋኔው ውስጥ ችግር ሲገጥማቸው ግን ልክ መራመድ በመሞከር ላይ ላለ ህፃን እንደሚደረግ አይነት ድጋፍ (scaffolding) ሊደረግላቸው ይገባል ከሚለው ሃሳብ ጋራ የሚስማማ ነው::

ስግ የንባብ ትምህርት ሂደት ለተማሪዎች ተሳትፎ ሰፊ ቦታ ከመስጠት ባሻገር ከላይ የተጠቆመውንም ተገቢ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል:: አፕሌቤና ላንገር /1984:183/ "በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የላቀ ችሎታ ያለው የቋንቋ ተጠቃሚ፥ አዲስ የቋንቋ ተጠቃሚ ወደፊት የሚያጋጥመውን ውስብስብ የቋንቋ ተጠቅሞ ያለ ድጋፍ ያከናውን ዘንድ አስፈላጊውን ድገፋ ያደረጋ::" በማለት የገለጹት፥ በስግ

የንባብ ትምህርት ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ስህተቶችን ማን ማቃናት እንዳለበት ወይም ድክመት ለሚያሳዩ ተማሪዎች ማን ድጋፍ መስጠት እንደአለበት ጥቆማ ይሰጣል:: ስግ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ የትምህርት ሂደት በአመዛኙ በቡድን በተደራጁ ተማሪዎች በውይይት የሚከናወን በመሆኑ ችግር ለሚገጥማቸው ተማሪዎች የቅርብ ድገፋ የሚሰጡት በየቡድኑ ውስጥ ያሉ የላቀ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ሲሆኑ፥ የየቡድኖቹን የስራ ክንውን እየዞሩ የሚቃኙትም መምህር ተገቢውን ድገፋ ያደርጋሉ /ባስቲዳስ. 1984:23፤ ቦርትኒክና ሎፖርዶ. 1973:298/::

መምህራን መስህብ ያላቸው ምንባቦችን በመምረጥ፥ በልምምዱ ላይ ክብደት የሚያስከትሉ ሁኔታዎችን በመቆጣጣር፥ ስለ አውዳዊ ፍንጮች አጠቃቀም ገለፃ በመስጠት፥ ወደ ፍሬያማ ትንበያ ስለሚያመራ ውይይት አንዳንድ ሀሳቦችን በመስጠት ለተማሪዎች ድገፋ ማድረግ እንደሚገባቸው ራይ/1982:54/ ያመለከቱ ሲሆን፥ በዚህ ስልት በመጠቀም ንባብን ማስተማር ከመጀመር አስቀድሞ ለተማሪዎቹ ስለ ስግ ሥርዓት ምንነትና ተግባራዊ አጠቃቀም አስፈላጊው ገለፃ ሊሰጥ እንደሚገባ ባስቲዳስ /1984:23/ በአጽንኦት አመልክተዋል::

በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ሂደት መቋጫ ላይ መምህራን የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽም መምህራን ለተማሪዎች ከሚያደረጉት ድገፋ አንዱና ዋነኛው ነው:: የዚህ ድገፋ አብይ ትኩረት ተማሪዎች ወደ ትክክለኛ ምላሽ የሚያመሩትን አቅጣጫዎች በሚመለከት ያላቸውን እውቀት ማጠናከር ነው:: "የስግ ስልት የንባብ ትምህርት ትኩረትና ግብ ተማሪዎች የተለያዩ ትንበያዎች በማመንጨት በሚያካሂዱት ውይይት ወደ ትክክለኛ መልስ ለመድረስ የሚደረጉትን ጥረት ማጠናከር እንጂ የሚሰጡትን መልስ ከትክክለኝነት አንፃር ማረምን የሚመለከት አይደለም" /ራይ. 1982:56/ የሚለውም ይህንኑ ሀሳብ ይደግፋል::

### 2.2.2.4. የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ አቅጣጫዎች

በቋንቋ ክሂሎች መካከል ከፍተኛ ቁርኝት ስላለ እነዚህን ክሂሎች ነጣጥሎ ለትምህርት ማቅረብ አይቻልም:: በስግ ስልት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ብዙዎች ለምሳሌ ኦላር /1972/ እና አልደርሰን /1979/ እንኳር የቋንቋ ብቃት (core language proficiency) በሚሉት በአንብቦ መረዳት ላይ የሚያተኩርና የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች ተሰናኝተው የሚገኙበት በመሆኑ፥ በዚህ ስልት የሚቀርብን የንባብ ትምህርት፥ በአንድ የቋንቋ ክሂል ላይ ብቻ እንዲያተኩር አድርጎ ለማቅረብ ያስቸግራል:: ይሁን እንጂ በቃላት ገደፋ አማራጮች በመጠቀም በአንድ የቋንቋ ክሂል ላይ በይበልጥ ለማተኮር የሚያስችሉ የስግ የንባብ ትምህርት አቀራረብ አቅጣጫዎችን ያመለከቱ

ጥናቶች አሉ። በነዚህ ጥናቶች ውስጥ የሚከተሉት የስግ ስልት የንባብ ትምህርት አቀራረብ አቅጣጫዎች ተጠቁመዋል።

ሀ. ከምንባብ ውስጥ የይዘት ቃላት (content words) ማለትም ስም፥ ቅፅል፥ ግስ፥ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ቃላት እየመረጡ በማስወገድ ስግ ምንባብ በማዘጋጀት፥ ትምህርቱ በሰዋሰዋዊ አገባብና በቃላት ፍቺ ትምህርት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ።

ለ. ከምንባብ ውስጥ የተግባር ቃላትን (structure words) ማለትም ቀደም ሲል የይዘት ቃላት በሚል ከተጠቀሱት ውጭ ያሉትን እንደ ተውላጠ ስም መስተዋድድና የመሳሰሉትን ቃላት እየመረጡ በማስወገድ ስግ ምንባብ በማዘጋጀት ትምህርቱ በምንባብ የተለያዩ ክፍሎች ተዛምዷዊ ግንኙነት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ።

ሐ. በቃል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ምዕላዶችን በመግደፍ ስግ ምንባብን በማዘጋጀት ትምህርቱ በቃል ትንተና (word analysis) ላይ እንዲያተኩር ማድረግ።

መ. የተለያዩ የጽሑፍ መልኮች ልዩ ገጽታን የሚያመለክቱ ማለትም ለምሳሌ የግጥምን የተረትን ወይም ቀልድን ልዩ ገጽታ የሚመለክቱ ጹሑፎችን በመምረጥ ቃላትን እየመረጡ በመግደፍ ስግ ምንባብን በማዘጋጀት፥ ትምህርቱ በነዚህ ለየት ያሉ የጽሑፍ መልኮች ለየት ያሉ የሀሳብ አቀራረቦችና ቅርፃዊ ይዞታዎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ።

/ቦርትኒክና ሎፖርዶ. 1973፡299፤ ቻፕማን. 1983፡110/

### 2.2.2.5. የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል

የስግ ስልት የንባብ ትምህርት አቀራረብ በቡድን የተደራጁ ተማሪዎች ስግ ምንባብን በመምህር አስተባባሪነት በውይይት ለመሙላት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ይገለፃል። በዚህ ስልት የንባብ ትምህርትን ለማቅረብ ተማሪዎችን በሁለት መንገድ ማደራጀት ይቻላል። ከነዚህ ውስጥ አንደኛው ክፍሉን እንደ አንድ ቡድን በመውሰድ ክፍል አቀፍ ቡድን በመመስረት ትምህርቱን ማቅረብን የሚመለከት ሲሆን ሌላው የክፍሉን ተማሪዎች በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ በመመደብ (እያንዳንዱ ቡድን ከ3-4 ተማሪዎች ሊይዝ ይችላል) ትምህርቱን ማቅረብን ይመለከታል /ራይ. 1982፡56/።

በሁለቱም መንገድ ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት፥ የክፍሉ ተማሪዎች ከስግ ሥርዓት ጋራ የማይተዋወቁ ከሆነ መምህሩ የተወሰነ ጊዜ ወስደው የሥርዓቱን ምንነት ማስተዋወቅ፥ ተማሪዎች ቃላትን እንዴት በአውዳዊ ፍንጮች እርዳታ በመተንበይ ስግ ምንባብን ማሟላት እንደሚችሉ በቂ ገለፃ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ያለ አንዳች ፍርሃት በክፍት ቦታዎች ውስጥ ሊገቡ የሚችሉትን ቃላት በመገመት መናገር እንዳለባቸውና፥ ሳይጨነቁ የመገመት ሙከራ የሚያደርጉ ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ለነዚህ ተማሪዎች የመማር እድል በር የሚከፍቱ መሆናቸውን በአጽንኦት መግለጽ አስፈላጊ ነው /ባስቲዳስ. 1984:23/። በዚህ ሁኔታ ለተማሪዎች አጠቃላይ ገለፃ ከተሰጠ በኋላ ትምህርቱን ከተማሪዎች ቡድናዊ አደረጃጀት አንፃር በሚከተሉት መንገዶች ማቅረብ እንደሚቻል ድርሳናት አመልክተዋል።

### 2.2.2.5.1. ለክፍል-አቀፍ ቡድን የሚቀርብ የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል።

ሀ. መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ትኩረትና የምንባቡን አርእስት በማስተዋወቅ የማስተማር ተግባራቸውን ይጀምራሉ። ስግ ምንባቡን ከማደላቸው በፊት ስለርእሱ አንዳንድ ጥያቄዎች ያቀርባሉ። በዚህ ተማሪዎች አንዳንድ ግምቶችን መገንባት ይጀምራሉ።

ለ. ከዚህ በኋላ መምህሩ ስግ ምንባቡን በማደል ተማሪዎች ምንም ያልተገደፉትን የመጀመሪያና የመጨረሻ አረፍተ ነገሮች በጸጥታ ፈጥነው በየግላቸው እንዲያነቡ መመሪያ ይሰጣሉ። በሁለቱ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተካተቱትን ሀሳቦች በመመርኮዝ ጥያቄዎችን በመሰንዘር ተማሪዎች የስግ ምንባቡን ምንነት በበለጠ በመመርመር ጥቅል መልእክቱን እንዲያገኙ ያደርጋሉ።

ሐ. እዚህ ላይ መምህሩ ባስፈላጊው ቦታ ሁሉ ተገቢውን ቆምታ እያደረጉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ስግ ምንባቡን ያነባሉ። ይህም ለተማሪዎች ምንባቡን መገንዘብ አንዳንድ ፍንጮች ይሰጣል። በሚያነቡበት ጊዜ ክፍት ቦታዎችን በአርምሞ ወይም 'ዳሽ' በማለት ሊያልፉ ይችላሉ። በዚህ ወቅት ተማሪዎችም ከመምህሩ ጋራ ምንባቡን በየግላቸው በጸጥታ ያነባሉ።

መ. እዚህ ደረጃ ላይ መምህሩ ተማሪዎች ስግ ምንባቡን በድጋሚ በጸጥታ በየግላቸው እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ የክፍሉን ተማሪዎች በሙሉ

የሚያሳትፈውን ውይይት መምራት ይጀምራሉ:: መምህሩ ተማሪዎች ለስግ ክፍተቶች ያላቸውን ግምቶች እንዲሰነዝሩ ከመጠየቃቸው በፊት፥ ተማሪዎች በቅርበት ከጠፉት ቃላት ኋላና ፊት ያሉትን መረጃዎችና በርቀት በአንቀጹ መጀመሪያ፥ መካከል ወይም መጨረሻ ያሉትን ሀሳቦች በትኩረት ማየት እንዳለባቸው መግለጽ ይኖርባቸዋል::

ሠ. ከዚህ በኋላ ተማሪዎች ድፃቸውን ከፍ በማድረግ ለያንዳንዱ ክፍት ቦታ ይስማማል የሚሉትን ግምት እንዲሰነዝሩ በመጋበዝ መምህሩ በያዙት የስግ ምንባብ ቅጂ ላይ ሙከራዎቹን ያስፍራሉ:: እዚህ ላይ መምህሩ ተማሪዎች እሳሳት ይሆን የሚለውን ፍራቻ በማስወገድ የጠፉትን ቃላት እንዲገምቱ ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፤ ይሁንና እያንዳንዱ ተማሪ ላቀረበው ግምትም ምክንያት እንዲያቀርብ ሊጠይቁ ይገባል:: መምህራን ለተማሪዎች ሊያደርጓቸው የሚገቡ ድጋፎችን የሚያሳየው የትምህርቱ ክፍል ይህ በመሆኑ፥ በተማሪዎቹ ግምቶችና ለግምቶቹ በሚያቀረቧቸው ምክንያቶች ላይ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች በትኩረት መታየትና መመዝገብ አለባቸው::

ረ. እዚህ ላይ መምህሩ የተፈጸሙትን ስህተቶች በማጤን ተማሪዎቹ በራሳቸው ጥረት ሊያቃኗቸው እንዲችሉ የተለያዩ ፍንጮችን (አገባባዊ፥ ትርጉማዊ፥ ምዕላዳዊ) ይሰጣሉ::

ሰ. በዚህ ደረጃ ላይ መምህሩ ተማሪዎች ከላይ በተዘረዘሩት መንገዶች በመወያየት የሞሉት ስግ ምንባብ ምን ያህል ስሜት እንደሚሰጥ ለማሳየት አንድ ተማሪ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲያነበው ትእዛዝ በመስጠት ያስፈጽማሉ::

ሸ. በመጨረሻም መምህሩ ኦርጅናሌውን (ገደፋ ከመካሄዱ በፊት የነበረውን) ምንባብ ለተማሪዎች በማደል እነሱ ከሰጡት መልስ ጋራ በማመሳከር የሙከራቸውን ውጤታማነት ደረጃ እንዲያውቁ ያደርጋሉ::

/ቦርኒክና ሎፖርዶ. 1973:297-298፤ ሹልዝ. 1983:131-132፤ ቻፕማን. 1983:109-110፤ ባስቲዳስ. 1984:23፤ ናታል. 1996:208/

### 2.2.2.5.2. በቡድን ለተከፋፈሉ ተማሪዎች የሚቀርብ የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል::

ሀ-ሐ. ቀደም ሲል በክፍል አቀፍ የትምህርት አቀራረብ ውስጥ ከሀ-ሐ የተዘረዘሩት ቅደም ተከተላዊ ክንውኖች በዚህም ውስጥ ተግባራዊ ይደረጋሉ::

መ. መምህሩ ተማሪዎች በየንኡስ ቡድናቸው ውስጥ ስግ ምንባቡን ደግመው በማንበብ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና የሚስነዘሩቸውን ግምቶች የቡድናቸው አባላት እንዲቀበሏቸው ግምቶቹን የመረጡበትን ምክንያት ማስረዳት እንዳለባቸው ገለፃ በመስጠት የቡድን ስራ ያስጀምራሉ:: የተሰጠውን ስራ ማከናወን የተሳነው ቡድን ካጋጠመ፥ ስለተገደፉት ቃላት ፍንጭ የሚሰጥ ለምሳሌ ይጠፉትን ቃላት መነሻ፥ መድረሻ ወይም የመሐል ፊደል በሚያመለክት ስግ ምንባብ (ቀደም ብሎ በመምህር የተዘጋጀ) ይለወጥላቸዋል::

ሠ. ተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ ለማከናወን በየቡድኑ ውስጥ ተሳትፎ በሚያደርጉበት ጊዜ መምህሩ እየተዘዋወሩ ከየቡድኖቹ ጋራ ተራክቦ በማድረግ ባስተባባሪነት ክንዋኔውን ይመራሉ::

ረ. ከዚህ በኋላ መምህሩ እያንዳንዱ ቡድን በመወያየት ያመነጫቸውን የጋራ ምላሾች ከነምክንያቱ እንዲያቀርብ ካደረጉ በኋላ፣ በውስጣቸው የሚታዩትን ስህተቶች በመመርመር ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ::

ሰ. በመጨረሻም መምህሩ ኦርጅናሌውን ምንባብ ለየቡድኖቹ በማደል ቀደም ሲል ከሰጧቸው ግምቶች ጋራ በማነጻጸር ውጤታቸውን እንዲገመግሙ ያደርጋሉ::

/ቦርኒክና ሎፖርዶ. 1973:297-298፣ ሹልዝ. 1983:131-132፣ ቻፕማን. 1983:109-110፣ ባስቲዳስ. 1984:23/

ከዚህ በላይ በቀረቡት ተዛማጅ ጽሑፎች ውስጥ የተነሱት የተለያዩ ሐሳቦች፥ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማጎልበት ብሎም አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታን ለማዳበር የሚቻልበትን መንገድ ለመሻት ለሚደረገው ለአሁኑ ጥናት መሠረት ናቸው ተብሎ ይታመናል::

በ2.1. ውስጥ የቀረበው በጥናቱ ርእስ ውስጥ የሚታየውን 'ስግ ሥርዓት' የሚባለውን ሥርዓት ምንነት፥ አዘገጃጀትና ጥቅሙን አስመልክቶ የተለያዩ ሐሳቦች በመፈንጠቅ ለጥናቱ ጻራዊ መደላድል ይሆናል::

የስግ ሥርዓትን የሙከራ ማቅረቢያነት ሚና በሚመለከት በ2.2.1.1. ውስጥ የቀረበው ሥርዓቱ አንብቦ መረዳትንና አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን ጨምሮ ስለሚዳስሳቸው ልዩ ልዩ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ግንዛቤ ከመስጠቱም በላይ

ይህንን ሥርዓት ከሙከራ መስጫነት ወደ ማስተማሪያ ስልትነት በመለወጥ ብንጠቀምበት ሊኖረው የሚችለውን ጠቀሜታ አጉልቶ ማሳየት ይችላል::

የስግ ሥርዓትን የማስተማሪያ ስልትነት ሚና በሚመለከት በ2.2.2. ውስጥ የቀረቡት ሐሳቦች ባሁኑ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ተደርጎ ውጤታማነቱ የሚሞከረውን በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ማስተማሪያ ስልት በቀጥታ የሚመለከት ነው:: በዚህም ምክንያት በዚህ ጥናት ተግባራዊ ተደርጎ የሚሞከረው የስግ ስልት የንባብ ትምህርት አቀራረብ መርህ፥ የማስተማሪያ ምንባቦች አዘገጃጀት፥ የትምህርት ሂደት ገጽታ፥ በትህርት ሂደቱ ውስጥ የሚዳሰሱት የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች፥ የትምህርቱ አቀራረብ ቅደም ተከተልና ለትምህርቱ ስኬታማነት የሚረዳ የተማሪዎች አቦዳደንና ተሳትፎ በዚህ ክፍል ውስጥ በተዘረዘረው መሰረት ይከናወናል::

በጥቅሉ በጥናቱ ተግባራዊ ተደረጎ የሚሞከረው በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ማስተማሪያ ስልት በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ውስጥ እንደተገለጸው የስነልቦናዊ ስነልሳን የንባብ ክንዋኔ መርህን በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ውስጥ በስግ ሥርዓት አማካይነት ተግባራዊ ማድረግ የሚኖረውን ውጤት ይመረምራል::

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

በዓላማው ላይ እንደተጠቆመው የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ስግ ሥርዓት ለአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ማቅረቢያነት ቢውል የሚኖረውን አስተዋጽኦ መመርመር በመሆኑ ይህንን ለይቶ ለማሳየት የተመረጠው አብይ የአጠናን መንገድ የሙከራ ምርምር (Experimental research) አቅጣጫ ነው:: ለዚህም የመጠናዊ የአጠናን ዘዴ አካል የሆነው የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ- ፈተና የአጠናን ንድፍ (two-group pre-test post- test design) በተግባር ላይ ውሏል:: በዚህ አቅጣጫ ምርምሩን በማካሄድ የተገኘውን ውጤት ተጨባጭነት ለማረጋገጥ ከሙከራ ምርምሩ በኋላ መረጃዎችን በማሰባሰብ የድህረ ሙከራ ጥናት ተካሂዷል:: የጥናቱ አካሄድ ዝርዝር እንደሚከተለው ነው::

### 3.1. የትምህርት ቤት፥የተጠኚ ተማሪዎችና የመምህራን አመራረጥ

#### 3.1.1. የሙከራ ምርምር

የሙከራ ምርምር ማካሄጃው ትምህርት ቤት የተወሰነው በምቾት ንሞና (convenience sampling) ዘዴ ነው:: የምቾት ንሞና ያቦሰጣዊ ንሞናን (random sampling) አቅጣጫ በመተው ከአጃባው (population) ወደ አንዱ የሚያዘነብል ቢሆንም ለጥናት ማካሄጃነት ፈቃድ በመስጠት የሚተባበር ትምህርት ቤት በሚጠፋበት ጊዜ ገቢራዊ ሊሆን የሚችል በመሆኑ ይህም ጥናት በዚሁ ሁኔታ ለጥናቱ መካሄድ በጎ ትብብር ባሳየው በከፍተኛ ሰባት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ሊያተኩር ችሏል::

በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ለየትኛው የክፍል ደረጃ ይበልጥ ተስማሚ እንደሆነ የሚጠቁሙ መረጃዎች ብዙ አይደሉም:: አንዳንድ መረጃዎች ግን ለምሳሌ ቻፕማን (1983፡113) በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ፥ በተለይ ተማሪዎች በሚያደርጉት ውይይት የሚደገፍ ከሆነ፥ በከፍተኛ የክፍል ደረጃ ላይ ባሉ ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ ቢደረግ ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆን ጠቁመዋል:: በዚህም ምክንያት የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የሚያደርጉትን ዝግጅት በግምት ውስጥ በማስገባት ይህንን ከፍተኛ የክፍል ደረጃ በመተው፥ ጥናቱ ከዚህ በታች ባለው ከፍተኛ የክፍል ደረጃ ላይ በሚገኙት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል::

ለጥናቱ ማካሄጃነት በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በ20 ምድቦች (sections) ተከፋፍለው፥ 12ቱ ምድቦች በጠዋቱ ፈረቃ 8ቱ ደግሞ በከሰዓት በኋላው ፈረቃ ውስጥ ተደልድለዋል፡፡ የሙከራ ጥናቱን በተገቢው መንገድ ለማካሄድ የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ በመሆን የሚመረጡት ሁለት ክፍሎች በአንድ ፈረቃ ወስጥ መሆን ስላለባቸው ከሁለቱ ፈረቃዎች አንዱን በእጣ መወሰን አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በዚህም መሠረት እጣ ተጥሎ የጠዋቱ ፈረቃ ተመርጧል፡፡ በጠዋት ፈረቃ ከሚማሩት 12 የ11ኛ ክፍል ምድቦች ሶስቱ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው(ከ16-28 ተማሪዎች) የሙያ ዘርፍ ተማሪዎች የሚገኙባቸው ክፍሎች በመሆናቸውና እጣው ቢደርሳቸው በጥናቱ ውስጥ የሚታቀፉትን ተጠኚዎች ቁጥር ስለሚያሳሱ እጣው ውስጥ እንዳይገቡ ተደርገዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ከቀሩት 9 ምድቦች ሁለቱን፥ ከሁለቱም የትኛው የቁጥጥር ቡድን (control group) የትኛው የሙከራ ምድብ (Experimental group) እንደሚሆን በእጣ በመወሰን 11[20] የቁጥጥር ቡድን 11[9] የሙከራ ቡድን በመሆን ተመርጠዋል፡፡

ለሙከራ ቡድኑ ተግባራዊ በሚደረገው የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት ከመስጠቱ በፊት በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ክፍል ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት ስለ ሥግ ሥርዓት ምንነትና በዚህ ሥርዓት አማካይነት ስለሚቀርበው የንባብ ትምህርት መግለጫ ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ የትምህርቱ አሰጣጥ የቁጥጥር ቡድኑ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ባለው ተለምዷዊ የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ፥ የሙከራ ቡድኑን በአጥኚው ተዘጋጅተው በሚቀረቡ ስግ ምንባቦችና የትምህርት አካሄድ መርህ መግለጫ መሰረት፥ በመደበኛዎቹ መምህራን እንዲከናወን ተወጥኖ የነበረ ቢሆንም፥ የሙከራውን ቡድን በተሰጠው መርህ አማካይነት ንባብን በማስተማር ረገድ ከአጀማመሩ በታዩ አንዳንድ ሁኔታዎች አመልካችነት የሙከራ ቡድኑን እራሱ አጥኚው የስግ ሥርዓትን የንባብ ትምህርት አቀራረብ መርህ በመከተል ለማስተማር ወስኗል፡፡

የሚካሄደው የሙከራ ምርምር ዓላማ በስግ ሙከራ የሚቀርብ የንባብ ትምህርት በተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ላይ የሚያመጣውን ለውጥ መፈተሽ በመሆኑ፥ በሙከራው ተግባራዊ የሚደረገው በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ማስተማሪያ ከተለምዷዊው የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ ልዩነት የለውም የሚል ባዶ መላምትን ($H_0$) መነሻ በማድረግ፥ የውጤት ለውጥ ከታየ ደግሞ፥ በስግ ሥርዓት በሚቀርብ የንባብ ማስተማሪያ ስልትና በተለምዷዊው የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ መካከል ልዩነት አለ የሚል አማራጭ መላምት ($H_1$) ተመርኩዞ ተከናውኗል፡፡

### 3.1.2. የድህረ ሙከራ ጥናት

የድህረ ሙከራ ጥናት የተካሄደው በሙከራ ምርምሩ ከተገኘው ውጤት ጋራ ሊነፃፃሩ የሚችሉ ሀሳቦችን ለማግኘት ነው:: ለድህረ ሙከራ ጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብ በጥናቱ ውስጥ በተጠኚነት የታቀፉት የ11[9] ክፍል ተማሪዎችና ተግባራዊ የተደረገውን የንባብ ትምህርት አቀራረብ በፈቃደኝነት ተገኝተው የተከታተሉ ስምንት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርገዋል:: በስግ ሥርዓት በመታገዝ በሚቀርበው የንባብ ማስተማሪያ የሚሰጠውን ትምህርት ከመከታተላቸው በፊት ለተማሪዎች አስፈላጊው መግለጫ እንደተሰጠ ሁሉ ለታዛቢ መምህራንም የትምህርት ሂደቱን በታዛቢነት መከታተል ከመጀመራቸው በፊት ስለ ስግ ሥርዓት ምንነትና በዚህ ስልት ስለሚቀርብ የንባብ ትምህርት አጭር መግለጫ ተሰጥቷል::

## 3.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.2.1. የሙከራ ምርምር

የሙከራ ምርምሩን ለማካሄድ በቅድሚያ በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል የችሎታ መበላለጥ እንደሌለ ለማረጋገጥ የሚረዳ ቅድመ ፈተና (pre-test) ተዘጋጀ:: ፈተናው በአንድ በኩል የክፍሉን ደረጃ እንዲመጥን ለዚህ ክፍል ከተዘጋጀ መጽሐፍ ጋር የተገናዘበና፥ በሌለ በኩል ስግ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴው የሚያተኩርባቸውን የአንብቦ መረዳት፥ የቃላትና የአገባብ ስልቶችን እንዲዳስስ ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን፥ በሰባት ልዩ ልዩ ክፍሎች ውስጥ የተካተቱ 50 ጥያቄዎችን የያዘ ነው::

ፈተናው ለተጠኚዎቹ ከመቅረቡ በፊት ባንድ በኩል ጥናቱ በሚመለከተው ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍሎችን በማስተማር ላይ ላሉ ሦስት የቢ.ኤ.(B.A.) የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን ቀርቦ የክፍሉን ደረጃ ስለመመጠኑ ባቀረቡት አስተያየትና፥ በሌላ በኩል ደግሞ ኤም.ኤ.(M.A.) እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ላላቸው የመስኩ ባለሙያዎች ቀርቦ በተሰጠ የማስተካከያና የእርምት ሐሳብ መሰረት እንደገና ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል:: (አባሪ 1ን ይመለከቷል::)

ከዚህ በኋላ ትምህርት ቤቱን የሁለት ክፍለ ጊዜያት ፈቃድ በመጠየቅ የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡ በተመሳሳይ ጊዜ ፥ የአንድ ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ጊዜ ተሰጥቷቸው ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደረገል:: የፈተናው ሂደት የተረጋጋ እንዲሆንና

ተማሪዎች ያላቸውን ችሎታ ሁሉ ተጠቅመው ፈተናውን እንዲሰሩ አግባብ ያላቸው የትምህርት ቤቱ ሃላፊዎች መመሪያ ሰጥተዋል::

ፈተናው ከተጠናቀቀ በኋላ የተሰበሰበው የመልስ መስጫ ወረቀት ሲቆጠር የቁጥጥር ቡድኑ 75 የሙከራ ቡድኑ 72 ሆኖ በመገኘቱ የሁለቱን ቡድኖች ተመጣጥኖ ለመጠበቅ ከቁጥጥር ቡድኑ የመልስ መስጫ ወረቀቶች ሦስቱ በእጣ ተለይተው እንዲወገዱ ተደርጓል:: በመቀጠልም ፈተናው በምርጫ የሚመለሱ ጥያቄዎችን ያካተተ በመሆኑ÷ በጥናቱ አቅራቢ በጥንቃቄ ታርሞ ውጤቱ ከታወቀ በኋላ በስታትስቲካዊ ሂደት ውስጥ አልፎ በ"t"- ሙከራ '(t-test) ተሰልቷል:: ከ"t" ሙከራ በተገኘው ውጤት÷ ለሙከራው ምድብ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት÷ በቁጥጥርና በሙከራ ምድብ መካከል በአንብቦ መረዳትም ሆነ በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ብቃት መሠረታዊ የሆነ የችሎታ ልዩነት እንደማይታይ ለማረጋገጥ ተችሏል:: (ሰንጠረዥ 7ና 9ን ይመለከቷል)

ከዚህ በኋላ አጥኚው የስግ ሥርዓትን የንባብ ማስተማሪያ መርህ በመከተል÷ ለቡድን መጠቀሚያነት እንዲያመቹ በኮምፒውተር ጎላ ጎላ ባለ ፊደል በማጻፍ ባዘጋጃቸው ልዩ ልዩ ስግ ምንባቦች (አባሪ 6ን ይመለከቷል) በመታገዝ ከየካቲት 29/1991 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 9/1991 ዓ.ም. ድረስ÷ ለስድስት ሳምንታት የሙከራ ምድቡን አስተምሯል:: የቁጥጥር ምድቡም በተለመደው የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በመደበኛው መምህር አማካይነት ትምህርቱን መከታተሉን አረጋግጧል::

በስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት ለተከታታይ ክፍለ ጊዜያት ማቅረብ ተማሪዎችን ሊያሰለች እንደሚችል ራይ/1982:86/ የጠቆሙት ችግር እንደይከሰት÷ አጥኚው በሳምንት ውስጥ ካሉት ሶስት የአማርኛ ክፍለ ጊዜያት በስግ ስልት ንባብን ያስተማረው በመጀመሪያውና በመጨረሻው ክፍለ ጊዜ ሲሆን÷ መከካል ላይ ባለው ክፍለ ጊዜ መደበኛው መምህር ስግ ሥርዓት በማይሸፍነው የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ ላይ በማተኮር የተለመደ የማስተማር ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ተደርጓል::

በስግ ሥርዓት በመታገዝ ለሙከራ ምድቡ በቀረበው የንባብ ትምህርት በየክፍለ ጊዜው አንድ÷ አንድ ስግ ምንባብ የቀረበ ሲሆን÷ ትምህርቱ በምዕራፍ ሁለት ቁጥር 2.2.2.5.1 እና 2.2.2.5.2. ላይ በተመለከተው የስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል መሠረት ተከናውኗል:: የተሠራባቸው ስግ ምንባቦች በሰንጠረዥ 3 ውስጥ የስግ ምንባብን የክብደት ደረጃ ይወስናሉ ተብለው ከተጠቀሱት ዝርዝር ነጥቦች በመነሳት ከቀላል ወደ ከባድ በቅደም ተከተል

ቀርበዋል:: ማራኪ ይዘት እንዲኖራቸውና የተለያዩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ እንዲሆኑም የተቻለው ጥረት ሁሉ ተደርጓል::

በአጠቃላይ ለትምህርት የቀረቡት 12 ስግ ምንባቦች ሲሆኑ÷ በነዚህ ምንባቦች አማካይነት በአንድ በኩል በየትኛውም ስግ ምንባብ አማካይነት በቀረበ ትምህርት ውስጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታና በውይይት ውስጥ በተነሱ ሐሳቦች መሠረትነት የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች በቅንጅት ሊዳበሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሲመቻች÷ በሌላ በኩል ደግሞ ስግ ምንባብ 1 እና 2 በምንባብ ተያያዥነት÷ ስግ ምንባብ 3÷ 4÷ 5 እና 6 በቃላት ችሎታ÷ ስግ ምንባብ 7 እና 8 በሥነ-ጽሑፋዊ አተረጓጎምና አገባብ ችሎታ÷ ስግ ምንባብ 9÷10÷ 11 እና 12 በሰዋሰዋዊ አገባብ ችሎታ ማዳበር ላይ የበለጠ ትኩረት በመስጠት ለማስተማሪያነት እንዲውሉ ተደርጓል::

የትምህርቱ አቀራረብ በሳምንት ውስጥ ካሉት ሁለት ክፍለ ጊዜያት በአንደኛው÷ ተማሪዎች በክፍል አቀፍ ቡድን ውስጥ ሆነው÷ በሌላው ክፍለ ጊዜ ደግሞ ከ3-4 አባላት ባላቸው ትንንሽ ቡድኖች ውስጥ ሆነው በሚያደርጉት የነቃ ተሳትፎ ተከናውኗል:: በተዘማጅ ጽሑፎች ቅኝት ውስጥ የመምህር የስራ ድርሻ የክፍሉን ተማሪዎች የቡድን ተሳትፎ ማስተባበር÷ ውይይትን መምራትና አስፈላጊ ምጋቤ ምላሽ (feedback) መስጠት እንደሆነ በተጠቀሰው መሠረት አጥኚው ይህንኑ በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ አድርጓል::

ታዛቢ መምህራንም በሙከራው ጊዜ ውስጥ ከ2 እስከ 3 ክፍለ ጊዜያት በመገኘት በ40 ደቂቃ ውስጥ የሚሰጠውን የስግ ስልት የንባብ ትምህርት አቀራረብ በታዛቢነት መከታተል ችለዋል::

ስድስቱ የትምህርት ሳምንት ከተጠናቀቀ በኋላ ከቅድመ ፈተናው ጋራ ከሁሉ አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ ድህረ ፈተና (post-test) ተዘጋጅቶ ለቅድመ ፈተናው አሰጣጥ የተደረገውን ጥንቃቄ በሙሉ በማድረግ ለቁጥጥርና ለሙከራ ምድቡ ቀርቧል:: ከትምህርት ቤቱ ሃላፊዎች ጋራ በመተባበር በፈተናው ወቅት የተረጋጋ የፈተና ድባብ እንዲኖርና የቁጥጥርም ሆነ የሙከራው ምድብ አባላት ፈተናውን ልክ እንደ መደበኛ ፈተና ሙሉ ትኩረት ሰጥተው እንዲያከናውኑ የተቻለው ጥረት ሁሉ ተደርጓል::

የድህረ ፈተና የመልስ መስጫ ወረቀት ከተሰበሰበ በኋላ ቀደም ሲል የተሰጠውን ቅደመ -ፈተና ከወሰዱት የቁጥጥር ቡድኑ አባላት አራቱ÷ ከሙከራው ቡድን አባላት ሁለቱ በድህረ ፈተናው ላይ ያልተገኙ መሆናቸው ስለተረጋገጠ የሁለቱን ምድብ አባላት በቁጥር ለማመጣጠን ከሙከራ ቡድን አባላት የሁለቱን

የመልስ መስጫ ወረቀት በእጣ በማስወገድ፥ የሁለቱ ምድብ አባላት ቁጥር 68፥68 እንዲሆን ተደርጓል:: የድህረ ፈተናው ጥያቄዎች ልክ እንደ ቅደመ ፈተናው ጥያቄዎች ምርጫ ስጪ በመሆናቸው፥ በራሱ በጥናቱ አቅራቢ በጥንቃቄ ታርመዋል::

### 3.2.2. የድህረ -ሙከራ ጥናት

የድህረ-ሙከራ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በጽሑፍ መጠይቆች አማካይነት ነው:: መጠይቆቹ የተሞሉት በተጠኚ ተማሪዎችና በስግ ሥርዓት በመታገዝ የቀረበውን የንባብ ትምህርት በተጋባዥነት በተከታተሉ መምህራን ሲሆን፥ እነዚህ መጠይቆች ከመሰራጨታቸው በፊት፥ ተፈላጊውን መረጃ ለማስገኘት መቻላቸውን ለማረጋገጥ አግባብ ባለው ሙያ ኤም.ኤ. (M.A.) እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ባላቸው ባለሙያዎች እንዲገመገሙ ተደርገው፥ ከግምገማው በተገኘው አስተያየትና ማረሚያ መሠረት ተገቢው ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል::

ለተጠኚ ተማሪዎችም ሆነ ለመምህራኑ የቀረቡት መጠይቆች ሦስት፥ ሦስት ክፍሎች ያሏቸው ሲሆን፥ የመጀመሪያው ክፍል እንደ ፆታ፥ አፍ መፍቻ ቋንቋና የመሳሰሉትን አጠቃላይ መረጃዎች የሚይጠቅ ነው:: ሁለተኛው ክፍል ተግባራዊ የተደረገውን የማስተማር ዘዴ በተመለከተ የተለያዩ ሐሳቦች በያዙ አረፍተ ነገሮች መነሻነት "በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ"፥ "እስማማለሁ"፥ "አልስማማም"ና "ፈጽሞ አልስማማም" ከሚሉት አማራጭ የስምምነት ደረጃዎች አንዱን በምልክት በማሳየት አስተያየት እንዲሰጥ የሚጠይቅ ነው:: እዚህ ላይ ከሊከርት የአስተያየት መለኪያዎች (Likert scales) በአማካይ ደረጃ ላይ ያለው (አስተያየት የለኝም) እንዲቀር የተደረገው ሴሊገርና ሾሃሚ /1989:175/ መላሾችን ወደ ግድ የለሽ አመላለስ የሚስብ ምርጫ መሆኑን የጠቀሱትን መሰረት በማድረግ ነው:: ሦስተኛው ክፍል ተጠኚ ተማሪዎችና ታዛቢ መምህራን ተግባራዊ በተደረገው የማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ የቀረበ ክፍት ጨራሽ (open ended)ጥያቄ ነው:: (አባሪ 13 እና 14ን ይመለከቷል::)

በሁለቱም መጠይቆች ውስጥ አስተያየት እንዲሰጥባቸው የቀረቡት የጋራ ሃሳቦች በአራት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው:: ከነዚህ አንደኛው በስግ ሥርዓት በመታገዝ የሚቀርብ የንባብ ትምህርት አንብቦ መረዳትን ለማዳበር ያለውን ድርሻ፥ ሁለተኛው የሰዋሰው ችሎታን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ፥ ሦስተኛው የቃላት ችሎታን ለማዳበር ያለውን ድርሻ፥ አራተኛው የቋንቋ ክሂሎችን በጥምረት ለማቅረብ ያለውን ብቃት የሚመለከት ሲሆን፥ በመምህራን መጠይቅ ላይ

የማስተማሪያ ዘዴው ለመምህራን የማስተማር ተግባር በሚሰጠው እገዛ ላይ አስተያየት የሚጠይቅ ተጨማሪ ነጥብ ታክሏል:: በነዚህ በተጠቀሱት ነጥቦች ዙሪያ አስተያየት እንዲሰጥባቸው የቀረቡትን ሐሳቦች መጠንና ስርጭት ከሚከተለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡

**ሰንጠረዥ አራት÷** ለተጠኚ ተማሪዎችና ለተጋባዥ መምህራን በቀረቡት መጠይቆች ላይ አስተያየት እንዲሰጥባቸው የቀረቡ ሐሳቦች መጠንና ስርጭት::

| ተ.ቁ. | ሐሳቦቹ የሚያጠነጥኑባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች | የጥያቄ ዓይነት | በመጠይቁ ላይ የተሰጠ ቁጥር | | ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለተማሪዎች | ለመምህራን | ለተማሪዎች | ለምህራን |
| 1 | የአንብቦ መረዳት ችሎታን ስለማብልጸግ | ዝግ ጨራሽ | 1÷4÷7÷10 | 2÷6÷10÷14 | 4 | 4 |
| 2 | የሰዋሰውችሎታን ስለማጎልበት | " | 3÷6÷9÷13 | 4÷8÷12 | 4 | 3 |
| 3 | የቃላት አፈታትን ብቃት ስለማሻሻል | " | 2÷5÷8÷11 | 3÷7÷11 | 4 | 3 |
| 4 | የቋንቋ ክሂሎችን በጥምረት ስለማብልጸግ | " | 12÷14 | 1÷15 | 2 | 2 |
| 5 | የማስተማሪያ ስልቱ ለመምህራን ስለሚሰጠው ሙያዊ ድጋፍ | " | - | 5÷9÷13 | - | 3 |
| 6 | ስለ ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ያለ ተጨማሪ አስተያየት | ክፍት ጨራሽ | 15 | 16 | 1 | 1 |
| | | | | ድምር | 15 | 16 |

የቀረበላቸውን የጽሑፍ መጠይቅ የሞሉት 70 የሙከራ ምድቡ አባላት መጠይቁን የሞሉት ከድህረ ፈተና በኋላ ሲሆን÷ ከአጥኚው የተሰጣቸውን ገለጻና ማብራሪያ በመስጠት መጠይቁን ያስሞሉት በአጥኚው ጥያቄ መሰረት ትብብር ያደረጉ የትምህርት ቤቱ መምህር ናቸው:: አጥኚው ተጠኚዎችን መጠይቅ ከማስሞላቱ ተግባር እራሱን ያገለለው በሙከራ ጥናቱ ውስጥ ትምህርቱን ያቀረበው እራሱ በመሆኑ÷ ይህ ተማሪዎች ለመጠይቁ በሚሰጡት ምላሽ ላይ ተጽእኖ እንዳይኖረው ለመከላከል ነው::

ለተጋባዥ መምህራን የተዘጋጀውን መጠይቅ÷ መምህራኑን ለተወሰነ ጊዜ በማሰባሰብ አስፈላጊውን ገለጻ በመስጠት ያሰራጨው አጥኚው ሲሆን÷ በቀነ ቀጠሮው ከተሰራጩት ዘጠኝ መጠይቆች ስምንቱ ተሞልተው መመለስ ችለዋል::

## 3.3. የመረጃ ትንተና

### 3.3.1. የሙከራ ምርምር

ለቁጥጥሩና ለሙከራው ምድብ አባላት የቀረበው ቅደመ ፈተና በአጥኚው በጥንቃቄ ከታረመ በኋላ ውጤቱ በተማሪዎች ስም ዝርዝር ላይ ተገለበጠ። ከዚህ በኋላ በቁጥጥርና በሙከራ ምድብ መካከል ያለውን የችሎታ እኩልነት ለመመዘን በተገቢው ስታትስቲካዊ አመዘጋገብና ስሌት ውስጥ በማለፍ የየምድቡ የተፈታኝ ቁጥር (n)፥ አማካይ ውጤት ($\bar{x}$) እና መደበኛ ልይይት (s) ከታወቀ በኋላ (የቅድመ-ፈተናን ውጤት ስታትስቲካዊ አመዘጋገብና ስሌት ከአባሪ 2-5 ላይ ይመለከቷል) እነዚህን በ"t"- ሙከራ (t-test) ቀመር ውስጥ በማስገባት ተሰልቶ በሁለቱ ምድቦች መካከል የጎላ የችሎታ መለያየት እንደሌለ ለማረጋገጥ ተችሏል። (ሰንጠረዥ 7 እና 9ን ይመለከቷል)

በስግ ስልት ለሙከራ ቡደኑ የቀረበው የንባብ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላም ድህረ-ፈተና ተሰጥቶ ታርሞና ተጠናቅሮ ውጤቱ ከላይ በተጠቀሰው የስሌት ቀመር ተሰልቷል።

### 3.3.2. የድህረ ሙከራ ጥናት

ለድህረ ሙከራ ጥናት ለተጠኚ ተማሪዎችና ለተጋባዥ መምህራን ቀርበው ከተሞሉ የጽሑፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች፥ ቀደም ሲል በተጠቀሰው አመዳደባቸው መሰረት (ሰንጠረዥ አራትን ይመለከቷል) ተለይተው ከተመዘገቡ በኋላ፥ በእያንዳንዱ ሐሳብ ላይ ከተጠኚ ተማሪዎች የተሰበሰቡ አስተያየቶች በቁጥርና በመቶኛ ከተቀመጡ በኋላ ውጤቱ ምን እንደሚያመለክት ትንተና ቀርቧል። የተጋባዥ መምህራኑ ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች በቁጥር ብቻ ተመዝግበው ተተንትነዋል። በሁለቱም መጠይቆች ላይ ከሚገኙት 1፥1 ክፍት ጨራሽ (open ended) ጥያቄዎች የተገኙትን አስተያየቶችም በመልክ በመልካቸው በማደራጀት ከዝግ ጨራሹ (close ended) ክፍል ከተገኘው ውጤት ጋራ ተገናዝቧል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ውጤት ትንተና

### 4.1. የሙከራ ምርምር

ከዚህ በታች በሚታየው ሰንጠረዥ ውስጥ የተመዘገቡት መረጃዎች የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ አባላት በቅድመ-ፈተና መልስ መስጫ ወረቀት ላይ ስለማንነታቸው እንዲገልጹ ለቀረቡላቸው ተጨማሪ ጥያቄዎች ከሰጧቸው ምላሾች የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች ሲሆኑ ከሰንጠረዥ ቀጥሎ በዝርዝር ይተነተናሉ፡፡

## ሰንጠረዥ አምስት፥ የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ አባላት ጾታ፥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፥ እድሜና በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ

| ተ. ቁ. | ምድብ | የየምድቡ ተጠኚዎች ቁጥር | ጾታ | | | | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | | | | እድሜ | | | | በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | | ሴት | | አማርኛ | | ከአማርኛ ውጭ* | | 15-17 | | 18-20 | | አለኝ | | የለኝም | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ቁጥጥር | 72 | 33 | 45.83 | 39 | 54.17 | 55 | 76.39 | 17 | 23.61 | 41 | 56.94 | 31 | 43.06 | 10 | 13.89 | 62 | 86.11 |
| 2 | ሙከራ | 72 | 31 | 43.06 | 41 | 56.94 | 71 | 98.61 | 1 | 1.39 | 51 | 70.83 | 21 | 29.17 | 13 | 18.06 | 59 | 81.94 |
| | አጠቃላይ ድምር | 144 | 64 | 88.89 | 80 | 111.11 | 126 | 175.00 | 18 | 22.00 | 92 | 127.77 | 52 | 72.23 | 23 | 31.95 | 121 | 168.05 |

---

*በቁጥጥር ምድብ ውስጥ ካሉት 17 ከአማርኛ ውጭ በሆነ ቋንቋ አፋቸውን ከፈቱት ውስጥ 9ኙ በኦሮምኛ፥ 2ቱ በትግርኛ፥ 4ቱ በጉራግኛ 1 በወላይትኛና 1 በአረብኛ አፋቸውን የፈቱ ሲሆኑ፥ በሙከራ ምድብ ውስጥ ያለው 1 ተማሪ ደግሞ በትግርኛ ቋንቋ አፉን የፈታ ነው።

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ከቁጥጥር ምድብ አባላት 33 (45.83%) ወንዶች ሲሆኑ÷ 39(54.17%) ሴቶች ናቸው:: ከሙከራ ምደቡ አባላት ደግሞ 31(43.06%) ወንዶች÷ 41(56.94%) ሴቶች ናቸው:: ከዚህ በሁለቱ ምድቦች መካከል ከጾታ ስርጭት አንፃር እምብዛም ልዩነት እንደሌለ እንገነዘባለን::

ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አንጻር ከቁጥጥር ምድብ አባላት 55(76.39%) አፋቸውን በአማርኛ የፈቱ ሲሆን÷ 17 ተማሪዎች (23.61%) ከአማርኛ ውጭ በሆኑ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ናቸው: ከሙከራ ምድቡ አባላት 71(98.61%) አፋቸውን በአማርኛ የፈቱ ሲሆን ቀሪው አንድ ተማሪ ከአማርኛ ውጭ በሆነ ቋንቋ አፉን የፈታ ነው:: እንዲህም በመሆኑ የሙከራ ምድቡ ከቁጥጥር ምድቡ ጋራ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አንፃር ሲወዳደር የሙከራ ምድቡ በአፍ ፈት የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቁጥር በመጠኑ በለጥ የሚል ሆኖ ተገኝቷል::

ከእድሜ አንፃር ከቁጥጥር ምደቡ ከ15-17 የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች 41(56.94%) ሲሆኑ÷ ከ18-20 ዓመት እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ 31(43.06%) ናቸው:: ከ15-17 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ የሙከራ ምድብ አባላት 51 (70.83%) ሲሆኑ÷ ቀሪዎቹ 21(29.17%) ደግሞ ከ18-20 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኙ በሰንጠዡ ላይ የሰፈረው ማስረጃ ያመለክታል:: እዚህም ላይ ልዩነቱ አነስተኛ ቢሆንም በቁጥጥር ምድቡ ውስጥ በእድሜ ገፋ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር በመጠኑ በዛ ያለ መሆኑ ይስተዋላል::

በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድን በሚመለከት ከቁጥጥር ምድቡ አባላት10(13.89%) በቤተ መጻእፍት የመጠቀም ልምድ እንዳላቸው ሲያመለክቱ ÷ 62(86.11%) ልምዱ እንደሌላቸው ገልጸዋል:: ከሙከራ ምድቡ 13 (18.06%)በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ እንዳላቸው ሲያመለክቱ 59(81.94%) በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ እንደሌላቸው ገልጸዋል:: ይህም መረጃ ሁለቱም ምድቦች ምንም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎቸ ቢሆኑም በተመጣጣኝ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ ጉድለት እንዳለባቸው ያመለክታል::

### 4.1.1. የቅድመ-ፈተና ውጤት ትንተና

#### 4.1.1.1. የቅድመ ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት ትንተና

የቅድመ-ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት፥ በአጠቃላይ ፈተና ውስጥ (አጠቃላዩን ፈተና አባሪ 1 ላይ ይመለከቷል) በተካተቱት ሦስት ምንባቦች ስር በቀረቡት 25 የግንዛቤ ጥያቄዎች የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ አባላት ከ50 ያስመዘገቡትን ውጤት የሚመለከት ሲሆን ይህንኑ ከሚከተለው ሰንጠረዥ ማየት ይቻላል።

ሰንጠረዥ ስድስት፥ የቅድመ-ፈተና (pre-test) የአንበቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት

| የቁጥጥር ምድብ (control group) | | | |
|---|---|---|---|
| 1.12 | 19.20 | 37.26 | 55.38 |
| 2.12 | 20.14 | 38.22 | 56.38 |
| 3.16 | 21.38 | 39.30 | 57.22 |
| 4.36 | 22.18 | 40.24 | 58.34 |
| 5.30 | 23.34 | 41.40 | 59.34 |
| 6.34 | 24.38 | 42.36 | 60.18 |
| 7.14 | 25.28 | 43.34 | 61.20 |
| 8.36 | 26.40 | 44.30 | 62.28 |
| 9.22 | 27.14 | 45.40 | 63.40 |
| 10.32 | 28.28 | 46.26 | 64.28 |
| 11.36 | 29.24 | 47.40 | 65.24 |
| 12.10 | 30.26 | 48.28 | 66.30 |
| 13.12 | 31.38 | 49.28 | 67.28 |
| 14.32 | 32.32 | 50.36 | 68.34 |
| 15.30 | 33.38 | 51.18 | 69.28 |
| 16.12 | 34.28 | 52.24 | 70.30 |
| 17.34 | 35.22 | 53.30 | 71.14 |
| 18.32 | 36.20 | 54.8 | 72.34 |

$n_1 = 72$

$\overline{X}_1 = 27.19$

$S_1 = 8.65$

| የሙከራ ምድብ (Experimental group) | | | |
|---|---|---|---|
| 1.34 | 19.26 | 37.37 | 55.36 |
| 2.12 | 20.32 | 38.20 | 56.12 |
| 3.38 | 21.26 | 39.34 | 57.22 |
| 4.34 | 22.40 | 40.38 | 58.16 |
| 5.34 | 23.28 | 41.26 | 59.38 |
| 6.38 | 24.22 | 42.12 | 60.22 |
| 7.34 | 25.38 | 43.18 | 61.30 |
| 8.24 | 26.22 | 44.34 | 62.26 |
| 9.18 | 27.30 | 45.34 | 63.34 |
| 10.22 | 28.26 | 46.34 | 64.32 |
| 11.10 | 29.34 | 47.32 | 65.26 |
| 12.12 | 30.26 | 48.30 | 66.30 |
| 13.26 | 31.26 | 49.32 | 67.24 |
| 14.24 | 32.20 | 50.18 | 68.16 |
| 15.36 | 33.38 | 51.32 | 69.28 |
| 16.36 | 34.30 | 52.34 | 70.24 |
| 17.36 | 35.36 | 53.18 | 71.30 |
| 18.28 | 36.28 | 54.26 | 72.40 |

$n_2 = 72$

$\overline{X}_2 = 28.19$

$S_2 = 7.74$

ሰንጠረዥ ስድስት ለሙከራ ቡድኑ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ከመስጠቱ በፊት በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኑ መካከል ያለውን የአንብቦ መገንዘብ ልዩነት ለመገምገም በአጠቃላይ ቅደመ-ፈተና ውስጥ የተካተተውን የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት ያሳያል:: ከሰንጠረዡ ግርጌ የተመዘገቡትን የሁለቱን ቡድኖች አማካይ ውጤቶች ስንመለከት የሙከራ ቡድኑ አማካይ ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ በ1 የሚበልጥ መሆኑ ይስተዋላል:: (የአማካይና የመደበኛ ልይይትን ስሌት አባሪ 2 ላይ ይመለከቷል)

በሁለቱ ቡድኖች መካከል የታየው ይህ መጠነኛ የአማካይ ውጤት ልዩነት ሁለቱ ቡድኖች በአንብቦ መገንዘብ ችሎታ ያላቸውን የችሎታ መበላለጥ ምን ያህል እንደሚያንጸባርቅ ለማየት ውጤቱ በ"t"-ሙከራ (t-test) ተሰልቶ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል:: (የስሌቱን ክንውን በአባሪ 3 ላይ ይመለከቷል)

ሰንጠረዥ ሰባት፦ የቅድመ ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የt ሙከራ (t-test) ስሌት ማጠቃለያ::

| የቁጥጥር ምድብ | | | የሙከራ ምድብ | | | በስሌት የተገኘ የ"t" ዋጋ | ከሰንጠረዥ የተገኘ የ"t" ዋጋ | የጎላ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአባላት ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የአባላት ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | | |
| 72 | 27.19 | 8.65 | 72 | 28.19 | 7.74 | 0.73 | 1.96 | የጎላ ልዩነት አይታይም |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ተሰልቶ የተገኘው የ"t"-ዋጋ 0.73 ነው:: በ142 የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) (የነፃነት ደረጃ ከሁለቱ ምድብ አባላት ቁጥር ድምር ላይ ሁለት በመቀነስ ይገኛል) በ$p< 0.05$ የጉልህነት መጠን በ"t"- ሰንጠረዥ ላይ ተመዝገቦ የተገኘው ቁጥር ደግሞ 1.96 ነው:: በመሆኑም ተሰልቶ የተገኘው የ"t"-ዋጋ በ"t"- ሰንጠረዥ ላይ ተመዝግቦ ከተገኘው የ"t" ዋጋ የሚያንስ በመሆኑ በቁጥጥርና በሙከራ ምድቡ መካከል አጥጋቢ የሆነ የአንብቦ መገንዘብ ችሎታ ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል::

## 4.1.1.2. የቅድመ-ፈተና (pre-test) የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ውጤት ትንተና

የቅድመ-ፈተና አጠቃላይ ውጤት፥ በቅድመ-ፈተና (አባሪ አንድን ይመለከቷል) ውስጥ በሰባት ንኡሳን ክፍሎች ተካፋፍለው በቀረቡት 50 ጥያቄዎች የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ አባላት ከ100 ያስመዘገቡትን ውጤት የሚመለከት ሲሆን ይህንኑ ከሚከተለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል።

**ሰንጠረዥ ስምንት፥ የቅድመ-ፈተና (pre-test) አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ውጤት**

| የቁጥጥር ምድብ (control group) | | | |
|---|---|---|---|
| 1.22 | 19.58 | 37.62 | 55.78 |
| 2.46 | 20.44 | 38.52 | 56.64 |
| 3.36 | 21.74 | 39.68 | 57.46 |
| 4.70 | 22.46 | 40.44 | 58.74 |
| 5.66 | 23.74 | 41.74 | 59.62 |
| 6.68 | 24.78 | 42.70 | 60.54 |
| 7.36 | 25.66 | 43.74 | 61.44 |
| 8.74 | 26.80 | 44.62 | 62.66 |
| 9.60 | 27.24 | 45.76 | 63.64 |
| 10.66 | 28.64 | 46.46 | 64.54 |
| 11.76 | 29.44 | 47.76 | 65.62 |
| 12.24 | 30.66 | 48.60 | 66.64 |
| 13.46 | 31.74 | 49.68 | 67.62 |
| 14.70 | 32.66 | 50.70 | 68.70 |
| 15.68 | 33.78 | 51.34 | 69.58 |
| 16.38 | 34.58 | 52.48 | 70.56 |
| 17.64 | 35.56 | 53.58 | 71.34 |
| 18.72 | 36.52 | 54.24 | 72.60 |

$n_1 = 72$

$\overline{X}_1 = 58.92$

$S_1 = 14.61$

| የሙከራ ምድብ (Experimental group) | | | |
|---|---|---|---|
| 1.56 | 19.54 | 37.80 | 55.68 |
| 2.30 | 20.70 | 38.44 | 56.32 |
| 3.74 | 21.56 | 39.66 | 57.56 |
| 4.70 | 22.62 | 40.72 | 58.40 |
| 5.60 | 23.54 | 41.52 | 59.74 |
| 6.78 | 24.60 | 42.38 | 60.54 |
| 7.70 | 25.78 | 43.60 | 61.66 |
| 8.60 | 26.54 | 44.68 | 62.56 |
| 9.42 | 27.50 | 45.68 | 63.70 |
| 10.48 | 28.44 | 46.64 | 64.62 |
| 11.46 | 29.68 | 47.64 | 65.60 |
| 12.32 | 30.50 | 48.68 | 66.52 |
| 13.52 | 31.42 | 49.70 | 67.58 |
| 14.56 | 32.46 | 50.38 | 68.50 |
| 15.76 | 33.76 | 51.74 | 69.56 |
| 16.72 | 34.64 | 52.64 | 70.52 |
| 17.74 | 35.64 | 53.50 | 71.64 |
| 18.58 | 36.58 | 54.54 | 72.84 |

$n_2 = 72$

$\overline{X}_2 = 59.06$

$S_2 = 12.14$

ሰንጠረዥ ስምንት ለሙከራ ምድቡ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ከመስጠቱ በፊት በቁጥጥርና በሙከራ ምድቡ መካከል ያለውን አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ለመገምገም የተሰጠውን አጠቃላይ የአማርኛ ቅደመ ፈተና (pre-test) ውጤት ያሳያል። ከሰንጠረዡ ግርጌ ተመዝግበው የሚገኙት የሁለቱ ምድቦች አማካይ ወጤቶች የቁጥጥር ምደቡ 58.92 የሙከራ ምደቡ 59.06 በመሆናቸው በጣም ተቀራራቢ መሆናቸው ይታያል። (የአማካይና የመደበኛ ልይይቱን ስሌት በአባሪ 4 ላይ ይመለከቷል።)

በሁለቱ ምድቦች አማካዮች መካከል ተቀራራቢነት የሚታይ ቢሆንም ያለው መጠነኛ ልዩነት በምድቦቹ መካከል ያለውን የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ልዩነት ምን ያህል እንደሚያንጸባርቅ ለማወቅ የሁለቱ ምድቦች ውጤት በ"t"- ሙከራ ተሰልቶ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል። (የስሌቱን ክንውን በአባሪ 5 ላይ ይመለከቷል።)

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፥ የቅድመ ፈተና አጠቃላይ ውጤት የ"t" ሙከራ(t-test) ስሌት ማጠቃለያ።

| የቁጥጥር ምድብ | | | የሙከራ ምድብ | | | በስሌት የተገኘ የ"t" ዋጋ | ከሰንጠረዥ የተገኘ የ"t"-ዋጋ | የጎላ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአባላት ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የአባላት ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | | |
| 72 | 58.92 | 14.61 | 72 | 59.06 | 12.14 | 0.06 | 1.96 | የጎላ ልዩነት አይታይም |

ከሰንጠረዥ እንደሚታየው ተሰልቶ የተገኘው የ"t"- ዋጋ (t-value) 0.06 ነው። በ142 የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) በ$p< 0.05$ የጉልህነት መጠን በ"t"- ሰንጠረዥ ላይ ተመዝግቦ የተገኘው የ"t"-ዋጋ 1.96 ነው። በመሆኑም ተሰልቶ የተገኘው የ"t"- ዋጋ በ"t" ስርጭት ሰንጠረዥ ላይ ከተገኘው የ"t" ዋጋ ያነሰ በመሆኑ በቁጥጥርና በሙከራ ምደቡ መካከል የጎላ የአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ልዩነት እንደሌለ ተረጋግጧል።

## 4.1.2. የድህረ ፈተና (Post-test) ውጤት ትንተና

### 4.1.2.1. የድህረ ፈተና (post-test) የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት ትንተና።

የድህረ-ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት፥ በአጠቃላይ ፈተና ውስጥ (አጠቃላዩን ፈተና አባሪ 8 ላይ ይመለከቷል) በተካተቱት ሦስት ምንባቦች ስር በቀረቡት 25 የግንዛቤ ጥያቄዎች የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ አባላት ከ50 ያስመዘገቡትን ውጤት የሚመለከት ሲሆን ይህንኑ ከሚከተለው ሰንጠረዥ ማየት ይቻላል።

**ሰንጠረዥ አሥር፥ የድህረ ፈተና** (post-test) **የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት**

| የቁጥጥር ምድብ (control group) | | | |
|---|---|---|---|
| 1.10 | 19.30 | 37.24 | 55.32 |
| 2.26 | 20.16 | 38.14 | 56.24 |
| 3.20 | 21.36 | 39.26 | 57.18 |
| 4.12 | 22.16 | 40.20 | 58.- |
| 5.26 | 23.30 | 41.- | 59.32 |
| 6.34 | 24.40 | 42.20 | 60.10 |
| 7.22 | 25.30 | 43.32 | 61.24 |
| 8.38 | 26.38 | 44.38 | 62.30 |
| 9.30 | 27.16 | 45.32 | 63.24 |
| 10.28 | 28.28 | 46.42 | 64.- |
| 11.36 | 29.16 | 47.34 | 65.28 |
| 12.10 | 30.22 | 48.38 | 66.12 |
| 13.14 | 31.36 | 49.26 | 67.22 |
| 14.34 | 32.26 | 50.- | 68.20 |
| 15.42 | 33.36 | 51.22 | 69.34 |
| 16.24 | 34.24 | 52.28 | 70.12 |
| 17.22 | 35.22 | 53.16 | 71.12 |
| 18.36 | 36.20 | 54.18 | 72.26 |

$n_1$ = 68

$\overline{X}_1$ = 25.53

$S_1$ = 8.60

| የሙከራ ምድብ(Experimental group) | | | |
|---|---|---|---|
| 1.30 | 19.28 | 37.40 | 55.36 |
| 2.42 | 20.24 | 38.18 | 56.- |
| 3.30 | 21.38 | 39.26 | 57.18 |
| 4.32 | 22.38 | 40.36 | 58.36 |
| 5.32 | 23.18 | 41.32 | 59.42 |
| 6.44 | 24.28 | 42.24 | 60.40 |
| 7.38 | 25.36 | 43.36 | 61.34 |
| 8.40 | 26.34 | 44.32 | 62.24 |
| 9.- | 27.34 | 45.42 | 63.34 |
| 10.34 | 28.- | 46.28 | 64.40 |
| 11.34 | 29.24 | 47.24 | 65.40 |
| 12.20 | 30.24 | 48.36 | 66.38 |
| 13.30 | 31.48 | 49.36 | 67.36 |
| 14.38 | 32.22 | 50.28 | 68.40 |
| 15.44 | 33.46 | 51.36 | 69.14 |
| 16.26 | 34.42 | 52.40 | 70.42 |
| 17.30 | 35.32 | 53.22 | 71.26 |
| 18.- | 36.32 | 54.22 | 72.48 |

$n_2$ = 68

$\overline{X}_2$ = 32.91

$S_2$ = 7.82

በሰንጠረዥ አሥር ግርጌ የተመዘገበው መረጃ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ አባላት 68÷ 68 መሆናቸውን÷ የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በዚሁ ቅደም ተከተል 25.53 እና 8.60 መሆኑን÷ የሙከራ ምድቡ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በዚሁ ቅደም ተከተል 32.91 እና 7.82 መሆኑ ተመልክቷል:: (ስለተጠቀሰው የቁጥጥርና ሙከራ ምድብ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ስሌት አባሪ 9ን ይመለከቷል)

ከተሰጠው መረጃ የሙከራ ምድቡ አማካይ ከቁጥጥር ምደቡ አማካይ በ7.38 የሚበልጥ ቢሆንም የታያው ልዩነት በሁለቱ ምድቦች መካከል ያለውን ጉልህ ልዩነት የሚያንጸባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ውጤቱ በ"t"- ሙከራ (t-test) ተሰልቶ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል::

ሰንጠረዥ አሥራ አንድ÷የድህረ-ፈተና (Post-test) የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የ"t"ሙከራ (t-test) ስሌት ማጠቃለያ::

| የቁጥጥር ምድብ | | | የሙከራ ምድብ | | | በስሌት የተገኘ የ"t" ዋጋ | ከሰንጠረዥ የተገኘ የt-ዋጋ | የጎላ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአባላት ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የአባላት ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | | |
| 68 | 25.53 | 8.60 | 68 | 32.91 | 7.82 | 5.23 | 1.96 | የጎላ ልዩነት ታይቷል |

በዚህ ሰንጠረዥ ላይ የሚታየው ተሰልቶ የተገኘ የ"t" ዋጋ (5.23) (የ"t"-ዋጋ እንዴት እንደሚሰላ አባሪ 10ን ይመለከቷል) በ134 የነፃነት ደረጃ(degree of freedom) በ$p < 0.05$ የጉልህነት መጠን በ"t"- ሰንጠረዥ ላይ ተመዝግቦ ከተገኘው ከ1.96 የሚበልጥ በመሆኑ (5.23>1.96) የሙከራ ቡድኑ በድህረ ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ከቁጥጥር ምድቡ የላቀ ውጤት እንዳስመዘገበ ማረጋገጥ ተችሏል::

### 4.1.2.2. የድህረ-ፈተና(post-test) የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ውጤት ትንተና ::

የድህረ-ፈተና አጠቃላይ ውጤት፥ በድህረ-ፈተና ውስጥ (አባሪ ስምንትን ይመለከቷል) በሰባት ንኡሳን ክፍሎች ተከፋፍለው በቀረቡት 50 ጥያቄዎች የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ አባላት ከ100 ያስመዘገቡትን ውጤት የሚመለከት ሲሆን ይህንኑ ከሚከተለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል::

**ሰንጠረዥ አሥራ ሁለት፥የድህረ ፈተና (post-test) አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ውጤት**

| የቁጥጥር ምድብ (control group) | | | |
|---|---|---|---|
| 1.26 | 19.62 | 37.66 | 55.72 |
| 2.64 | 20.38 | 38.44 | 56.54 |
| 3.44 | 21.76 | 39.58 | 57.36 |
| 4.40 | 22.28 | 40.48 | 58.- |
| 5.66 | 23.68 | 41.- | 59.72 |
| 6.78 | 24.76 | 42.52 | 60.40 |
| 7.26 | 25.64 | 43.72 | 61.56 |
| 8.72 | 26.78 | 44.72 | 62.54 |
| 9.76 | 27.38 | 45.74 | 63.48 |
| 10.60 | 28.60 | 46.70 | 64.- |
| 11.80 | 29.36 | 47.68 | 65.66 |
| 12.26 | 30.46 | 48.74 | 66.32 |
| 13.34 | 31.70 | 49.66 | 67.64 |
| 14.70 | 32.64 | 50.- | 68.46 |
| 15.86 | 33.82 | 51.26 | 69.72 |
| 16.50 | 34.54 | 52.54 | 70.42 |
| 17.50 | 35.52 | 53.42 | 71.38 |
| 18.72 | 36.46 | 54.44 | 72.58 |

| የሙከራ ምድብ(Experimental group) | | | |
|---|---|---|---|
| 1.66 | 19.50 | 37.82 | 55.76 |
| 2.82 | 20.52 | 38.44 | 56.- |
| 3.62 | 21.82 | 39.66 | 57.48 |
| 4.76 | 22.68 | 40.76 | 58.70 |
| 5.72 | 23.52 | 41.62 | 59.78 |
| 6.84 | 24.64 | 42.66 | 60.72 |
| 7.78 | 25.74 | 43.74 | 61.74 |
| 8.68 | 26.74 | 44.66 | 62.56 |
| 9.- | 27.62 | 45.84 | 63.72 |
| 10.66 | 28.- | 46.68 | 64.78 |
| 11.70 | 29.66 | 47.64 | 65.70 |
| 12.56 | 30.50 | 48.76 | 66.70 |
| 13.68 | 31.90 | 49.74 | 67.68 |
| 14.70 | 32.54 | 50.72 | 68.78 |
| 15.86 | 33.88 | 51.68 | 69.56 |
| 16.68 | 34.76 | 52.82 | 70.42 |
| 17.76 | 35.64 | 53.64 | 71.62 |
| 18.- | 36.64 | 54.54 | 72.90 |

$n_1 = 68$

$\overline{X}_1 = 56.47$

$S_1 = 16.04$

$n_2 = 68$

$\overline{X}_2 = 69.15$

$S_2 = 10.41$

በሰንጠረዥ አሥራ ሁለት መጨረሻ ላይ የሰፈረው መረጃ የቁጥጥርና የሙከራ ምደብ አባላት ቁጥር 68÷68 መሆኑን÷ የቁጥጥር ምድብ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በዚሁ ቅደም ተከተል 56.47 እና 16.04 መሆኑን÷ የሙከራ ምድብ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በዚሁ ቅደም ተከተል 69.15 እና 10.41 መሆኑን ያመለክታል:: (የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡን የአማካይ ውጤትና የመደበኛ ልይይት ስሌት በአባሪ 11 ላይ ይመለከቷል::)

እንዲህም በመሆኑ የተጠቀሰው መረጃ የሙከራ ምድቡ በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ያስመዘገበው አማካይ ውጤት ቁጥጥር ምድቡ ካስመዘገበው በአንፃ ሲታይ በ12.68 የሚበልጥ መሆኑን አሳይቷል:: ይህ የውጤት ልዩነት በሁለቱ ምድቦች መካከል የችሎታ መለያየት እንዳለ ቢያመለክትም ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የሁለቱ ምድቦች ውጤት በ"t" ሙከራ (t-test) ተሰልቶ እንደሚከተለው ተጠቃሏል::

ሰንጠረዥ አሥራ ሦስት÷የድህረ ፈተና (post-test) አጠቃላይ ውጤት የ"t"-ሙከራ (t-test) ስሌት ማጠቃለያ::

| የቁጥጥር ምድብ | | | የሙከራ ምድብ | | | በስሌት የተገኘ የ"t" ዋጋ | ከሰንጠረ ዥ የተገኘ የ"t" ዋጋ | የጎላ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአባላት ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የአባላት ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | | |
| 68 | 56.47 | 16.04 | 68 | 69.15 | 10.41 | 5.47 | 1.96 | የጎላ ልዩነት ታይቷል |

ከዚህ በላይ ባለው የ"t"-ስሌት ማጠቃለያ ሰንጠረዥ ውስጥ የሚታየው ተሰልቶ የተገኘ የ"t"-ዋጋ (5.47) (የ"t"-ዋጋውን ስሌት በአባሪ 12 ላይ ይመለከቷል) በ134 የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) በ$p<0.05$ የጉልህነት መጠን በ"t"-ሰንጠረዥ ላይ ተመዝግቦ ከተገኘው የ"t" ዋጋ (1.96) የሚበልጥ በመሆኑ (5.47> 1.96) ስሌቱ የሙከራ ቡድኑ በድህረ ፈተና ያስመዘገበው የአማርኛ ቋንቋ ጥቅል ውጤት የቁጥጥር ምድቡ ካስመዘገበው የላቀ እንደሆነ አመልክቷል::

ሰንጠረዥ አሥራ አራት÷የቅድመ ፈተናና የድህረ ፈተና የ"t"-ሙከራ ስሌት ማጠቃለያ

| ፈተና | | የአባላት ቁጥር | የቁጥጥር መደብ | | የሙከራ ምድብ | | በስሌት የተገኘ የ"t"-ዋጋ | ከሰንጠረዥ የተገኘ የ"t"-ዋጋ | የጎላ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | | |
| ቅድመ-ፈተና | የአንብቦ መረዳት ንኡስ ክፍል | 72 | 27.19 | 8.65 | 28.19 | 7.74 | 0.73 | 1.96 | የጎላ ልዩነት አልታየም |
| | አጠቃላይ የቋንቋ ፈተና | 72 | 58.92 | 14.61 | 59.06 | 12.14 | 0.06 | 1.96 | የጎላ ልዩነት አልታየም |
| ድህረ-ፈተና | የአንብቦ መረዳት ንኡስ ክፍል | 68 | 25.53 | 8.60 | 32.91 | 7.82 | 5.23 | 1.96 | የጎላ ልዩነት ታይቷል |
| | አጠቃላይ የቋንቋ ፈተና | 68 | 56.47 | 16.04 | 69.15 | 10.41 | 5.47 | 1.96 | የጎላ ልዩነት ታይቷል |

ከሰንጠረዥ 14 እንደምንረዳው ይህ ጥናት ሲጀመር (ለሙከራ ምድቡ በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት) ቅደመ ፈተና ተሰጥቶ የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡ ያገኙት ውጤት በ"t"- ሙከራ (t-test) ሲሰላ የተገኘው ውጤት የአንብቦ መረዳት 0.73 የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ 0.06 በመሆኑና÷ይህ በ"t"-ሰንጠረዥ ላይ በ142 የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) በ$p<0.05$ የጉልህነት መጠን ተመዝግቦ ከተገኘው ከ1.96 የሚያንስ በመሆኑ በሁለቱ ምድቦች መካከል በአንብቦ መረዳትና በአጠቃላይ ቋንቋ ችሎታ የጎላ የችሎታ ልዩነት እንደሌለ ያረጋገጠ ሲሆን÷ ለስድስት የሙከራ ሳምንታት ለቁጥጥር ምድቡ የተለመደው የአማርኛ ትምህርት እየቀረበ ለሙከራ ምድቡ በስግ ስልት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ከተሰጠ በኋላ ለሁለቱ ምድቦች ድህረ- ፈተና ተሰጥቷቸው ያስመዘገቡት ውጤት የ"t"-ሙከራ ስሌት ውጤት የአንብቦ መረዳት 5.23÷ የአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ 5.47 ሆኖ በመገኘቱና÷ ይህ ውጤት በ"t"-ሰንጠረዥ ላይ በ134 የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) በ$p<0.05$ የጉልህነት መጠን ተመዝግቦ ከተገኘው ከ1.96 የሚበልጥ በመሆኑ÷ የሙከራ ምድቡ በአንብቦ መረዳትም ሆነ በአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ከቁጥጥር ምድቡ የጎላ የችሎታ ብልጫ እንዳለው በማመልከቱ በዚህ ውጤት መረጃነት አጥኚው ይዞት የተነሳውን ባዶ መላ ምት ($H_0$) ማስወገድ ችሏል።

## 4.2. የድህረ ሙከራ ጥናት

በምዕራፍ ሦስት ውስጥ በሚገኘው በሰንጠረዥ አራት ውስጥ እንደተገለጸው ለሙከራ ምድብ አባላትና ለተጋባዥ መምህራን በቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች ላይ አስተያየት እንዲሰጥባቸው የተነሱት ሐሳቦች ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ፥ የቃላት ችሎታ፥ የሰዋሰዋዊ አገባብ ችሎታና የክሂሎች ጥምረት ከሚሉት አራት ዋና ዋና ጉዳዮች ጋራ ያለውን ግንኙነት የሚዳስሱ ናቸው፡፡ ለተጋባዥ መምህራን በቀረበው መጠይቅ ላይ ከነዚህ በተጨማሪ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ለመምህራን የሚሰጠውን ሙያዊ እገዛ የሚመለከቱ ሐሳቦች አስተያየት እንዲሰጥባቸው ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ለተጠኚ ተማሪዎችም ሆነ ለተጋባዥ መምህራን ተሰራጭተው ከተሞሉ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች በተዘረዘሩት አምስት ምድቦች ተደልድለው ይተነተናሉ፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋ. ጥ. ተ. ቤተ መጻሕፍት ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

## 4.2.1. ለሙከራ ምድብ አባላት ከተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**ሰንጠረዥ አስራ አምስት÷**በስግ ሥርዓት የሚቀረብ የንባብ ትምህረት የአንብቦ መረዳትን ብቃት ከማበልጸግ አንፃር ስላለው ሚና ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘ መረጃ::

| ተ.ቁ. | ሐሳብ | አስተያየት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፈጽሞ አልስማማም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ከስግ ክፍት ቦታ በመነሳት ወደፊትና ወደ ኋላ እያሰሱ ከምንባብ ውስጥ መረጃዎችን የመፈለግ ተግባር አንብቦ የመረዳት ችሎታህ(ሽ)ን ለማዳበር አግዟል:: | 35 | 50 | 29 | 41.43 | 3 | 4.28 | 3 | 4.29 |
| 4 | በቡድን እየተወያያችሁ ስግ ምንባቦችን በምታሟሉበት ወቅት ስለፈጸምካ(ሻ)ቸው ስህተቶች ከቡድን አባላትና ከመምህር የተሰጡ የእርማት አስተያየቶች ድክመትህ(ሽ)ን መቅረፋቸው ለአንብቦ መረዳት ችሎታህ(ሽ) መዳበር አሰተዋጽኦ አድርጓል:: | 45 | 64.29 | 19 | 27.14 | 4 | 5.71 | 2 | 2.86 |
| 7 | ባደረጋችሁት የቡድን ውይይት ወቅት አያያዥ ቃላት ለስግ ምንባብ ክፍት ቦታዎች መሙያነት ለምን እነደተመረጡ የቀረቡ ምክንያቶች÷ በምንባብ ውስጥ ያሉ ሐሳቦችን እያገናዘቡ ስለማንባብ አስፈላጊነት | 39 | 55.71 | 25 | 37.71 | 3 | 4.29 | 3 | 4.29 |
| 10 | ለስግ ምንባብ ማሟያነት የተመረጡ ቃላት ለምን እነደተመረጡ የተሰጡ ምክንንያቶች ባመዛኙ በመላሾች የቀድሞ እውቀት ላይ የተመሰረተ መሆን÷ አንብቦ ለመረዳት ዳራዊ እውቀት ከፍተኛ ድረሻ እንዳለው ለመገንዘብ አስችሎሃ(ሻ)ል:: | 21 | 30 | 36 | 51.43 | 7 | 10 | 6 | 8.57 |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው መጠይቁን ከሞሉት 70 የሙከራ ምድቡ አባላት በስግ ምንባብ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች ለማግኘት ያከናወኑት በምንባብ ውስጥ ወደፊትና ወደኋላ የማሰስ ክንዋኔ ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መዳበር እገዛ እንዳደረገ ለሚጠቁመው በተራ ቁጥር 1 ላይ ለቀረበ ሐሳብ 35 (50%) በከፍተኛ ደረጃ አስማማለሁ÷ 29(41.43%) እስማማለሁ በማለት÷ በጥቅል 64(91.43%) የስምነት አስተያየት ሲሰጡ ÷ 3(4.29%) አልስማማምና 3 ደግሞ (4.29%)ፈጽሞ አልስማማም በማለት በድምሩ 6(8.57%) አሉታዊ አስተያየት ሰጥተዋል::

በስግ ምንባብ መሙላት ክንውን ውስጥ የሚፈጽሙት ስህተት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የማዳበር ሚና እንዳለው የሚያመለክተውን በተራ ቁጥር 4 ላይ የቀረበ ሐሳብ ከተጠኚ ተማሪዎች 45 (64.29%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ 19 (27.14%) እስማማለሁ በማለት፥ በጥቅሉ 64 (91.45%) የስምምነት አስተያየት ሲሰጡ 4 አልስማማም 2 ደግሞ ፈጽሞ አልስማማም በማለት በጥቅል 6(8.57%) አሉታዊ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በተራ ቁጥር 7 ላይ ለክፍት ቦታ መሙያነት ስለሚመረጡ አያያዦች መመረጥ የሚሰጥ ምክንያት እያገናዘቡ ስለማንበብ አስፈላጊነት ጥቆማ እንደሰጣቸው ለቀረበው ሐሳብ ከተጠኚዎቹ 39 (55.71%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 25 (37.71%) እስማማለሁ በማለት፥ በጥቅሉ 64 (91.45%) በስምምነት አስተያየት ሲሰጡ 3 አልስማማም 3 ፈጽሞ አልስማማም በማለት በድምሩ 6 (8.55%) አሉታዊ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በስግ ሥርዓት የንባብ ትምህርት ክንውን ውይይት ውስጥ አንዳንዶች ለስግ ክፍት ቦታዎች መሙያነት ስለሚሰነዝሯቸው ግምቶች ተገቢነት በቀድሞ እውቀታቸው ላይ የተመሰረተ ምክንያት ማቅረባቸው አንብቦ ለመረዳት ዳራዊ እውቀት ስላለው ድርሻ አስገንዝቦሃ/ሻ/ል ለሚለው በተራ ቁጥር 10 ላይ ለቀረበ ሐሳብ ከተጠኚዎቹ 21(30%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 36 (51.43%) እስማማለሁ በማለት በድምሩ 57 (81.43%) የስምምነት አስተያየት ሲሰጡ፥ 7(10%) አልስማማም፥ 6(8.57%) ፈጽሞ አልስማማም በማለት በድምሩ 13(18.17%) የተቃውሞ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በስግ ስልት የቀረበላቸው የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ማዳበሩን በሚመለከት በሰንጠረዥ 14 ላይ የቀረቡት ሐሳቦች ከ81.43% እስከ 91.45% የሚደርሱትን ተጠኚዎች ድጋፍ ያገኘ በመሆኑ በዚህ ክፍል ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘው መረጃ ተጠኚዎቹ ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ሊያደብርላቸው መቻሉን እንደሚቀበሉ አመልክቷል፡፡ ተግባራዊ የተደረገው የንባብ ማስተማሪያ ስልት ዳራዊ እውቀት ለአንብቦ መረዳት ተግባር ሊጠቅም የሚችልበትን ሁኔታ ሁሉ የሚያመቻች ቢሆንም ከተጠኚዎቹ 13(18.17%) ዳራዊ እውቀት ለአንብቦ መረዳት የሚሰጠውን ድጋፍ በተራ ቁጥር 10 ላይ መቃወማቸው፥ ይህንን ጉዳይ ቀደም ሲል የማያውቁትና አዲስ እንደሆነባቸው

ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንፃር ብዙዎቹ በሐሳቡ ላይ መስማማታቸው ትምህርቱ በዚሁ መጠን ግቡን መምታት መቻሉንም ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ አስራ ስድስት÷** በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቃላት ችሎታን ከማበልጸግ አንፃር ስላለው ሚና ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘ መረጃ፡፡

| ተ.ቁ. | ሐሳብ | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፈጽሞ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2 | አንዳንድ ጊዜ ከተገደፉ ቃላት አጠገብ ያሉ ቃሎችና ሐረጎች ስለተገደፈው ቃል ምንነት ቀጥተኛ ጥቆማ የሚሰጡ መሆኑ በተሟላ ምንባብ ውስጥም ከእንደነዚህ ዓይነቶቹ ጥቆማ ሰጪ ቃሎችና ሐረጎች በመነሳት ቃላትን በሙሉ አንድ ባንድ ማየት ሳያስፈልግ በፍጥነት ማንባብ እንደሚቻል ግንዛቤ ሰጥቶሃ(ሻ)ል፡፡ | 33 | 47.14 | 31 | 44.29 | 5 | 7.14 | 1 | 1.43 |
| 5 | በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ለአንድ ክፍት ቦታ ማሟያነት የተለያዩ ተገቢነት ያላቸው አማራጭ መልሶች የመሰንዘራቸውው ሁኔታ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስለመስጠት ግንዛቤ እንድታገኝ(ኚ) ረድቷል፡፡ | 39 | 55.71 | 24 | 34.29 | 2 | 2.86 | 5 | 7.14 |
| 8 | በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ልዩ ልዩ አይነት ምንባቦች (ግጥም÷ታሪክ÷ ልቦለዳዊ ምንባቦች ... ወዘተ) መቅረባቸው ቃላትና ሐረጋትን ከነዚህ ምንባቦች ልዩ ባህርይ አንፃር ለመተርጎም አስችሎሃ/ሻ/ል፡፡ | 26 | 37.14 | 35 | 50 | 4 | 5.72 | 5 | .14 |
| 11 | በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ያደረግከ(ሽ)ው ተሳትፎ የቃላትን ፍቺ ከአውደ ምንባብ ለመገመት አስችሎሃ(ሻ)ል፡፡ | 25 | 35.71 | 31 | 44.29 | 8 | 11.43 | 6 | 8.57 |

በሰንጠረዥ 15 ውስጥ ከተመዘገበው መረጃ በስግ ምንባብ ውስጥ ያልተደገፉ ቃላት ስለተገደፉት ቃላት የሚሰጡት ፍንጭ ከቃላት እውቀት ጋራ በተገናዘበ መልኩ ለፍጥነት ንባብ ችሎታ እንደሚረዳ ግንዛቤ ይሰጣል ለሚለው በቁጥር 2 ላይ የቀረበ ሐሳብ ከተጠኚዎቹ 33(47.14%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ÷ 31 (44.29%)

እስማማለሁ በማለት በድምሩ 64(91.43%) የስምምነት አስተያየት ሲሰጡ 6(8.57%) አሉታዊ (5 አልስማማም፥ 1 ፈጽሞ አልስማማም) አስተያየት ሰጥተዋል።

በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ለአንድ ክፍት ቦታ ማሟያነት የተለያዩ ተገቢነት ያላቸው አማራጭ መልሶች መቅረባቸው ለቃላት ተመሳሰይ ፍቺ ስለመስጠት ግንዛቤ ያስገኛል ለሚለው በተራ ቁጥር 5 ውስጥ የቀረበ ሐሳብ ከተጠኚዎች 39(55.71%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 24(34.29%) እስማማለሁ በማለት፥ በድምሩ 63 (90%) የስምምነት አስተያየት ሲሰጡ 7(10%) በዚህ ሐሳብ ላይ የተቃውሞ አስተያየት ሰጥተዋል።

በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ልዩ ልዩ ዓይነት ምንባቦች እየተመረጡ መቅረባቸው ቃላትን ከነዚህ የተለያዩ ምንባቦች ልዩ ባህርይ አንፃር ለመተርጎም አስችሎሃ/ሻ/ል በሚል በቁጥር 8 ላይ ለተሰነዘረው ሐሳብ 26 (37.14%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 35(50%) እስማማለሁ በማለት፥ በድምሩ 61 ተጠኚዎች (84.14%) የስምምነት አስተያየት ሲያቀርቡ፥ 9 (12.86%) የተቃውሞ አስተያየት ሰነዘረዋል።

በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ያደረግከ/ሽ/ው ተሳትፎ የቃላትን ፍቺ ከአውደ ምንባብ ለመገመት አስችሎ ሃ/ሻ/ል፥ በሚል በተራ ቁጥር 11 ውስጥ ለቀረበው ሐሳብ ከተጠኚዎች 25 (35.71%)በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 31(44.29%) እስማማለሁ በማለት በጥቅሉ 56 ተጠኚዎች (80%) የድጋፍ አስተያየት ሲያቀርቡ፥ 8(11.43%) አልስማማም፥ 6(8.57%) ፈጽሞ አልስማማም በማለት፤ በድምሩ 14(20%) የተቃውሞ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በዚህም ሰንጠረዥ ውስጥ ለቀረቡት የተለያዩ ሐሳቦች የተሰጡት የተጠኚዎች አስተያየቶች ድጋፍን የሚመለከቱ በመሆናቸው (89% - 91.43%) ተጠኚዎቹ ስግ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ የቃላት ችሎታቸውን እንደሚያዳብር እምነት እንዳላቸው ያመለክታል።

ሰንጠረዥ አስራ ሰባት፥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የሰዋሰዋዊ አገባብ ችሎታን ለማዳበር ስላለው ሚና ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘ መረጃ።

| ተ. ቁ. | ሐሳብ | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፈጽሞ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3 | በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ያደረግከ(ሽ)ው ተሳትፎ ቅጥያዎች ሰዋሰዋዊ ሙያ እንዳላቸው እንድትገነዘብ (ቢ) ረድቶሃ(ሻ)ል። | 30 | 42.86 | 31 | 44.29 | 5 | 7.14 | 4 | 5.71 |
| 6 | በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ገደፋ ካልተካሄደበት የስግ ምንባብ ክፍል የቃላት አደረጃጀት ምልከታ እንድትነሳ(ሺ) መደረጉ የሰዋሰው ችሎታህ(ሽ)ን ለማዳበር ረድቶሃ(ሻ)ል። | 24 | 34.29 | 33 | 47.14 | 11 | 15.71 | 2 | 2.86 |
| 9 | ስግ ምንባብን ለማሟላት ባደረግከ(ሽ)ው ተሳትፎ ውስጥ ስለፈጸምካ(ሻ)ቸው ስህተቶች ከመምህርና ከቡድንህ(ሽ) አባላት የተሰጡህ(ሽ) የማስተካከያ ሀሳቦች የሰዋሰዋዊ አገባብ እውቀትህ(ሽ)ን ለማዳበር ረድተዋል። | 44 | 62.86 | 19 | 27.14 | 5 | 7.14 | 2 | 2.86 |
| 13 | ለክፍት ቦታዎች መሟያነት የተሰነዘሩ ቃላት ለምን እንደተመረጡ ከቡድንህ(ሽ) አባላት የሚቀርቡ ምክንያቶች ስለቃላትና ሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ግንዛቤ እንድታገኝ(ኚ) ረድተውሃ(ሻ)ል። | 31 | 44.29 | 32 | 45.71 | 4 | 5.71 | 3 | 4.29 |

በዚህ ሰንጠረዥ ውስጥ በተራ ቁጥር 3 ላይ በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ያደረግከ(ሽ)ው ተሳትፎ ቅጥያዎች ሰዋሰዋዊ ሙያ እንዳላቸው እንድትገነዘብ (ቢ) ረድቶሃ/ሻ/ል። በሚል ለቀረበው ሐሳብ ከተጠኚዎች 30(42.86%)በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 31(44.29%) እስማማለሁ በማለት በድምሩ 61(87.15%) የስምምነት አስተያየት ሲሰጡ 9(12.85%) የተቃውሞ አስተያየት አቅርበዋል።

በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ካልተገደፉት ቃላት አሳካክ በመነሳት ክፍት ቦታዎቹን ለማሟላት እንዲሞክሩ መደረጋቸው የሰዋሰው ችሎታቸውን ለማዳበር ድጋፍ እንዳደረገ ላመለከተው በተራ ቁጥር 6 ላይ የቀረበ ሐሳብ 24(34.29%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 33 (47.14%) እስማማለሁ በማለት፥ በድምሩ 57(81.43%) ተጠኚዎች የስምምነት አስተያየት ያቀረቡ ሲሆን

11(15.71%) አልስማማም፥ 3 ፈጽሞ አልስማማም በማለት በሐሳቡ የማይስማሙ መሆናቸውን ባቀረቡት አስተያየት አመልክተዋል።

በተራ ቁጥር 9 ላይ በትምህርቱ ክንዋኔ ውስጥ ስለፈጸሙት ስህተት ከክፍል ጓደኞቻቸው እና ከመምህር የተሰጣቸው ማረምያ የሰዋሰው እውቀታቸውን ስለማበልጸጉ የቀረበውን ሐሳብ 44(62.86%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ 19(27.14%) እስማማለሁ በማለት በድምሩ 63(90%) የስምምነት አስተያየታቸውን አቅርበዋል። 7(10%) (5 አልስማማም 2 ፈጽሞ አልስማማም በማለት) ሐሳቡን እንደሚቃወሙ አስተያየት ሰጥተዋል።

ለክፍት ቦታ ማሟያነት የሰነዘሩትን ግምት ለምን እንደመረጡ የቡድናቸው አባላት የሚያቀርቡት ሐሳብ ስለ ቃላትና ሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ግንዛቤ እንዳስገኘላቸው በተራ ቁጥር 13 ላይ ለተሰነዘረው ሐሳብ 31 (44.29%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 32 (45.71%) እስማማለሁ በማለት በጥቅሉ 63(90%) ተጠኚዎች የስምምነት አስተያየታቸውን ሲሰጡ፥ 7(10%) ተጠኚዎች ግን ሐሳቡን እንደማይደግፉ አስተያየት ሰጥተዋል።

በዚህ ሰንጠረዥ ውስጥ ለተካተቱት አራት ሐሳቦች ተጠኚዎች የሰጡት አስተተያየት በአመዛኙ ስምምነታቸውን የሚገልጽ በመሆኑ (87.15-90%) ተጠኚዎቹ በስግ ስልት የቀረበላቸው የንባብ ትምህርት የሰዋሰዋዊ አገባብ ችሎታቸውን እንዳሻሻለላቸው እንደሚያምኑ ያመለክታል።

**ሰንጠረዥ አስራ ስምንት፥** በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቋንቋ ክሂሎች በጥምረት ከማዳበር አንፃር ስላለው ሚና ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘ መረጃ።

| ተ. ቁ. | ሐሳብ | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፈጽሞ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 12 | በቡድን ያከናወናችሁት ስግ ምንባብን የማሟላት ክንውን ከአንብቦ መረዳት ጋራ በተቀናጀ ሁኔታ በሌሎች ክሂሎች (መናገር፥መጻፍ፥ ማዳመጥ) ያለህ(ሽ)ን ብቃትም አበልጽጓል። | 28 | 40 | 31 | 44.29 | 7 | 10 | 4 | 5.71 |
| 14 | ስግ የንባብ የማስተማሪያ ስልት በእናንተ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት መዋሉ አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታህ(ሽ)ን አዳብሮልሃ(ሻ)ል። | 33 | 47.14 | 23 | 32.86 | 5 | 7.14 | 9 | 12.86 |

በሰንጠረዥ 17 ላይ በተራ ቁጥር 12 ለቀረበው ሐሳብ 28(40%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 31 (44.29%) እስማማለሁ በማለት በጥቅሉ 59(84.29%) ተጠኚዎች የድጋፍ አስስተያየአታቸውውን በመስጠት በቡድናዊ ውይይት ያከናወኑት ስግ ምንባብን የማሟላት ክንውን ከአንብቦ መረዳት ጋራ ሌሎቹንም የቋንቋ ክሂሎቻቸውን ብቃት እንደበለጸገ ሲስማሙ፥ 11(15.71%) ተጠኚዎች ግን በዚህ ሐሳብ እንደማይስማሙ አመልክተዋል።

በክፍላቸው ተግባራዊ የተደረገው በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታቸውን እንዳበለጸገ የሚያመለክተውን በተራ ቁጥር 14 ላይ የቀረበ ሐሳብ 33(47.14%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 23(32.86%) እስማማለሁ በማለት በድምሩ 56(80%) ተጠኚዎች የስምምነት ሐሳባቸውን ሲገልጹ 5(7.14%) አልስማማም፥ 9(12.86%) ፈጽሞ አልስማማም በማለት 14(20%) ተጠኚዎች አሉታዊ አስተያየታቸውን አቅርበዋል።

ከዚህ በላይ በቀረቡት አራት ሰንጠረዦች ውስጥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳትን፥ የቃላት ችሎታን፥ የሰዋሰዋዊ አገባብ ብቃትንና የቋንቋን የተለያዩ ክሂሎች በቅንጅት ለማዳበር ስለመቻሉ በቀረቡት ሐሳቦች ላይ ተጠኚዎች ያቀረቡት አስተያየት የንባብ ማስተማሪያ ዘዴው እነዚህን የቋንቋ ዘርፎች የማዳበር ችሎታ እንዳለው አመልክቷ። እነዚህን የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች በሚመለከት ለቀረቡት 14 ሐሳቦች ከ59-64 የሚሆኑት ተጠኚዎች (ከ80%-91.45%) የድጋፍ አስተያየታቸውን የሰጡ መሆኑ ደግሞ የንባብ ማስተማሪያ ስልቱ ውጤታማ ስለመሆኑ ብዙዎች ተጠኚዎች ያላቸውን አዎንታዊ አስተያየት ያንጸባርቃል። በመሆኑም ለሙከራ ቡድኑ አባላት ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው መረጃ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳትን ብሎም አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታን ለማዳበር እገዛ እንደሚያደርግ ግንዛቤ ማግኘት ተችሏል።

ለሙከራ ምድቡ ከቀረበው ክፍት ጨራሽ ተጨማሪ አስተያየት መስጫ የመጠይቅ ክፍል የተገኙት የተጠኚዎቹ አስተያየቶችም በዝግ ጨራሽ ክፍሉ ከሰጡት አስተያየት ጋራ የሚደጋገፍ ሲሆን በተደጋጋሚ ከቀረቡት አስተያየቶች ውስጥ የሚከተሉትን እናገኛለን።

- ክፍት ቦታዎቹን ለመሙላት ስመራመር ድሮ ልብ ብዬ የማለያቸውን የቋንቋ አጠቃቀሞች በትኩረት ማየት ችያለሁ፡፡
- በውይይቱ ውስጥ በቡድናችን ውስጥ ስለሚጥምና የማይጥም የቋንቋ አገባብ በተደጋጋሚ ከተነሳው ሃሳብ ስለ ቋንቋ አገባብ ትምህርት አግኝቻለሁ፡፡
- ትምህርቱ በጣም የሚስብና የቋንቋ ችሎታን የሚያፍታታ ነው፡፡ ግን ትምህርቱ የቀረበበት ጊዜ አጠረ፡፡
- ለምን ለሚለው ጥያቄ መልስ እየፈለግሁ እንዳነብ ረደቶኛል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ተደጋጋሚ የድጋፍ አስተያየቶች በተቃራኒ ደግሞ የሚከተሉት የተቃውሞ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

- ትምህርቱ ጥሩ ቢሆንም ከምንማረው ትምህርት ጋራ ስለማይመሳሰል የፈተና ውጤታችንን ያበላሽብናል ብዬ እሰጋለሁ፡፡
- ምንም አይነት ለውጥ አላገኘሁም፡፡ ከመደበኛው የአማርኛ ትምህርት ጊዜ ብዙ ስለባከነብን ፈተና ምን ብዬ እንደምመልስ አሳስቦኛል፡፡
- የሚቀጥለው አመት ማትሪክ ተፈታኞች ስለሆንን እንዲህ ያለ የማይታወቅ ነገር ባታመጡብን ይሻላል፡፡

በነዚህ የተቃውሞ አስተያየቶች ውስጥ በጣም ጎልቶ የተንጸባረቀው በዚህ የሙከራ ትምህርት ላይ ጊዜ ስላባከነ የመደበኛውን አማርኛ ፈተና እንዴት እንሰራለን የሚለው ሐሳብ ነው፡፡

## 4.2.2. ለተጋባዥ መምህራን ከተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የተሰራጩትን መጠይቆች ሞልተው የመለሱ ተጋባዥ መምህራን ቁጥር 8 ሲሆን፥ ከነዚህ ውስጥ 5 ወንዶች 3 ሴቶች ናቸው፡፡ ከትምህርት ደረጃ አንፃርም 4 የዲፕሎማ ምሩቆች ሲሆኑ (12+2) ቀሪዎቹ 4ቱ ቢ.ኤ.(B.A.) ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡ ስምንቱም መምህራን አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ሲሆኑ፥ 5 ከ2-20 ዓመት፥ 3 ከ21-30 ዓመት በመምህርነት ሙያ ያገለገሉ ናቸው፡፡ ቀጥሎ ከነዚህ መምህራን የተገኙት መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡

ሰንጠረዥ አስራ ዘጠኝ÷ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳትን ብቃት ከማበልፀግ አንፃር ስላለው ሚና ከተጋባዥ መምህራን የተገኘ መረጃ::

| ተ.ቁ. | ሐሳብ | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት |
| 2 | አያያዥ ቃላትን በስግ ክፍት ቦታዎች የመሙላት ልምምድ ተማሪዎች የምንባብን የተለያዩ ክፍሎች በማገናዘብ መልእክቱን እንዲረዱ እገዛ ያደርጋል:: | 2 | 6 | - | - |
| 6 | ተማሪዎች ለስግ ክፍት ቦታዎች በሙያነት ስላቀረቧቸው ምላሾች ተገቢነት ወደ ፊትና ወደኋላ እያሰሱ ከስግ ምንባብ ውስጥ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ በደረጉ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ያጠናክራል:: | 2 | 5 | 1 | - |
| 10 | ለክፍት ቦታዎች መሙያነት የሰነዘሯቸውን ግምቶች ለምን እንደመረጡ ሲጠየቁ ብዙዎቹ ምክንያታቸውን ከቀድሞው እውቀታቸው ጋራ ማያያዛቸው÷ የአንብቦ መረዳትን ብቃት ለማጠናከር ዳራዊ እውቀት ያለውን ወሳኝነት ለተማሪዎች ያስገነዝባል:: | 2 | 5 | 1 | - |
| 14 | ለስግ ክፍት ቦታ መሙያነት ከተማሪዎች የሚመነጨ ግምቶች ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶች ድክመታቸውን በመጠቀም እንዲያቃኑ የሚያደርጉ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማበልጸግ ድጋፍ ያደርጋሉ:: | 3 | 5 | - | - |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው በተራ ቁጥር 2 ላይ አያያዥ ቃላትን በስግ ክፍት ቦታዎች የመሙላት ልምምድ ተማሪዎች የምንባብን የተለያዩ ክፍሎች በማገናዘብ መልእክቱን እንዲረዱ ያደርጋል ለሚለው ሐሳብ 2 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ 6 መምህራን እስማማለሁ በማለት ሁሉም መምህራን በሐሳቡ ላይ የስምምነት አስተያየት ሰጥተዋል::

በተራ ቁጥር 6 ላይ ተማሪዎች ለስግ ክፍት ቦታዎች ስላቀረቡት ምላሽ ተገቢነት ማስረጃ እንዲያቀርቡ መደረጉ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ያዳብራል ለሚለው ሐሳብ 2 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ÷ 5 መምህራን

እስማማለሁ በማለት በጥቅሉ 7 መምህራን ስምምነታቸውን ስገልጹ 1 መምህር ግን ተማሪዎች ከምንባብ ውስጥ ማስረጃ እየፈለጉ እንዲያቀርቡ መደረጋቸው የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ያዳብራል በሚለው ሐሳብ የማይስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

አንዳንዶች ለክፍት ቦታዎች መሙያነት የሰነዘሯቸውን ግምቶች ለምን እንደመረጡ ሲጠየቁ ምክንያታቸውን ከቀድሞ እውቀታቸው ጋራ ማያያዛቸው ዳራዊ እውቀት የአንብቦ መረዳት ብቃትን ለማጠናከር እንደሚችል ለተማሪዎች ግንዛቤ ይሰጣል ለሚለው በተራ ቁጥር 10 ላይ የሚገኝ ሐሳብ 2 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 5 መምህራን እስማማለሁ በማለት በድምሩ 7 መምህራን ስምነታቸውን የገለጹ ሲሆን 1 መምህር አልስማማም በማለት ይህንን ሐሳብ ተቃውመዋል፡፡

በተራ ቁጥር 14 ላይ ተማሪዎች በስግ ምንባብ ማሟላት ክንውን ውስጥ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ድክመታቸውን በመግለጽ የእርማት አስተያየት እንዲያገኙ በማድረግ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ያበለጽጋል በሚለው ሐሳብ 3 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 5 መምህራን እስማማለሁ በማለት በድምሩ ሁሉም መምህራን በሐሳቡ ላይ የስምምነት አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳትን ችሎታ ማዳበሩን አስመልክቶ በሰንጠረዥ አስራ ዘጠኝ በተራ ቁጥር 6 ና 10 ላይ የቀረቡትን ሐሳቦች አንድ መምህር ከመቃወማቸው በስተቀር አጠቃላይ መምህራን የድጋፍ አስተያየታቸውን የሰጡ በመሆኑ የንባብ ማስተማሪያ ስልቱ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የሚያበለጽግ መሆኑን ብዙዎች መምህራን እንደሚቀበሉ ከአስተያየታቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ ሃያ፥ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቃላት ችሎታን ከማበልጸግ አንፃር ስላለው ሚና ከተጋባዥ መምህራን የተገኘ መረጃ።

| ተ.ቁ. | ሐሳብ | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት |
| 3 | በስግ ስልት የትምህርት ክንውን ውስጥ ተማሪዎች ለአንድ ክፍት ቦታ የሚሰነዝሯቸው የተለያዩ ምላሾች ስለ ቃላት አፈታት ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳሉ። | 3 | 5 | - | - |
| 7 | የተለያየ መልክ ያላቸው ምንባቦች (ግጥም፥ ታሪክ፥ ሥነ-ጽሑፋዊ ምንባቦች ...ወዘተ) ለማስተማሪያነት መዋላቸው ተማሪዎች ቃላትንና ሐረጋትን ከነዚህ ምንባቦች ልዩ ባህርይ አንፃር መተረጎም እንዲችሉ ይረዳል። | 2 | 5 | 1 | - |
| 11 | ተማሪዎች የተሳተፉበት የስግ ክፍት ቦታዎችን የመሙላት ልምምድ ስለ ቃላት አውደ ንባባዊ አተረጓጎም ግንዛቤ ያስጨብጣል። | 1 | 7 | - | - |

ከዚህ በላይ በሚታየው ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር 3 ላይ በስግ ስልት የትምህርት ክንውን ውስጥ ተማሪዎች ለአንድ ክፍት ቦታ የሚሰነዝሯቸው የተለያዩ ምላሾች ስለ ቃላት አፈታት ግንዛቤ ይሰጣቸዋል በሚል በቀረበው ሐሳብ ላይ 3 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ 5 መምህራን እስማማለሁ በማለት በሙሉ የስምምነት አስተያየታቸውን አቅርበዋል።

በተራ ቁጥር 7 ላይ የተለያየ መልክ ያላቸው ምንባቦች ለትምህርት መቅረባቸው ተማሪዎች ቃላትንና ሐረጋትን ከነዚህ ምንባቦች ልዩ ባህር አንፃር መተረጎም እንዲችሉ ያደርጋል በሚል በቀረበው ሐሳብ ላይ 2 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ 5 መምህራን እስማማለሁ በማለት በድምሩ 7 መምህራን ስምምነታቸውን ሲገልጹ፤ አንድ መምህር ግን አልስማማም በማለት አሉታዊ አስተያየታቸውን አቅርበዋል።

የስግ ክፍት ቦታዎችን የማሟላት ልምምድ ለተማሪዎች ስለ ቃላት አውደ ንባባዊ አተረጓጎም ግንዛቤ ያስጨብጣል ለሚለው በተራ ቁጥር 11 ላይ የቀረበ ሐሳብ 1 መምህር በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ ሲሉ 7 መምህራን እስማማለሁ በማለት

ሁሉም መምህራን በሐሳቡ የሚስማሙ መሆናቸውን በሰጡት አስተያየት አረጋግጠዋል፡፡ በአጠቃላይ አንድ መምህር በተራ ቁጥር 7 ላይ በቀረበው ሐሳብ ላይ የተቃውሞ አስተያየት ከማቅረባቸው በስተቀር ሁሉም መምህራን በዚህ ሰንጠረዥ ውስጥ ለቀረቡት ሐሳቦች የድጋፍ አስተያየት በመስጠታቸው በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቃላት ችሎታን እንደሚያጎለብት አብዛኞቹ መምህራን እንደሚገነዘቡ ከአስተያየታቸው መረዳት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ ሃያ አንድ፥** በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የሰዋሰዋዊ አገባብ ችሎታን ለማዳበር ስላለው ሚና ከተጋባዥ መምህራን የተገኘ መረጃ፡፡

| ተ. ቁ. | ሐሳብ | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት |
| 4 | በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ተማሪዎች የተገደፉትን ቃላት ከመገመታቸው በፊት ባልተገደፈው የስግ ምንባብ የቋንቋ አወቃቀር ላይ እንዲያተኩሩ መደረጉ ስለ ቅጥያዎች፥ ስለ ቃላትና ስለ ሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳል፡፡ | 5 | 3 | - | - |
| 8 | ለስግ ምንባብ ክፍት ቦታዎች መሚያነት ሚሰነዘሩት ግምቶች ውስጥ ስለሚፈጸሙ ስህተቶች መምህርና የላቀ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው የማረሚያ አስተያየቶች ለተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ መጎልበት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ | 2 | 5 | 1 | - |
| 12 | ተማሪዎች ለስግ ክፍት ቦታዎች ማሟላት ያመነጬዋቸውን ግምቶች ስለመረጡበት ምክንያት የሚያቀርቧቸው ሐሳቦች ስለ ቅጥያዎች፥ ስለቃላትና ስለሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ያላቸውን ነባር ውስጣዊ እውቀት ፊት ለፊት አውጥተው በመማማር ወደ ላቀ የሰዋሰው ግንዛቤ ለመምራት ያስችላቸዋል፡፡ | 1 | 7 | - | - |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ በተራ ቁጥር 4 ላይ በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ተማሪዎች የተገደፉትን ቃላት ከመገመታቸው በፊት ባልተገደፈው የስግ ምንባብ የቋንቋ አወቃቀር ላይ እንዲያተኩሩ መደረጉ ስለ ቅጥያዎች፥ ስለቃላትና ስለ ሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳል

በሚል ለቀረበው ሐሳብ 5 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፥ 3 መምህራን እስማማለሁ በማለት በድምሩ በታዛቢነት የትምህርቱን ሂደት የተከታተሉት መምህራን በሙሉ የድጋፍ አስተያየት ሰጥተዋል።

በተራ ቁጥር 8 ላይ ለስግ ምንባብ ክፍት ቦታዎች መሙያነት በሚሰነዝሩት ግምቶች ውስጥ ስለሚፈጸሙ ስህተቶች መምህርና የላቀ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው የማረሚያ አስተያየቶች ለተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ መጎልበት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፤ በሚል ለቀረበው ሐሳብ 2 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ 5 መምህራ እስማማለሁ በማለት በሐሳቡ ላይ ያላቸውን የድጋፍ አስተያየት ሲያቀርቡ፥ አንድ መምህር አልስማማም በማለት የተቃውሞ አስተያየት ሰንዝረዋል።

በተራ ቁጥር 12 ላይ፥ ተማሪዎች የስግ ምንባብ ክፍት ቦታዎችን ለማሟላት የሰነዘሯቸውን ግምቶች ስለመረጡበት ምክንያት የሚያቀርቡት አስተያየት፥ ውስጣዊ የሰዋሰው እውቀታቸውን ፊት ለፊት በማውጣት እንዲማማሩና ወደ ላቀ የሰዋሰዋዊ አገባብ ግንዛቤ ለማምራት ያስችላቸዋል በሚል ለቀረበው ሐሳብ 1 መምህር በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ 7 መምህራን እስማማለሁ በማለት በጥቅሉ ሁሉም መምህራን በሐሳቡ እንደሚስማሙ አስተያየት አቅርበዋል።

በዚህ ክፍል በተራ ቁጥር 4 ላይ ለቀረበው ሐሳብ 5 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ የሚለውን ጫን ያለ የስምምነት ደረጃ አመልካች ምርጫ መምረጣቸውና ቀሪዎቹ 3ቱም ስምምነታቸውን መግለጻቸው ታዛቢ መምህራኑ በትምህርት ሂደቱ ውስጥ ተማሪዎች ለክፍት ቦታዎች ግምቶችን ከመሰንዘራቸው በፊት ባልተገደፈው የስግ ምንባብ የቋንቋ አወቃቀር ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ መደረጉ ስለ ቅጥያዎች፥ ቃላትና ሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል የሚል ከፍተኛ እምነት እንዳላቸው ያመለክታል፤ በቁጥር 8 እና 12 ላይ ለቀረቡት ለሌሎቹም ሐሳቦች 1፥1 የተቃውሞ አስተያየት ከመኖሩ በስተቀር ብዙዎቹ መምህራን አዎንታዊ አስተያየት መሰንዘራቸው መምህራኑ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የተማሪዎችን የሰዋሰዋዊ አገባብ እውቀት ያበለጽጋል ብለው እንደሚያምኑ ያመለክታል።

## ሰንጠረዥ ሃያ ሁለት፦በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ለመምህራን የሚሰጠውን ሙያዊ እገዛ በሚመለከት ከተጋባዥ መምህራን የተገኘ መረጃ::

| ተ. ቁ. | ሐሳብ | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስ ማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት |
| 5 | የስግ ሥልት የንባብ ትምህርት ክንውን በአመዛኙ በተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የሚሸፈን መሆኑ የመምህርን የሥራ ጫና ያቃልላል:: | 1 | 6 | 1 | - |
| 9 | ለስግ ክፍት ቦታ ማሟያነት የሚሰነዘሩ የተለያዩ ግምቶች ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች መምህራን የተማሪዎችን ድክመቶች ለይተው እንዲያውቁ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራሉ:: | 2 | 5 | 1 | - |
| 13 | የማስተማሪያ ስልቱ ተማሪዎችን በሂደታዊ ክንዋኔ ውስጥ በማስገባት በክፍል ውስጥ ጸጥታን የሚያሰፍን በመሆኑ የመምህራንን የሥራ አካባቢ ከረብሻ ነፃ ያደርጋል:: | 1 | 6 | 1 | - |

በስግ ሥርዓት የሚመራ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ለመምህራን ስለሚሰጠው ሙያዊ ድጋፍ ከላይ ከቀረቡት ሐሳቦች በተራ ቁጥር 5 ላይ ለቀረበው 1 መምህር በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፦ 6 መምህራን እስማማለሁ በማለት የድጋፍ አስተያየት ሲሰጡ 1 መምህር ግን የትምህርት ክንውኑ በአማዛኙ በተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የሚሸፈን መሆኑ የመምህራንን የሥራ ጫና ያቃልላል በሚለው ሐሳብ እንደማይስማሙ አመልክተዋል::

ክፍት ቦታዎችን ለማሟላት በሚሰነዘሩት ግምቶች ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች የተማሪዎችን ድክመቶች ለይተው ማየት እንዲችሉ ለመምህራን እገዛ ያደርጋል ለሚለው በተራ ቁጥር 9 ላይ በቀረበው ሐሳብ ላይ 2 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ 5 መምህራን እስማማለሁ በማለት አስተያየት ሲያቀርቡ 1 መምህር አልስማማም በማለት አሉታዊ አስተያየት ሰጥተዋል::

ስግ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎችን በሂደታዊ ክንዋኔ ውስጥ በማስገባት ጸጥታን የሚያሰፍን በመሆኑ የመምህራንን የሥራ አካባቢ ከረብሻ ነጻ ያደርጋል ለሚለው በተራ ቁጥር 13 ላይ የሚገኝ ሐሳብ 1 መምህር በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ፦ 6 መምህራን እስማማለሁ በማለት የድጋፍ አስተያየታቸውን ሲሰነዝሩ፦ አንድ መምህር አልስማማም በማለት ሐሳቡን የሚቃወም አስተያየት ሰጥተዋል::

በዚህ ክፍል ውስጥ ለቀረቡት ሶስት ሀሳቦች በየሐሳቦቹ ውስጥ 1÷1 መምህራን አልስማማም የሚል የቅዋሚ አስተያየት ከማቅረባቸው በስተቀር የተቀሩት መምህራን የስምምነት አስተያየታቸውን የገለጹ በመሆኑ÷ የብዙዎቹ ታዛቢ መምህራን አስተያየት ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ለመምህራን ሙያዊ ድጋፍ እንደሚሰጥ አመልክቷል።

**ሰንጠረዥ ሃያ ሶስት÷** በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የቋንቋ ክሂሎችን በጥምረት ከማዳበር አንፃር ያለውን ሚና በሚመለከት ከተጋባዥ መምህራን የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ. | ሐሳብ | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት |
| 1 | የማስተማሪያ ስልቱ ስግ ምንባብን በማሟላት ሂደታዊ ክንውን ውስጥ የተማሪዎችን የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች በጥምረት ያዳብራል። | - | 7 | 1 | - |
| 15 | ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ እየቀሰሙ በአእምሯቸው ውስጥ ያከማቹትን የቋንቋ ብቃት በማንቃት ለእርስ በርስ መማማሪያነት እንዲያውሉት የማድረግ ችሎታ አለው። | 2 | 6 | - | - |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት የቋንቋ ክሂሎችን አጣምሮ ለትምህርት በማቅረብ የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ያዳብራል ለሚለው በተራ ቁጥር 1 ላይ የቀረበ ሐሳብ 7 መምህራን እስማማለሁ÷ በማለት የድጋፍ አስተያየት ሲያቀርቡ 1 መምህር አልስማማም በማለት ሐሳቡን ተቃውመዋል።

በተራ ቁጥር 15 ላይ ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ ሂደት ያከማቹትን የቋንቋ ብቃት በማንቃት ለእርስ በርስ መማማሪያነት እንዲያውሉት የማድረግ ችሎታ አለው በሚል ለቀረበው ሐሳብ 2 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ÷ 6 መምህራን እስማማለሁ በማለት በንባብ ማስተማሪያ ስልቱ የቀረበውን ትምህርት በታዛቢነት የተከታተሉ መምህራን በሙሉ የድጋፍ አስተያየታቸውን አቅርበዋል።

አንድ መምህር በተራ ቁጥር 1 ላይ በቀረበው ሐሳብ ላይ ከሰነዘሩት የተቃውሞ ሐሳብ በስተቀር በዚህም ክፍል የቀረቡት ሁለት ሐሳቦችበአመዛኙ የታዛቢ መምህራኑን ድጋፍ ያገኙ በመሆኑ÷ አስተያየት ሰጪ መምህራኑ የንባብ ማስተማሪያ ስልቱ የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን በጥምረት ለትምህረት በማቅረብ የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር ያስችላል የሚል አመለካከት እንደላቸው ያሳያል::

ለታዛቢ መምህራኑ በቀረበው መጠይቅ መጨረሻ ክፍል ላይ÷ በታዛቢነት ተገኝተው ስለተከታተሉት ስለ ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ካዩት በመነሳት ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት ባጭሩ ይግለጹ በሚል ለቀረበላቸው ክፍት ጨራሽ (open ended) የመጠይቁ ክፍል ታዛቢ መምህራኑ

- የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚያበረታታ የማስተማሪያ ስልት ነው::
- በመጠይቁ ውስጥ የተጠየቁትን ጉዳዮች ከሞላ ጎደል ሊያሟላ ይችላል::

የሚሉት÷ (በተለይ የተማሪዎችን ተሳተፎ ያበረታታል የሚለው) በተደጋጋሚ የቀረቡ የድጋፍ አስተያየቶች ሲሆኑ

- በጊዜው ከሚታየው የተማሪዎች የዲሲፕሊን ጉድለት ጋራ ይጣጣማል ብዬ አላምንም::
- የማስተማሪያ ስልቱ የንባብንና የሌሎቹንም የቋንቋ ችሎታዎች ለማዳበር የሚረዳ ቢሆንም ከአገራችን ኢኮኖሚ ጋራ አይጣጣምም::

የሚሉ የተቃውሞ አስተያዮች ቀርበዋል:: ከተቃውሞ አስተያየቶቹ የማስተማሪያ ስልቱ ከአገራችን የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋራ አይጣጣምም የሚለው በተደጋጋሚ የቀረበ ሲሆን፤ ይህም በሙከራ ትምህርቱ ለቡድን ሥራ ክንውን እንዲያመች በመጠኑ ጎላ ጎላ ባለ የኮምፒውተር ጽሑፍ የቀረበውን ዓይነት ስግ ምንባብ በመደበኛው ትምህርት ውስጥ መጠቀም ከኢኮኖሚ አንፃር የማይደፈር እንደሆነ ለመጠቆም የቀረበ ይመስለናል:: ይህ ደግሞ የማስተማሪያ ስልቱ ተቀባይነት አግኝቶ ስራ ላይ የሚውል ከሆነ መፍትሄ የሚያገኝና ብዙ አማራጭ አቀራረብ ያለው በመሆኑ አሳሳቢነት አይኖረውም::

በጥቅሉ በስግ ሥርዓት የቀረበውን የንባብ ትምህርት በታዛቢነት የተከታተሉ ብዙዎች መምህራን የማስተማሪያ ስልቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት እንደሚያግዝ÷ የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር እንደሚረዳ የሰዋሰዋዊ አገባብ ችሎታቸውን ለማሻሻል እንደሚያስችል÷ በአጠቃላይም የቋንቋ ክሂሎችን በጥምረት ለትምህርት ለማቅረብ እገዛ እንደሚያደርግና ለመምህራንም ሙያዊ እገዛ

እንደሚያደርግ ከዚህ በላይ በሰጡት አስተያየት አመልክተዋል። ይህም ቀደም ሲል ከተገለጸው የሙከራ ምርምር ውጤትና፥ ተጠኚ ተማሪዎች በቀረበላቸው መጠይቅ ላይ በተነሱት ሐሳቦች ላይ በመመርኮዝ ካቀረቡት አስተያየት ጋራ የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት እንደ የትኛውም የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ሁሉ ተማሪዎች ምንባቦችን አንብበው ከምንባቦቹ ቀጥለው ለሚቀርቡ የግንዛቤ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን እንዲያቀርቡ በማድረግ የሚከናወን ነው:: በዚህ መልክ የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ሊያጎለብት እንደማይችል የንባብ ትምህርት መስክ ባለሙያዎች አበክረው ያስገነዝባሉ:: /ሲልበርስይን. 1987:30/ እንደ ንባብ መስክ ባለሙያዎች አስተያየት የአንብቦ መረዳትን ችሎታ ሊያበለጽግ የሚችለው ተማሪዎች ከምንባብ ለሚወጡ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ እንዲሰጡ መደረጋቸው ሳይሆን÷ የሰጡትን ማንኛውም ዓይነት መልስ ለምን እንደመረጡ ምክንያት እንዲያቀርቡ መጠየቃቸው ነው:: ተማሪዎች ምላሻቸውን ለምን እንደሰጡ በመጠየቅ÷ ምክንያታቸውን ለማቅረብ ሲሉ ምንባብን ከተለያየ አንጻር እንዲመረምሩ ከሚጋብዙ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ በስግ ሥርዓት በመታገዝ የሚቀርብ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ነው:: /ናታል. 1996:181/

በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ በስግ ምንባብ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች እየገመቱ መሙላትን የሚያለማምድ መሆኑ÷ በ1970ዎቹ ብቅ ያለውንና የንባብን ሂደት በተሻለ ሁኔታ መግለጽ የቻለውን የስነልቦናዊ ስነልሣንን የንባብ መርህ (Psycholinguistic Principles of reading) በንባብ ትምህርት ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ካስቻሉ የንባብ ማስተማሪያ ስልቶች አንዱ እንዲሆን አድርጎታል:: በስነልቦናዊ ስነልሣን የንባብ መርህ አፍላቂዎች አስተያየት ንባብ በአንባቢ ነባር እውቀትና በምንባብ ውስጥ በሚገኙ መረጃዎች ሂደታዊ መስተጋብር የሚከናወን ነው:: /ስሚዝ. 1985:12/

ከላይ እንደተገለጸው የአንባቢ ነባር እውቀት በገጸ ንባብ ውስጥ ከሚገኙ መረጃዎች ይልቅ ለተሻለ አንብቦ የመረዳት ደረጃ እንደሚያበቃ የስነልቦናዊ ስነ-ልሣን የንባብ መርህ ቢያመለክትም በተለምዷዊው የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ውስጥ ግን ይህ አመላካከት ቦታ ያገኘ አይመስልም:: በዚህ ጥናት ተግባራዊ ተደርጎ የተሞከረው በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ያስገኘው አመርቂ

ውጤት የስነልቦናዊ ስነ-ልሳን የንባብ መርህ ለአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት የሚሰጠውን ድጋፍ ለማወቅ አስችሏል።

ምሁራን የአንብቦ መረዳት ችሎታ አንኳር የቋንቋ ክሂል (core language proficiency) እንደሆነና ይህንን የቋንቋ ክሂል በስግ ሥርዓት በመጠቀም ለትምህርት ማቅረብ የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን በጥምረት ለትምህርት ለማቅረብ እንደሚያስችል አመልክተዋል። /አትኬን. 1977:52/ ይህ ሁኔታ ባሁኑ ጥናት በስግ ሥርዓት ታግዞ የቀረበው የንባብ ትምህርት ለአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ መዳበር የሰጠውን ተጨባጭ ድጋፍ ያመለክታል።

ከዚህ በላይ የተነሱት ነጥቦች በዚህ ጥናት ለአማርኛ ቋንቋ የንባብ ማስተማሪያነት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ ተደርጎ የተሞከረው በስግ ሥርዓት አማካይነት የቀረበ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ የአንብቦ መረዳትንና አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ከማበልጸግ አንፃር ያለውን ብቃት የሚያመለክቱ ንደፈ ሐሳባዊ እውነታዎች ሲሆኑ፥ በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ትምህርት ለአማርኛ ማስተማሪያነት ተግባራዊ ቢደረግ በአንብቦ መረዳትና በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ላይ ምን ያህል ለውጥ ያመጣል? የሚለውን ያሁንን ጥናት አብይ ጥያቄና ሌሎቹንም ንኡሳን ጥያቄዎች ለመመለስ የተደረገው ጥናት ውጤትም ይህንኑ አረጋግጧል። ውጤቱን ቀጥሎ እንመለከታለን።

### ሀ. የሙከራ ምርምር

በስግ ሥርዓት የሚታገዝ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ለአማርኛ ቋንቋ የንባብ ማስተማሪያነት ቢውል በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ብሎም በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ መዳበር ላይ የሚኖረውን ሚና ለመፈተሽ የተደረገው ጥናት የተከተለው ዋና የአጠናን ስልት የሙከራ ምርምር (experimental research) ነው። እንዲህም በመሆኑ የጥናቱ አካሄድ በሚፈቅደው መሠረት በመጀመሪያ በአቦሰጣዊ ንሞና (random sampling) ሁለት የ11ኛ ክፍል ምድቦችን በእጣ በመምረጥ በዚሁ ዘዴ አንደኛው የቁጥጥር ሌላው የሙከራ ምድብ እንዲሆኑ ተደረገ። ከዚህ በኋላ ለሙከራ ምደቡ በተለየ መንገድ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት በሁለቱ ምድቦች መካከል የችሎታ መበላለጥ አለመኖሩን ለማረጋገጥ በአንበቦ መረዳት፥ በቃላት፥ በሰዋሰዋዊ አገባብና በሌሎችም የቋንቋ ክሂሎች ላይ ያተኮረ ቅደመ ፈተና (pre-test) ተሰጠ። ፈተናው ከታረመ በኋላ የሁለቱ ምድቦች መካከል በአንብቦ መረዳትም ሆነ በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ (ስታቲስቲካዊ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል) ጉልህ የሆነ ልዩነት እንደሌለ ተረጋግጧል።

በመቀጠልም የክፍሉን ደረጃ የትምህርት ይዘት በመመርኮዝ፥ የቁጥጥር ምድብ በመደበኛው መምህር አማካይነት በተለመደው የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ መንገድ፥ የሙከራ ምድብ በሳምንት ውስጥ ካሉት ሶስት ክፍለ ጊዜያት በመጀመሪያውና በመጨረሻው በአጥኚው አማካይነት በስገ ሥርዓት የታገዘ የንባብ ትምህርት፥ በመሀል ላይ ባለው ክፍለ ጊዜ በስገ ሥርዓት በሚታገዘው የንባብ ማስተማሪያ መሸፈን የማይችለውን የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ በተለመደው መንገድ በመደበኛው መምህር እንዲሸፈን በማድረግ ለስድስት ሳምንታት እንዲማሩ ተደረገ።

የሙከራው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ከቅድመ ፈተናው ጋራ ተመጣጣኝ የሆነ ድህረ ፈተና (post-test) ተዘጋጅቶ ለሁለቱ ምድቦች ተሰጥቶ ያገኙት ውጤት በ"t"-ሙከራ (t-test) ሲሰላ የሙከራ ምድቡ በአንብቦ መረዳትም ሆነ በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ከቁጥጥር ምደቡ የላቀ ሆኖ ተገኝቷል። የሙከራ ምርምሩ ውጤት ተጠኚው ምድብ ከቁጥጥር ምደቡ የጎላ የችሎታ ብልጫ እንዳለው በማሳየቱም አጥኚው ይዞት የተነሳውን ባዶ መላ ምት ($H_0$) ማስወገድ ችሏል።

## ለ. የድህረ ሙከራ ጥናት

የድህረ ሙከራ ጥናት የተደረገው በሙከራ ምርምሩ ከተገኘው ውጤት ጋራ ሊደጋገፉ የሚችሉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሲሆን እነዚህን መረጃዎች ለማግኘት 70 የሙከራ ምድብ አባላትና ተግባራዊ የተደረገውን የንባብ ትምህርት በተጋባዥነት የተከታተሉ 8 የት/ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሑፍ መጠይቆች እንዲሞሉ ተደርጓል።

የሙከራ ምድብ አባላትና ተጋባዥ መምህራኑ በቀረቡላቸው መጠይቆች ላይ በስገ ሥርዓት አማካይነት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳት፥ የቃላትና የሰዋሰዋዊ አገባብ ችሎታን እንዲሁም የቋንቋ ክሂሎችን አጣምሮ ለትምህርት በማቅረብ ከማዳበር አንፃር ያለውን ሚና በሚመለከት የቀረቡላቸውን ሐሳቦች መነሻ በማድረግ በሰጡት ምላሽ የንባብ ማስተማሪያ ስልቱ የተጠቀሱትን የቋንቋ ክሂሎች ከማበልጸግ አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የሚያመለክቱ አስተያየቶች አቅርበዋል። (ያቀረቧቸውን ዝርዝር አስተያየቶች በ4.2 ላይ ማየት ይቻላል) ይህም ከተገለጸው የሙከራ ምርምር ውጤት ጋራ የሚጣጣም በመሆኑ ከዚህ ጥናት የተገኘው ጥቅል ውጤት በስገ ሥርዓት አማካይነት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት በአማርኛ ትምህርት አሰጣጥ ውስጥ ተግባራዊ ቢደረግ የተማሪዎችን የአንብቦ

መረዳትና ብሎም አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ሊያበለጽግ ከመቻሉም በላይ ለመምህራንም ሙያዊ ድጋፍ እንደሚሰጥ አመልክቷል፡፡

## 5.2. አስተያየት

በዚህ ጥናት ውስጥ በሙከራ ምርምሩ ክንውን ውስጥ ከተስተዋሉት ሁኔታዎችና የጥናቱን ውጤት ፈለግ በመከተል የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

5.2.1. የአንብቦ መረዳትን ብሎም አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ለማዳበር ተማሪዎችን በንባብ ሂደታዊ ክንዋኔ ውስጥ በማስገባት መልእክትን በስልት ፈልፍሎ ማውጣትን የሚያለማምድ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ አስፈላጊ ነው፡፡ በስግ ሥርዓት በመታገዝ የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የዚህ ዓይነቱን ተግባር የመፈጸም ብቃት ያለው ያማስተማሪያ ዘዴ በመሆኑ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት ቢውል የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ሊያደብር ይችላል፡፡

5.2.2. በስግ ሥርዓት ተግዞ በሚቀርብ የንባብ ትምህርት ውስጥ የሚታየው ማራኪ ይዘት ባላቸውና ከቀላል ወደ ከባድ በደረጃ በተሰደሩ ስግ ምንባቦች የመጠቀም ሁኔታ በአማርኛ ትምህርት ውስጥ እንደተከሰተ በየጥናቶቹ የተጠቆመውን የተማሪዎች ተሳትፎ መቀዝቀዝ በማንቃት ተማሪዎች ከፍዝ ተቀባይነት ወደ ንቁ ተሳታፊነት እንዲሸጋገሩ ከማድረጉም በላይ፥ የትምህርት ጊዜ በአመዛኙ በተማሪዎች ተሳትፎ የመሸፈኑ ሁኔታ የመምህራንን የሥራ ጫና ሊቀንስ እንደሚችል ማወቅ ተችሏል፡፡

5.2.3. ተማሪዎች ለስግ ምንባቦች ማሚያነት በሚሰነዝሯቸው ግምቶች ውስጥ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ድክመቶቻቸውን በሚመለከት ለመምህራን ግልጽ ጥቆማዎች በማድረግ መምህራን በነዚህ ተጨባጭ ችግሮች ላይ ያተኮረ ምጋቤ ምላሽ (feedback) መስጠት እንዲችሉ ስለሚረዳ ይህ የማስተማሪያ ስልት ለአማርኛ ማስተማሪያነት ተግባራዊ ቢደረግ የአማርኛ መምህራን በዚህ ነጥብ ውስጥ የተጠቀሰውን ሙያዊ ድጋፍ ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል፡፡

5.2.4. በስግ ሥርዓት አማካይነት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ተማሪዎች ለምላሻቸው ምክንያት እንዲያቀርቡ በማድረግ ለውይይት ስለሚጋብዝ የተማሪዎችን የቋንቋ ብቃት (linguistic competence) ብቻ ሳይሆን ተግባቦታዊ ብቃታቸውንም (communicative competence) ሊያዳብር ይችላል፥ እንዲህም በመሆኑ ይህ የማስተማሪያ ስልት ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት ቢውል ባሁኑ ጊዜ የተዳከመውን በተግባቦታዊ ሁኔታ ላይ ያተኮረ የትምህርት አቀራረብ ሊያነቃና ሊያሻሽል ይችላል።

5.2.5. በተለይ በዚህ ጥናት ውስጥ በቁጥጥርና በሙከራ ምድብ አባልነት እንደታቀፉት ላሉ አፍ ፈት ተናጋሪዎች ለሚበዙበት ስብስብ በስግ ሥርዓት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት መስጠት፥ አፍ ፈት ተማሪዎቹ በቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ የቀሰሙትን የዳበረ የቋንቋ ብቃት በትምህርቱ ውስጥ በሚያካሄዱት ውይይት በግልጽ በማውጣት እንዲሚማማሩበት ስለሚያደርግ ከዚህ አንፃር ይህ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ለአፍ ፈት የአማርኛ ተናጋሪዎች ቢውል ጠቀሜታው የጎላ ሊሆን ይችላል።

5.2.6. በስግ ሥርዓት አማካይነት የሚቀርብ የንባብ ትምህርት የተጓደሉ የምንባብ ክፍሎችን ማሟላትን የሚያለማምድ በመሆኑ ችግርን መፍታትን የሚያለማምዱ መልመጃዎች (problem solving exercises) አካል ነው። እንዲህ በመሆኑ በስግ ሥርዓት በመታገዝ የሚቀርብን የንባብ ትምህርት ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት ተግባራዊ በማደረግ የተጠቀሰውን የመልመጃ አቀራረብ ወደ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ማስገባት በአማርኛ ቋንቋ የመልመጃ አቀራረብ ውስጥ የሚታየውን ተደጋጋሚና አሰልቺ የመልመጃ አቀራረብ ሊያሻሽል ይችላል።

5.2.7. በዚህ ጥናት በስግ ሥርዓት አማካይነት የቀረበው የንባብ ትምህርት በአንብቦ መረዳትና በአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ላይ ከፍተኛ ልዩነት ማስከተል መቻሉ ለአማርኛ

መርሃ ትምህርት ነዳፊዎች፥ ለአማርኛ የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆችና ለመምህራን ለንባብ ትምህርት ሊሰጠው ስለሚገባ ትኩረት ግንዛቤ ይሰጣል።

5.2.8. በዚህ ጥናት ውስጥ በስግ ሥርዓት በመታገዝ በቀረበው የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ስግ ምንባቦች ለማሟላት የሚያካሂዱት የቡድን ውይይት ስለያንዳንዱ ተማሪ ድክመት፥ ጥንካሬና የንባብ እስትራተጂ ጠቃሚ መረጃዎችን ማስገኘት እንደሚችል ግንዛቤ ተገኝቷል፥ ይህም በዚህ ርእስ፥ በተለይም ተማሪዎች በሚፈጽሟቸው የስህተት ዓይነቶች ትንተና ወይም በንባብ እስትራተጂያቸው ላይ ቀጣይ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ ፍንጭ ሊሆን ይችላል።

# ዋቢዎች (Bibliography)


ማስተዋል ውበቱ፥ 1989 ዓ.ም.፥ "የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት" አ.አ.ዩ. በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ መሟያ የቀረበ።

ሰለሞን ሐለፎም፥ 1989 ዓ.ም.፥ "አማርኛን በማስተማር ዘዴነት ያቃል ጽሕፈት (Dictation) ሚና፥" ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት፥ ለአማርኛ ማስተማር (TEAM) ኤም.ኤ. ዲግሪ መሟያ የተዘጋጀ።

በየነ ማሞ፥ 1985 ዓ.ም.፥ "ዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው?" ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ የኤም ኤ. ቴሲስ።

አስፋው አመና፥ 1975 ዓ.ም.፥ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ በሁለት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች"፥ አ.አ.ዩ. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለቤ. ኤ ዲግሪ መመሟያ የቀረበ።

የኔሰው ደሴ፥ 1990 ዓ.ም.፥ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ"፥ አ.አ.ዩ. በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ መሟያ የቀረበ።

ጌታቸው አዱኛ፥ 1986 ዓ.ም. " ለ10ኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ" አ.አ.ዩ. በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

Alderson, J.C. 1979. “The Cloze Procedure and Proficiency in English as Foreign Language.” TESOL Quarterly. 13/2: 219-227.

_________________ 1980. “Native and Non-native Speakers Performance on Cloze Tests” Language Learning. 30/1: 59-76.

_________________. 1996. “The Testing of Reading” in C. Nuttall. Teaching Reading Skills in a Foreign Language. Oxford: Heinemann.

Applebee, A.N. and Judith A. Langer. 1984. “Instructional Scaffolding: Reading and Writing as Natural Language Activities” in: Composing and Comprehension. Julie J. (ed.) . Illinois: Clearinghouse of Reading and Communication Skills.

Aitken, K.G. 1977. “Using Cloze Procedure as an Overall Language Proficiency.” TESOL Quarterly. 11/1:50-67.

Bachman, L. F. 1985. “Performance on Coze Tests with Fixed-Ratio and Rational Deletions.” TESOL Quarterly 19/3:535-554.

Bastidas A, J.A. 1984. ‘The Cloze Procedure as a Teaching Technique to Improve Reading Comprehension’. English Teaching Forum. 22/2: 20-24.

Bortnick, R. and G.S. Lopardo. 1973. "An Instructional Application of the Cloze Procedure". Journal of Reading. 16: 296-300.

Brown, J.D. 1980. "Relative Merits of Four Methods for scoring Cloze Tests". Modern Language Journal. 64/3: 311-317.

Celce- Murcia, Mariane. 1988. Techniques and Resources in Teaching Grammar. Oxford: Oxford University Press.

Chapman, L. J. 1983. Reading Development and Cohesion. London: Heinemann Educational Books.

Chaves-oller, Mary Anne, T. Chihara, K.A. Weaver and J.W. Oller., Jr. 1985. "When Are Cloze Items Sensitive to Constraints Across Sentences?" Language Learning. 35/2: 181-206.

Chihara, T. , J.W. Oller, Jr. , K. Weaver, and Mary Anne Chavez. 1977. "Are Cloze Items Sensitive to Constraints Across Sentences?" Language Learning. 27/1: 63-69.

Clarke, M.A., and S. Silberstein. 1977. "Towards a Realization of Psycholinguistic Principles in the ESL Reading Classroom." Language Learning. 27/1: 135-154.

Davies, A. 1984. "Simple, Simplified and Simplification: What Is Authentic?" In: Reading in a Foreign Language. J.C. Alderson and A. H. Urquhart(eds.) London: Longman.

Elley, W.B. 1984. "Exploring the Reading Difficulties of Second Language Learners in Fiji." In: Reading in Foreign Language. J.C. Alderson and A.H. Urquhart (eds.) London: Longman.

Fisher, R.A. 1981. "Measuring Linguistic Competence in Foreign Language" IRAL. 29/3: 207-216.

Gebremedhin Simon. 1993. "Individualized Reading for E.A.P. for Social Science First Year Students in Addis Ababa University: A Study of a Possible Approach for Teaching" A Theses submitted to School of Graduate Studies A.A.U. For the degree of Ph.D. In TEFL.

Gefen, P. 1979. "An Experiment with Cloze Testing." English Language Teaching Journal. 32/2: 122-126.

Goodman, K.S. 1967. 'Reading: A psycholinguistic guessing game' Journal of the Reading Specialist. 6:126-135.

_______________ 1986. What is Whole in Whole Language. Portsmouth: Heinman Educational Books.

_______________ 1988. "The Reading Process." In: Interactive Approaches to Second Language Reading. P.L. Carrell, J. Devine, D.E. Eskey (eds.) Cambridge: Cambridge University Press.

Grabe, W. 1991. "Current Development in Second Language Reading Research". TESOL Quarterly. 25/3: 375-397.

Haile Michael Aberra. 1984. "The Communicative V. The Traditional Approach to the Teaching of English Reading Comprehension at Addis Ababa University Freshman Level: A comparative study." A thesis submitted to the School of Graduate Studies, A.A.U. for the degree of M.A. in TEFL.

Halliday, M.A.K. and R. Hassan. 1976. Cohesion in English. London: Longman.

Heaton, J. B. 1988. Writing English Language Test. London: Longman.

Hubbard, P., H. Jones, B. Thornton, and R. Wheeler. 1983. A Training Course for TEFL. Oxford. Oxford University Press.

Harrison, A. 1983. A Language Testing Handbook. London: Macmillan.

Harrison, C. 1980. Readability in the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Jongsna, E. 1971. The Coze Procedure as a Teaching Techniques. Newark, Delaware: International Reading Association.

_____________ 1980. Cloze Instruction Research: a Second Look. Newark. Delaware: International Reading Association.

Jonz, J. 1976. "Improving on the Basic Egg : The M-C Cloze". Language Learning: 10/2: 255-265.

Lunzer, E and K. Gardner. 1979. The Effective Use of Reading. London Heinemann Educational Books.

Nuttall, C. 1996. Teaching Reading Skills in a Foreign Language. Oxford: Heinmann.

Oller, J.W. Jr. 1972. "Scoring Methods and Difficulty Levels for Cloze testes of Proficiency in English as a second Language." Modern Language Journal. 56:151-158.

____________ 1973. 'Cloze Tests of second Language Proficiency and What They Measure.' Language Learning. 23/1: 105-118.

____________ 1975. "Cloze, discourse, and Approximations to English." In Marina K. Burt and Heidi C. Dulay (eds.) New Directions in Second Language

Teaching and Bilingual Education. On TESOL' 75. Washington, D.C.: TESOL, 345-355

______________ 1979. Language Testing at School. London: Longman.

Porter, D. 1978. "Cloze Procedure and Equivalence." Language Learning. 28/2: 333-340.

Rye, J. 1982. Cloze Procedure and the Teaching of Reading. London: Longman Educational Books.

Schulz, R. 1983. "From Word to Meaning: Foreign Language Reading Instruction after the Elementary Course." Modern Language Journal. 67/2: 127-134

Seliger, H.W. and E. Shohamy. 1989. Second Language Research Methods. Oxford. Oxford University Press.

Silberstein, S. 1987. "Let's Take Another Look at Reading: Twenty-Five Years of Reading Instruction" English Teaching Forum. 25/4: 28-35.

Smith, F. 1985. Reading. (Second edition) Cambridge: Cambridge University Press.

Stubbs, J.B. and G.R. Tucker. 1974. 'The Cloze Test as a Measure of English Proficiency.' Modern Language Journal. 58: 239-241.

Taylor, W. 1953. "Cloze Procedure: a New Tool for Measuring Readability." Journalism Quarterly. 30: 415-433.

Wallace, C. 1992. Reading. Oxford: Oxford University Press.

William's, R. And D. Dallas. 1984. "Aspects of Vocabulary in the Readability of Con tentArea L2 Educational Text books: a case study" in: Reading in a Foreign Language. J.C. Alderson and A.H. Urquhart (eds.). London: Longman

# አባሪ 1

አጠቃላይ መመሪያ፦ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች የትክክለኛውን መልስ ፊደል መርጣችሁ ለመልስ መስጫ በተዘጋጀ የተለየ ወረቀት በተገቢው ቦታ ላይ በመፃፍ መልሱ::

## I. የሚከተለውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ ከምንባቡ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በመምረጥ መልሱ::

### ጦር ሰፈር (ምንባብ -1)

ኮዳዬን አውጥቼ ውሃ ጠጣሁ:: ሙቅ ነበር:: ቀዝቃዛ ውሃ በአይኔ ዞረ:: አንድ ጠርሙስ ቀዝቃዛ ውሃ ባገኝ የተጠየኩትን ዋጋ እከፍል ነበር:: ከሰአት በኋላ 17ኛ ክፍለጦር የሰፈረበት ቦታ በሰፈርነት ተመርጦ አዳር እዚያ እንዲሆን ተደረገ:: ትልቁግራር ላይ "አምባ ሶይራ" የሚል ጽሑፍ ተለጥፎበታል መለስ ካለው ግራር ላይ ደግሞ "ኢያላ" የሚል ፅሁፍ ይታያል:: የበረሃ ሀረጎችን በማያያዝ የተሰሩ ዳስ መሳይ ነገሮች ላይ "አምባሳደር" "ቻው" "ከረን" የሚሉ የሆቴል ስሞች ተፅፈው ይነበባሉ:: መቼም የሰው ልጅ ገሀነም ውስጥ ቢወድቅም ገነት መመኘቱ አይቀርምና ነገሩ ያሳቀኝን ያህል አሳዘነኝ:: ሰፈሩ በአንድ ጊዜ በወታደራዊ እንቅስቃሴ ተሞላ:: ዘቦች ቦታ ቦታቸውን ያዙ:: ሹካና ማንኪያ የሚል የመተላለፊያ ምልክት ተሰጠ:: ውሃ አቀዝቅዞ ለመጠጣት የሚደረገው ሩጫና ጥረት የሚያስደንቅ ነው:: አንዳንዱ ኮዳውን በእርጥብ ጆንያ አስሮ ከዛፍ ላይ ይሰቅላል ሌላው ኮዳውን ወስዶ ከደረቅ ወንዝ ዳር አሸዋ ውስጥ ይቀብራል:: ጋዜጠኞች እንደ እንቁላል የሚሰበሩ ይመስል የጦሩ አባሎች በሙሉ ሊንከባከቡን ይጥሩ ነበር:: አንዳንዶቹ ከንፈራቸውን በሃዘን እየመጠጡ ያዝኑልናል:: አሁን እንዲያው እዚህ ምን አመጣችሁ? የሚሉ ይመስላሉ::

ፀሃይ ከመጥለቋ በፊት የራሻይዳ ብሄረሰብ አባሎች ከየት መጡ ሳይባል፤ ተሰባስበው በመምጣት ከጦር ሰፈሩ ትንሽ ራቅ ብላ በምትገኝ ገላጣ ስፍራ ላይ ተከማችተው ይታዩ ነበር:: ከእግር ጥፍራቸው እስከ ራስ ጠጉራቸው በጥቁር ጨርቅ የተሸፈኑ ሴቶች ከወንዶች ኋላ ተቀምጠዋል:: ፊታቸው አይታይም:: አንድ የራሻይዳ ሴት በአስር ወይም በአስራ ሁለት አመቷ ከተዳረች በኋላ ከባሏ ሌላ ማንም ወንድ ፊቷን ሳያይ ኖራ ትሞታለች ሲባል ሰምቻለሁ:: ምግብ ስተበላም ሆነ ውሀ ስተጠጣ ተሸፍና ስለሆነ ባሏም ቢሆን ከንፈሯን አያይ ይባላል:: "ምን ይመስሉ ይሆን? ያንዷን ፊት ገልጨ ባየሁት" የሚል ስሜት ቢያድርብኝም "የራሻይዳ ባል የሚሰቱን

ፊት ገልጦ ያየበትን ወንድ እጅ በያዘው ሰይፍ ቆርጦ ሳይጥል አይመለስም" የሚል ታሪክ ስላለ ... ስሜቴን ገትቼ ዝም አልኩ። ፊልም አንሺያችን ያንድን ሴት ፊት ገልጦ ለማንሳት ሲሞክር ሩጩ ያዝኩት። አንዱ የራሻይዳ ጎረምሳ ሰይፉን ለመምዘዝ ይዳዳው ነበር፤ ወይም መሰለኝ። ለፊልም አንሺው ታሪኩን ስነግረው ደንግጦ የፊልም ማንሻ መሳሪያውን ጥሎ ሊሮጥ ምንም አልቀረው።

ወደጦሩ የፖለቲካ ኮሚሳር ጠጋ ብዬ "እነዚህ ሰዎች ምን ሊፈልጉ ነው የመጡት?" ብዬ ጠየኩት ወደ ረሻይዳዎች እየመለከትኩ።

"የወባ መድሃኒት" አለኝ
"ምነው ሁሉ ታመዋል?

"የለም አብዛኞዎቹ ከኪኒኑ ጋር ለሚሰጠው ውሀ ሲሉ ነው የሚመጡት" በማለት መለሰልኝ።

ውሀ ማግኘት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ጭንቅላቴን መታኝ። የሰው ልጅ በእንደዚህ ያለ የተረገመ ምድር መኖርን የሚመርጥበት ምድራዊ ምክንያት አልታይህ አለኝ።

በዓሉ ግርማ÷ 1975 ዓ.ም÷ ኦሮማይ÷ ገጽ÷ 307-308

1. የዚህ ታሪክ ተራኪ "ቀዝቃዛ ውሃ ባገኝ የተጠየኩትን ዋጋ እከፍል ነበር።" ያለው ________ ለማለት ነው።

ሀ. ለቀዝቃዛ ውሃ ዋጋ አነሰው
ለ. ባካባቢው ቀዝቃዛ ውሃ አይገኝም
ሐ. ቀዝቃዛ ውሀ በጣም አማረኝ።
መ. ውሀ ጥም አሳረረኝ

2. ከሚከተሉት "አምባ ሶይራ ሆቴል" የትኛው ነው?

ሀ. መለስተኛው ግራር
ለ. የበረሃ ሀረጉ ዳስ
ሐ. ትልቁ ግራር
መ. የጦር ሰፈሩ እንዳለ

3. "ኒያላ ሆቴል" ለመዝናናት የፈለገ ወታደር የት መሄድ ይገባዋል?

ሀ. ወደ ትልቁ ግራር
ለ. ወደ መለስተኛው ግራር
ሐ. ወደ ዳስ መሳይ ነገሮች
መ. ወደ በረሃ ሃረጎች

4. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሰው ሹካና ማንኪያ ምንድነው?

ሀ. የፖስታ መመገቢያ
ለ. የወገን መለያ
ሐ. የጠላትን መምጣት መጠቆሚያ
መ. የጋዜጠኞች ቅፅል ስም

5. የታሪኩ ተራኪ ሙያ ምንድነው?

ሀ. ወታደር　　ለ. ጋዜጠኛ
ሐ. ኮሚሳር　　መ. ሃኪም

6. በጦሩ አባሎች ያለቦታቸው እንደተገኙ የተቀጠሩት________ ናቸው::

ሀ. ራሻይዳዎች　　ለ. ኮሚሳሮች
ሐ. ጋዜጠኞች　　መ. ሆቴሎች

7. የራሻይዳ ብሄረሰብ አባሎች ተሰብስበው የመጡበት አብይ ምክንያት ምንድነው?

ሀ. ጦሩን ለመርዳት　　ለ. ውሀ ለመጠጣት
ሐ. የወባ ኪኒን ለማግኘት　　መ. ጦሩን ለመሰለል

8. ያላገባች የራሻይዳ ብሄረሰብን ልጃገረድ ፊት ያየ ምን ይደርስበታል?

ሀ. እጁን የማጣት አደጋ
ለ. ምንም አይደረስበትም
ሐ. ውሃ እንዳይጠጣ ይከለከላል
መ. የወባ ክኒን አይሰጠውም

9. ፊልም አንሺውን የፊልም ማንሻውን ጥሎ ለመሮጥ እስከመከጀል ያስደነገጠጠው ምንድነው?

ሀ. የጦርነቱ እየጠነከረ መምጣት
ለ. የራሻይዳ ጎረምሳ የመዘዘው ሰይፍ
ሐ. እጁን ሊያጣ እንደነበር መስማቱ
መ. የተሸፈነች የራሻይዳ ሴትን ፊት ገልጦ ማየቱ

10. ተራኪው ያለበትን አካባቢ "የተረገመ ምድር.." ያለው በዋናነት የከፋ _______ ችግር በማየቱ ነው።

ሀ. የውሃ
ለ. የመድሃኒት
ሐ. የሰላም እጦት
መ. ያለመተማመን

## II. ከዚህ በታች ካለው ምንባብ ቀጥሎ በ"ሀ" ረድፍ በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች የሚወክሉ ቁጥሮች በቅደም ተከተል ተደርድረዋል። በ "ለ" ረደፍ ደግሞ ክፍት ቦታዎቹን በትክክል ለማሟላት የሚያስችሉ አማራጭ ቃላት ከሀ-በ በፊደል ተራ ተደርድረዋል። በመሆኑም ምንባቡን በትክክል የተሟላ የሚያደረጉትን ቃላት ፊደል ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ በ"ሀ" ረድፍ ውስጥ ከተመለከቱት የክፍት ቦታዎች ወኪል ቁጥሮች ጋራ በማዛመድ መልስ ስጡ።

### በእሳት ቀለበት የታጠረች ከተማ (ምንባብ 2)

የተዋበው የሀምሌ ሌሊት ከምን ጊዜውም የበለጠ ውበት (11) _______ ነበር። ተጨማሪ ውበት የሰጡትም ገና አመድ ሆነው (12) _______ አሁንም የሚነዱት የአካባቢው መንደሮች ናቸው። በአንዱ ስፍራ የእሳቱ (13) _______ በዝግምታና በታላቅ (14) _______ ወደ ሰማይ የሚንዝ ይመስላል። በሌላው ደግሞ ነበልባሉ የሚነድ ነገር እያጋጠመው(15) _______ እንደሚያነሳው አፈር ብትን ብሎ በልዩ ልዩ አንፃር ይወረወራል። ነዶ የከሰለው የገዳሙ ህንፃ ጥቁር ሆኖ ቆሞ በአካባቢው ነበልባሉ በደነፋ ቁጥር (16) _______

ብሎ ይታያል፡፡ በዚህ ሁሉ መሃል አንድ (17)________ አይሁድ ወይም መነኩሴ ከህንፃ ግድግዳ ወይም ከአንድ ዛፍ ቅርንጫፍ ተንጠልጥሎ እሳቱ (18)________ ይታያል፡፡ በሰማይ ላይ ርቀው የሚበሩ አእዋፍ በአንድ የነበልበል መስክ ላይ ያሉ ጥቋቁር (19) ________ ይመስላሉ፡፡ የተከበበው ከተማ ያንቀላፋ ይመስላል፡፡ የቤቶቹ ጣራና ምሽጉ በሩቅ ካለው ቃጣሎ በሚደርስባቸው (20) ________ ብዥብዥ እያሉ ይታያሉ፡፡

ኒኮላይ ጎጎል፥ 1988፥ ታራስ ቡልባ፥ ገጽ 51

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 11. ________ | ሀ. ነበልባል |
| 12. ________ | ለ. መስቀሎች |
| 13. ________ | ሐ. ያልታደለ |
| 14. ________ | መ. ውጋጋን |
| 15. ________ | ሠ. አውሎነፋስ |
| 16. ________ | ረ. ሲለበልበው |
| 17. ________ | ሰ. ወገግ |
| 18. ________ | ሸ. ግርማ |
| 19. ________ | ቀ. ተጎናፅፎ |
| 20. ________ | በ. ያልጠፉትና |

**III. ከዚህ ቀጥሎ ባለው ግጥም ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በግጥሙ መንፈስ መሰረት በትክክል የሚያሟሉትን ቃላት ከየክፍት ቦታዎቹ አንፃር ከጥያቄ ተራ ቁጥር ጋር ተያይዘው ከተሰጡ አማራጮች በመምረጥ መልሱ፡፡**

አንዲቱን ቀዘባ (ምንባብ 3)

እንደ ሐምሌ ውራት ፊቷ ጭፍና ለብሶ፥

21. ሀ. አደይ ለ. ቡቱቱ እንደ መኸር_____ ልብሷ ተልከስክሶ፥

ሐ. ድርቆሽ　መ. ውበት　አየኋት ለየኋት አንዷቱን ቀዘባ÷

22. ሀ. ጉድባ　ለ. አእዋፍ　ዘንጠፍ ዘና ብላ እንደ መስክ____

ሐ. አበባ　መ. ገለባ

ፊቷ ጭፍና ቢለብስ÷

ልብሷ ቢልከሰከስ÷

ግና ሥግው ሁኖ ውበት ተደብቆ÷

23. ሀ. የታል　ለ. አንጸባረቀብኝ　______ ተገለጠ ድንገት አሽብርቆ

ሐ. ታይኝ　መ. ፊቷ

ልብሷ የባላገር አየሯ ገጠር÷

24. ሀ. ሲያምራት ለ. ይዛ　ኩለንታዊ ውበት____ የምትኖር÷

ሐ. ታርዛ　መ. ባዝና　አየኋት ከመስኩ ወደገጠር ሄጄ÷

ተፈጥሮን ስፈልግ ተፈጥሮን ወድጄ::

ነባይ አባይ ማለት በተፈጥሮ ቤት÷

አንዷቱ ቀዘባ አክሊል የውበት÷

ያልተጻደፈችው በሰው ሠራሽ ፊሊጥ ከንቱ ፈንደለላ÷

25. ሀ. ሰንደቅ　ለ. ቆነጃጂት　አየኋት ለየኋት የገጠሯን____የገጠሯን አፍላ::

ሐ. ፍቅሬን　መ. ኮበሌ

ዮሐንስ አድማሱ÷ 1990 ዓ.ም.÷ <u>እስኪ ተጠየቁ</u> ... ገጽ÷ 57::

## IV. የሚከተሉትን የአማርኛ ቅኔዎች የወርቅ ትርጉም በመምረጥ መልሱ::

26. አጭር ነው ቀጭን ነው ድሃ ነው አትበሉ::

ይከበር በቅጡ ባላባት ነው አሉ::

ሀ. ባለርስትን ማክበር ተገቢ ነው

ለ. ባል እንደ አባት ይቆጠራል

ሐ. የታወቀው በላባ ነው

መ. ባላባቱ ሰውዬ አልሄዱም::

27. ትልቁን አጉዛ ሸጠችው በብር
ትንሽ ለምድ አመጣች የማያኗኑር

ሀ. ብጣቂ ለምድ አመጣች
ለ. ከባሏ ውጪ መሄድ ጀመረች
ሐ. ትንሽ ለምድ ለኑሮ አይበጅም
መ. መሸጥ መለወጥ ክፉ አመል ነው::

28. አዳራሹ ሰፊ በሩ አልጠበባችሁ
በተራ በተራ ምነው መግባታችሁ::

ሀ. በረሃብተኛ ወረፋ ለምን ገባችሁ
ለ. በቅደም ተከተል ሳትጋፉ ግቡ
ሐ. በተራራው አቋርጣችሁ ግቡ
መ. የገባችሁበት አዳራሽ ተራ ነው::

## V. የሚከተሉትን ተረትና ምሳሌዎች በትክክል የሚያሟሉትን የተለመዱ አባባሎች በመምረጥ መልሱ::

29. ግመል ሰርቆ_________::

ሀ. ከአረብ ታርቆ
ለ. ተጨናንቆ
ሐ. አጎንበሶ
መ. ዘንግ ይዞ

30. _____ ማሞጥሞጥ ነው::

ሀ. ከኛ በላይ ዘፈን
ለ. ካወሩ አይቀር
ሐ. ከኛ በላይ ፉጨት
መ. ከሰብቅ ይልቅ

31. _____ ድሮም አልቅስ አልቅስ ይለኛል::

ሀ. ዘንድሮ ባበዛውም
ለ. እንኳን አሁንና
ሐ. እንኳን እናቴ ሞታ
መ. እንኳን በል ብለውኝ

32. ተመክሮ ልብ_______::

ሀ. ገድሎ ሰበብ

ለ. ተፈርቶ ጅብ

ሐ. አሉ እማሆይ

መ. ተሸምቶ ድልብ

## VI. ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆኑትን በመምረጥ መልሱ::

33. ገበታ ከፍ ሲል መድረሱ ለኮቴ ደረቅነቱ ማስረጃ ይሆናል::

ሀ. ወግ ሲያበቃ

ለ. ማእድ ሲነሳ

ሐ. መብል ሲወደድ

መ. ምግብ ሲሚጠጥ

34. እናቴ በመስኮት አስግጋ አየችኝ::

ሀ. አሾልቃ

ለ. ተንጠራርታ

ሐ. አቆልቁላ

መ. እንጋጣ

35. ሶስት ቀን ሙሉ በአፌ እህል አልዞረም::

ሀ. ጠግቤ አልበላሁም

ለ. ጦሜን አደርኩ

ሐ. እህል አልቀመስኩም

መ. እህል አስጠላኝ

36. እንዲያ ሲጀነን የነበረ ሰው ሲሽቆጠቆጥ በማየቴ ተገረምኩ::

ሀ. ሲፎክር

ለ. ሲሽቀረቀር

ሐ. ሲንቀባረር

መ. ሲያስደነብር

37. በገጠመው መልካም እድል በደስታ ፈነደቀ::

ሀ. ቆዘመ

ለ. ፈነጠዘ

ሐ. ተዋጠ

መ. ሰመጠ

38. የታዘዘልህን ኪኒን ካልወሰድክ ልትድን አትችልም::

ሀ. ካልዋጥክ ለ. ካልተቀበልክ

ሐ. ካልተወጋህ መ. ሁሉም መልስ ነው::

39. ለአካባቢው ባይተዋር ባይሆን ኖሮ ሁሉን ነገር ትክ ብሎ አያይም ነበር::

ሀ. በአትኩሮት ለ. በቸልታ

ሐ. አፍጥጦ መ. የጎሪጥ

40. የመጣው ደብተር ለተማሪዎች በነፍስ ወከፍ አራት አራት ሊዳረስ ይችላል::

ሀ. በጥቅሉ ለ. በቅንጅት

ሐ. በየግል መ. ብቻ ለብቻ

## VII. ከዚህ በታች ያሉትን የተጓደሉ አረፍተ ነገሮች በትክክል ሊያሟሉ የሚችሉትን ቃላትና ሐረጋት በመምረጥ መልሱ::

41. አስቴር ወንድሟን ልካ እህቷን ከሃገር ቤት________ ::

ሀ. አመጣች ለ. አስመጣች

ሐ. መጣችላት መ. መጣች

42. ________ ሁለታችሁ እህትማማች መሆናችሁን አላወቀችም::

ሀ. እሱ ለ. እሷ

ሐ. እነሷ መ. እሷን

43. እኔ________ ቀሰቀስኳችሁ::

ሀ. እናንተ ለ. እናንተን

ሐ. አንተን መ. እርስዎን

44. አልማዝ________ አስተማረቻት::

ሀ. ልጇ ለ. ልጅ

ሐ. ልጇን መ. ልጂት

45. እንቺ________ ጥፋት ፈጽመሻል።

ሀ. መልካም　　ለ. ስህተት

ሐ. ትልቅ　　መ. ለእሷ

46. እናቴ እኔንና እህቴን__________ ።

ሀ. አስጠነቀቀቻት　　ለ. አስጠነቀቀቻቸው

ሐ. አስጠነቀቀችን　　መ. ተጠነቀቀች

47. እራስን ለመቻል የግል________ መቀለስ ያስፈልጋል።

ሀ. ፎቅ　　ለ. ቤቶች

ሐ. ስልት　　መ. ጎጆ

48. ታታሪዋ ሴት______ ማልዳ ለሥራ ታጠቀች።

ሀ. እንደልማዷ　　ለ. እንደምንም

ሐ. ፈጽሞ　　መ. ለጥቂት

49. እኛ ቁልቁል እሱ______ ሲሄድ መንገድ ላይ ተገናኘን።

ሀ. ከኋላ　　ለ. ፊት ለፊት

ሐ. ሽቅብ　　መ. በችኮላ

50. ቀይዋ______ ልጅ ችግሩን በቀላሉ አስወገደች።

ሀ. ብልኋ　　ለ. ጎብዟ

ሐ. ቀልጣፋ　　መ. ጠይም

## አባሪ 2

## የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ የቅድመ ፈተና (pre-test) የአንበቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የአማካይና መደበኛ ልይይት ስሌት።

| የቁጥጥር ምድብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| score | f | $x_1$ | d | $d^2$ | $d^2xf$ |
| 8 | 1 | 8 | -19.19 | 368.26 | 368.26 |
| 10 | 1 | 10 | -17.19 | 295.50 | 295.50 |
| 12 | 4 | 48 | -15.19 | 230.74 | 922.94 |
| 14 | 4 | 56 | -13.19 | 173.98 | 695.90 |
| 16 | 1 | 16 | -11.19 | 125.22 | 225.22 |
| 18 | 3 | 54 | -9.19 | 84.46 | 253.37 |
| 20 | 3 | 60 | -7.19 | 51.70 | 155.09 |
| 22 | 4 | 88 | -5.19 | 26.94 | 107.74 |
| 24 | 4 | 96 | -3.19 | 10.18 | 40.70 |
| 26 | 3 | 78 | -1.19 | 1.42 | 4.25 |
| 28 | 9 | 252 | 0.81 | 0.66 | 5.94 |
| 30 | 7 | 210 | 2.81 | 7.90 | 55.30 |
| 32 | 4 | 128 | 4.81 | 23.14 | 92.54 |
| 34 | 8 | 272 | 6.81 | 64.38 | 257.52 |
| 36 | 5 | 180 | 8.81 | 77.62 | 388.08 |
| 38 | 6 | 228 | 10.81 | 116.86 | 701.14 |
| 40 | 5 | 200 | 12.81 | 164.10 | 820.48 |
| ድምር | 72 | 1958 | | | 5389.97 |

| የሙከራ ምድብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| score | f | $x_2$ | d | d | $d^2xf$ |
| 10 | 1 | 10 | -18.19 | 330.88 | 330.88 |
| 12 | 4 | 48 | -16.19 | 262.12 | 1048.46 |
| 16 | 2 | 32 | -12.19 | 148.60 | 297.19 |
| 18 | 4 | 72 | -10.19 | 103.84 | 415.34 |
| 20 | 2 | 40 | -8.19 | 67.08 | 134.15 |
| 22 | 5 | 110 | -6.19 | 38.32 | 191.58 |
| 24 | 4 | 96 | -4.19 | 17.56 | 70.22 |
| 26 | 9 | 234 | 2.19 | 4.80 | 43.16 |
| 28 | 4 | 112 | 0.19 | 0.04 | 0.14 |
| 30 | 6 | 180 | 1.81 | 3.28 | 19.66 |
| 32 | 5 | 160 | 3.81 | 14.52 | 72.58 |
| 34 | 11 | 374 | 5.81 | 33.76 | 371.32 |
| 36 | 6 | 216 | 7.81 | 61.00 | 365.98 |
| 38 | 7 | 266 | 9.81 | 96.24 | 673.65 |
| 40 | 2 | 80 | 11.81 | 139.48 | 278.95 |
| ድምር | 72 | 2030 | | | 4313.26 |

በነዚህ ሰንጠረዦች ውስጥ ያሉትን መረጃዎች በመጠቀም የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑን የአንብቦ መረዳት ንኡስ ክፍል ውጤት አማካይ እና መደበኛ ልይይት ከማስላታችን በፊት በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትንና በስሌት ውስጥ የምንጠቀምባቸውን መልክቶች (symbols) ትርጓሜ ቀጥሎ እናቀርባለን።

$n_1$ = የቁጥጥር ምድብ አባላት አጠቃላይ ቁጥር

$x_1$ = የቁጥጥር ምድብ አባላት ተናጥል ውጤት

$\bar{x}_1$ = የቁጥጥር ምድብ አባላት አማካይ ውጤት (mean)

$s_1$ = የቁጥጥር ምድብ አባላት መደበኛ ልይይት (standard deviation)

$n_2$ = የሙከራ ምድብ አባላት አጠቃላይ ቁጥር

$x_2$ = የሙከራ ምድብ አባላት ተናጥል ውጤት

$\bar{x}_2$ = የሙከራ ምድብ አባላት አማካይ ውጤት

$s_2$ = የሙከራ ምድብ አባላት መደበኛ ልይይት

$\Sigma$ = (summation) ጠቅላላ ድምር የሚል ትርጉም አለው::

f = (frequency) -ድግግም- እያንዳንዱ ውጤት በተለያዩ ተጠኚዎች ተደጋግሞ የመመዝገቡን መጠን ያመለክታል:: እንዲሁም በመሆኑ የድግግም አጠቃላይ ድምር ($\Sigma$f) የአንድን ምድብ አባላት አጠቃላይ ቁጥር ይሰጠናል::

d = (deviation) - ልይይት- ይህ ከተናጥል ውጤት (individual score) (x) ላይ አማካይ ውጤትን ($\bar{x}$) በመቀነስ የሚገኝ ውጤት ሲሆን፥ ተናጥል ውጤት ከአማካይ ያለውን ርቀር ያሳያል::

$d^2$ = (deviation squared) የተናጥል ውጤትን (x) ልይይት (d) እርስ በእርሱ በማበዛት የሚገኝ ውጤት ነው::

$d^2xf$= (deviation squared times frequency) የተናጥል ውጤት ልይይት እርስ በርሱ ተባዝቶ የተገኘውን ውጤት በድግግም በማበዛት የሚገኝ ውጤት ነው::

ቀጥሎ ከሰንጠረዦቹ የሚገኙትን መረጃዎች በመጠቀም የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡን አማካይ ውጤት እና መደበኛ ልይይት እናሰላለን::

**የቁጥጥር ምድብ አማካይ ስሌት**

$n_1 = 72$

$\Sigma x_1 = 1958$

$\bar{x}_1 = \frac{\Sigma x_1}{n_1}$

$\bar{x}_1 = \frac{1958}{72}$

$\bar{x}_1 = \underline{\underline{27.19}}$

**የሙከራ ምድብ አማካይ ስሌት**

$n_2 = 72$

$\Sigma x_2 = 2030$

$\bar{x}_2 = \frac{\Sigma x_2}{n_2}$

$\bar{x}_2 = \frac{2030}{72}$

$\bar{x}_2 = \underline{\underline{28.19}}$

የቁጥጥር ምድብ መደበኛ

ልይይት ስሌት

$\Sigma d_1^2 = 5389.97$

$S_1 = \sqrt{\frac{\Sigma d_1^2}{n_1}}$

$S_1 = \sqrt{\frac{5389.97}{72}}$

$S_1 = \sqrt{74.86}$

$S_1 = \underline{\underline{8.65}}$

የሙከራ ምድብ መደበኛ

ልይይት ስሌት

$\Sigma d_2^2 = 4313.26$

$S_2 = \sqrt{\frac{\Sigma d_2^2}{n_2}}$

$S_2 = \sqrt{\frac{4313.26}{72}}$

$S_2 = \sqrt{59.91}$

$S_2 = \underline{\underline{7.74}}$

# አባሪ 3

## የቅድመ ፈተና (pre-test) የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የ"t" ዋጋ ስሌት፡፡

| የቁጥጥር ምድብ | | | የሙከራ ምድብ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| $n_1$ | = | 72 | $n_2$ | = | 72 |
| $\bar{x}_1$ | = | 27.19 | $\bar{x}_2$ | = | 28.19 |
| $S_1$ | = | 8.65 | $S_2$ | = | 7.74 |

**የ "t"- ሙከራ (t-test) ቀመር**

$$t_0 = \frac{\bar{x}_1 - \bar{x}_2}{\sqrt{\frac{s_2}{n_1} + \frac{s_2}{n_2}}}$$

ቀመሩን በመጠቀም የ"t" ን ዋጋ ለማስላት መጀመሪያ የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡን የጋራ መደበኛ ልይይት (common standard divaition) (s) ዋጋ በሚከተለው ቀመር እንፈልጋለን፡፡

$$S = \sqrt{\frac{(n_1 - 1)\ s_1^2 + (n_2 - 1)\ s_2^2}{n_1 + n_2 - 2}}$$

$$S = \sqrt{\frac{(72-1)\ 8.65^2 + (72-1)\ 7.74^2}{72 + 72 - 2}}$$

$$S = \sqrt{\frac{5312.40 + 4253.44}{142}}$$

$$S = \sqrt{\frac{9565.84}{142}}$$

$$S = \underline{\underline{8.21}}$$

የሁለቱን ምድቦች የጋራ መደበኛ ልይይት (s) ካገኘን በኋላ ከላይ በተቀመጠው የ"t"- ሙከራ ቀመር የ"t"ን ዋጋ እንደሚከተለው እናሰላለን፡፡

$$t_0 = \frac{\bar{X}_1 - \bar{X}_2}{\sqrt{\frac{s^2}{n_1} + \frac{s^2}{n_2}}}$$

$$t_0 = \frac{27.19 - 28.19}{\sqrt{\frac{8.21^2}{72} + \frac{8.21^2}{72}}}$$

$$t_0 = \frac{1}{1.37}$$

$$t_0 = \underline{\underline{0.73}}$$

# አባሪ 4

## የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ የአጠቃላይ ቋንቋ የቅድመ ፈተና (pre-test) ውጤት

## የአማካይና መደበኛ ልይይት ስሌት

| የቁጥጥር ምድብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| score | f* | $x_1$ | d | $d^2$ | $d^2xf$ |
| 22 | 1 | 22 | -36.92 | 1363.09 | 1363.09 |
| 24 | 3 | 72 | -34.92 | 1219.41 | 3658.23 |
| 34 | 2 | 68 | -24.92 | 621.01 | 1242.01 |
| 36 | 2 | 72 | -22.92 | 525.33 | 1050.65 |
| 38 | 1 | 38 | -20.92 | 437.65 | 437.65 |
| 40 | 4 | 176 | -14.92 | 222.61 | 890.43 |
| 46 | 5 | 230 | -12.92 | 166.93 | 834.63 |
| 48 | 1 | 48 | -10.92 | 119.25 | 119.25 |
| 52 | 2 | 104 | -6.92 | 47.87 | 95.77 |
| 54 | 2 | 108 | -4.92 | 24.21 | 48.41 |
| 56 | 2 | 112 | -2.92 | 8.53 | 17.05 |
| 58 | 4 | 232 | -0.92 | 0.85 | 3.39 |
| 60 | 3 | 180 | 1.08 | 1.17 | 3.50 |
| 62 | 5 | 310 | 3.08 | 9.49 | 47.45 |
| 64 | 5 | 320 | 5.08 | 25.81 | 129.03 |
| 66 | 6 | 396 | 7.07 | 50.13 | 300.76 |
| 68 | 4 | 272 | 9.08 | 82.45 | 329.79 |
| 70 | 5 | 350 | 11.08 | 122.77 | 613.83 |
| 72 | 1 | 72 | 13.08 | 171.09 | 171.09 |
| 74 | 7 | 518 | 15.08 | 227.41 | 1591.84 |
| 76 | 3 | 228 | 17.08 | 291.73 | 875.18 |
| 78 | 3 | 234 | 19.08 | 364.05 | 1092.14 |
| 80 | 1 | 80 | 21.08 | 444.37 | 444.37 |
| ድምር | 72 | 4242 | | | 15359.54 |

| የሙከራ ምድብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| score | f | $x_2$ | d | $d^2$ | $d^2xf$ |
| 30 | 1 | 30 | -29.06 | 844.48 | 844.48 |
| 32 | 2 | 64 | -27.06 | 732.24 | 1464.49 |
| 38 | 2 | 76 | -21.06 | 443.52 | 887.05 |
| 40 | 1 | 40 | -19.06 | 363.28 | 363.28 |
| 42 | 2 | 84 | -17.06 | 291.04 | 582.09 |
| 44 | 2 | 88 | -15.06 | 226.80 | 453.61 |
| 46 | 2 | 92 | -13.06 | 170.56 | 341.13 |
| 48 | 1 | 48 | -11.06 | 122.32 | 122.32 |
| 50 | 4 | 200 | -9.06 | 82.08 | 328.33 |
| 52 | 4 | 208 | -7.06 | 49.84 | 199.37 |
| 54 | 5 | 270 | -5.06 | 25.60 | 128.02 |
| 56 | 6 | 336 | -3.06 | 9.36 | 56.18 |
| 58 | 3 | 174 | -1.06 | 1.12 | 3.37 |
| 60 | 5 | 300 | 0.94 | 0.88 | 4.42 |
| 62 | 2 | 124 | 2.94 | 8.64 | 17.29 |
| 64 | 6 | 384 | 4.94 | 24.40 | 146.42 |
| 66 | 2 | 132 | 6.94 | 48.16 | 96.33 |
| 68 | 5 | 340 | 8.94 | 79.92 | 399.62 |
| 70 | 5 | 350 | 10.94 | 19.68 | 598.42 |
| 72 | 2 | 144 | 12.94 | 167.44 | 334.89 |
| 74 | 4 | 296 | 14.94 | 223.20 | 892.81 |
| 76 | 2 | 152 | 16.94 | 286.96 | 573.92 |
| 78 | 2 | 156 | 18.94 | 358.72 | 717.45 |
| 80 | 1 | 80 | 20.94 | 438.48 | 438.48 |
| 84 | 1 | 84 | 24.94 | 622.00 | 622.00 |
| ድምር | 72 | 4252 | | | 10615.78 |

$n_1 = 72$ $\qquad \Sigma d_1^2 = 15359.54$

$\Sigma x_1 = 4242$ $\qquad S_1 = \sqrt{\dfrac{\Sigma d_1^2}{n_1}}$

$\bar{x}_1 = \dfrac{\Sigma x_1}{n_1}$

$\bar{x}_1 = \dfrac{4242}{72}$ $\qquad S_1 = \sqrt{\dfrac{15359.54}{72}}$

$\bar{x}_1 = \underline{\underline{58.92}}$ $\qquad S_1 = \underline{\underline{14.61}}$

$n_2 = 72$ $\qquad \Sigma d_2^2 = 10615.78$

$\Sigma x_2 = 4252$ $\qquad S_2 = \sqrt{\dfrac{\Sigma d_2^2}{n_2}}$

$\bar{x}_2 = \dfrac{\Sigma x_2}{n_2}$ $\qquad S_2 = \sqrt{\dfrac{10615.78}{72}}$

$\bar{x}_2 = \dfrac{4252}{72}$ $\qquad S_2 = \underline{\underline{12.14}}$

$\bar{x}_2 = \underline{\underline{59.06}}$

* የምልክቶቹን (symbols) ትርጓሜ ከአባሪ ሁለት ላይ ይመለከቷል:

## አባሪ 5

### የቅድመ ፈተና (pre-test) የአጠቃላይ ቋንቋ ችሎታ ውጤት የ"t" ዋጋ ስሌት

**የቁጥጥር ምድብ**

$n_1 = 72$

$\bar{x}_1 = 58.92$

$s_1 = 14.61$

**የሙከራ ምድብ**

$n_2 = 72$

$\bar{x}_2 = 59.06$

$s_2 = 12.14$

<u>የt-ሙከራ (t-test) ቀመር</u>

$$t_0 = \frac{\bar{X}_1 - \bar{X}_1}{\sqrt{\frac{s^2}{n_1} + \frac{s^2}{n_2}}}$$

ቀመሩን በመጠቀም የ t ን ዋጋ ለማስላት በመጀመሪያ የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡን የጋራ መደበኛ ልይይት (common standard diviation) (s) ዋጋ በሚከተለው ቀመር እንፈልጋለን፥

$$S = \sqrt{\frac{(n_1 - 1)\, s_1^2 + (n_2 - 1)\, s_2^2}{n_1 + n_2 - 2}}$$

$$S = \sqrt{\frac{(72-1)\, 14.61^2 + (72-1)\; 12.14}{72 + 72 - 2}}$$

$$S = \sqrt{\frac{15155.10 + 10463.95}{142}}$$

$$S = \sqrt{180.42}$$

$$S = 13.43$$

ከዚህ በኋላ ያገኘነውን የ s ዋጋ ተጠቅመን ከላይ በተሰጠው የ"t"- ሙከራ ቀመር የ"t" ን ዋጋ እንደሚከተለው እናሰላለን።

$$t_0 = \frac{\bar{X}_1 - \bar{X}_2}{\sqrt{\frac{s^2}{n_1} + \frac{s^2}{n_2}}}$$

$$t_0 = \frac{58.92. - 59.06}{\sqrt{\frac{13.43^2}{72} + \frac{13.43^2}{72}}}$$

$$t_0 = \frac{0.14}{2.24}$$

$$t_0 = 0.06$$

# አባሪ 6

# በስግ ሥርዓት በመታገዝ በቀረበው የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ውስጥ አንብቦ መረዳትንና ሌሎችንም የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበሪያነት በሥራ ላይ የዋሉ ስግ ምንባቦች

## ሀ. የምንባብ ተያያዥነት የማገናዘብ ችሎታን ለማጠናከር የቀረቡ ስግ ምንባቦች

### ስግ ምንባብ 1

### በኃይል አቃናለሁ ብሎ መስበር

ሁለት ሊስትሮዎች በመጣላት ላይ ሳሉ አንድ መካከለኛ ቁመት ያላቸው ጠና ያለ ሰው ልጆቹን ለመገላገል በማሰብ ከመሥሪያ ቤታቸው ቅጥር ግቢ ይወጣሉ:: ለመገላገል መሰባቸው በጎ ሆኖ ሳለ ፀባኞቹ አጠገብ እንደደረሱ አስማምቶ ከማስታረቅ ________ (1) አንደኛውን ልጅ በእርግጫ ይመቱታል:: በዚህ ጊዜ ይተመታው ልጅ በመመታቱ እልህ ይይዘውና ከአጠገባቸው ራቅ በማለት ይሰድባቸዋል:: ሰውዬውም ________(2) ተደፈርኩ በሚል በንዴት ጦፈው ተለቅ ያለ ድንጋይ አንስተው ልጁ________ (3) ይወረውራሉ:: የተወረወረው ድንጋይ ግን እንደሳቸው ሀሳብ ሳይሆን መሬት ነጥሮ ለሁለት በመከፈል ከፊት ለፊት የምትመጣ አነስ ያለች የቤት መኪና________ (4) በማረፍ የፊት መስታወቷንና መብራቷን ይሰብረዋል:: የተሰበረችውን መኪና አቁሞ የወረደው ሾፌር ድንጋዩን ________ (5) እንደወረወረ መለየት ተስኖት ግራ በመጋባት ላይ ሳለ - ግራ መጋባቱን ያጤኑት ገላጋይ ተብዬ አጋጣሚ ያገኙ መስሏቸው ሌላ ልጅ ላይ ይጠቁሙና እግሬ አውጭኝ ይላሉ:: ሾፌሩም የተጠቆመለትን ልጅ አንቆ ይይዛል:: ________ (6) ጊዜ እውነታውን ይመለከቱ የነበሩ ሰዎችና የተያዘው ልጅ ጓደኞች ወርዋሪው ________ (7) ሳይሆን በመፈርጠጥ ላይ ያሉት ሰውዬ እንደሆኑ ይነግሩታል:: ሾፌሩም ገስግሶ ይይዛቸዋል:: ________ (8) ከሐቅ ማምለጥ እንደማይችሉ ሲገነዘቡ የሰሩትን ስህተት አምነው መኪናዋን ለማሰራት ተስማምተው ሄዱ:: በኃይል አቃናለሁ ብሎ ከመስበር በሥርዓት ማረም አይሻልም?

ሪፖርተር ጋዜጣ÷ 4:29/186÷ 1991 ዓ.ም÷ ገጽ÷16

## ስግ ምንባብ 2

## ሳይንስ የገነት መግቢያ በር

የአረብ ሊቃውንት "የሰው ዋናው ሀብት እውቀት ነው።" በማለት ገልጸዋል። በዚህም መሰረት በግዛተ ከሊፍ__________ (1) በነበሩ ሀገሮች ውስጥ ከእደጥበብና ከንግድ __________ (2) የተያያዙ የሳይንስ ዘርፎች ማለትም ሂሳብ፥ አስትሮኖሚና ጂኦግራፊ ዳብረዋል። በትልልቅ ከተሞች __________(3) ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ነበሩ። ባግዳድ ውስጥ የግሪክ ምሁራን እጅግ ጠቃሚ ጽሑፎች ተሰብስበው __________ (4) አንድ ታላቅ የጥበብ ቅርስ ተጠብቀዋል።

የአረብ የሂሳብ ሊቆች አልጀብራን ቀምረዋል። የተጠቀሙት የህንድ ቁጥሮችን ነበር፣ ከጊዜ በኋላ__________ (5) ቁጥሮች አውሮፓውያን የተዋሱአቸው ሲሆን__________ (6) አሁንም የአረብ ቁጥሮች በመባል ይታወቃሉ።

የአስትሮኖሚ ሊቆች የተራቀቁ መሣሪያዎችን በመጠቀም የዓለምን ስፋት በጥቅሉ ለመተመን በቅተዋል። የማእከላዊ እስያ ምሁር የነበረው አል-ቢሩኒ__________ (7) መሬት በፀሐይ ዙሪያ መሽከርከሯን የሚመለከት የሚደነቅ መላ-ምት አራምዷል።

በአረብ ዓለም ውስጥ እጅግ የተከበረ የትምህርት ዘርፍ ጂኦግራፊ ነበር። " ለሳይንስ __________ (8) መንገድ የሚጓዝ ሁሉ ገነት ለመግባት የመጀመሪያው ይሆናል" የሚል አባባልም በጊዜው ይነገር ነበር።__________ (9) መሰረት የአረብ ተጓዦች በግዛተ ከሊፍ ስር የነበሩ ሀገሮችን፣ ህንድና ቻይናን አስተዋውቀዋል፣ __________ (10) አፍሪካ ዘልቀው ገብተዋል፣ ምስራቅ አውሮፓን ዳሰዋል። የሚያውቋቸውን ሀገሮችና ባህሮች በካርታ ላይ ነድፈዋል።

የመካከለኛው ዘመን ታሪክ፥ 1990፥ ገጽ 84 - 85

## ለ. የቃላት ችሎታን ለማበልጸግ የቀረቡ ስግ ምንባቦች

### ስግ ምንባብ 3

### መተሳሰብ

ከፋብሪካው ዋና በር ጥቂት ፈንጠር ብሎ አስረሱ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብሏል። እናቱን ወይዘሮ ትሁኔ ላንትይደሩን __________ (1) እስኪወጡ ይጠብቃል። ከአጠገቡ ደግሞ ኮራ የተባለው የነአስረሱ__________ (2) ውሻ የኋላ እግሩን አጥፎ ቁጢጥ ብሏል። አስረሱ ኩስስ ባለ ሰውነቱ __________ (3) ላይ ተቀምጦ እሱም ሌላ ድንጋይ መስሏል። አልፎ አልፎ እንዳቀረቀረ ሲያንቀላፋ ሾል ያለ __________ (4) ከታጠፈ ጉልበቱ ላይ እንደ ኳስ ይነጥረና እተቀመጠበት ያባንነዋል። ኮራ ግን__________ (5)። እንደ ንቁ ዘበኛ ፊቱን ኮስተር÷ልቡን ደፈር አድረጎ ወደ __________ (6) በር ልብ ብሎ ያያል። እሱም እንደ አስረሱ __________ (7) ተጭኖታል። እንስሳው ኮራ እመቤቱን÷ ወይዘሮ ትሁኔ ላንትይደሩን ከሥራ ሲወጡ የመቀበል÷ __________ (8) እቤት የማድረስ ኃላፊነት ተሸክሟል። ነፍስ ለነፍስ ልጅ ለእናቱ÷ ውሻ ለእመቤቱ በማሰብ እንደ ወትሮው ዛሬም ትሁኔን ለመጠበቅ ዘብ ቆመዋል።

የገራዱ ዋሽንት÷ 1982 ዓ.ም÷ ገጽ÷97

### ስግ ምንባብ 4

### አስፈሪው ዱለኛ

በማንኛውም ቀን ካንዱ ካገኘው ሰው ጋራ በመጣላት ያንን የተጣላውን ሰው አፈር-መሬት አስግጦ ስለሚለቀው ሰው ሁሉ የጠላውና የፈራው ነው። ብዙዎች እሱንም በተራቸው ለመደብደብ __________ (1)። ነገር ግን የሚሞከርላቸው አይደለም። እርሱን ለመደብደብ __________ (2) ማንኛውም ሰው ባየ ቁጥር አጠገቡ ያገኘውን ድንጋይ÷__________ (3) እንጨት ውይንም የብረት ቆመጥ አፈፍ አድርጎ ጨብጦ እግሮቹን__________ (4) በመከፈት ሊመታው የቃጣውን ሰው ቆሞ ይጠብቀዋል። በፀጉር __________ (5) እጆቹ እና ፊቱ÷ ከአይኖቹ አንስቶ እስከ አንገቱ ድረስ__________ (6) የወረደው ጥቁሩ ጢሙ ማንንም ሰው __________ (7) ነው። ሰዎች ግን በተለይ የሚፈሩት አይኖቹን ነው፤ አይኖቹ ትንንሽ ናቸው። ነገር ግን በጥልቀት __________ (8) የሚመለከቱ ስለሆኑ÷ በሌላው ሰው አእምሮ ውስጥ ጠልቀው __________ (9) ይመስላሉ። እነዚህን አይኖቹን የተመለከተ ማንም ሰው÷

በሃሳቡ እንዳችም ፍርሃት ባልተፈጠረበት ይቅርታ-ቢስ አጥቂ አውሬ ፊት የቆመ ያህል ይሰማዋል።

እናት፥ 1986፥ ገጽ፥ 25-26

## ስግ ምንባብ 5
## በምድር ላይ ያለ የውሃ መጠን ይቀንስ ይሆን?

ወደ ስድስት ቢሊዮን የተጠጋው የዓለማችን ህዝብ በነብስ-ወከፍ በየቀኑ በአማካይ ቢያንስ ሁለት ሊትር ተኩል ገዳማ ውሃ መውሰድ አለበት። በዚህ ላይ የእንስሳትና የእፅዋት የየቀን የውሃ ________ (1) ሲታሰብ፥ የምድር ውሃ ውሎ አድሮ ________ (2) መስሎ ሊሰማን ይችላል። የሚገርመው ነገር ግን ይህ ሁሉ ውሃ ________ (3) ላይ ቢውልም አንዲት ጠብታ ውሃ እንኳን በማንኛውም ________ (4) ውስጥ ገብታ ወደ ሌላ ነገር ያለመለወጥዋ፥ በምንም ሁኔታ አለመፈጠርዋና በማንኛውም መንገድ አለመባከንዋ ነው። ________ (5) የተጠቀምንባት ውሃ እጅግ ቀደም ባለው ዘመን የአንድ ዳይኖሰር ጥም ________ (6) ልትሆን ትችላለች። ምክንያቱም አሁን ያለው ውሃ በሙሉ ________ (7) ከተፈጠረችበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ፥ በውሃ ኡደት አማካይነት ________ (8) ያለንበት ዘመን ላይ የደረሰና ወደፊትም የሚኖር በመሆኑ ነው። ውሃ በፕላኔታችን ላይ በውሃ ________ (9) አማካይነት ያለማቋረጥ ይሽከረከራል። ከውቅያኖስ ወደ አየር ከዚያ በዝናም ________ (10) ወደ ምድር፥ ቀጥሎ በወንዞች በኩል ወደ ________ (11) ተመልሶ ይገባል። በዚህ መልክ ለሚሊዮኖች አመታት ________ (12)። የተፈጥሮ ህግ ነውና ሂደቱ በዓለማችን የውሃ መጠን ላይ ምንም ለውጥ ሳያስከትል ለዝንተ ዓለም በዚሁ መልክ ይቀጥላል።

ጦቢያ ጋዜጣ፥ 5:46፥ የካቲት 18/1991 ዓ.ም.

## ስግ ምንባብ 6
## "ጉሮ ወሸባዬ!"

እግረኛው የወገን ሰራዊት ከአፍ እስከ ገደፍ ታጥቆ የመጣው የጠላት ጦር ከተማውን እንዳይዝ የሞት ሽረት ፍልሚያ ይዟል። በእንዲህ እንዳለ ከየት መጡ

ሳይባል ስድስት የተከላካይ ሰራዊት ድጋፍ ሰጪ የጦር ጄቶች ኋላና ፊት ________ (1) ደርሰው ምድርን ቁና አደረጓት። ሁለት ሁለት እየሆኑ ኻቸው እያሉ ይወርዱና በወራሪው ሰራዊት ላይ ሞትን ________ (2) ሽቅብ ይወንጨፋሉ። ሁለቱ ሲሄዱ ሁለቱ ________ (3)፥ የተተኩት ሲያልፉ፥ ዞረው የመጡት ሲተኩ፥ ያንን ________ (4) ወራሪ ሰራዊት በያለበት ቀጡት። በጄቶቹ ጥቃት ________ (5) የጠላት ጦር መድረሻ አጥቶ ሲታመስ ________ (6) በምብ ጣይ አውሮፕላን ድምፁን አለስልሶ ________ (7) መጣና የቦንብ ናዳውን እንደ ኮረት ________ (8)። ምድር ቀውጢ ሆነች። አካባቢው ጨሰ። አፈር ይነድ ________ (9)። ታንኩ ሳይቀር እንደ ሳር ጎጆ ተንቀልቀሎ ________ (10) ጀመር። የድል ብሥራት ተሰማ። በጦርነቱ ምክንያት ከተማዋን ለቀው ያለወጡ ነዋሪዎች ተሰብስበው "ጉሮ ወሸባዬ!"ን አቀለጡ።

የገራዱ ዋሽንት፥ 1982 ዓ.ም.፥ ገጽ፥ 54-55

## ሐ. የሥነ-ጽሑፍ አተረጓጎምና አገባብ ችሎታን ለማጠናከር የቀረቡ ስግ ምንባቦች

### ስግ ምንባብ 7*

### ዶፍ ሊጥል ....

ሰማዩ ከአድማስ እስከ አድማስ እንደተተበተቡ የሸረሪት ድሮች ጠቁሯል። በጣት ________ (1) ያህል ወደ መሬት ቀርቧል።

በቡድን እየሳቁ ፎቆች ላይ ያርፋሉ። ተነስተውም ከተማውን ወደ ከበቡት ተራሮች ይበራሉ።

ፎቆች በፀሐይ ሙቀት ወደ ሰማይ ________ (3) ሁሉን እነደበለጡ ለማሳየት የሚጥሩ እንዳልመሰሉ ________ (4) -የተደበቱ። ራቂታቸውን ፀሐይ

ከጳመናዎቹ ዝቅ በሎ ከዶፍ ለማምለጥ የሚሯሯጡ ________ (2)

---

* ስግ ምንባብ 7 እና 8 ለትምህርት ሲቀርቡ ድርሳናት በሚጠቁሙት መሰረት የተገደፉት ቃላት ተሰባጥረው ከምንባቦቹ ግርጌ ትሰጥተዋል።

የሚሞቁ እንደ ሐር የሚነሰነስ __________ (5) ያላቸው ልጃገረዶች አይታዩም:: ወደ ታች አጎንብሰው መንገደኛውን እንደ ውሻ የሚለክፉ __________ (6) አይታዩም:: ፍቅረኞች እንደ ዘበት ወርወር የሚያደርጉት __________ (7) ጠፍቷል::

በእውቀት የተዘነጉ የማይጠቅሙ __________ (8) ከተንጠለጠሉበት ሽቦ ላይ እንደ ባንዲራ ይውለበለባሉ::

ሰዎች እንደ ጨለማ የሚጫነውን __________ (9) ፈርተው በየቤታቸው ክፍሎች ተደብቀዋል:: ቀን ቀን በፀሐዩ መስታወቶቹ የሚያብለጨልጨው የከተማው አንደኛ ረዥም ህንፃ ብዙ ውጊያዎች ረግጠውት ያለፈ አሮጌ __________ (10) መስሏል:: የህንፃው በረንዳዎች ተራቁተዋል::

ዝናብ ማንጠባጠብ ጀመረ::

ማሕሌት÷ 1981 ዓ.ም.÷ ገጽ÷ 63

## ስግ ምንባብ 8
## ሰይጣን ሰለጠነ

ሰይጣን ሰለጠነ÷
ቀንዶቹን ነቃቅሎ÷
__________ (1) ቆርጦ÷
ከሰው ልጆች ጋራ አንድነት ተቀምጦ
ሊኖር ነው ጨምቶ÷
ከሰው ልጆች ጋራ ሊጋባ__________ (2)

ሰይጣን ሰለጠነ÷:
ዘመናዊ ሆነ፤
ፊደል__________ (3) ዳዊትም ደገመ÷
በስመ አብ ብሎ÷ ውዳሴ ማርያምን÷
አንቀጸ ብርሃንን÷ መልካ መልኩን ሁሉ÷
__________ (4) ፈጠመ::

ከዚህም በኋላ ጾም ጸሎት__________ (5)
በመጨረሻውም አቡን ተክሌ እጥምቀው
ክርስትና አነሡት::
ግና ተቸገረ፤
እንዲያው__________ (6)
ጨርሶ አላወቀም ለማን እንደሆነ________ (7) ጸሎቱ÷
ቢጨንቀው ጊዜና ቆይቶ ሰንብቶ÷
ክርስቲያን የሆነ አንድ ሰው__________ (8)÷
ተወዳጀውና ብሶቱን ነገረው ሁሉንም ዘርዝሮ÷
__________ (9) ቋንቋ በውነት አሳምሮ::

"አትቸገር" አለው ክርስቲያን ወዳጁ አጽናናው_________ (10)
ሰይጣኑ ካሰበው አለመጠን ብሶ፤
"ይህስ ቀላል ነገር ችግርም የለው÷
አንደኛው ክርስቲያን ሆንክ ማለት ነው::"

እስኪ ተጠየቁ .... ÷ 1990 ዓ.ም÷ ገጽ÷ 108

## መ. የሰዋሰዋዊ አገባብ ችሎታን ለማበልጸግ የቀረቡ ስግ ምንባቦች

### ስግ ምንባብ 9
### የጥንት ጭሰኞች -አዳሪዎች እጣ ፋንታ

ቀደም ባለው ዘመን በካፒታሊዝም መስፋፋት ከመሬታቸው የተፈናቀሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ገበሬዎች ከትውልድ ቀያቸው እየተሰደዱ ጭሰኞች-አዳሪዎች ወይም ምፅዋተኞች ይሆኑ ነበር:: ________ (1) የማግኘት እድላቸውም የመነመነ ነበር:: በከተማዎች የነበሩ_________ (2) ጥቂት ነበሩ፤ በገጠር ደግሞ_________ (3) ገበሬዎች ያርሱበት በነበረው ሁዳድ ላይ የሚያስፈልገው__________ (4) እረኛ ብቻ ነበር:: በዚህ ምክንያት _________ (5) ሥራ ወይም መጠለያ ባለማግኘታቸው በየመንገዱ መለመን ጀመሩ:: በሺህ የሚቆጠሩትም በብርድ÷ በረሃብና በበሽታ የተነሳ__________ (6) አጡ::

ይህ አልበቃ ብሎ በየአካባቢው ያለ __________ (7) ጭሰኞች-አዳሪዎችንና ምፅዋተኞችን በመቃወም ህግ አወጣ:: ___________ (8) ህግ የተደረሰበት ጭሰኞች-

አዳሪ ከጋሪ ጋራ ከታሰረ በኋላ በደም __________ (9) ድረስ በአለንጋ እንዲገረፍ ያዝ ነበር፤ አሳልፎ ለሰጠው ሰው ________ (10) በመሆን እንዲያገለግልም ይደነግግ ነበር:: በዚህ ህግ መሠረት አንድ ዱር - አዳሪ ________ (11) አምልጦ እንደገና ከተያዘ÷ ጆሮው ተቆርጦ በጋለ ብረት ________ (12) ምልክት ከተደረገበት በኋላ ይታሰራል:: ለሦስተኛ ጊዜ ከተያዘ ደግሞ _________ (13) ይቀጣል::: በአውራ ጎዳናዎችና በገብያ ሥፍራዎች ስቅላት የሚካሄድባቸው ________ (14) ተተክለው ይታዩ ነበር:: በ16ኛው ምዕተ አመት የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ እንግሊዝ ውስጥ ከ70 ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በዚህ አኳኋን ተገለዋል::

የመካከለኛው ዘመን ታሪክ÷ 1990÷ ገጽ÷ 269-270

## ስግ ምንባብ 10
## ትንሳኤ ናዚ

ፀጉራቸው ሙሉ ለሙሉ ተላጭቶ ጭንቅላታቸው በሰም የተወለወለ ቅል ይመስላል:: ወጣቶች ቢሆኑም _________ (1) ናቸው:: በተለይ ከሌላ አገር የመጡ ስደተኞች ሲያዩ ደግሞ ኮስታራው ፊታቸው ይበልጥ _________ (2) ይመስላል:: ስደተኞችን አገጫቸውን ዘመም አድርገው _________ (3) ነው የሚያዩዋቸው:: እነኚህ ወጣቶች "እስኪን ሄድስ" በመባል የሚታወቁ ሲሆን በጀርመን አገር _________ (4) ላይ ያለው የትንሳኤ ናዚ ቡድን አባላት ናቸው::

ይህ በጀርመን አገር አቆጥቁጦ አውሮፓን ቀስ በቀስ _________ (5) ላይ ያለው የአፍቃሬ ናዚነት በሽታ አስጊነቱ ከቀን ወደ ቀን _________ (6) በመሄድ ላይ ነው:: አውሮፓን እያዳረሱ የመጡት _________ (7) ናዚ ንቅናቄዎች ከዚህች አህጉር የተነሱ _________ (8) ሲታሰብ ሊመጣ የሚችሉ አደጋ _________ (9) ፍፁም ከግምት በላይ ይሆናል:: የዚህ ዓይነቱ ንቅናቄ ጀርመን ውስጥ _________ (10) ከመንደር በማትሻል አንዷት የአፍሪካ አገር ውስጥ መፈጠር ዓለምን በማወክ ኃይሉ ከፍተኛ ልዩነት አለው:: "የአውሮፓ የትኛውም ጫፍ ሲነካ ድፍን ዓለም ይነዝራታል" የሚባለውም ለዚህ ነው::

እፎይታ መጽሔት÷ 1:6 1984 ዓ.ም÷ ገጽ÷18

## ስግ ምንባብ 11

## ያባቱ ልጅ

ሲጋራውን እየጨሰ ስታድዮሙ ዘንድ ደረሰ:: .... በቤንዚን ማደያው ________ (1) ግድግዳ አጠገብ ሲያልፍ የለመደውን የራሱን________ (2) አየ:: ከውልደቱ ይሁን ከአኗኗሩ ጎባጣ ነው:: ________ (3) ፀጉሩ ሞላላ አናቱን አጋልጦታል:: ቀጫጭን ________ (4) ወደ ሰደርያ ከተለወጠ ሰፊ ጃኬቱ ወጥተው ተንጠልጥለዋል:: ከራሱ ________ (5) ትእዛዝ ሳይሆን በነፋስ የሚውለበለቡ ይመስላሉ:: ________ (6) ሱሪው የእግሮቹን ጡንቻዎች ሰልባቸዋለች::

________ (7) እንጂ አባቱን ይመስላል:: አባቱ ዕድሜያቸው አርባ ________ (8) የወለዱት ነው:: ትንባሆ ሞኖፖል ይሠራሉ:: ________ (9) አበሳጭቷቸው ይሁን የፋብሪካው ሽታ አላምዷቸው እንደ እሱው ሲጋራ ያጨሳሉ:: ________ (10) አዳክሞአቸው ይሁን ከሚበሉት-ሰውነታቸው ኮስምኗል:: ________ (11) ሥር ቀንም ማታም የማይለያቸው ካናቴራ÷ ከሸሚዛቸው ላይ እጀ ሙሉ________ (12)÷ ከሹራባቸው ላይ ኮት÷ ከኮታቸው ላይ ጋቢ÷________ (13) ላይ ካፖርት ይለብሳሉ:: ይህም ሆኖ እንደ________(14) ዘወትር ያማርራሉ:: ከጉልበታቸው በላይ ልብስ በመደራረብ እንዲገዝፍ የተደረገውን ሰውነታቸውን በቀጫጭን እግሮቻቸው ተሸክመው በቀስታ ሲሄዱ የሚንሳፈፉ ይመስላሉ::

.... እንዳባቱ ነው

ማሕሌት÷ 1981 ዓ.ም÷ ገጽ÷ 202-203

## ስግ ምንባብ 12

## ያራዳው ጠበቃ

ባሻ ገላጋይ ቀደም ሲል የመንግሥት ሠራተኛ ነበሩ:: ዛሬ ትንሽ የጡረታ አበል አለቻቸው:: ________ (1) ልጅ አላቸው፤ ግን የት እንዳለ አያውቁም:: ዛሬ ፀሐይ የምትባል ሠራተኛ አለቻቸው:: ይሰድቧታል÷ ያስቋታል÷ ያሳዝኑአታል÷ ደመወዝ ይከለክሉአታል:: እሷ ግን ________ (4) ብላ ይኸው ስምንት ዓማቷ

ከሳቸው ጋራ። ጧት ________ (5) ወደ ሥራቸው ይሄዳሉ። ሥራቸው አራዳ ____________ (6) ነው። ዙሪያዋን በሳጣራ የተከበበችና በሦስት ቆርቆሮ የተከደነች ቢሮ አለቻቸው። __________ (7) ላይ እኔ ነኝ ያለ ኀበዝ የማያነሳቸው አራት ድንጋዮች__________ (8)። እውስጥዋም አንድ ትንሽ አግዳሚ ወንበር__________ (9)፥ አንድ ድንክ የጠፍር ወንበር ለራሳቸው፥ አንድ ረዘም ያለ የእንጨት ወንበር ለጸሐፊያቸው ይገኙባታል። አንድ __________ (10) መኪና በአንዲት አነስተኛ ጠረጴዛ መሀል ላይ፥ ________ (11) ኪስ ውስጥ ደግሞ ሁለት የወንጀለኛ መቅጫ _________ (12) አሉ። መዝገቢያዋ ግማሹ ቆርቆሮ ፥ _________ (13) የሳሙና ጣውላ ነው። ከቤቷ ፊት ለፊት "ማንኛውንም ጉዳይ __________ (14)" የሚል ውልግድግድ ያለ ማስታወቂያ አለ።

ባሻ ገላጋይ __________ (15) ጉዳይ የለም። ሰው ሲጣላ አስታራቂ ይሆናሉ። ሰው ሲበደል __________ (16) ልሁን ይላሉ። ታዲያ በዚህ የተነሳ ___________ (17) "ያራዳ ጠበቃ" ይላቸዋል። የሠፈር ውሪዎች ይህንኑ ___________ (18) "ያራዳ ጠበቃ" እያሉ ያሾፉባቸዋል። ባሻ _________ (19) እንዲህ ሲሏቸው አይወዱም። "ይኸ የስሙኒ __________ (20) ሁሉ" ብለው ልግደል ይላሉ ። ልጆቹም አያርፉ ባለፉ ባገደሙ ቁጥር እየተከታተሉ ያበሽቋቸዋል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ገላጋይን ትተው "አጋዳይ" ይሏቸዋል።

የእግር እሳት፤ 1979 ዓ.ም.፥ ገጽ፥ 106-107

# አባሪ 7

## ለማስተማሪያ ከዋሉት ስግ ምንባቦች ውስጥ የተገደፉ ቃላት

### ስግ ምንባብ 1

1.ይልቅ 2. እንዴት 3. ላይ 4. ላይ 5. ማን 6. በዚህ
7.እሱ 8. እሳቸውም

### ስግ ምንባብ 2

1. ስር 2. ጋራ 3. ውስጥ 4. እንደ 5. እነዚህን
6.እስከ 7.ደግሞ 8. ሲል 9. በዚህም 10. ወደ

### ስግ ምንባብ 3

1. ከሥራ 2. ታማኝ 3. እድንጋይ 4. ግንባሩ 5. እያንቀላፋም
6. ፋብሪካው 7. ሃላፊነት 8. ተቀብሎም

### ስግ ምንባብ 4

1. ሞክረዋል 2. የሚቃጣ 3. ፍልጥ 4. እንፈራጠ 5. የተወረሩት
6. ተንገርግጎ 7. የሚያስበረግግ 8. አተኩረው 9. የሚገቡ

### ስግ ምንባብ 5

1. ፍጆታ 2. የሚሟጠጥ 3. ጥቅም 4. አካል 5. ዛሬ
6.ያረካች 7. ምድር 8. እየተገላበጠ 9. ኡደት 10. መልክ
11. ውቅያኖስ 12. ተሽከርክሯል

### ስግ ምንባብ 6

1. ተሰባጥረው 2. ዘርተው 3. ሲተኩ 4. የተኩራራ 5. የተሳከረው
6.ግዙፍ 7. እያቃሰተ 8. ዘረገፈው 9. ገባ 10. ይጋይ

### ስግ ምንባብ 7

1. የሚነኩት 2. ወፎች 3. እየተንጠራሩ 4. ትሽማቀዋል 5. ፀጉር
6. ህፃናት 7. ጨርቆች 8. ሳቅ 9. ዳመና 10. ምሽግ

## ስግ ምንባብ 8

1. ጭራውንም 2. ተጫጭቶ 3. ቆጠረና 4. አጠና 5. ጀመረ
6.በየለቱ 7. ጸምና 8. አግኝቶ 9. በጣፈጠ 10. መልሶ

## ስግ ምንባብ 9

1. ሥራ 2. ፋብሪካዎች 3. ብዙ 4. አንድ
5. ዱር-አዳሪዎች 6. ህይወታቸውን 7. መስተዳድር 8. ይወጣው
9. እስኪዋኙ 10. ባሪያ 11. ከጌታው 12. ተተኩሶ
13. በስቅላት 14. እንጨቶች

## ስግ ምንባብ 10

1. ኮስታሮች 2. ሳንባ 3. የጎድን 4. በማቆጥቆጥ 5. በማጥለቅለቅ
6. እየጨመረ 7. የትንሳኤ 8. መሆናቸው 9. ግዝፈት 10. መጠንሰስና

## ስግ ምንባብ 11

1. የመስታወት 2. ምስል 3. የተላጨው 4. እጆቹ
5. የሚወጣ 6. የምታጣብቅ 7. አልሸመገለም 8. ሲሞላ
9. ኑሮ 10. ትምባሆው 11.ሸሚዛቸው 12. ሹራብ
13. ከጋቢያቸው 14. በረዳቸው

## ስግ ምንባብ 12

1. አንድ 2. በልጅነታቸው 3. ፈተዋል 4. አባቴ
5. ተነስተው 6. መሀል 7. ከቆርቆሮዋ 8.ተጎልተውባታል
9. ልባለጉዳዮች 10. የጽሕፈት 11.በጠረጴዛዋ 12. ጥራዞች
13. ግማሹ 14. እንጽፋለን 15. የማይገቡበት 16. ጥበቃ
17. ሠፍረተኛው 18. ይዘው 19. ልጆች 20. ልጅ

# አባሪ 8

**አጠቃላይ መመሪያ፦** ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ትክክለኛውን መልስ መረጣችሁ ለመልስ መስጫ በተዘጋጀው የተለየ ወረቀት በተገቢው ቦታ ላይ በመፃፍ መልሱ::

## I. የሚከተለውን ምንባብ በሚገባ ካነበባችሁ በኋላ ከምንባቡ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በመምረጥ መልሱ::

### የአፈር መሸርሸር (ምንባብ 1)

የመሬትን የላይኛውን ክፍል የሸፈነው ለም አፈር የሰው ልጅ የሕይወት ምንጭ ነው:: ራሳችንን ከልዩ ልዩ በሽታ ጥቃት የምንከላከለውን ያህል የመሬትን የላይኛውን ክፍል የሸፈነውን ለም አፈር ከተለያዩ ጥፋቶች እንዲጠበቅ ማድረግ ይገባናል:: ለለም አፈር መከላት ምክንያት የሚሆኑ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ጥፋቶች ሁሉ ሕልውናችንን በአያሌው የሚፈታተኑ መሆናቸው ለአፍታም ሊዘነጋ አይገባውም:: ለለም አፈር ብክነት በምክንያትነት የሚቀርቡ ጥፋቶች በርካታ ናቸው::

ከነዚህም ምክንያቶች አንዱ የደን ጭፍጨፋ ነው:: የሰው ልጅ ለዘለቄታው ጥቅሙ ከማሰብ ይልቅ፥ ለጊዜያዊ ጥቅሙ በማድላት በደን ላይ ገደብ የለሽ ጭፍጨፋ ወይም ቃጠሎ ሲያካሂድ ኖሯል:: እያካሄደም ነው:: ይህ ድርጊት የተፈጥሮ ሚዛናዊ ቅንብር መናጋትን ያስካትላል:: በዚህ መሠረትም የደን ጭፍጨፋ ለለም አፈር መራቆት፥ የለም አፈር መራቆት ለድርቅና ረሃብ መከሰት፥ በመጨረሻም ለሰው ልጅ እልቂት ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው::

ከደን መጨፍጨፍ ተለይቶ የማይታይ ሌላም ጎጂ ድርጊት አለ:: ይህም ለም አፈራችንን የሸፈኑት ዕፅዋት ከመጠን በላይ ለግጦሽ አገልግሎት እንዲውሉ መደረጋቸው ነው:: የግጦሽ ሥፍራ በተፈጥሮ ሊሸከም ከሚችለው እንስሳት በላይ እንዲያስተናግድ ይደረጋል:: በዚህ ጊዜ ለገጦሽ ያዋሉት እፅዋት ከነሥራቸው እየተመነገሉና እየተነጩ ለእንስሳቱ ምግብ ይሆናሉ:: በዚህ ወቅት አፈሩ ከተፈጥሯዊ እፅዋት ይራቆታል:: ቀጥሎ እርቃኑን የቀረው የላይኛው ለም አፈር በነፋስ በኖ ይጠፋል፤ በዝናብ እየታጠበ ከነበረበት እየተጓዘ ባክኖ ይቀራል::

ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ለእርሻ ቦታ ማስፋፋት ሲባል የሚከናወነው የደን ምንጣሮና ቃጠሎ፥ በደጋማና ወይናደጋማ አካባቢዎች የሚሰፍሩ ሰዎችና እንስሳት መበራከትና በዳገታማ ቦታዎች የሚከናወን ሳይንሳዊ ይዘት የሌለው አስተራረስ ለለም አፈራችን ብክነት ተጨማሪ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የካቲት መጽሔት፥ 15፡12፥ 1984 ዓ.ም ገጽ፥24

1. በምንባቡ ውስጥ የሰው ልጅ የህይወት ምንጭ ነው የተባለው ምንድነው?
   ሀ. በሽታን መከላከል
   ለ. አፈር ጥበቃ
   ሐ. ለም አፈር
   መ. ሁሉም መልስ ነው
2. የመሬት የላይኛውን ክፍል ለሸፈነው ለም አፈር የምናደርገው እንክብካቤና ጥበቃ ከምን ጋራ ይነጻጸራል?
   ሀ. ከሕይወት ምንጭ
   ለ. ከጤና ጥበቃ
   ሐ. ክህፃናት ክብካቤ
   መ. "ሀ" እና "ሐ"
3. የሰውን ልጅ ህልውና በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚፈታተኑ የተጠቀሱት ምንድናቸው?
   ሀ. ለለም አፈር መሸርሸር መንስኤ ይሆኑ ምክንያቶች
   ለ. ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ብክለቶች
   ሐ. የለም አፈር አፍታዊ ግብአቶች
   መ. ምልሱ የለም።
4. "የለም አፈር መከላት" በሚለው ውስጥ የ"መከላት" ፍቺ ምንድነው?
   ሀ. መከልከል ለ. መሸርሸር ሐ. መበርበር መ. መጠቃት
5. በምንባቡ ውስጥ እንደሰው ልጅ ጊዜያዊ ጥቅም ከታዩት ነገሮች አንዱ ምን ሊሆን ይችላል?
   ሀ. ልምላሜ ለ. ግጦሽ ሐ. ደን መ. ማገዶ
6. ለለም አፈር መሸርሸር እንደ ምክንያት ሊታዩ ከሚችሉት ጥፋቶች ውስጥ ሊካተት የማይችለው የትኛው ነው?
   ሀ. ልክ የለሽ ግጦሽ
   ለ. ደን ጭፍጨፋ
   ሐ. የማገዶ አቅርቦት
   መ. የደን ምንጣሮ
7. የደንን ጭፍጨፋ ተከትሎ ወዲያው የሚመጣ ውጤት ምንድነው?
   ሀ. የሰው ልጅ እልቂት
   ለ. የለም መሬት መራቆት
   ሐ. የድርቅና ረሃብ መከሰት
   መ. "ለ" እና "ሐ"
8. የእፅዋት ከነሥራቸው መመንገል ምክንያት ምንድነው?
   ሀ. አስተራረስ
   ለ. እንስሳት
   ሐ. ንፋስ
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል

9. "እርቃኑን የቀረው" የሚለው ________ ለማለት ነው::

ሀ. የታረዘው

ሐ. የተዘረፈው

ለ. የተሸለተው

መ. የተጋለጠው

10. ሳይንሳዊ ይዘት የሌለው አስተራረስ የተባለው የሚከናወነው ምን አካባቢ ነው?

ሀ. በደጋማ

ሐ. በወይናደጋማ

ለ. በተዳፋታማ

መ. "ሀ እና "ሐ"

**II ከዚህ በታች ካለው ምንባብ ቀጥሎ በ"ሀ" ረድፍ በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች የሚክሉ ቁጥሮች በቅደም ተከተል ተደርድረዋል፥ በ"ለ" ረድፍ ደግሞ ክፍት ቦታዎቹን በትክክል ለማሟላት የሚያስችሉ አማራጭ ቃላት ከሀ-በ በፊደል ተራ ተደርድረዋል:: በመሆኑም ምንባቡን በትክክል የተሟላ የሚያደርጉትን ቃላት ፊደል ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ በ"ሀ" ረድፍ ውስጥ ከተመለከቱት የክፍት ቦታዎቹ ወኪል ቁጥሮች ጋር በማዛመድ መልስ ስጡ::**

## ፋብሪካውና አካባቢው (ምንባብ 2)

ጥላሸት ለብሶ በጠቆረው መሬት ላይ (11)____________ እና ጭሱ ወደ ሰማይ ቡል- ቡል የሚለው ፋብሪካ (12)____________ ሲመለከቱት ትልቅ ቀይ ሸረሪት ይመስላል:: ከበታቹ የወዝ-አደሮቹ ጎጆዎች (13)____________:: እነዚህ ግራጫ እና (14)____________ የሆኑ ትንንሽ ጎጆዎች ትናንሽ መስኮቶቻቸው ተከፍተው እርስበርሳቸው (15)____________ እና በደስታ-ቢስነት እየተያዩ የረግረጋማውን መሬት ጠርዝ በመታከክ (16)____________ ተቀልሰዋል:: ከቤቶቹ በላይ (17)____________ ብሎ የሚታያው ቤተክርስቲያን ለአከባቢው የተረጋጋ ድባብ ሰጥቷል:: (18)____________ ቁመት ከፋብሪካው ጭስ መውጫዎች ቁመት ዝቅ ያለ ሲሆን ልክ እንደፋብሪካው (19)____________ የለበሰ ቀይ መልክ አለው:: ቤተክርስቲያኑ ከፋብሪካው በግዝፈት ዝቅ ያለ ቢሆንም በመንፈሳዊ (20)____________ ምክንያት ከፍ ያለ መስሎ ይታያል::

ማክሲም ጎርኪ፥ 1986፥ <u>እናት</u>፥ ገጽ፥336

"ሀ" "ለ"

11. ______________ ሀ. ጥላሸት
12. ______________ ለ. ገሮቅ
13. ______________ ሐ. የጉልላቱ
14. ______________ መ. ደሳሳ
15. ______________ ሰ. ተጠጋግተው
16. ______________ ረ. ተጽእኖው
17. ______________ ሠ. ባሻገር
18. ______________ ሸ. ተገጥግጠዋል
19. ______________ ቀ. የተንሰራፋው
20. ______________ በ. በትካዜ

III ከዚህ በታች ያሉትን የተጓደሉ አረፍተ ነገሮች በአገባብም ሆነ በትርጉም በትክክል ሊያሟሉ የሚችሉትን ቃላትና ሐረጋት በመምረጥ መልሱ።

21. ከበደ________ ተቆጣው።
ሀ. ልጁ ለ. ልጅ ሐ. ልጁን መ. ልጅን
22. አንድ ሰው እራሱን ለመቻ የግሉን_______ መቀለስ ይገባዋል።
ሀ. ቤቶች ለ. ህንፃ ሐ. ጎጆ መ. ዘዴ
23. ስመ-ጥሩ ገጣሚ______ ተሸለመ።
ሀ. በጣም ለ. ቢሆንም ሐ. እንደልማዱ መ. ብዙ
24. አልማዝ እኔና ከበደን________።
ሀ. ቀጣችኝ ለ. ቀጣችን ሐ. ቀጣችው መ. ቀጣቻቸው
25. ቀጭኑ_______ ልጅ ከባዱን ጥያቄ መለሰ።
ሀ. ቀይ ለ. ረዥሙ ሐ. ብልሁ መ. ወፍራም
26. አንተ_________ጥፋት ፈጽመሃል።
ሀ. ጥሩ ለ. ጉልህ ሐ. ስህተት መ. ለእኔ
27. እናንተ_______ መታችሁን።
ሀ. እኛን ለ. እኛ ሐ. እነኛን መ. ለእኛ
28. _______ ሁለታችሁ ወንድማማች መሆናችሁን አላወቅኩም።
ሀ. አንተ ለ. እሷ ሐ. እሱ መ. እኔ

29. አንተ________ እኛ በፍጥነት እንከተልሃለን::

ሀ. ና ለ. አትሂድ ሐ. ለጥቅ መ. ቅደመን

30. ከበደ ሰው ልኮ ወንድሙን ከሀገር ቤት________::

ሀ. አመጣ ለ. አስመጣ ሐ. መጣለት መ. መጣ::

## IV. ከዚህ በታች ባሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ መልሱ::

31. የተፈጠረውን ተአምር ለማየት ሕዝቡ <u>በነቂስ</u> ውጥቷል::

ሀ. አንድ ባንድ ለ. አንድ ሳይቀር ሐ. አንዱ ባንዱ ላይ መ. በከፊል

32. <u>ውጣ ውረድ</u> አልፈልግም የምትሸጥበትን ንገረኝ::

ሀ. አታካሮ ለ. ውዝግብ ሐ. ክርክር መ. ንዝንዝ

33. ጫጫታው በረዶ ጸጥታ <u>ሲነግሥ</u> ተበዳዩ የሚናገረው ይሰማ ጀመር::

ሀ. ሲጎላ ለ. ሲመጣ ሐ. ሲረጋጋ መ. ሲሰፍን

34. ገንዘቡ የጠፋ መስሎኝ <u>እጢዬ ዱብ አለ</u>::

ሀ. ፈራሁ ለ. ተቆጨሁ ሐ. ደነገጥሁ መ. ተጠራጠርኩ

35. ከበደ በትህትና አንገቱን <u>ቀልሶ</u> ቆሟል::

ሀ. አስግጎ ለ. ቀና አድርጎ ሐ. ዝቅ አድርጎ መ. ጠምዝዞ

36. ሮጦ ሊያመልጠኝ ሲል እጁን <u>አፈፍ</u> አድርጌ ያዝኩት::

ሀ. ጭምድድ ለ. ለቀም ሐ. ጨበጥ መ. ጥብቅ

37. መምህሩ በተማሪዎቹ የትምህርት ክትትል <u>እምብዛም</u> አልተደሰተም::

ሀ. በጣም ለ. በአመዛኙ ሐ. እስከዚህም መ. እጅጉን

38. የሆነ ያልሆነውን <u>መወሻከት</u> የኋላ ኋላ ተደማጭነት ያሳጣል::

ሀ. መቀላመድ ለ. ማሳበቅ ሐ. ማማት መ. መለፍለፍ

39. <u>ለወጉ ያህል</u> ትከሻውን ይነቀንቃል እንጂ እስክስታ አይችልም::

ሀ. ግዳጁን ለመወጣት ሐ. ለጉራ ብሎ

ለ. ለደንቡ ያህል መ. ለጫዋታ ያህል

40. የሰውን <u>ባህርይ</u> ለማወቅ አብሮ መኖር ያስፈልጋል::

ሀ. ህይወት ለ. ጸባይ ሐ. ኑሮ መ. አድራጎት

## V. የሚከተሉትን ተረትና ምሳሌዎች በትክክል የሚያሟሉትን አባባሎች በመምረጥ መልሱ

41. ________ በልጥ በረየ።
ሀ. ይህን ያየ ለ. እባብ ያየ ሐ. ትል የለመደ መ. ሀ እና ለ

42. ________ ሲለግም ቅቤ አይወጋም።
ሀ. ወይፈን ለ. ጣት ሐ. ወሰፌ መ. ባላገር

## VII ከዚህ ቀጥሎ ባለው ግጥም ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በግጥሙ መንፈስ መሰረት በትክክል የሚያሟሉትን ቃላት ከየክፍት ቦታዎቹ አንፃር ከጥያቄዎቹ ተራ ቁጥር ጋራ የተያይዘው ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ መልሱ።

<u>አንዷቷን ቀዘባ</u> (ምንባብ -3)

እንደ ሐምሌ ወራት ፌቷ ጭፍና ለብሶ፤
እንደ መኸር ድርቆሽ ልብሷ ተልከስክሶ፥
አየኋት ለየኋት አንዷቱን ቀዘባ፥
_____ ዘና ብላ እንደ መስክ አበባ።

47. ሀ. እጥፍጥፍ ለ. ዘንጠፍ
ሐ. ልጥፍ መ. ቅጥፍ

ፊቷ ጭፍና ቢለብስ፥
ልብሷ ቢልከሰከስ፥
ግና ሥግው ሁኖ ውበት ተደበቆ፥
ታየኝ ተገለጠ ድንገት_________።

48. ሀ. ተብለጭልጮ ለ. ቦግ ብሎ
ሐ. አሽብርቆ መ. ርቆ ርቆ

ልብሷ የባላገር አየሯ ገጠር፥
ኩለንታዊ ውበት ይዛ የምትኖር፥
አየኋት ከመስኩ ወደ ገጠር ሄጄ፥
_____ ስፈልግ ተፈጥሮን ወድጄ።

49. ሀ. ተመክሮን ለ. ተፈጥሮን
ሐ. ልጅቷን መ. ሳፈላልግ

ነባይ አባይ ማለት በተፈጥሮ ቤት፥
አንዷቱ ቀዘባ________ የውበት፥
ያልተጻደፈችው በሰው ሰራሽ ፊሊጥ
ከንቱ ፈንደላላ፥

50. ሀ. ውብ ናት ለ. ጽልመት
ሐ. አክሊል መ. ፍንድቅድቅ

አየኋት ለየኋት የገጠሯን ሰንደቅ
የገጠሯን አፍላ።

ዮሐንስ አድማሱ፥ 1990 ዓ.ም.፥ <u>እሰኪ ተጠየቁ</u> ..... ገጽ 57።

# አባሪ 9

## የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ የድህረ ፈተና (post-test) የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የአማካይና መደበኛ ልይይት ስሌት

| የቁጥጥር ምድብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| score | f* | x | d | $d^2$ | $d^2xf$ |
| 10 | 3 | 30 | -15.53 | 241.18 | 723.54 |
| 12 | 4 | 48 | -13.53 | 183.06 | 732.24 |
| 14 | 2 | 28 | -11.53 | 132.94 | 265.88 |
| 16 | 5 | 80 | -9.53 | 90.82 | 454.10 |
| 18 | 2 | 36 | -7.53 | 56.70 | 113.40 |
| 20 | 5 | 100 | -5.53 | 30.58 | 152.90 |
| 22 | 6 | 132 | -3.53 | 12.46 | 74.77 |
| 24 | 6 | 144 | -1.53 | 2.34 | 14.05 |
| 26 | 6 | 156 | 0.47 | 0.22 | 1.33 |
| 28 | 4 | 112 | 2.47 | 6.10 | 24.40 |
| 30 | 5 | 150 | 4.47 | 19.98 | 99.90 |
| 32 | 4 | 128 | 6.47 | 41.86 | 167.44 |
| 34 | 4 | 136 | 8.47 | 71.74 | 286.96 |
| 36 | 5 | 180 | 10.47 | 109.62 | 548.10 |
| 38 | 4 | 152 | 12.47 | 155.50 | 622.00 |
| 40 | 1 | 40 | 14.47 | 209.38 | 209.38 |
| 42 | 2 | 84 | 16.47 | 271.26 | 542.52 |
| ድምር | 68 | 1736 | | | 5032.91 |

| የሙከራ ምድብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| sco-re | f | x | d | $d^2$ | $d^2xf$ |
| 14 | 1 | 14 | -18.91 | 357.59 | 357.59 |
| 18 | 3 | 54 | -14.91 | 222.31 | 666.93 |
| 20 | 1 | 20 | -12.91 | 166.67 | 166.67 |
| 22 | 3 | 66 | -10.91 | 119.03 | 357.08 |
| 24 | 6 | 144 | -8.91 | 79.39 | 476.33 |
| 26 | 3 | 78 | -6.91 | 47.75 | 143.24 |
| 28 | 4 | 112 | -4.91 | 24.11 | 96.43 |
| 30 | 4 | 120 | -2.91 | 8.47 | 33.87 |
| 32 | 6 | 192 | -0.91 | 0.83 | 4.97 |
| 34 | 6 | 204 | 1.09 | 1.19 | 7.13 |
| 36 | 5 | 324 | 3.09 | 9.55 | 85.93 |
| 38 | 5 | 190 | 5.09 | 25.91 | 129.54 |
| 40 | 7 | 280 | 7.09 | 50.27 | 351.88 |
| 42 | 5 | 210 | 9.09 | 82.63 | 413.14 |
| 44 | 2 | 88 | 11.09 | 122.99 | 245.98 |
| 46 | 1 | 46 | 13.09 | 171.35 | 171.35 |
| 48 | 2 | 96 | 15.09 | 227.71 | 455.42 |
| ድምር | 68 | 2238 | | | 4163.48 |

$n_1 = 68$  $\Sigma d_1^2 = 5032.91$  $n_2 = 68$  $\Sigma d_2^2 = 4163.48$

$\Sigma x_1 = 1736$  $S_1 = \sqrt{\frac{\Sigma d_1^2}{n_1}}$  $\Sigma x_2 = 2238$  $S_2 = \sqrt{\frac{\Sigma d_2^2}{n_2}}$

$\bar{x}_1 = \frac{\Sigma x_1}{n_1}$  $S_1 = \sqrt{\frac{5032.91}{68}}$  $\bar{x}_2 = \frac{\Sigma x_2}{n_2}$  $S_2 = \sqrt{\frac{4163.48}{68}}$

$\bar{x}_1 = \frac{1736}{68}$  $\bar{x}_2 = \frac{2238}{68}$

$\bar{x}_1 = \underline{25.53}$  $S_1 = \underline{8.60}$  $\bar{x}_2 = \underline{32.91}$  $S_2 = \underline{7.82}$

---

*የምልክቶቹን (symbols) ትርጓሜ ከአባሪ ሁለት ላይ ይመለከቷል።

# አባሪ 10

## የድህረ ፈተና የአንብቦ መገንዘብ ንኡስ ክፍል ውጤት የ"t" ዋጋ ስሌት

**የቁጥጥር ምድብ**

$n_1 = 68$ (የአባላት ብዛት)
$\bar{x}_1=25.53$ (አማካይ ውጤት)
$s_1=8.60$ (መደበኛ ልይይት)

**የሙከራ ምድብ**

$n_1 = 68$ (የአባለት ብዛት)
$\bar{x}_1 = 32.91$ (አማካይ ውጤት
$s_1 = 7.82$ (መደበኛ ልይይት)

**የ"t"-ሙከራ (t-test) ቀመር**

$$t_0 = \frac{\bar{X}_1 - \bar{X}_2}{\sqrt{\frac{s^2}{n_1} + \frac{s^2}{n_2}}}$$

ቀመሩን በመጠቀም የ"t"ን ዋጋ ለማስላት መጀመሪያ የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡን የጋራ መደበኛ ልይይት (common standard diviation) (s) ዋጋ በሚከተለው ቀመር እንፈልጋለን።

$$S = \sqrt{\frac{(n_1-1)\ s_1^2 + (n_2-1)\ s_2^2}{n_1 + n_2 - 2}}$$

$$S = \sqrt{\frac{(68-1)\ 8.60^2 + (68-1)\ 7.82^2}{68 + 68 - 2}}$$

$$S = \sqrt{\frac{4955.32 + 4097.21}{134}}$$

$$S = \underline{\underline{8.22}}$$

ከዚህ በላይ ያለውን የሁለቱን ምድቦች የጋራ መደበኛ ልይይት ካገኘን በኋላ ከላይ በተቀመጠው ቀመር የ"t" ዋጋ እንደሚከተለው እናሰላለን።

$$t_0 = \frac{\bar{x}_1 - \bar{x}_2}{\sqrt{\frac{s^2}{n_1} + \frac{s^2}{n_2}}}$$

$$t_0 = \frac{25.53 - 32.91}{\sqrt{\frac{8.22^2}{68} + \frac{8.22^2}{68}}}$$

$$t_0 = \frac{7.38}{1.41}$$

$$t_0 = \underline{\underline{5.23}}$$

# አባሪ 11

## የቁጥጥርና የሙከራ ምድብ የድህረ ፈተና አጠቃላይ ውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት ስሌት

| score | f* | x | d | $d^2$ | $d^2xf$ |
|---|---|---|---|---|---|
| 26 | 4 | 104 | -30.47 | 928.42 | 3713.68 |
| 28 | 1 | 28 | -28.47 | 810.54 | 810.54 |
| 32 | 1 | 32 | -24.47 | 598.78 | 598.78 |
| 34 | 1 | 34 | -22.47 | 504.90 | 504.90 |
| 36 | 2 | 72 | -20.47 | 419.02 | 838.04 |
| 38 | 3 | 114 | -18.47 | 341.14 | 1023.42 |
| 40 | 2 | 80 | -16.47 | 271.26 | 542.52 |
| 42 | 2 | 84 | -14.47 | 209.38 | 418.76 |
| 44 | 3 | 132 | -12.47 | 155.50 | 466.50 |
| 46 | 3 | 138 | -10.47 | 109.62 | 328.86 |
| 48 | 2 | 96 | -8.47 | 71.74 | 143.48 |
| 50 | 2 | 100 | -6.47 | 41.86 | 83.72 |
| 52 | 2 | 104 | -4.47 | 19.98 | 39.96 |
| 54 | 4 | 216 | -2.47 | 6.10 | 24.40 |
| 56 | 1 | 56 | -0.47 | 0.22 | 0.22 |
| 58 | 2 | 116 | 1.53 | 2.34 | 4.68 |
| 60 | 2 | 120 | 3.53 | 12.46 | 24.92 |
| 62 | 1 | 62 | 5.53 | 30.58 | 30.58 |
| 64 | 4 | 256 | 7.53 | 56.70 | 226.80 |
| 66 | 3 | 198 | 9.53 | 90.82 | 272.46 |
| 68 | 3 | 204 | 11.53 | 132.94 | 398.82 |
| 70 | 3 | 210 | 13.53 | 183.06 | 549.18 |
| 72 | 7 | 504 | 15.53 | 241.18 | 1688.27 |
| 74 | 2 | 148 | 17.53 | 307.30 | 614.60 |
| 76 | 3 | 228 | 19.53 | 381.42 | 1144.26 |
| 78 | 2 | 156 | 21.53 | 463,54 | 927.08 |
| 80 | 1 | 80 | 23.53 | 553.66 | 553.66 |
| 82 | 1 | 82 | 25.53 | 651.78 | 651.78 |
| 86 | 1 | 86 | 29.53 | 872.02 | 872.02 |
| ድምር | 68 | 3840 | | | 17496.89 |

| sco-re | f | x | d | $d^2$ | $d^2xf$ |
|---|---|---|---|---|---|
| 44 | 1 | 44 | -25.15 | 632.52 | 632.52 |
| 48 | 1 | 48 | -21.15 | 447.32 | 447.32 |
| 50 | 2 | 100 | -19.15 | 366.72 | 733.45 |
| 52 | 2 | 104 | -17.15 | 294.12 | 588.25 |
| 54 | 3 | 162 | -15.15 | 229.52 | 688.57 |
| 56 | 3 | 168 | -13.15 | 172.92 | 518.77 |
| 62 | 4 | 248 | -7.15 | 51.12 | 204.49 |
| 64 | 4 | 256 | -5.15 | 26.52 | 106.09 |
| 66 | 6 | 396 | -3.15 | 9.92 | 59.54 |
| 68 | 7 | 476 | -1.15 | 1.32 | 9.26 |
| 70 | 5 | 350 | 0.85 | 0.72 | 3.61 |
| 72 | 4 | 288 | 2.85 | 8.12 | 32.49 |
| 74 | 6 | 444 | 4.85 | 23.52 | 141.14 |
| 76 | 6 | 456 | 6.85 | 46.92 | 281.54 |
| 78 | 4 | 312 | 8.85 | 78.32 | 313.29 |
| 82 | 4 | 328 | 12.85 | 165.12 | 660.49 |
| 84 | 2 | 168 | 14.85 | 220.52 | 441.05 |
| 86 | 1 | 86 | 16.65 | 283.92 | 283.92 |
| 88 | 1 | 88 | 18.85 | 355.32 | 355.32 |
| 90 | 2 | 180 | 20.85 | 434.72 | 869.45 |
| ድምር | 68 | 4702 | | | 7370.56 |

$n_1 = 68$

$\Sigma x_1 = 3840$

$\bar{x}_1 = \frac{\Sigma x_1}{n_1}$

$\bar{x}_1 = \frac{3840}{68}$

$\bar{x}_1 = 56.47$

$\Sigma d_1^2 = 17496.89$

$s_1 = \sqrt{\frac{\Sigma d_1^2}{n_1}}$

$s_1 = \sqrt{\frac{17496.89}{68}}$

$s_1 = 16.04$

$n_2 = 68$

$\Sigma x_2 = 4702$

$\bar{x}_2 = \frac{\Sigma x_2}{n_2}$

$\bar{x}_2 = \frac{4702}{68}$

$\bar{x}_2 = 69.15$

$\Sigma d_2^2 = 7370.56$

$s_2 = \sqrt{\frac{\Sigma d_2^2}{n_2}}$

$s_2 = \sqrt{\frac{7370.56}{68}}$

$s_2 = 10.41$

---

*የምልክቶቹን (symbols) ትርጓሜ ከአባሪ ሁለት ላይ ይመለከቷል::

# አባሪ 12

## የድህረ ፈተና አጠቃላይ ውጤት የ"t" ዋጋ ስሌት

**የቁጥጥር ምድብ**

$n_1 = 68$ (የአባላት ብዛት)

$\bar{x}_1 = 56.47$ (አማካይ ውጤት)

$s_1 = 16.04$ (መደበኛ ልይይት)

**የሙከራ ምድብ**

$n_2 = 68$ (የአባላት ብዛት)

$\bar{x}_2 = 69.15$ (አማካይ ውጤት)

$s_2 = 10.41.$ (መደበኛ ልይይት)

**የ"t"- ሙከራ (t-test) ቀመር**

$$t_0 = \frac{\bar{x}_1 - \bar{x}_2}{\sqrt{\frac{s^2}{n_1} + \frac{s^2}{n_2}}}$$

**ቀመሩን በመጠቀም የ"t"ን ዋጋ ለማስላት መጀመሪያ የቁጥጥርና የሙከራ ምድቡን የጋራ መደበኛ ልይይት** (common standard diviation) (s) **ዋጋ በሚከተለው ቀመር እንፈልጋለን::**

$$S = \sqrt{\frac{(n_1-1)\, s_1^2 + (n_2 - 1)\, s_2^2}{n_1 + n_2 - 2}}$$

$$S = \sqrt{\frac{(68-1)\, 16.04^2 + (68-1)\, 10.41^2}{68 + 68 - 2}}$$

$$S = \sqrt{\frac{(67 \times 257.28) + (67 \times 108.38)}{134}}$$

$$S = \sqrt{\frac{17237.67 + 7260.79}{134}}$$

$$S = 13.52$$

**ከዚህ በላይ ያለውን የሁለቱን ምድቦች የጋራ መደበኛ ልይይት ካገኘን በኋላ ከላይ በተቀመጠው ቀመር የ"t"ን ዋጋ እንደሚከተለው እናሰላለን::**

$$t_0 = \frac{\bar{x}_1 - \bar{x}_2}{\sqrt{\frac{s^2}{n_1} + \frac{s^2}{n_2}}}$$

$$t_0 = \frac{56.47 - 69.15}{\sqrt{\frac{13.52^2}{68} + \frac{13.52^2}{68}}}$$

$$t_0 = \frac{12.68}{2.32}$$

$$t_0 = 5.47$$

## አባሪ 13

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር 1991 ዓ.ም.

### ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ

**የተከበራችሁ ተማሪዎች፥** የዚህ መጠይቅ ዓላማ በስግ ስልት የቀረበው የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ብሎም አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ለማበልፀግ ያለውን ሚና ለማጥናት፥ ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን በስብስብ ነው:: ከዚህ መጠይቅ የሚገኘው መረጃ የታቀደውን ጥናት ለማሳካት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል:: ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ለጥናቱ ከግብ መድረስ አጋዥነት አለው:: ስለዚህ ትክክለኛ መስሎ የታያችሁን መልስ በመስጠት እንደትተባበሩኝ እጠይቃለሁ:: መጠይቁን በመሙላት ለምታደረጉልኝ ትብብር በቅድሚያ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

**አጠቃላይ ማሳሰቢያ፥** -ስም መፃፍ አያስፈልግም::

-መጠይቁን ከሌላ ተማሪ ጋራ ተባብሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ ምላሽ የሚሰጠው በግል ነው::

**ክፍል አንድ፥** በባዶ ቦታ ላይ ትክክለኛውን መረጃ ጻፍ/ፊ/

1. ጾታ_______
2. እድሜ_______
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ_________
4. በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ _____(አለኝ/የለኝም) አንዱን በመምረጥ በክፍት ቦታው ላይ ጻፍ/ፊ

**ክፍል ሁለት፥** ከዚህ በታች ከተራ ቁጥር 1-14 በስግ ስልት በዚህ ክፍል ውስጥ የተሰጠውን የንባብ ትምህርት አስመልክቶ የተለያዩ ሐሳቦች የያዙ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል:: የነዚህን አረፍተ ነገሮች ሐሳብ አንብበህ/ሽ በሚገባ ከተረዳህ/ሽ በኋላ

አስተያየት ከሚለው በታች ካሉ አማራጮች አንዱን በመምረጥ ስለአረፍተነገሩ ያለህ(ሽ)ን አስተያየት "√" በማድረግ አመልክት፡፡

| ተ.ቁ. | ሐ ሳ ብ | አ ስ ተ ያ የ ት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማ |
| 1 | በስግ ስልት የንባብ የትምህርት ክንውን ውስጥ ከስግ ምንባብ ክፍት ቦታ በመነሳት ወደ ፊትና ወደኋላ እያሰሱ ከምንባብ ውስጥ መረጃዎችን የመፈለግ ተግባር አንብቦ የመረዳት ችሎታህ(ሽ)ን ለማዳበር አግዟል፡፡ | | | | |
| 2 | አንዳንድ ጊዜ ከተገደፉ ቃላት አጠገብ ያሉ ቃላትና ሐረጋት ስለተገደፈው ቃል ምንነት ቀጥተኛ ጥቆማ የሚሰጡ መሆኑ በተሟላ ምንባብ ውስጥም ከእንደነዚህ ዓይነቶቹ ጥቆማ ሰጪ ቃላትና ሐረጋት በመነሳት፥ቃላትን በሙሉ አንድ ባንድ ማየት ሳያስፈልግ እየገመቱ በፍጥነት ማንበብ እንደሚቻል ግንዛቤ ሰጥቶሃ(ሻ)ል፡፡ | | | | |
| 3 | በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ያደረግከ(ሽ)ው ተሳትፎ ቅጥያዎች ሰዋሰዋዊ ሙያ እንዳላቸው እንድትገነዘብ(ቢ) ረድቶሃ(ሻ)ል፡፡ | | | | |
| 4 | በቡድን እየተወያያችሁ ስግ ምንባቦችን በምታሟሉበት ወቅት ለፈጸምካ(ሻ)ቸው ስህተቶች ከቡድን አባላትና ከመምህር የተሰጡ የእርማት አስተያየቶች ድክመትህ(ሽ)ን መቅረፋቸው ለአንብቦ መረዳት ችሎታህ(ሽ) መዳበር አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ | | | | |
| 5 | በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ለአንድ ክፍት ቦታ ማሟያነት የተለያዩ ተገቢነት ያላቸው አማራጭ መልሶች የመሰንዘራቸው ሁኔታ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስለመስጠት ግንዛቤ እንድታገኝ(ኚ) ረድቷል፡፡ | | | | |
| 6 | በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ገደፋ ካልተካሄደበት የስግ ምንባብ ክፍል የቃላት አደረጃጀት ምልከታ እንድትነሳ(ሺ) መደረጉ የሰዋሰው ችሎታህ(ሽ)ን ለማዳበር ረድቷል፡፡ | | | | |
| 7 | ባደረጋችሁት የቡድን ውይይት ወቅት አያያዥ ቃላት ለስግ ምንባብ ክፍት ቦታዎች መሙያነት ለምን እነደተመረጡ የቀረቡ ምክንያቶች፥ በምንባብ ውስጥ ያሉ ሐሳቦችን እያገናዘቡ ስለማንበብ አስፈላጊነት እንድትገነዘብ(ቢ) ረድተዋል፡፡ | | | | |
| 8 | በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ልዩ ልዩ ዓይነት ምንባቦች (ግጥም፥ ታሪክ፥ ልቦለዳዊ ምንባቦች …) መቅረባቸው ቃላትና ሐረጋትን ከነዚህ ምንባቦች ልዩ ባህርይ አንፃር ለመተርጎም አስችሎሃ(ሻ)ል፡፡ | | | | |
| 9 | ስግ ምንባብን ለማሟላት ባደረግከ(ሽ)ው ተሳትፎ ውስጥ ስለፈጸምካ(ሻ)ቸው ስህተቶች ከመምህርና ከቡድንህ(ሽ) አባላት የተሰጡህ(ሽ) የማስተካከያ ሀሳቦች የሰዋሰዋዊ አገባብ እውቀትህ(ሽ)ን ለማዳበር ረድተዋል፡፡ | | | | |
| 10 | ለስግ ምንባብ መሚያነት የተመረጡ ቃላት | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለምን እንደተመረጡ የተሰጡ ምክንያቶች ባመዛኙ በመላሾች የቀድሞ እውቀት ላይ የተመሠረቱ መሆን÷ አንብቦ ለመረዳት ዳራዊ እውቀት ከፍተኛ ድረሻ እንዳለው ለመገንዘብ አስችሎሃ(ሻ)ል:: | | | | |
| 11 | በስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ያደረግከ(ሽ)ው ተሳትፎ የቃላትን ፍቺ ከአውደ ምንባብ ለመገመት አስችሎሃ(ሻ)ል:: | | | | |
| 12 | በቡድናዊ ውይይት ያከናወናችሁት ስግ ምንባብን የማሟላት ክንውን ከአንብቦ መረዳት ጋራ በተቀናጀ ሁኔታ በሌሎች ክሂሎች (መናገር÷መጻፍ÷ ማዳመጥ) ያለህ(ሽ)ን ብቃት አበልጽጓል:: | | | | |
| 13 | ለክፍት ቦታዎች መሚያነት የተሰነዘሩ ቃላት ለምን እንደተመረጡ ከቡድንህ(ሽ) አባላት የሚቀርቡ ምክንያቶች ስለ ቃላትና ሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ግንዛቤ እንድታገኝ(ኚ) ረድተውሃ(ሻ)ል:: | | | | |
| 14 | ስግ የማስተማሪያ ስልት በእናንተ ክፍል ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት መዋሉ አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታህ(ሽ)ን አደብሮልሃ(ሻ)ል:: | | | | |

## ክፍል ሦስት

15. ስለ ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት በተግባር ካየኸ(ሽ)ው ተጨማሪ አስተያየት ካለህ(ሽ) ባጭሩ ግለጽ(ጪ)::

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________

አባሪ 14

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር 1991 ዓ.ም.

## ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ

**የተከበራችሁ መምህራን፡-** የዚህ መጠይቅ ዓላማ በስግ ስልት የቀረበው የንባብ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ብሎም አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን ለማበልፀግ ያለውን ሚና ለማጥናት፥ ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው፡፡ ከዚህ መጠይቅ የሚገኘው መረጃ የታቀደውን ጥናት ለማሳካት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡ ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ለጥናቱ ከግብ መድረስ አጋዥነት አለው፤ ስለዚህ ትክክለኛ መስሎ የታየዎትን መልስ በመስጠት እንድትተባበሩኝ እጠይቃለሁ፡፡ መጠይቁን በመሙላት ለምታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

**አጠቃላይ ማሳሰቢያ፡-**
- ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡
- መጠይቁን ከሌላ ሰው ጋራ ሐሳብ በመለዋወጥ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ ምላሽ የሚሰጠው በግል ነው፡፡

**ክፍል አንድ፡-** በባዶው ቦታ ላይ ትክክለኛውን መረጃ ይጻፉ

1. ጾታ ____________
2. የአገልግሎት ዘመን ________________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ________________
4. የትምህርት ደረጃ ________________

**ክፍል ሁለት፡-** ከዚህ በታች ከተራ ቁጥር 1-15 ተግባራዊ ሲደረግ የተከታተሉትን የስግ ስልት የንባብ ትምህርት አስመልክቶ የተለያዩ ሐሳቦች የያዙ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ በነዚህ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተካተቱትን ሐሳቦች በሚገባ አንብበው ከተረዱ በኋላ አስተያየት ከሚለው በታች ካሉት አማራጮች አንዱን በመምረጥ ስለአረፍተነገሩ ያለዎትን አስተያየት "✓" በማድረግ ያመልክቱ፡፡

| ተ.ቁ. | ሐ ሳ ብ | አ ስ ተ ያ የ ት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
| 1 | የማስተማሪያ ስልቱ ስግ ምንባብን በማሟላት ሂደታዊ ክንውን ውስጥ የተማሪዎችን የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች በጥምረት ያዳብራል | | | | |
| 2 | አያያዥ ቃላትን በስግ ክፍት ቦታዎች ውስጥ የመሙላት ልምምድ፥ ተማሪዎች የምንባብን የተለያዩ ክፍሎች በማገናዘብ መልዕክቱን እንዲረዱ እገዛ ያደርጋል:: | | | | |
| 3 | በስግ ስልት የትምህርት ክንውን ውስጥ ተማሪዎች ለአንድ ክፍት ቦታ የሚሰነዝሯቸው የተለያዩ ምላሾች ስለቃላት አፈታት ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳሉ:: | | | | |
| 4 | በስግ የንባብ ትምህርት ክንውን ውስጥ ተማሪዎች የተገደፉትን ቃላት ከመገመታቸው በፊት ባልተገደፈው የስግ ምንባብ የቋንቋ አወቃቀር ላይ እንዲያተኩሩ መደረጉ ስለ ቅጥያዎች፥ ስለቃላትና ስለሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳል:: | | | | |
| 5 | የስግ ስልት የንባብ ትምህርት ክንውን በአመዛኙ በተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የሚሸፈን መሆኑ የመምህርን የሥራ ጫና ያቃልላል:: | | | | |
| 6 | ተማሪዎች ለስግ ክፍት ቦታዎች መሙያነት ስላቀረቧቸው ምላሾች ተገቢነት ወደፊትና ወደኋላ እያሰሱ ከስግ ምንባብ ውስጥ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ መደረጉ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ያጠናክራል:: | | | | |
| 7 | የተለያየ መልክ ያላቸው ምንባቦች (ግጥም፥ ታሪክ፥ ስነ-ጽሑፋዊ ምንባብ...ወዘተ) ለማስተማሪያነት መዋላቸው ተማሪዎች ቃላትንና ሐረጋትን ከነዚህ ምንባቦች ልዩ ባህርያት አንፃር መተርጎም እንዲችሉ ይረዳል:: | | | | |
| 8 | ለስግ ምንባብ ክፍት ቦታዎች መሙያነት በሚሰነዘሩት ግምቶች ውስጥ ስለሚፈጸሙ ስህተቶች መምህርና የላቀ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው የማረሚያ አስተያየቶች ለተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ መጎልበት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:: | | | | |
| 9 | ለስግ ክፍት ቦታዎች ማሟያነት የሚሰነዘሩ የተለያዩ ግምቶች ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች መምህሩን የተማሪዎችን ድክመቶች ለይተው እንዲያውቁ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራሉ:: | | | | |
| 10 | ለክፍት ቦታዎች መሙያነት የሰነዘሯቸውን ግምቶች ለምን እንደመረጡ ሲጠየቁ፥ ብዙዎች ምክንያታቸውን ከቀድሞው እውቀታቸው ጋራ ማያያዛቸው፥ የአንብቦ መረዳትን ብቃት ለማጠናከር ዳራዊ እውቀት ያለውን ወሳኝነት ለተማሪዎች ያስገነዝባል:: | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 11 | ተማሪዎች የተሳተፉበት የስግ ክፍት ቦታዎችን የመሙላት ልምምድ ስለ ቃላት አውደ ንባባዊ አተረጓጎም ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡ | | | | |
| 12 | ተማሪዎች ለስግ ክፍት ቦታዎች ማሟላት ያመነጩዋቸውን ግምቶች ስለመረጡበት ምክንያት የሚያቀርቧቸው ሐሳቦች ስለ ቅጥያዎች÷ ስለ ቃላትና ስለ ሐረጋት ሰዋሰዋዊ አገባብ ያላቸውን ነባር ውስጣዊ እውቀት ፊት ለፊት አውጥተው በመማማር ወደ ላቀ የሰዋሰው ግንዛቤ ለማምራት ያስችላቸዋል፡፡ | | | | |
| 13 | የማስተማሪያ ስልቱ ተማሪዎችን በሂደታዊ ክንዋኔ ውስጥ በማስገባት በክፍል ውስጥ ጸጥታን የሚያሰፍን በመሆኑ÷ የመምህርን የሥራ አካባቢ ከረብሻ ነጻ ያደርጋል፡፡ | | | | |
| 14 | ለስግ ክፍት ቦታ መሙያነት ከተማሪዎች የሚመነጩ ግምቶች ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶች ድክመታቸውን በመጠቆም እንዲቃኑ የሚያደርጉ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማበልጸግ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ | | | | |
| 15 | ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ ሂደት እየቀሰሙ በአእምሮአቸው ውስጥ ያከማቹትን የቋንቋ ብቃት በማንቃት ለእርስ በእርስ መማሪያነት እንዲያውሉት የማድረግ ችሎታ አለው፡፡ | | | | |

## *ክፍል ሦስት*

16. በታዛቢነት ተገኝተው ስለተከታተሉት ስለ ስግ የንባብ ማስተማሪያ ስልት በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ካዩት በመነሳት ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት ባጭሩ ይገለጹ፡፡

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት፥ ይህ ጥናት የራሴ ሥራ መሆኑንና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎች ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም ጌታቸው ወዮሳ

ፊርማ

አድራሻ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል፥ አዲስ አበባ።

የማስረከቢያ ቀን፥ 15/10/91 9.50

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS AB... UNIVERSITY